# ፍለጋ የሌለውን ባለጸግነት ውረስ

## ገንዘብ ሊገዛው የማይችለውን ነገር ንብረትህ አድርግ

ከዋረን ደብልዩ ዌርዝቢ
ትርጉም- ግርማዊ
እርማት - በፍቃዱ ገብሬ

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት
የኤስ. አይ. ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል
የፖ.ሣ.ቁጥር 127፥ አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ

Copyright © 1976 by SP Publications, Inc.
Chariot Victor Publishing, 4050 Lee Vance View,
Colorado Springs, Colorado 80918 U.S.A.
All rights reserved.

# ማውጫ ገጽ


መቅድም

1. ሕያው የሆኑ ቅዱሳን! ........................................ 1
2. ምን ያህል ብልጹግ ነህ! ........................................ 10
3. የሂሣብ መዝገብ ........................................ 19
4. ከመቃብሩ ውጡ ........................................ 27
5. ታላቅ የሰላም ተልዕኮ ........................................ 39
6. አንድ ምሥጢር አውቃለሁ ........................................ 50
7. ብልጽግናህን ከእጅህ አስገባ ........................................ 61
8. አብረን እንጓዝ ........................................ 70
9. አሮጌውን ሰው አስወግዱ! ........................................ 81
10. አባታችንን መምሠል ........................................ 92
11. መንግሥተ ሰማይን በቤትህ ........................................ 103
12. የክርስቶስን ጌትነት መኖር ........................................ 144
13. መንፈሳዊ ውጊያ! ........................................ 125

# መቅድም

ከዓመታት በፊት የሰማሁት አንድ ታሪክ የዚህን መጽሐፍ መልእክት ደህና አድርጎ ያጠቃልለዋል።

አንድ በቂ ምግብ ያላገኘ ልጅ በከተማዪቱ ጎዳና ላይ ይገኝና ወደ ሆስፒታል ይወሰዳል። ነርሶቹ ሰውነቱን አጥበው ልብስ ካለበሱት በኋላ አልጋ ላይ አስቀምጠው እራቱን የያዘ ትሪ አቀረቡለት። በዚያ ትሪ ላይ ወተት የተሞላበት ትልቅ ብርጭቆ ይታይ ነበር። የልጁ እጆች ብርጭቆውን ሲይዙ ዓይኖቹ በደስታ በርተው ከነርሶቹ ላይ ተተከሉ። ከዚያም፥

«ሁሉንም መጠጣት እችላለሁ?» ሲል ልባቻውን የሚነካ ጥያቄ አቀረበላቸው።

ይህም ልጅ በቤቱ በቂ የሆነ ነገር እንደማያገኝ አስገነዘባቸው። ይህ ታሪክ የአትላንቲክ ውቅያኖስን እየተመለከተች፥ «እንዲህ የተትረፈረፈ ነገር እንዳለ መገንዘቡ መልካም ነው» ስትል የተናገረችውን ሴት እንዳስታውስ አደረገኝ።

ክርስቶስ ባለጸጎች አድርጎን ሳለ ብዙ ክርስቲያኖች ግን በድህነት ታስረው ይኖራሉ። በመተኪያዎች (ሃይማኖታዊ መተኪያዎች ሳይቀር) መኖራችንን አቁመን በክርስቶስ ያለንን ባለጸግነት ለመጠቀም ጊዜው አሁን አይደለምን?

ወዳጄ ሆይ፥ በክርስቶስ ባለጸጋ ሁን!

## ኤፌ. 1፥1–3

በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ ጳውሎስ፥ በኤፌሶን ላሉት ቅዱሳን በክርስቶስ ኢየሱስም ላሉት ምእመናን፤

ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።

# 1

# ሕያው የሆኑ ቅዱሳን!

በታሪክ የምትታወቀው «ታላቋ የአሜሪካን ቆንቋና» በመባል ነው። ሄቲ ግሪን በ 1916 ስትሞት ከመቶ ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚገመት ሀብት ጥላ አልፋለች። ይህች ሴት ምግቧን እንኳ የምትበላው ቀዝቃዛውን ነበር፤ ምክንያቱም ምግቧን ካሞቀች ገንዘብ ታወጣለች። የገዛ ልጇ በእግር በሽታ ተይዞ ሊድን ወደማይችልበት ደረጃ የደረሰው ነፃ ሕክምና ስታፈላልግ ነበር። ሴትዮዋ ሀብታም ብትሆንም በድህነት ለመኖር መረጠች።

ይህ ያልተለመደ በመሆኑ ዕብደት ነው እንል ይሆናል። ምናልባት ይህች ሴት ዕብድ ልትሆን ትችላለች። ይህንን ማረጋገጥ የሚችል ግን ማንም የለም። ከሞኝነት የተነሣ ቅቤው ስለወጣለት ወተት መጠጣት ሽንቧን ገትራ ስትከራከር፥ ስሜቶችን ለሚገድል እና የመንቀሳቀስ ችሎታ ለሚያሳጣ የአንጎል በሽታ በመዳረጓ ሞቷን አፍጥናለች። ሄት ግሪን ግን ዛሬ እጅግ ብዙ ክርስቲያን አማኞችን ለመግለጽ ታገለግላለች። በዋጋ ሊተመን የማይችል ሀብት እያላቸው በድህነት ይኖራሉ። ጳውሎስ የኤፌሶንን መልእክት የጻፈው ለእንዲህ ዓይነት ክርስቲያኖች ነው።

1. ጸሐፊው (1፡1)

በታሪክ ውስጥ ቶሎ የምንለያቸው ስሞች አሉ። ከእንደዚህ ዓይነት ስሞች አንዱ «ጳውሎስ» ነው። የመጀመሪያ ስሙ «ሳውል» ይባል ነበር (የሐዋ. 7፡58)። ከብንያም ነገድ በመሆኑ (ፊልጵ. 3፡5)፥ በመጀመሪያ የእስራኤል ንጉሥ ስም ተጠርቶ ይሆናል (1ኛ ሳሙ. 9)። (በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ «ሳኦል» እና «ሳውል» ተብለው የተለዩት ስሞች አንድ ናቸው)። ይሁንና የተርሴሱ ሳውል በታዣዥነትና በታማኝነት እግዚአብሔርን አገልግሎአል። ራሱን የሰጠ የአይሁድ መምህር (ረቢ) እንደ መሆኑ መጠን፥ ሳውል በኢየሩሳሌም የፀረ–ክርስቲያኖች እንቅስቃሴ መሪ በመሆን አገልግሏል (የሐዋ. 9፡1–2፤ ገላ. 1፡13–14)። በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ሳለ ግን ጳውሎስ በኢየሱስ ክርስቶስ «ታስሮ» ተለወጠ (የሐዋ. 9፡3፤ የሐዋ. 26)።

የጤርሴሱ ሳውል የአሕዛብ ሐዋርያ ነው (የሐዋ. 9፡15)። በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ሲያገለግል ሳለ ወንጌልን ለአሕዛብ ይሰብክ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ስለ ጠራው ታዞ ወጣ (የሐዋ. 13፡1–3)። ጳውሎስ በሮም ግዛት ሁሉ ወንጌልን ለማሰራጨት ሦስት ዐበይት ሚስዮናዊ

ጉዞዎችን እንዳደረገ ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንረዳለን። ይህም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ከተካሄዱት ታላላቅ የወንጌል ስርጭት እንቅስቃሴዎች አንዱ ነው። ጳውሎስ በኤፌሶን የመጀመሪያው የወንጌል አገልግሎት የሰጠው በ 53 ዓ.ም አካባቢ ቢሆንም፥ በዚያ ግን አልተቀመጠም (የሐዋ. 18:19–21)። ከሁለት ዓመት በኋላ በሦስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞ ቢያንስ ለሁለት ዓመት በኤፌሶን ተቀምጦ ያንን ሰፊ አካባቢ በወንጌል አዳርሷል (የሐዋ. 19:1–20)። በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ዲያና የተባለች ጣዖት ትመለክ በነበረችበት አካባቢ ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን መሥርቷል። ጳውሎስ በኤፌሶን ያካሄደው አገልግሎት በሐዋርያት ሥራ 20 የተብራራ ሲሆን፥ በዚህ አገልግሎት የገጠመው ተቃውሞ በሐዋርያት ሥራ 19:21–41 ተገልጾአል።

ጳውሎስ በኤፌሶን ለሚገኙት ወዳጆቹ የጻፈላቸው ከአሥር ዓመታት በኋላ ነበር። በዚህ ጊዜ ጳውሎስ በሮም እስር ላይ ቢሆንም (ኤፌ. 3:1፤ 4:1፤ 6:20)፥ ጌታ ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን ያስተማረውን ታላላቅ እውነቶች ሊያካፍላቸው ወደደ። ስለ ታሪካዊ ዳራው ግንዛቤ ለማግኘት ኤፌሶን 6:21–22ን ከቆላስይስ 4:7–9 እና ከፊልሞና ጋር አነጻጽር። አናሲሞስ በቆላስይስ ይኖር ከነበረው ጌታው ከፊልሞና ሸሽቶ የሄደ ባሪያ ነበር። አናሲሞስ ሮም በነበረበት ወቅት ከጳውሎስ ጋር ተገናኝቶ በክርስቶስ አመነ። ከቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን (ምናልባትም በፊልሞና ቤት) አገልጋዮች አንዱ የነበረው ቲኪቆስም ከጳውሎስ ጋር ስለ አንዳንድ ጉዳዮች ለመነጋገር ወደ ሮም ሄዶ ነበር። በመሆኑም ጳውሎስ በእነዚህ ሁለት ወዳጆቹ አማካኝነት ሦስት ደብዳቤዎችን ላከ፤ እነዚህም ለኤፌሶን፥ ለቆላስይስና ለፊልሞና የተላኩት መልእክቶች ናቸው። አናሲሞስን ወደ ጌታው የመለሰው በዚሁ ጊዜ ነው።

ስለዚህ ደብዳቤው የተጻፈው ከሮም ሲሆን፥ ጊዜውም 62 ዓ.ም. አካባቢ ነው። ምንም እንኳ ጳውሎስ በችሎት ሂደት ላይ ቢሆንም፥ ለመሠረታቸው አብያተ ክርስቲያናት መንፈሳዊ ሕይወት ይገድደው ነበር። ሐዋርያ እንደ መሆኑ መጠን («ሐዋርያ» ማለት የተላከ ማለት ነው) የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማርና በእምነት ለማጽናናት አደራ አለበት (ኤፌ. 4:11–12)።

## 2. ጉባኤው (1:1–2)

ጳውሎስ ይድረስ «ለቅዱሳን» የሚል ደብዳቤ በመጻፉ ተደንቀህ ይሆን? በመሠረቱ ቅዱሳን ሙታን ናቸው፤ «ቅዱሳን» የሚለውም የተለየ ማዕረግ የሚሰጣቸው ከመንፈሳዊ ሕይወታቸው አንጻር ነው።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ «ቅዱስ» የሚለውን ቃል ያህል የተሠቃየ ቃል አይገኝም። መዝገበ ቃላት እንኳ «ቅዱስ» የሚለውን ቃል የሚተረጉሙት «ቅዱስ በሆነ ሕይወት ይፋዊ እውቅና ያገኘ» በማለት ነው። ይህን ይፋዊ እውቅና የሚሰጠው ማን ነው? ይህ እውቅና የሚሰጠው በተወሰኑ የሃይማኖት አካላት ሲሆን፥ ሂደቱም «የቅድስና አወጃ» (canonization) ይባላል። የሞተው ሰው «ቅዱስ» የሚለው ማዕረግ ይገባው እንደሆነ ለመወሰን ሕይወቱ በሚገባ ይመረመራል። የዕጩው ባሕርይና አኗኗር ነቀፋ የሌለበት ከሆነና በሕይወት ዘመኑ ቢያንስ ሁለት ተአምራት ካደረገ «ቅዱስ» የሚል ማዕረግ ይሰጠዋል።

ሂደቱ አስገራሚ ቢሆንም የመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ ተሰጥቶት አንመለከትም። ጳውሎስ በዚህች አጭር መልእክቱ ተደራስያኑን ዘጠኝ ጊዜ ቅዱሳን ሲል ጠርቶአቸዋል (1:1፥ 15፥18፤ 2:19፤ 3:8፥ 18፤ 4:12፤ 5:3፤ 6:18)። እነዚህ ቅዱሳን ምንም እንኳን «በበደላቸው በኃጢአታቸው ሙታን» (2:1-3) ቢሆኑም ሕያዋን እንጂ ሙታን አይደሉም። እንዲሁም ክርስቶስ አዳኝ መሆኑን ባመኑ ጊዜ ተአምራዊ ገጠመኝ በሕይወታቸው ውስጥ ቢፈጸምም (2:4-10) እነዚህ ሰዎች ተአምራት አድራጊዎች አልነበሩም። በአዲስ ኪዳን ውስጥ «ቅዱስ» የሚለው ቃል «በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት የሚያምን» የሚለውን አሳብ ለመግለጽ ከገቡት በርካታ ቃላት አንዱ ነው። ይህ ሰው በአካሉ ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊ ሕይወቱም ሕያው ነው (ኤፌ. 2:1)። ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 9 ስታነብ ክርስቲያኖች «ደቀ መዛሙርት» (9:1፥10፥ 19፥25-26፥ 36፥38)፤ «በዚህ መንገድ ያሉ ሰዎች» (9፥2) እና «ቅዱሳን» (9:13:32:41) ተብለው ተጠርተዋል።

«ቅዱስ» ማለት «የተለየ» ማለት ነው። አንድ ኃጢአተኛ ሰው በክርስቶስ ሲያምን ከዓለም ተለይቶ «በክርስቶስ ውስጥ» ያድራል። አማኝ ምንም እንኳ በአካላዊ ሕይወቱ በዓለም ውስጥ ቢኖርም በመንፈሳዊ ሕይወቱ የዓለም አይደለም (ዮሐ. 17:14-16)። በውኃ ውስጥ ጠልቆ ለመዋኘት የሚያስችል ልዩ መሣሪያ እንዳለው ሰው በባዕድ ምድር ይኖራል። የአማኙ መሣሪያም በልቡ ውስጥ የሚኖረው የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው (1ኛ ቆሮ. 6:19-20፤ ሮሜ 8:9)። ክርስቲያን በዓለም ውስጥ ሊኖርና ሊያገለግል የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው።

ዋናው ጥያቄ «እነዚህ የኤፌሶን ሰዎች እንዴት ቅዱሳን ሊሆኑ ቻሉ?» የሚለው ነው። መልሱን የምናገኘው «ምእመናን» እና «ጸጋ» (1:1-2) በሚሉት ሁለት ቃላት ውስጥ ነው። ጳውሎስ «ለቅዱሳን. . . በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉትም ምእመናን [በሌሎች ትርጉሞች ‹የታመኑ› ተብሎአል]» እያለ ሲጽፍ መልእክቱን የሚያስተላልፈው

ለሁለት የተለያዩ ቡድኖች ወይም ሰዎች አልነበረም። «መእመናን» ወይም «የታመኑ» የሚለው ቃል «በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉትን» ያመለክታል። እነዚህ ሰዎች የዳኑት ታማኞች ሆነው ስለኖሩ ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ስላመኑና በእርሱም ስለዳኑ ነው። ይህንንም በ 1:12-14 እና 1:19 በግልጽ መመልከት ይቻላል።

«ጸጋ» የሚለው ቃል በኤፌሶን መጽሐፍ ውስጥ 12 ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን፥ «ጸጋ ለማይገባቸው ሰዎች እግዚአብሔር ያሳየውን ቸርነት» ያመለክታል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጸጋና ምሕረት አብዛኛውን ጊዜ በአንድነት ተጠቅሰው እናገኛለን። በአማኙ የደኅንነት ልምምድም ውስጥ አብረው የሚገኙ ናቸው። አንድ ሰው፥ «እግዚአብሔር በምሕረቱ የሚሰጠኝ የሚገባኝን አይደለም፤ እግዚአብሔር በጸጋው የሚሰጠኝ የማይገባኝን ነው» ሲል ጸጋንና ምሕረትን በግሩም ሁኔታ ገልጾአል። ጸጋና እምነት አብረው የሚሄዱ ናቸው፤ ምክንያቱም ጸጋንና ደኅንነትን ማግኘት የሚቻለው በእምነት አማካይነት ብቻ ነው (ኤፌ. 2:8-9)።

«በክርስቶስ ኢየሱስ» የሚለው ሐረግ በዚህ መልእክት ውስጥ 27 ጊዜ ተጠቅሶአል። ይህም የአማኞችን መንፈሳዊ ስፍራ የሚገልጽ ነው፤ አማኙ ከክርስቶስ ጋር ስለተባበረና በክርስቶስም ውስጥ ስለሚኖር፥ ለዕለታዊ ሕይወቱ የሚያስፈልገውን ሁሉ ከክርስቶስ ብልጽግና ሊያገኝ ይችላል።

### 3. ዓላማው (1:3)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ መጻሕፍት የተለያዩ ጉዳዮችን ቢያወሱም፥ ሁሉም የየራሳቸው የሆነ ልዩ መልእክትና ጭብጥ አላቸው። ኦሪት ዘፍጥረት «የጅማሬ» መጽሐፍ ነው፤ የማቴዎስ ወንጌል «የእግዚአብሔር መንግሥት» መጽሐፍ ነው፤ የገላትያ መልእክት ደግሞ «የነጻነት» መጽሐፍ ነው። የኤፌሶን ጭብጥ በ 1:3 ላይ ተጠቅሶአል፤ ይህም *ክርስቲያኖች በክርስቶስ አማካይነት ያገኙት በረከት ነው።*

*የበረከታችን ምንጭ–* «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።» እግዚአብሔር አብ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት አበልጽጎናል። በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ዳግም በተወለድህ ጊዜ፥ ባለጸጋ ሆነህ ተወልደሃል። ይህም በክርስቶስ አማካይነት የእግዚአብሔርን ጸጋ (1:7፤ 2:7)፥ የእግዚአብሔርን ክብር (1:8፤ 3:16)፥ የእግዚአብሔርን ምሕረት (2:4) እንዲሁም «ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለጠግነት» (3:8) ትከፍላለህ። ሰማያዊ አባታችን

ሀብታም እንጂ ደሀ አይደለም፤ በመሆኑም በልጁ አማካይነት አበልጽጎናል።

ጄ. ፖል ጌት በዓለም ላይ እጅግ ሀብታም ሰው ሲሆን፥ የሀብቱም መጠን ወደ 1.3 ቢሊዮን ዶላር ይጠጋል። የነዳጅ ነጋዴዎች ሳምንታዊ ገቢ በብዙ ሚሊዮን ዶላር ይቆጠራል። ይህ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ካገኘነው መንፈሳዊ ሀብት ጋር ሲነጻጸር «የማንቲም» ያህል ብቻ ነው። በዚህ መልእክት ውስጥ ጳውሎስ እነዚህ ብልጽግናዎች ምን እንደሆኑና ለፍሬያማ ክርስቲያናዊ አኗኗር እንዴት ልንጠቀምባቸው እንደምንችል ይነግረናል።

*የበረከታችን ልክ–* «በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ።» ይህንን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በማገናዘብ «የመንፈስ በረከት ሁሉ» ብሎ መተርጎም ይቻላል። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ለእስራኤላውያን ቢታዘዙት ቁሳዊ በረከትን እንደሚሰጣቸው ቃል ገብቶ ነበር (ዘዳ. 28፡1–13)። ዛሬም የሚያስፈልገንን ሁሉ «እንደ ባለጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ» እንደሚሰጠን ተናግሮአል (ፊልጵ. 4፡19)። ይሁን እንጂ ከድህነት ወይም ከሥቃይ ነፃ እንደሚያደርገን አልተናገረም። አባታችን የመንፈስ በረከት ሁሉ ሰጥቶናል። ፍሬያማና ደስ የሚያሰኝ ክርስቲያናዊ ሕይወት ለመምራት የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ ሰጥቶናል። *መንፈሳዊው ሀብት ከቁሳዊው እጅግ ይልቃል።*

መንፈስ ቅዱስ በዚህ መልእክት ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሶአል። ምክንያቱም በረከታችንን ከአብ በወልድ አማካይነት ወደ እኛ የሚያስተላልፈው እርሱ ነው። የመንፈስ ቅዱስን ልገሳ አለማወቅና በእርሱ ላይ አለመደገፍ ለመንፈሳዊ ጉስቁልና ይዳርጋል። ጳውሎስ በኤፌሶን አገልግሎቱን የጀመረው አምነናል የሚሉትን የኤፌሶንን ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስን በትክክል ያውቁ እንደሆነ መጠየቁ የሚያስደንቅ አይደለም (የሐዋ. 19፡1–7)። ዛሬም «ክርስቲያኖችን «ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?» ብንላቸውና መልሳቸው «አልተቀበልንም» ቢሆን «አልዳናችሁም» ልንላቸው እንችላለን (ይህ በመንፈስ ቅዱስ ስለመሞላት አለመሆኑን አጢን)። «የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም» (ሮሜ 8፡19)። የመንፈስ ቅዱስን ምስክርነት ሳታገኝ የመንፈስ ቅዱስን በረከት ልትቀበል አትችልም (ሮሜ 8፡15፥16)።

*የበረከታችን ስፍራ–* «በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ።» ያልዳነ ሰው ልቡ ሁሉ ያለው በምድራዊ ነገር ላይ ነው፤ ምክንያቱም የሚኖረው በዚሁ ነው። እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎችን ኢየሱስ ክርስቶስ «የዚህ ዓለም ልጆች» ሲል ጠርቶአቸዋል (ሉቃ. 16፡8)። የክርስቲያን ሕይወት

ሰማይን ያማከለ ሲሆን፥ ዜግነቱ በሰማይ ነው (ፊልጵ. 3፡20)። ስሙም በሰማይ ተጽፎአል (ሉቃስ 10፡20)። አባቱም የሚኖረው በሰማይ በመሆኑ ፍቅሩና ልቡ ሁሉ በሰማያዊ ነገሮች ላይ ሊያተኩር ይገባል (ቆላ. 3 ከቁጥር 1 ጀምሮ)። ወንጌላዊ ዲ. ኤል. ሙዲ «በሰማያዊ ነገሮች ከመጠን በላይ የተያዙ ሰዎች ለዚህ ምድር የሚሆን ነገር የላቸውም» በማለት ያስጠንቅቁ ነበር። እዚህ ላይ ግን ጳውሎስ የሚናገረው ስለዚህ ጉዳይ አይደለም። «በሰማያዊ ስፍራ» ሲል ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን የሚኖርበትንና (1፡2) አማኞች ከእርሱ ጋር የተቀመጡበትን ስፍራ ነው (2፡6)። የእኛ ውጊያ ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን «በሰማያዊ ስፍራ» ካሉት የሰይጣን ኃይላት ጋር ነው (6፡12)።

እንደ እውነቱ ከሆነ ክርስቲያን የሁለት ዓለማት ሰው ነው፤ ይኸውም የሰብአዊውና የመለኮታዊው፥ እንዲሁም የሚታየውና የማይታየው። በሥጋው አሁን የሚኖረው ሥጋዊ አካል ለብሶ ነው፤ በመንፈስ ግን ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊ ስፍራ ተቀምጦአል። ለምድራዊው ጉዞ ኃይልና አቅጣጫ የሚሰጠው ግን ይኸው ሰማያዊ ስፍራ ነው። የአንድ አገር ፕሬዘዳንት ሁልጊዜ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ በሚገኘው መንበሩ ላይ መቀመጥ አያስፈልገውም፤ መንበሩ የሕይወቱንና የሥልጣኑን ስፍራ ይወክላል። የትም ቢሄድ የዚያች አገር ፕሬዘዳንት እርሱ ነው፤ ምክንያቱም በመንበሩ ላይ የመቀመጥ መብት ያለው እርሱ ብቻ ነው። ክርስቲያኖችንም አስመልክቶ ልክ እንዲሁ ነው። በዚህ ምድር የትምህ ቢሆን፥ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በሰማያዊ ስፍራ ተቀምጦአል። ይህም የሕይወቱና የሥልጣኑ መሠረት ነው።

ንግሥት ቪክቶሪያ ወጣት በነበረች ጊዜ ተተኪዋ የእንግሊዝ ንግሥት እርሷ እንደሆነች አልተነገራትም ነበር። ይህም የሆነው ሕይወቷ እንዳይበላሽ ነበር። አንድ ቀን መምህሯ የእንግሊዝ ንግሥት እንደምትሆን ስትነግራት ንግሥት ቪክቶሪያ እንዲህ አለች፤ «ያኔ መልካም ሰው እሆናለሁ»። ሕይወቷ በሥልጧና ይገዛል። የትም ትሁን የት ንግሥቲቱ በእንግሊዝ ዙፋን ላይ እቀመጣለሁ በሚለው እውነታ ተገዝታለች።

ኤፌሶን የእስያ ባንክ እንደ ሆነች ስለሚነገር ጳውሎስ ስለ ብልጽግና ለተደራስያኑ ሲጽፍ የሚያስተላልፍላቸው ጠቃሚ ነበር። ከሰባቱ የዓለም አስደናቂ ነገሮች አንዱ፥ በኤፌሶን የሚገኘው የዲያና ቤተ መቅደስ ነበር። ይህ ቤተ መቅደስ የጣዖት አምልኮ ብቻ ሳይሆን የሀብትም ማዕከል ነበረ። አንዳንድ የጥንቱ ዓለም ታላላቅ የኪነጥበብ ሀብቶች የሚቀመጡት በዚህ ማራኪ ሕንፃ ውስጥ ነበር። በዚህ መልእክት ውስጥ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ከቤተ ጣዖት ጋር በማነጻጸር ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያኖረውን ታላቅ

ብልጽግና ያብራራል። ጳውሎስ ቀደም ሲል *በረከት* የሚለውን ቃል ጠቅሷል። እንደ *ርስት* (1፡11፥14፥18፤ 5፡5) እና *ሙላት* (1፡10፥ 23፤ 3፡19፤ 4፡10፥ 13፤ 5፡18) የመሳሰሉትም የመዋዕለ ንዋይ ቃላት ተጠቅሰዋል። እንግዲህ ጳውሎስ «ብልጹግ ሁኑ!» እያለን ነው።

## 4. ትንተና

ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች የጻፈላቸው መልእክት እንደዚያ ታላቅ የዲያና ቤተ ጣዖት በጥንቃቄ የተዋቀረ ሲሆን፥ ከዚያ የላቀ ውበትና ብልጽግና የነገሠበት ነው። የሚከተለውን አስተዋጽኦ በጥንቃቄ አጥንተህ ጳውሎስ *አስተምህሮን (ዶክትሪንን) ከተግባር ጋር* እንዴት እንደሚያዛምድ አስተውል። ሀብቱን የምንወርሰው በእምነት ነው፤ የምንገልጸውም በሥራ ነው። ይህንን ሚዛን ካልጠበቅን መንፈሳዊ ሀብታችን ምንም አይፈይድልንም።

# የኤፌሶን መልእክት አስተዋጽኦ

ጭብጥ- አማኞች በክርስቶስ ያገኙት በረከት

መግቢያ 1፡1-2

I. አስተምህሮ- በክርስቶስ ያገኘነው በረከት (ምዕ. 1-3)

ቁልፍ ጥቅስ-1፡3

ቁልፍ ቃል «በረከት»

*ሀ. በክርስቶስ ያገኘነው መንፈሳዊ ሀብት* (1፡4-14)

1.ከአብ ያገኘነው መንፈሳዊ ሀብት (1፡4-6)

2. ከወልድ ያገኘነው መንፈሳዊ ሀብት (1፡7-12)

3. ከመንፈስ ቅዱስ ያገኘነው መንፈሳዊ ሀብት (1፡13-14)

*የመጀመሪያ ጸሎት፤* የልባቸው ዓይኖች እንዲበሩ (1፡15-23)።

*ለ. በክርስቶስ ያገኘነው መንፈሳዊ ስፍራ* (2፡1-22)

1. ከሙታን አስነሥቶ በዙፋኑ ላይ አስቀመጠን (2፡1-10)

2. ታርቀን ወደ መቅደሱ ገብተናል (2፡11-12)

*ሁለተኛው ጸሎት፤* በውስጥ ሰውነታቸው እንዲጠነክሩ (3፡1-21)

(ቁጥር 2-13 ስርዋጽ ነው)

II. ተግባር፡- በክርስቶስ ያለንን ኃላፊነት (ምዕራፍ 4-6)

ቁልፍ ጥቅስ-4፡1

ቁልፍ ቃል - «ተመላለሱ»

ሀ. በአንድነት ተመላለሱ (4፡1-16)

ለ. በልብ ንጽሕና ተመላለሱ (4፡17-5፡17)

1. እንደ ሌሎች አሕዛብ አትመላለሱ (4፡17-32)

2. በፍቅር ተመላለሱ (5፡1-6)

3. እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ (5፡7-14)

4. በጥንቃቄ ተመላለሱ (5፡15-17)

ሐ. በመስማማት ተመላለሱ (5፡18-6፡9)

1. ባሎችና ሚስቶች (5፡18-33)

2. ወላጆችና ልጆች (6፡1-4)

3. ጌቶችና ባሮች (6፡5-9)

መ. በድል ተመላለስ (6፡10-24)

ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን። በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን። በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ። በውድ ልጁም፥ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት። ጸጋውንም በጥበብና በአእምሮ ሁሉ አበዛልን። በክርስቶስ ለማድረግ እንደ ወደደ እንደ አሳቡ፥ የፈቃዱን ምሥጢር አስታውቆናልና፤ በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው። እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራ እንደ እርሱ አሳብ፥ አስቀድመን የተወሰንን በክርስቶስ ደግሞ ርስትን ተቀበልን፤ ይኸውም በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ ያደረግን እኛ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው፥ እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል፥ ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል፥ ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ፥ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ፤ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው፥ ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ አስኪዋጅ ድረስ፥ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል።

# 2

# ምን ያህል ብልጹግ ነህ!

እስከአሁን ካየኋቸው እጅግ አስቂኝ ካርቱኖች አንዱ አንድ ተመጻዳቂ ጠበቃ የደንበኛውን ኑዛዜና ቃል ለቆንጆና ዘመዶቹ ሲያነብ የሚያሳይ ሥዕል ነው። ከሥዕሉ ሥር የተጻፈው ዐረፍተ ነገር እንዲህ ይላል፤ «እኔ ጆን ጆንስ ጤናማ አእምሮና አካል እያለኝ ገንዘቤን ሁሉ ተጠቅሜ ጨርሻለሁ!»

ኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻ ቃሉንና ኪዳኑን ለቤተ ክርስቲያኑ በጻፈ ጊዜ መንፈሳዊ በረከት እንድንካፈል አድርጎናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉንም ከማባከን ይልቅ ሁሉንም ስለ እኛ ከፍሎአል። የመስቀል ሞቱና ትንሣኤው ደኅንነታችንን እውን አድርጎታል። እኛን ከኑዛዜው ውስጥ አካትቶን ሲያበቃ ኑዛዜው እውን ይሆን ዘንድ ስለ እኛ ሞተ። ከዚያም ኑዛዜው ተፈጻሚ እንዲሆን ሰማያዊ ጠበቃ ይሆንልን ዘንድ ከሞት ተነሣ።

በዚህ ረዥም ነገር ውስጥ ጳውሎስ መንፈሳዊ ሀብት ስላስገኙልን በረከቶች ጥቂት ነገሮችን ይዘረዝራል።

## 1. ከእግዚዘብሔር አብ የተቀበልናቸው በረከቶች (1፡4–6)

*በክርስቶስ መረጠን* (1፡4)። ይህ አንዳንዶችን ያደናገረና ሌሎችን ግራ ያጋባ ድንቅ የምርጫ አስተምህሮ ነው። አንድ የሰሚናሪ ፕሮፌሰር እንዲህ አለኝ፤ «ስለ ምርጫ ለማስረዳት ብትሞክር አእምሮህን ልታጣ ትችላለህ። የምርጫን አለመኖር ለመግለጽ ብትሞክር ነፍስህን ልታጣ ትችላለህ!» ደኅንነት የሚጀምረው ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰው እንዳልሆነ በሁሉም ክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነት አለው። «እኔ መረጥኋችሁ እንጂ አልመረጣችሁኝም» (ዮሐ. 15፡16)። በገዛ መንገዱ የሚቅበዘበዝ ኃጢአተኛ እግዚአብሔርን ሊፈልግ አይችልም (ሮሜ 3፡10–11)፤ እግዚአብሔር ግን ከፍቅሩ የተነሣ ኃጢአተኛውን ይፈልጋል (ሉቃ. 19፡10)።

እግዚአብሔር ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት እንደ መረጠን ልብ በል፤ ይህንንም ያደረገው ደኅንነታችን በእርሱ ጸጋ ላይ እንጂ በእኛ ድካም ላይ የተመሠረተ እንዳይሆን ነው። የመረጠን በክርስቶስ እንጂ በራሳችን አይደለም። የመረጠንም ቅዱሳንና ነውር የሌለን እንሆን ዘንድ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ምርጫ ሁልጊዜ ለአንድ ነገር

መታጨትን የሚያመለክት ሲሆን፥ ታላቅ ኃላፊነት ያለበት በረከት ነው።

ኃጢአተኛው የእግዚአብሔርን ጸጋ የሚቀበለው ከፈቃዱ ውጭ ነው? አይደለም፤ የእግዚአብሔርን ጸጋ የሚቀበለው የእግዚአብሔር ጸጋ ፈቃደኛ እንዲሆን ስለሚያደርገው ነው። የእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና የሰብአውያን ኃላፊነት ምሥጢር በዚህ ምድር የሚፈታ አይደለም። ሁለቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተወስተዋል (ዮሐ. 6:37)። ሁለቱም እውነትና አስፈላጊ ነገሮች ናቸው።

በግጻዌ መለኮት ውስጥ ያሉት ሦስቱ አካላት በደኅንነታችን ውስጥ እንደተካፈሉ ትገነዘባለህ (1ኛ ጴጥሮስ 1:3 ተመልከት።) የዳንኸው እግዚአብሔር አብ፥ ከዘላለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ በመረጠህ ጊዜ ነው። ነገር ግን ይህ ብቻ አያድንህም። እግዚአብሔር ወልድን በተመለከተ፥ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ ድነሃል። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ፥ የእርሱን የወቀሳ ድምፅ ሰምተህ በክርስቶስ አዳኝነት ባመንህ ጊዜ ድንሃል። ከዘላለም ዘመናት በፊት የተጀመረው ሥራ በአሁኑ ዘመን ተፈጽሞአል፤ ለዘላለም ይቀጥላል።

*ልጆቹ አደረገን* (1:5)። እዚህ ላይ ሰዎች በቀላሉ የሚስቱትንና «ቅድመ ውሳኔ» የሚለውን አሳብ እናገኛለን። ይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለዳኑት ሰዎች ያደረገውን ነገር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሲዖል ተወስነዋል ብሎ የሚናገር ክፍ አናነብም፤ ምክንያቱም ቃሉ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ሰዎች ብቻ ነው። የቃሉ ፍች «አስቀድሞ መወሰን፥ አስቀድሞ መመደብ» የሚል ነው። መረጠ የሚለው ቃል «ሰዎችን»፥ ቅድመ ውሳኔ ግን «ዓላማን» የሚያመለክት ይመስላል። ከክርስቶስ ስቅለት ጋር የተያያዙ ሁነቶች በቅድሚያ ተወስነዋል (የሐዋ. 4:25–28)። እግዚአብሔር ልጆቹ እንደምንሆንና (ኤፌ. 1:5)፥ ክርስቶስን እንድንመስል (ሮሜ 8:29–30)፥ እንዲሁም ወደፊት ስለምንቀበለው ርስት (ኤፌ. 1:11) አስቀድሞ ወስኖአል።

ልጅነት ሁለት ፍች አለው፤ እርሱም የአሁንና የወደፊት ፍች ነው። ወደ እግዚአብሔር ቤተሰቡ የምንገባው በልጅነት ሳይሆን በአዲስ ልደት ነው (ዮሐ. 3:1–18፤ 1ኛ ጴጥ. 1:22–25)። ልጅነት እግዚአብሔር «አዲስ ለተወለዱት» በቤተሰቡ ውስጥ የጎልማሳነት ደረጃ የሚሰጥበት ነው። ይህንን የሚያደርገው ለምንድን ነው? ርስታችንን በመያዝ መንፈሳዊ ሀብታችንን ወዲያውኑ መጠቀም እንድንጀምር ነው! ሕፃን ልጅ ይህንን ርስት በሕግ ሊጠቀም አይችልም (ገላ. 4:1–7)። ጎልማሳ ሰው ግን ይችላል፤ መቻልም ይኖርበታል!

በክርስቶስ ያለንን በረከት ለመውረስ ሽማግሌ እስክንሆን ድረስ መጠበቅ የለብንም ማለት ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ሲመለስ የምናገኘው የከበረ አካል ማለትም የልጅነት *የወደፊት ገጽታችን* የሚገኘው በሮሜ 8፡22–23 ነው። ዓለም ባታየውም ቀድሞውኑ በእግዚአብሔር ፊት የጎልማሳነትን ደረጃ አግኝተነዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ይህ «የማይታየው ልጅነት» ለሁሉም ገሃድ ይወጣል።

*ተቀብሎናል* (1፡6)። እኛ ራሳችንን እግዚአብሔር እንዲቀበልን ማድረግ አንችልም። እርሱ ግን በጸጋው በክርስቶስ ተቀብሎናል። ይህ ከቶውንም የማይለወጥ ዘላለማዊ ስፍራችን ነው። በአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይኸው አሳብ፥ «በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን» ተብሏል። (ይህ በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ የቀረበበት አገላለጽ ነው።) ቃል በቃል በቀጥተኛ አገላለጽ ደግሞ «በውድ ልጁ ጸጋውን ችሮናል» ተብሎም ሊተረጎም ይችላል። ዞሮ ዞሮ አሳቡ አንድ ነው። እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ከገለጸው ጸጋ የተነሣ ተቀባይነትን አግኝተናል። ጳውሎስ ለፊልሞና በጻፈው ደብዳቤ ላይ ኮብላዩን ባሪያውን አናሲሞስን እንዲቀበል ለማበረታታት ይህንኑ አሳብ ተጠቅሟል። «እንደ እኔ አድርገህ ተቀበለው. . . በአንዳች ነገር የበደለህ ቢኖር. . . በእኔ ላይ ቁጠር» (ቁ. 17–19)። የአሳቡን ተጓዳኝነት ለመመልከት ቀላል ነው።

## 2. ከእግዚአብሔር ወልድ ያገኘናቸው በረከቶች (1፡7–12)

ሁሉም ደኅንነታችንን እውን ለማድረግ ስለሚሠሩ፥ በግጻዌ መለኮት ውስጥ ያሉ አካላት ለብቻቸው እንደሚሠሩ ማሰብ ተገቢ አይሆንም። ይሁንና እያንዳንዱ አካል የሚፈጽመው ልዩ አገልግሎትና በሕይወታችንም ውስጥ የሚያከማቸው ልዩ «መንፈሳዊ ሀብት» አለው።

*ተቤዥቶናል* (1፡7)። መቤዠት ማለት «ዋጋ ከፍሎ ነፃ ማውጣት» ማለት ነው። በሮም ግዛት ውስጥ እንደ ዕቃ የሚሸጡና የሚገዙ ስድስት ሚሊዮን ባሪያዎች ነበሩ። በዚህ ጊዜ ሰው ባሪያን ገዝቶ ነፃ ሊያወጣ ይችል ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ያደረገው ይህንኑ የሚመስል ተግባር ነውና ዋጋው የገዛ ደሙ ነበር (1ኛ ጴጥ. 1–18 ጀምሮ)። ይህም ማለት እኛ ከሕግ (ገላ. 5፡1)፥ ከኃጢአት ባርነት (ሮሜ 6)፥ ከሰይጣንና ከዓለም ኃይል (ገላ. 1፡4 እና ቆላ 1፡13–14) ነፃ ነን ማለት ነው። ባሪያዎች ብንሆን ድሆች እንሆን ነበር፤ ልጆች በመሆናችን ግን ሀብታሞች ነን!

*ይቅር ብሎናል* (1:7)። «ይቅር» የሚለው ቃል «አስወግድ» የሚል ፍች አለው። ይህ ሊቀ ካህኑ በአይሁድ የስርየት በዓል ዕለት ፍየል ወደ በረሃ የሚለቅበትን ሥርዓት ያስታውሰናል (ዘሌ. 16)። መጀመሪያ ሊቀ ካህኑ ከሁለቱ ፍየሎች አንደኛውን አርዶ በእግዚአብሔር የምሕረት መክደኛ አጠገብ ደሙን ይረጫል። ከዚያም የእስራኤልን ኃጢአት ሕያው በሆነው ፍየል ላይ ተናዝዞ ፍየሉን ወደ በረሃ ይሰደዋል። ክርስቶስ ኃጢአታችን ዳግም እስከማይታይ ድረስ ለማስወገድ ሲል ሞተ [ ዮሐ. 1:29፤ መዝ. (103):12]። ኃጢአታችን ስለተወገደ ከእንግዲህ የሚከሰን የሕግ ጽሕፈት የለም! ኃጢአት ድሆች አደረገን፥ ጸጋው ግን ሀብታሞች አደረገን።

*የእግዚአብሔርን ፈቃድ ገለጸልን* (1:8-10)። በዚህ መልእክት ውስጥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው ዕቅድ በሰፊው ተገልጾአል። ይህም በጳውሎስ ዘመን ሳይቀር ሙሉ በሙሉ ሰዎች ያልተገነዘቡት ነው። «ምሥጢር» የሚለው ቃል ጨርሶ እንግዳ የሆነ ከሚለው ጋር የሚዛመድ አይደለም። ይልቁንም «በአንድ ወቅት ተሰውሮ የነበረ፥ አሁን ግን ለእግዚአብሔር ሕዝብ የተገለጸ» ማለት ነው። እኛ አማኞች የእግዚአብሔር አሳብ አካላት ነን። እግዚአብሔር አንድ ቀን ሁሉንም በክርስቶስ ይጠቀልላል የሚለውን ምሥጢር እንጋራለን። ኃጢአት ወደ ዓለም ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ነገር ዓለሙ ተበላሽቶአል። መጀመሪያ ሰው ከእግዚአብሔር ተለየ (ዘፍጥ. 3)። ከዚያም ሰው ከሰው ተለየ። ለዚህም ቃየል አቤልን መግደሉ በዋነኛነት ሊጠቀስ ይችላል (ዘፍጥ 4)። ሰዎች በባቤል ግንብ አማካኝነት አንድነትን ለመጠበቅ ቢጥሩም (ዘፍጥ. 11)፥ እግዚአብሔር ፍርዱን በመላክ በዓለም ሁሉ በትኖአቸዋል። እግዚአብሔር አብርሃምን በመጥራት በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ልዩነትን አደረገ። ይህም ልዩነት ክርስቶስ በመስቀል ላይ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ዘልቆአል። ኃጢአት ሁሉንም ነገር እያፈራረሰ ቢሆንም እግዚአብሔር በዘመን ፍጻሜ ሁሉንም በክርስቶስ ይጠቀልላል። እኛ የዚህ ታላቅ ዘላለማዊ ቢጋር አካል ነን።

*ርስትን ሰጥቶናል* (1:11-12)። የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ «በክርስቶስ ርስትን ተቀበልን» ይላል። በእርሱ «ርስት ተደረገ» ተብሎ ቢተረጎምም ያስኬዳል። ሁለቱም እውነት ሲሆኑ አንዱ ሌላውን ያጠቃልላል። በክርስቶስ ታላቅ ርስት አለን (1ኛ ጴጥ.1:1-4)። እኛም በክርስቶስ ርስት ነን። ለእግዚአብሔር ዋጋ ያለን ሰዎች ነን። እግዚአብሔር እኛን ገዝቶ የርስቱ አካል ለማድረግ ምን ያህል ዋጋ እንደከፈለ ልብ እንበል! እግዚአብሔር ወልድ ለእኛ የአብ ፍቅር ስጦታ ሲሆን፥ እኛ ደግሞ ለወልድ የአብ የፍቅር ስጦታዎች ነን። በዮሐንስ ምዕራፍ 17 ላይ ክርስቶስ «እኛን ስንት ጊዜ «አንተ

የሰጠኸኝ» እያለ እንደጠራን እናጢን። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል (ኤፌ. 1፡22-23)፥ ናት። የክርስቶስ የወደፊት ርስት በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ተጠቃሏል። እኛም ከክርስቶስ ጋር አብረን የምንወርስ ነን (ሮሜ 8፡17)። ይህም ማለት ያለ እኛ ርስቱን አይወስድም ማለት ነው።

## 3. ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ያገኘናቸው በረከቶች (1፡13-14)

ከዘላለም ዘመናት (ቁ. 4-6) በፊት የተከናወነውን ነገር አልፈን (ቁ. 7-12) ወደ ኤፌሶን ክርስቲያኖች የወቅቱ ልምምድ እንሸጋገራለን። መንፈስ ቅዱስ በእነዚህ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ሠርቷል። እነርሱም ይህንኑ ተገንዝበዋል።

*አትምናል* (1፡13)። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ጠቅላላው የደኅንነት ሂደት ስለተገለጸ በጥንቃቄ መመርመሩ ተገቢ ነው። ጥቅሱ ኃጢአተኛ እንዴት ወደ ቅዱስነት እንደሚሸጋገር ይገልጽልናል። በመጀመሪያ የመዳንን ወንጌል ይሰማል። ይህም ክርስቶስ ለኃጢአታችን እንደ ሞተ፥ እንደተቀበረና እንደተነሣ የሚያስረዳው የምሥራች ነው (1ኛ ቆሮ. 15 ከቁጥር 1 ጀምሮ)። ይኸው የምሥራቹ ወንጌል መጀመሪያ ለአይሁዶች ደረሰ። የኤፌሶን ሰዎች ደግሞ አሕዛብ ነበሩ። ነገር ግን አይሁዳዊው ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል እየሰበከ ለአሕዛብ ወንጌልን አሰራጨ።

የኤፌሶን ሰዎች ወንጌሉን ሰምተው የደኅንነት መንገድ መሆኑን ተገነዘቡ (ቁጥር 13)። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ምርጫ መናገር ብቻ ሳይሆን፥ «ወደ ዓለም ሁሉ ስበኩ» የሚል መልእክትም አዝሎአል (ማር. 16፡15)። አንድ ወንጌል ሰባኪ ካልዳኑት ሰዎች ጋር ስለ ምርጫ አይነጋገርም። ምክንያቱም ይህ ለቅዱሳን ቤተሰቦች የተገለጠ ምሥጢር ነው። የእርሱ ድርሻ የወንጌሉን እውነት እያወጀ ሰዎች በክርስቶስ እንዲያምኑ መጋበዝ ነው። ቀሪው የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ ይሆናል። ዲ. ኤል. ሙዲ፥ «ጌታ ሆይ፥ እባክህ የተመረጡትን አድን፤ ከዚያም ሌሎችን ምረጥ!» እያሉ ይጸልዩ ነበር። ፍጻሜውን ማለትም የሰዎችን መዳን የወሰነው አምላክ ወደ ፍጻሜ የሚያደርሰውንም መንገድ ማለትም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የወንጌልን መሰበክ ወስኗል።

የኤፌሶን ሰዎች ቃሉን ሰምተው በማመናቸው ደኅንነትን አገኙ (2፡8-9)። ይህ ጳውሎስ በሮሜ 10፡13-15 የጻፈውን አሳብ የሚከተል በመሆኑ ይህንኑ ክፍል በጥንቃቄ ማጥናቱ ጠቃሚ ነው። ይህ አሳብ የእግዚአብሔር የወንጌል ስርጭት ዕቅድ ነው። የኤፌሶን ሰዎች ባመኑ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ታትመዋል። በቁጥር 13 ላይ «በክርስቶስ

አምናችሁ» የሚለው «በክርስቶስ ባመናችሁ ጊዜ» ተብሎ ሊተረጎም ያሻል። በክርስቶስ ባመንን ጊዜ መንፈስ ቅዱስን እንቀበላለን። ይህ ከደኅንነት በኋላ የሚከሰት ልምምድ አይደለም (የሐዋ. 10:34–48)።

ለመሆኑ የዚህ የመንፈስ ቅዱስ ማኅተም ጠቀሜታ ምንድን ነው? አንደኛው *ስለተጠናቀቀው የግብይት ተግባር* የሚያስረዳ መሆኑ ነው። ዛሬም እንኳ የሕጋዊ ሰነዶች ልውውጥ በሚደረግበት ጊዜ በሰነዶቹ ላይ ማኅተም ይታተማል። ማኅተም *የባለቤትነት* ማረጋገጫ ነው። እግዚአብሔር የእርሱ እንሆን ዘንድ በዋጋ ስለገዛን አትሞናል (1ኛ ቆሮ. 6:19–20)። ማኅተም *የዋስትናና የጥበቃም* ምልክት ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ *መቃብር* ላይ የተደረገው የሮማውያን ማኅተም ይህ ፍቺ ነበረው (ማቴ. 27:62–66)። እንግዲህ አማኞች የእግዚአብሔር ንብረት ናቸው፤ እርሱ ስለ ገዛቸውም በእርሱ ጥበቃ ሥር ናቸው። ዮሐንስ 14:16–17 እንደሚያስረዳን፥ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ ለዘላለም ይኖራል። መንፈስ ቅዱስን ስናሳዝን የአገልግሎቱን በረከቶች ከመቋደስ ልንታቀብ ብንችልም (ኤፌ. 4:30)፥ ምን ጊዜም አይለየንም።

በሌላ በኩል ደግሞ ማኅተም የእውነተኛነት ምልክት ነው። የደብዳቤ ላይ ፊርማ የሰነዱን እውነተኛነት እንደሚያመለክት ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ መኖር የአማኙን እውነተኛነት ያሳያል። «የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም» (ሮሜ 8:9)። የምንናገረውን እውነተኛ የሚያደርገው የአፋችን ቃል፥ ሃይማኖታዊ ሥራችን ወይም በጎ ተግባራችን ብቻ ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስም ምስክርነት ነው።

*የርስታችን መያዣ ነው* (1:14)። *መያዣ* የሚለው ቃል ልዩ ቃል ነው። ቃሉ በጳውሎስ ዘመን «የአንድ ሸቀጥ ወይም ንብረት ግዥ የዋስትና ቀብድ» የሚል ፍች ነበረው። ዛሬም እንኳ የመሬትና መሰል ንብረት ባለቤቶች ስለ *መያዣ* ይናገራሉ። እግዚአብሔር *ሥራውን* ፈጽሞ ወደ ክብር እንደሚያመጣቸው ለልጆቹ የሚገልጽበት ቀዳሚ ዋስትና መንፈስ ቅዱስ ነው። «ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ» የሚለው ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ የሚከናወነውን የሰውነትን መቤዠት ያመለክታል። (ሮሜ 8:18–23፤ 1ኛ ዮሐ. 3:1–3)። የመቤዠታችን ተግባር በሦስት ደረጃዎች የተከፈለ ነው።

- በኢየሱስ ክርስቶስ አምነን *ድነናል* (ኤፌ. 1:7)።
- *መንፈስ ቅዱስ ይበልጥ ክርስቶስን እንድንመስል በሕይወታችን* ውስጥ በመሥራቱ *በመዳን ላይ እንገኛለን* (ሮሜ 8:1–4)።
- ክርስቶስ ሲመለስና እርሱን ስንመስል *እንድናለን*።

«መያዣ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል «የትጭጭት ቀለበት»ም ሊባል ይችላል። ዛሬ በግሪክ ይህንን ቃል ሰዎች በዚህ መልኩ ይጠቀሙበታል። ይኸውም የትጭጭት ቀለበት የተገቡት የተስፋ ቃሎች እንደሚጠበቁ ዋስትና የሚሰጡ ማረጋገጫዎች ናቸው። በክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት የንግድ መልክ የያዘ ብቻ ሳይሆን ግላዊ የፍቅር ልምምድም ነው። እርሱ ሙሽራ ሲሆን፥ ቤተ ክርስቲያን ሙሽሪት ነች። መንፈሱንና የተስፋ ቃሉን እንደ «ትጭጭት ቀለበት» ስለሰጠን መጥቶ እንደሚሞሽረን እናውቃለን። ከዚህ የበለጠ ምን ማረጋገጫ ያስፈልገናል?

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በክርስቶስ ስላለን ብልጽግና የሚናገሩትን መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች ተመልክተናል። እነዚህ ክፍሎች የሚያስተምሩትን መለስ ብሎ መከለሱ ጠቃሚ ነው።

1. *እውነተኛ ብልጽግና የሚመጣው* ከእግዚአብሔር ነው። አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እኔን ባለጸጋ ለማድረግ ተግተው እየሠሩ መሆናቸውን መረዳት በእጅጉ የሚያበረታታ አሳብ ነው። እግዚአብሔር ደስ ይለን ዘንድ ሁሉንም አትረፍርፎ መስጠት ብቻ ሳይሆን (1ኛ ጢሞ. 6፡17) *ዘላለማዊ* ብልጽግናንም ይሰጠናል፤ ያለዚህ ዘላለማዊ ብልጽግና ሌላው ሀብት ሁሉ ከንቱ ነው።

አንዲት ግራ የተጋባች የቤት እመቤት ክርስቲያን የጋብቻ አማካሪ አፈላልጋ ሊፈራርስ የደረሰውን የትዳርዋን አሳዛኝ ታሪክ አወጋችው። «ግን ብዙ ነገሮች አሉን! ከጣቴ ላይ ያለውን የአልማዝ ቀለበት ተመልከት። ብዙ ሺህ ገንዘብ ያወጣል! በምርጥ ቦታ ውድ ዋጋ የሚያወጣ ቤት አለን። ሦስት መኪኖችና በተራሮች ውስጥ ለመዝናናት በምንሄድበት ጊዜ የምናርፍበት ቤት ጭምር አለን። በገንዘብ ሊሸመት የሚችል ነገር ሁሉ አለን!» እያለች ትናገር ጀመር።

አማካሪውም፥ «ገንዘብ የማይገዛቸውን ነገሮች ሳይጥሉ ገንዘብ የሚገዛቸውን ነገሮች ማካበቱ ክፋት የለውም። ትዳር እየፈረሰ የውድ ቤት ባለቤትን ምን እርባና ይኖረዋል? ወይስ ፍቅር ሳይኖር ውድ የአልማዝ ቀለበት መግዛት ምን ይረባል?» ሲል ምላሽ ሰጥቷል።

እኔና አንተ በክርስቶስ «ገንዘብ የማይገዛቸው ነገሮች» አሉን። እነዚህ መንፈሳዊ ሀብቶችም ለሁላችንም የእግዚአብሔርን ሰፊ ፍጥረት ብልጽግና ሁሉ ይከፍቱልናል። ሰጭውን ስለምናውቅና ስለምናፈቅር በስጦታዎቹ ደስ እንሰኛለን።

2. *እነዚህ ሁሉ በረከቶች በእግዚአብሔር ጸጋና ለእግዚአብሔር ክብር የሚሰጡን ናቸው።* ጳውሎስ ከቁ. 4–14 በሚገኘው ምንባብ በእያንዳንዱ ዐቢይ ክፍል ውስጥ ከስጦታዎቹ ባሻገር ስላለው ዓላማ እንደጠቀሰ ልብ ብለሃል? እግዚአብሔር አብ የመረጠን፥ ልጆቹ

ያደረገንና የተቀበለን ለምንድን ነው? «ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው»። እግዚአብሔር ወልድ የተቤዠን፥ ይቅር ያለን፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የገለጠልንና የእግዚአብሔር ርስት ተካፋይ እንድንሆን ያደረገን ለምንድን ነው? «ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው» (ቁ. 12)። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ያተመንና የወደፊት በረከታችን ዋስትና የሆነው ለምንድን ነው? «ለክብሩ ምስጋና» (ቁጥር 14) እንድንሆን ነው።

ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን የሚያድነው ስለሚያዝንላቸው ወይም ከዘላለም ፍርድ ሊታደጋቸው ስለሚፈልግ ነው ብለን እናስባለን። የእግዚአብሔር ዋንኛ ዓላማ ግን የእርሱ መከበር ነው። ፍጥረቱ ጥበቡንና ኃይሉን፥ ቤተ ክርስቲያኑ ደግሞ ፍቅሩንና ጸጋውን ትገልጣለች። እነዚህን መንፈሳዊ ሀብቶች በእምነት መቀበል እንጂ በመብት ወይም በሥራ ልናገኛቸው አንችልም።

3. *እነዚህ በረከቶች ጅማሬ ብቻ ናቸው!* ከጌታ ጋር በምንኖርበት ጊዜ ሁሉ ተጨማሪ መንፈሳዊ በረከቶች እናገኛለን። መጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ የምናገኝበት መጽሐፍ ነው። መንፈስ ቅዱስ መምህራችን ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በምንመረምርበት ጊዜ በክርስቶስ ያሉንን ተጨማሪ በረከቶች እናስተውላለን። እነዚህ ሀብቶች በአብ የታቀዱ፥ በወልድ የተገዙና በመንፈስ ቅዱስ የተበረከቱ ናቸው። ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር በረከት እያለልን በድህነት ልንኖር አይገባም!

አንድ ወዳጄ ከሚስቱ ጋር ስለ ገንዘብ ጉዳይ እየተነጋገሩ ሳለ ልጃቸው እየሰማቸው መሆኑን ልብ አላሉም ነበር። በመጨረሻም ትንሹ ልጅ፥ «ለምን ከእነዚያ ወረቀቶች አንዱን አትጽፉም» ሲል አሳብ አቀረበ። ወረቀት (ቼክ) የሚጻፈው በባንክ ገንዘብ መኖሩ ሲረጋገጥ እንደሆነ ትንሹ ልጅ አልተገነዘበም ነበር። መንፈሳዊ በረከቶቻችንን በተመለከተ ግን እንዲህ ዓይነት ችግር አይገጥመንም።

«በእምነት ባንክ የተቀመጠ የቼክ ቡክ» በሚል ርእስ ቻርልስ ስፐርጅን የጻፉት አነስተኛ የጽሞና መጽሐፍ አለ። በዚህች መጽሐፍ ውስጥ ለእያንዳንዱ ዕለት ከመጽሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃልና አጭር የጽሞና መልእክት ቀርቦአል። ደራሲው በእምነት ለሚቀበል እያንዳንዱ የተስፋ ቃል በባንክ ቤት እንዳለ ገንዘብ ያህል አስተማማኝ እንደሆነ ገልጾአል። የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል በእምነት በመቀበል በሚያስፈልገን ነገር ሁሉ ሊሞላ የሚችል ወሰን የሌለው ብልጽግናውን ልንጠቀም እንችላለን።

## ኤፌሶን 1፡15–23

ስለዚህ እኔ ደግሞ በእናንተ ዘንድ ስለሚሆን በጌታ በኢየሱስ ስለማመንና ለቅዱሳን ሁሉ ስለሚሆን መውደድ ሰምቼ፥ ስለ እናንተ እያመሰገንሁ ስጸልይ ስለ እናንተ ማሳሰብን አልተውም፤ የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ። ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምንም ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው፤ ክርስቶስንም ከሙታን ሲያስነሣው ከአለቅነትና ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይና በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግሞ ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው በክርስቶስ ባደረገው ሥራ የብርታቱ ጉልበት ይታያል፤ ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው። እርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት።

# የሒሳብ መዝገብ

ጃኑዋሪ 6/1822 የአንድ ጀርመናዊ ምስኪን መጋቢ ሚስት የሆነች ሴት ልጅ ወለደች። ይህ ልጅ አንድ ቀን በዓለም ላይ አሉ ከሚባሉ ሀብታሞች መካከል አንዱ ሊሆን እንደሚችል አልማ አታውቅም። ሄንሪክ ሽሌማን የ7 ዓመት ልጅ በሆነ ጊዜ የጥንቷ ትሮይ በእሳት ስትጋይ የሚያሳየው ሥዕል አሳቡን ወሰደው።

ብዙ ሰዎች ከሚያምኑበት አሳብ በተቃራኒ ሄንሪክ «ኤልያድ» እና «አዲሴ» የሚባሉት ታላላቅ የሆሜር ግጥሞች በታሪካዊ እውነታዎች ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን በመግለጽ እውነትነቱን ለማረጋገጥ ጥረት ማድረጉን ቀጠለ። በ1873 ወደ ጥንቷ የትሮይ ከተማ በመሄድ አንዳንድ አስደናቂ ሀብቶችን ሊወስድ ችሏል። ይህም የቱርክን መንግሥት አስቆጥቶአል። ሽሌማን ጥንታዊውን ዘገባ በማመኑና ባመነውም መሠረት ተግባራዊ እርምጃ በመውሰዱ ዝነኛና ከበርቴ ሊሆን በቅቷል።

በክርስቶስ ባመንን ጊዜ «ሀብታሞች ሆነን መወለዳችንን» እንረዳለን። ይሁንና ይህ ብቻውን በቂ አይደለም፤ ለእግዚአብሔር ክብር ማዋል ካለብን ስለ ብልጽግናችን ከፍተኛ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል። በርካታ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት በመዝገባቸው ውስጥ ያስቀመጠላቸውን ከፍተኛ መንፈሳዊ በረከት ለማግኘት የሒሳብ መዝገቡን አላነበቡም። እነዚህ ሰዎች ከዓለም ዙሪያ የኪነጥበብ መዛግብትን በማሰባሰብ ለማግኘት እንደሞከሩት እንደ ሚች ዊሊያም ራንዶልፍ ሄርስት ዓይነት ናቸው። ሄርስት አንድ ቀን የራሴ ንብረት ሊሆኑ ይገባል ሲሉ ያሰቧቸውን ጠቃሚ ዕቃዎች ዝርዝር አገኙ። ወኪሉን ወደ ውጭ አገር በመላክ እነዚህን ዕቃዎች ለማግኘት ጥረት አደረጉ። ከብዙ ወራት ፍለጋ በኋላ ወኪሉ ዕቃዎቹን ከሚስተር ሄርስት ዕቃ ቤት ውስጥ እንዳገኘ አስታወቀ። ሄርስት ቀደም ሲል የነበሩዋቸውን ነገሮች በከፍተኛ ጥረት በመፈለግ ላይ ነበሩ። የሀብታቸውን ዝርዝር መግለጫ አንብበው ቢሆን ኖሮ ብዙ ችግርና ገንዘብ ለመቆጠብ ይችሉ ነበር።

ጳውሎስ የኤፌሶን ክርስቲያኖች በክርስቶስ ምን ያህል የከበረ በረከት እንዳላቸው እንዲገነዘቡ ይፈልጋል። ጳውሎስ እምነታቸውንና ፍቅራቸውን ያውቅ ስለ ነበር በዚህ ደስ ተሰኝቶአል። የክርስትና ሕይወት ሁለት አቅጣጫዎች አሉት- እግዚአብሔርን ማመንና

ሰዎችን ማፍቀር። ሁለቱን መነጣጠል አይቻልም። ይሁንና ጳውሎስ እነዚህ ጅምር እርምጃዎች መሆናቸውን ያውቅ ነበር። የኤፌሶን ሰዎች ገና ብዙ ይቀራቸው ነበር። ለዚህም ነው ጳውሎስ ለእነርሱና ለእኛ የጸለየው።

ጳውሎስ በእርሱ አገልግሎት ወደ ክርስቶስ የተመለሱት ሰዎች እንዲያገኙ የሚፈልጋቸውን በረከቶች እስር ቤት ሆኖ ባቀረበው ጸሎቱ ውስጥ እንመለከታለን (ኤፌ. 1፡15–23፤ 3፡14–21፤ ፊልጵ. 1፡9–11፤ ቆላ. 1፡9–12)። የጳውሎስ ጸሎት መንፈሳዊ ዓይናቸው ተከፍቶ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ነገር እንዲያስተውሉ እንጂ ምድራዊ ሀብት እንዲያገኙ አይደለም። ጳውሎስ የሚጸልየው እግዚአብሔር የሌላቸውን ነገር እንዲሰጣቸው ሳይሆን ያላቸውን እንዲያሳያቸው ነበር።

ጳውሎስ የልቡናቸው ዓይኖች እንዲከፈቱ ባቀረበው ጸሎት ውስጥ ያካተታቸውን አራት ጥያቄዎች ከመመልከታችን በፊት ሁለት እውነቶችን ማጤን ይኖርብናል። በመጀመሪያ ደረጃ አብርሆት የሚመጣው ከመንፈስ ቅዱስ ነው። እርሱ «የጥበብና የመገለጥ መንፈስ» ነው (ኢሳ. 11፡2፤ ዮሐ. 14፡25–26፤ 16፡12–14)። ሰው በተፈጥሮአዊ አእምሮው የእግዚአብሔርን ነገሮች ሊረዳ አይችልም። ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ የልቦናውን ዓይኖች ሊያበራለት ይገባል (1ኛ ቆሮ. 2፡9–16)። መንፈስ ቅዱስ ከቃሉ ውስጥ እውነትን በመግለጥ የምንረዳበትንና ተግባራዊ የምናደርግበትን ጥበብ ይሰጠናል። በተጨማሪም በእውነት እንኖር ዘንድ ያስችለናል (ኤፌ. 3፡14–21)።

ሁለተኛው ይህ አብርሆት ወደ አማኙ ልብ ይመጣል (1፡18)። «የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ» የሚለው የሚያሳስበንም ይሄንኑ ነው። ልብ የሰው ስሜታዊ ክፍል እንደሆነ እናውቃለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ግን ልብ ውስጣዊ ሰው ሲሆን ስሜትን፥ አእምሮንና ፈቃድን ያጠቃልላል። ውስጣዊው ሰው ይኸውም ልብ እንደ አካላዊ ሕዋሳት ሁሉ መንፈሳዊ ክፍሎች አሉት። ውስጣዊው ሰው *ሊያይ* [መዝ. (119)፡18፤ ዮሐ. 3፡3]፥ ሊሰማ (ማቴ. 13፡9፤ ዕብ. 5፡11)፥ *ሊቀምስ* [መዝ. (34)፡8፤ 1ኛ ጴጥሮስ 2፡3]፥ *ሊያሸትና* (ፊልጵ. 4፡18፤ 2ኛ ቆሮ. 2፡14) *ሊዳስስ* ይችላል (የሐዋ. 17፡27)። ኢየሱስ ስለ ሕዝቡ፥ «እያዩ ስለማያዩ፥ እየሰሙ ስለማይሰሙ» ሲል ይህንን መጥቀሱ ነበር (ማቴ. 13፡13)። መንፈሳዊ ነገሮችን አይቶ አለማስተዋል የልብ እንጂ የአእምሮ ዕውቀት አይደለም። የልባችን ዓይኖች በእግዚአብሔር መንፈስ ሊገለጡ ይገባል።

ጳውሎስ የኤፌሶን አማኞች ዓይኖች ተከፍተው አራት መንፈሳዊ እውነቶችን እንዲያስተውሉ ይጸልያል።

1. እግዚአብሔርን ያውቁ ዘንድ (1:17)። ይህ ከሁሉም የላቀ እውነት ነው። ኢአማንያን እግዚአብሔር እንደሌለ ሲናገሩ፥ አግኖስቲኮች ደግሞ እግዚአብሔር ቢኖርም ልናውቀው እንደማንችል ይናገራሉ። ጳውሎስ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እግዚአብሔርን ስላወቀ፥ እግዚአብሔርን ሳያውቁ ስለሌሎች ነገሮች ብዙም መረዳት እንደማይቻል ያምናል።

ይህ እግዚአብሔርን ሆን ብሎ አላውቅህም ማለት ሰዎችን ለውድቀትና ለጥፋት ዳርጓል። ጳውሎስ በሮሜ 1 ከቁጥር 18 ጀምሮ የሰዎችን ውድቀት ይዘረዝራል። እግዚአብሔርን ለማወቅ ካለመፈለግ ወደ አምልኮተ ጣዖት (እውነትን በሐሰት መለወጥ) ወደ ምግባረ ብልሹነትና ሌሰኝነት ዘቅጠዋል። ይህ ሁሉ ከየት ጀመረ? የጀመረው እግዚአብሔር ፈጣሪ፥ ሕይወት ሰጭ፥ አስተዳዳሪ፥ አዳኝና ዳኛ መሆኑን ለማወቅ ካለመፈለግ ነው።

አማኙ እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግ አለበት። እግዚአብሔርን በግል ማወቅ ደኅንነት ነው (ዮሐ. 17:3)። እግዚአብሔርን ይበልጥ እያወቁ መሄድ ቅድስና ነው (ፊልጵ. 3:10)። እግዚአብሔርን በፍጹም ማወቅ ክብረት ነው (1ኛ ቆሮ. 13:9-12)። በእግዚአብሔር አምሳል ስለተፈጠርን (ዘፍጥ. 1:26-28)፥ እግዚአብሔርን ይበልጥ ባወቅን መጠን ራሳችንንና ሌሎችን በተሻለ መንገድ እናውቃለን። እግዚአብሔርን እንደ አዳኝ ብቻ ሳይሆን እንደ አባት፥ ጓደኛና መሪም ልናውቀው ይገባል። ይበልጥ ባወቅነው መጠን መንፈሳዊ ሕይወታችንም ይበልጥ መልካም ይሆናል።

አንድ ቀን መጽሐፍ ቅዱስ አስተምሬ እንደጨረስሁ አንድ አማኝ፥ «በመምጣቴ ደስ ብሎኛል» ለዚያ ክፉ ጎረቤቴ የምጠቀማቸውን ሁለት ጥቅሶች አግኝቻለሁ!» አለኝ። የእግዚአብሔር ቃል ጠላትን ለማጥቃት እንደ ሰይፍ የምንጠቀምበት ጊዜ ቢኖርም መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ግን ለዚህ ዓላማ አይደለም። አንድ የታወቀ መዝሙር፥ «ከተቀደሰው መጽሐፍ በስቲያ አንተን እሻለሁ። ሕያው ቃል ሆይ፥ መንፈሴ አንተን ይጠማል።» ይላል።

2. የእግዚአብሔርን ጥሪ እናውቅ ዘንድ (1:18)። «ጥሪ» በክርስቲያኖች ዘንድ በጣም አስፈላጊ ነው። «ቤተ ክርስቲያን» የሚለው የግሪክ ቃል «ተጠርተው» የወጡ የሚል ፍች ካላቸው ሁለት የግሪክ ቃላት የተመሠረተ ነው። ጳውሎስ እግዚአብሔር «በጸጋው» እንደ ጠራው ደጋግሞ ገልጾአል (ገላ. 1:15)። ለጢሞቴዎስም አማኞች «ቅዱስ ጥሪ» እንዳላቸው አስታውቆአል (2ኛ ጢሞ. 1:9)። እኛንም «ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን» (1ኛ ጴጥ. 2:19) እና ለክብር ጠርቶናል (2ኛ

ጴጥ. 1፡3)። እግዚአብሔር የሚጠራን በጸጋው እንጂ ከእኛ በሆነ አንዳች ነገር አይደለም።

ጳውሎስ ከዚህ ጥሪ የተነሣ የእኛ የሆነውን ተስፋ እንድንገነዘብ ይሻል (ኤፌ. 4፡4)። አንዳንድ ጥሪዎች የተስፋ ምንጭ የላቸውም። እኛ በክርስቶስ ያለን ጥሪ ግን በደስታ የተሞላ ጥሪ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተስፋ ይህ ይሆንልኛል ወይም ይሰጠኛል ብለን ተስፋ የምናደርገው ነገር ዓይነት እንዳልሆነ መገንዘብ ያሻል፤ ልክ አንድ ልጅ በገና በዓል ጊዜ እንደሚሰጠው ስጦታ። ቃሉ የተረጋገጠ ተስፋ ይዟል። የአማኞች ተስፋ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መምጣት ነው (1ኛ ተሰ. 4፡13-18፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡1-3)። በኃጢአታችን ምክንያት ከደኅንነት ርቀን በጠፋን ጊዜ «ያለተስፋ» ነበርን (ኤፌ. 2፡12)። ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ዕለት በዕለት የሚያበረታታን «ሕያው ተስፋ» አለን (1ኛ ጴጥ. 1፡3)።

ዶክተር ኬነት ካፊን የሚባሉ የታወቁ የባፕቲስት ደራሲ አባሎቻቸውን ለመጎብኘት ከከተማ ወጣ ብሎ ወደሚገኘው ውብ አካባቢ ስለሄዱ አንድ መጋቢና ዲያቆን የሚናገሩት ታሪክ አላቸው። ሁለት ውድ መኪኖች በግቢው ውስጥ ቆመዋል፤ በመስኮቱ አሻግረው ሲያዩ የሚኅበኙት ሰውዬ በምቹ ወንበር ላይ ተቀምጦ ባለ ቀለም ቴሌቪዥን ሲያይ ተመለከቱ። ዲያቆኑ ወደ መጋቢው ዘወር ብሎ፥ «ለዚህ ሰው የሚሆን ምን ዓይነት መልካም የምሥራች አለን?» ሲል ጠየቀ።

ብዙውን ጊዜ ምድራዊውን ሀብት ከዘላለማዊው ሀብት ጋር እናምታታዋለን። ኤፌሶን ሀብታም ከተማ ነበረች። ከጥንቱ ዓለም አስደናቂ ነገሮች መካከል አንዱ የሆነው የዳያና ቤተ ጣዖት የሚገኘው በዚህች ከተማ ነው። ዛሬ ኤፌሶን የሥነ ቅርስ ተመራማሪዎች ገነት ስትሆን፥ ሀብቷና ክብሯ ሁሉ ወድሞአል። በአንድ ወቅት በዚያ የነበሩ ክርስቲያኖች ዛሬ በመንግሥተ ሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር ደስ እየተሰኙ ናቸው!

የመጥራቱ ተስፋ የሕይወታችን አንቀሳቃሽ ኃይል በመሆኑ፥ ንጹሐን (1ኛ ዮሐ. 2፡28-3፡3)፥ ታዛዦች (ዕብ. 13፡17) እና ታማኞች እንድንሆን ሊያበረታታን ይገባል (ሉቃ. 12፡42-48)። አንድ ቀን ክርስቶስን አይተን እርሱን የምንመስል የመሆናችን እውነት ዛሬ ክርስቶስን እንድንመስል ሊያነቃቃን ይገባል።

3. የእግዚአብሔርን ባለጸግነት እናውቅ ዘንድ (1፡18)። ይህ ሐረግ የሚያመለክተው እኛ በክርስቶስ ያለንን ርስት ሳይሆን (1፡11)፥ እርሱ በእኛ ያለውን ርስት ነው። እግዚአብሔር እኛን የታላቅ በረከቱ አካል

አድርጎ መመልከቱ አስደናቂ ነው! አንድ ሰው ሀብቱ ክብርን እንደሚያመጣለት ሁሉ እግዚአብሔርም ለእኛ ከሰጠን በረከት የተነሣ ከቤተ ክርስቲያን ክብርን ያገኛል። ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ «የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ» ምክንያት እንሆናለን (1፡6)።

እግዚአብሔርም በእኛ ሕይወት ሥራውን የሚሠራው በቀደመው ታሪካችን መሠረት ሳይሆን በወደፊቱ ታሪካችን መሠረት ነው። ፍርሃት ለሚንጠው ጌዴዎን፥ «አንተ ጽኑዕ ኃያል ሰው፥ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው» ብሎታል (መሳ. 6፡12)። ኢየሱስ ለእንድርያስ ወንድም «አንተ. . . ስምዖን ነህ፤ አንተ ኬፋ [ዓለት] ትባላለህ» ብሎታል (ዮሐ. 1፡43)። እንደተባለውም ጌዴዎን ጽኑና ኃያል፥ ጴጥሮስም ዓለት ሆኖአል። እኛ ክርስቲያኖች ክርስቶስ ሲመለስ ወደፊት በምንሆነው ሁኔታ ቁጥጥር ሕይወታችንን እንመራለን። የእግዚአብሔር ርስት በመሆናችን እርሱን ለማስደሰትና ለማክበር እንኖራለን።

ከዚህ እውነት እንደምንረዳው፥ ቤተ ክርስቲያን ይህን በረከት ካልተካፈለች፥ ክርስቶስ ወደተነገረለት ክብር አይገባም። ከመሞቱ በፊት ለዚህ ጉዳይ የጸለየ ሲሆን፥ ጸሎቱም ይሰማለታል (ዮሐ. 17፡24)። ክርስቶስ ገና ይከብራል (2ኛ ተሰ. 1፡10)፤ እኛም በእርሱ እንከብራለን (ቆላ. 3፡4)። ይህንን እውነት መረዳት አማኞችን ወደ ተሰጠና ለጌታ ወደ ተገዛ ሕይወት ሊመራቸው ይችላል።

4. የእግዚአብሔርን ኃይል እናውቅ ዘንድ (1፡19–23)። እግዚአብሔር እኛን ርስቱ በማድረግ ፍቅሩን አሳይቶናል። ግሩም የተስፋ ቃል በመስጠት ተስፋችንን ሕያው አድርጓል። ጳውሎስ እምነታችንን ሊያጸና ፈልጎ፥ «ለምናምንም ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን» ሲል ጽፎአል (ቁ. 19)። ይህ እጅግ ታላቅ እውነት በመሆኑ ጳውሎስ አሳቡን በግልጽ ለማስቀመጥ ሲል በርካታ የተመረጡ የግሪክ ቃላትን ተጠቅሞአል፤ እነርሱም «ዱናሚስ»፥ (ኃይል፤ ልክ ዲናሞና ድማሚት እንዳላቸው ዓይነት ኃይል)፤ «ኤነርጂያ» (አሠራር፤ አንድ ኃይል እንደሚሠራው ዓይነት)፤ «ክራቶስ» (ጉልበት)፤ «ኢስከስ» (ኃይል) ናቸው። ቁጥር 19 «እንደ ብርታቱ ኃይል አሠራር ለእኛ ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንደሆነ ታውቁ ዘንድ ነው» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ጳውሎስ የሚናገረው ለእኛ ስለተሰጠን መለኮታዊ ኃይልና፥ ዘላለማዊ ጉልበት ነው!

ባለህ ሀብት ለመጠቀም የማትችል ምስኪን ከሆንህ፥ ሀብትህ ምን ይሠራልሃል? ወይም ደግሞ ዘራፊዎች ይነጥቁኛል ብለህ የምትሰጋ

ከሆንህ፥ ምን ረብ ይሰጥሃል? ጆን ዲ. ሮክፌለር የዓለም የመጀመሪያው ቢልየነር ነበሩ። እኚህ ሰው ስለ ሀብታቸው ብዙ ከመጨነቃቸው የተነሣ ለጨጓራ በሽታ በመዳረጋቸው ከብስኩትና ወተት በቀር አይበሉም ነበር ይባላል። ሌሊት ጥሩ እንቅልፍ ተኝተው አያድሩም። ዘበኞቹ ከደጃፍ አካባቢ አይጠፉም። ሀብታም- ግን ስኪን! በከፍተኛ የምግባረ ሰናይ ተግባር በመሳተፍ ሀብታቸውን ለድሆች ማካፈል በጀመሩ ጊዜ ግን ጤንነታቸው መሻሻል በማሳየቱ እስከ እርጅናቸው ድረስ በሰላም ሊኖሩ ችለዋል።

እኛ ክርስቲያኖች ለብዙ ነገሮች ኃይል ያስፈልገናል። በመጀመሪያ ደረጃ ይህንን ሀብት ለማድነቅ፥ የራሳችን ለማድረግና እንደሚገባም ለመጠቀም በተፈጥሮአችን በጣም ደካሞች ነን። «መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው» (ማቴ. 26:41)። ይህንን ታላቅ መንፈሳዊ ሀብት ለተራ ሰው መስጠት፥ ለሁለት ዓመት ልጅ አቶሚክ ቦምብን እንደ መስጠት ነው። የእግዚአብሔር ኃይል የእግዚአብሔርን በረከት እንድንጠቀም ያስችለናል።

ይሁንና የእግዚአብሔርን ኃይል የምንሻበት ሌላም ምክንያት አለ። በረከታችንን ለመንጠቅ የሚፈልጉ ጠላቶች አሉ (ኤፌ. 1:21፤ 6:11-12)። እነዚህን መንፈሳዊ ጠላቶች በምንም ዓይነት በራሳችን ኃይል ልናሸንፋቸው አንችልም። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ግን ልናሸንፋቸው እንችላለን። ጳውሎስ በረከታችንን በሚገባ እንድንጠቀምና ጠላትም እንዳይዘርፈን የእግዚአብሔርን ኃይል ታላቅነት እንድንገነዘብ ይሻል።

ኃይሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ውስጥ ታይቷል። በብሉይ ኪዳን ሰዎች የእግዚአብሔርን ኃይል ይለኩ የነበረው በፍጥረቱ (ኢሳ. 40:12-17) ወይም የእስራኤላውያንን ከግብፅ አውጥቶ ወደ ከነዓን ለመውሰድ በፈጸመው ተአምር ነበር (ኤር. 16:14)። ዛሬ ግን የእግዚአብሔርን ታሪክ የምንለካው በክርስቶስ የትንሣኤ ተአምር ነው። ክርስቶስን ከሞት ማስነሣቱ ብቻ ሳይሆን ብዙ ተግባራትም ተከናውነዋል። ከነዚህም መካከል አንዱ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ዐርጎ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ መቀመጡ ነው። እርሱ አዳኝ ብቻ ሳይሆን ልዑልም ነው (የሐዋ. 2:25-36)። ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስን የሚልቅ ምንም ዓይነት የሰው ወይም የመንፈስ ሥልጣን ወይም ኃይል በዓለም የለም። እርሱ ከሁሉም እጅግ ይልቃል። ከኃይላት ሁሉ በላይ ስለሚልቅ ወደፊትም የሚያሸንፈው ኃይል የለም።

ይህ ግን ዛሬ ከአንተና ከእኔ ሕይወት ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው? በቁጥር 22 እና 23 ላይ ጳውሎስ ተግባራዊ መልስ ይሰጠናል። አማኞች በመሆናችን የክርስቶስ አካል በሆነችው ቤተ ክርስቲያን

ውስጥ እንገኛለን። እርሱ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው። ይህም በአንተና በክርስቶስ መካከል ሕያው ግንኙነት እንዳለ ያመለክታል። አካልን የወሰድን እንደሆነ፥ ሰውነትን የሚቆጣጠረውና በትክክል እንዲሠራ የሚያደርገው ራስ ነው። የተወሰኑ የአእምሮ ክፍሎች ከተጎዱ ተጓዳኝ የአካል ክፍሎች ሽባ ይሆናሉ። ክርስቶስ መንፈሳዊ ራሳችን ነው። በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እንደ አካሉ ክፍሎች ከእርሱ ጋር ተጣብቀናል። ይህም ማለት ትንሣኤውን፥ ዕርገቱንና ክብሩን እንጋራለን ማለት ነው። (ጳውሎስ ወደ ኋላ ላይ የዚህን አሳብ ምንነት በስፋት ያብራራል።) እኛ በሰማያዊ ስፍራ ስለ ተቀመጥን (2፥6) ሁሉንም ነገር ከእግራችን በታች ሆኗል።

ጳውሎስ «ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንደሆነ» እናውቅ ዘንድ መፈለጉ የሚያስደንቅ አይሆንም። ያለዚህ ኃይል በክርስቶስ ያለንን ታላቅ በረከት ልንጠቀም አንችልም።

አንድ ባል የግል መዝገቡን በመጠቀም ሚስቱ ብድሩን ለመክፈል ትችል ዘንድ ፊርማውን ያኖርላት ዘንድ ለማግባባት ከቤተ ክርስቲያን ሰዎች ጋር ወደ ሆስፒታል የሄድንበትን ዕለት አልዘነጋውም። ሰውዬው ከመድከሙ የተነሣ ሊፈርም አልቻለም። በሰነዱ ላይ የሆነ ምልክት ለማድረግ እንኳ የዓይን ምስክሮች መጠቀም ነበረባት። በአካል መድከሙ ሀብቱን እንዳትጠቀም እንዳትችል ሊያደርጋት ነበር።

ክርስቲያኖች ሁሉ ከሞት በተነሣውና ወደ ሰማይ ባረገው በክርስቶስ አማካይነት የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በእምነት ሊቀበሉ ይችላሉ። ኃይሉ ለምናምን ሁሉ ተሰጥቶናል (ቁ. 19)። ይህን በረከት የሚያዘጋጅልን ጸጋ ነው፤ ሆኖም የሚያስጨብጠን ግን እምነት ነው። «ጸጋው በእምነት» አድኖናል (ኤፌ. 2፥8–9)። «ጸጋው በእምነት» ያኖረናል (1ኛ ቆሮ. 15፥10)።

በአራቱ ወንጌላት ውስጥ የእግዚአብሔር ኃይል በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሲሠራ እንመለከታለን። በሐዋርያት ሥራ ደግሞ ያው ተመሳሳይ ኃይል የክርስቶስ አካል በሆኑት ተራ የቤተ ክርስቲያን አባላት ሲሠራ እንመለከታለን። በወንጌላት መጨረሻና በሐዋርያት ሥራ መጀመሪያ መካከል በጴጥሮስ ሕይወት ውስጥ የተፈጸመው ለውጥ አስደናቂ ነው። ልዩነቱን ያስከተለው ምንድን ነው? የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ ኃይል ነው (የሐዋ. 1፥8)።

ዛሬ ትልቅ የኃይል እጥረት ያለው በጀነሬተሮቻችን ወይም በጋዝ ማጠራቀሚያዎቻችን ሳይሆን በግል ሕይወታችን ነው። የጳውሎስ ጸሎት በሕይወትህ ምላሽ ያገኘ ይሆን? ከዛሬ ጀምሮ እግዚአብሔርን ይኸውም የእግዚአብሔርን ጥሪ፥ የእግዚአብሔርን ብልጽግናና የእግዚአብሔርን ኃይል በመለማመድ ልታውቀው ትፈቅዳለህን?

## ኤፌሶን 2፡1-10።

በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ በእነርሱም፥ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው። በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን፤ እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን። ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ፥ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፥ በጸጋ ድናችኋልና፥ በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ፥ ከእርሱ ጋር አስነሣን፤ በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን። ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም። እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።

# 4

# ከመቃብሩ ውጡ

ጳውሎስ በክርስቶስ ያገኘነውን መንፈሳዊ በረከት ከገለጸ በኋላ ወደ አንድ ዋና እውነታ ማለትም በክርስቶስ ወዳገኘነው መንፈሳዊ ስፍራ ይሸጋገራል። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለኃጢአተኞች ሁሉ ምን እንዳደረገ ይናገራል። ከዚያም ለአሕዛብ በተለይ ምን እንዳደረገ ይገልጻል። በክርስቶስ የሚያምን ከሞት ተነሥቶ ከዙፋን ላይ ተቀምጦአል (2፡1–10)። የሚያምኑ አይሁዶችና አሕዛብ ዕርቅን አግኝተው ወደ ቤተ መቅደሱ ተቀላቅለዋል (2፡11–22)። ይህ እንዴት ያለ ታላቅ የእግዚአብሔር ጸጋ ተአምር ነው! ከታላቅ የኃጢአት መቃብር ወጥተን በክብር ዙፋን ላይ ተቀምጠናል።

ምናልባትም ይህንን ረዥም አንቀጽ ለማብራራት ቀላል የሚሆነው ከውስጡ አራት ውስን ሥራዎችን መለየቱ ይሆናል።

## 1. የኃጢአት ተቃውሞ (2፡1–3)

አንድ አሳታሚ የካሴት መልእክቶቼን ለማሰራጨት እንዲችል ሙሉ ታሪኬን የሚያሳይ ፎቶግራፍ እንድሰጠው ጠየቀኝ። አንድ ወዳጄ ፎቶዬን አነሣ። ይህ ለእኔ አዲስ ልምምድ ነበር። ጉርድ ፎቶግራፍ የመነሣት ልምድ ቢኖረኝም፥ መላው እኔነቴን የሚያሳይ ፎቶግራፍ መነሣቱ ግን አንዲስ ነገር ነበር። እግሮቼ፥ ክንዶቼና እጆቼ በትክክለኛ ስፍራ መሆን ነበረባቸው። ደግነቱ ፎቶ አንሺው ወዳጄ የታወቀ ባለሙያ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተስማሚ ፎቶግራፍ ለማግኘት ተቻለ። በእነዚህ ሦስት ቁጥሮች ጳውሎስ ያልዳነውን ሰው አስከፊ መንፈሳዊ ሁኔታ በስፋት (ሙሉ በሙሉ) ያቀርብልናል። እስቲ የዚህን ባሕርይ እናጢን።

*ይህ ሰው ሙት ነው* (2፡1)። ይህ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ የሞተ ማለትም መንፈሳዊ ነገሮችን ለመረዳትና ለማስተዋል የማይችል ነው። መንፈሳዊ ሕይወት ስለሌለው እግዚአብሔርን ሊያስደስት አይችልም። በሥጋው የሞተ ሰው ከሰውነቱ ለሚመጡ መልእክቶች ምላሽ ሊሰጥ እንደማይችል ሁሉ በመንፈሱ የሞተው ሰው ለመንፈሳዊ ነገሮች ምላሽ ሊሰጥ አይችልም። አንድ አስከሬን በቀብር ስፍራ የሚደረገውን ውይይት አይሰማም። የመብላት ወይም የመጠጣት ፍላጎት የለውም። ሕመም አይሰማውም፤ ሞቶአልና። ደኅንነትን ያላገኘው ሰው፥ ውስጣዊ ነገሩም ልክ እንዲሁ ነው። መንፈሳዊ አካላቱ በሥራ ላይ

ካለመሆናቸውም በላይ እግዚአብሔር ሕይወትን እስኪሰጣቸው ድረስ ምንም ዓይነት ተግባር ሊያከናውኑ አይችሉም። «እያዩ ስለማያዩ እየሰሙ ስለማይሰሙ ስለማያስተውሉም. . .» (ማቴ. 13፡13)። የዚህ መንፈሳዊ ሞት መነሾው «በደልና ኃጢአት» ነው (ኤፌ. 2፡1) «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው» (ሮሜ 6፡23)። በመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ሞት ማለት መለየት ማለት ነው። ይህም መንፈስ ከሥጋ የሚለይበት አካላዊ ሞት ብቻ ሳይሆን መንፈስ ከእግዚአብሔር የሚለይበት መንፈሳዊ ሞትም ጭምር ነው (ኢሳ. 59፡2)።

የማያምን ሰው በሽተኛ ሳይሆን ሙት ነው። የሚያስፈልገው ትንሣኤ እንጂ አእምሮን ከመሳት መንቃት አይደለም። ደኅንነት ያላገኙ ኃጢአተኞች ሁሉ ሙታን ሲሆኑ፥ አንዱ ከሌላው የሚለየው በመበስበስ ደረጃው ብቻ ነው። አንድ ያልዳነ በረንዳ አዳሪ ሰው በውጫዊ ሁኔታው ሲታይ ካልዳነው የማኅበረሰብ መሪ ይበልጥ የተበላሸ ቢመስልም፥ ሁለቱም በኃጢአት ሞተዋል። ስለሆነም አንዱ አስከሬን ከሌላኛው የበለጠ ሙት ሊሆን አይችልም! ይህም ዓለማችን በቁማቸው በሞቱ ሰዎች የተሞላች ታላቅ መቃብር ቤት እንደሆነች ያመለክታል (1ኛ ጢሞ. 5፡6)።

*አይታዘዝም* (2፡2–3)። የሰው መንፈሳዊ ሞት የሚጀምረው ከዚሁ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ካለመታዘዝ ነው። እግዚአብሔር፥ «ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና» ብሎአል (ዘፍጥ. 2፡17)። ሰይጣን ግን «ሞትን አትሞቱም» አለ (ዘፍጥ. 3፡4)። የመጀመሪያዎቹ ወንድና ሴት ይህንን ውሸት ባመኑ ጊዜ ወዲያውኑ በመንፈሳቸው ሲሞቱ፥ የኋላ ኋላም ለሥጋዊ ሞት ተዳርገዋል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጅ ለእግዚአብሔር ጀርባውን ሰጥቶ በመኳዝ ላይ ይገኛል። ሰዎች እምቢተኞች እንዲሆኑ የሚገፋፉአቸው ሦስት ኃይሎች አሉ። እነርሱም ዓለም፥ ዲያብሎስና ሥጋ ናቸው። ዓለም ወይም የዓለም ዘይቤ እያንዳንዱ ሰው ከዓለም ሥርዓት ጋር እንዲስማማ ተጽዕኖ ያሳድራል (ሮሜ 12፡2)። ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ ዓለም አልነበረም። ሕዝቡም እንዲሁ ከዚህ ዓለም አይደሉም (ዮሐ. 8፡23፤ 17፡14)። ደኅንነትን ያላገኘ ሰው ግን አውቆም ሆነ ሳያውቅ በዚህ ዓለም እሴቶችና አመለካከቶች ቁጥጥር ሥር ይኖራል።

ዲያብሎስ በዚህ ዘመን በማይታዘዙ ልጆች መካከል ይሠራል። ይህ ማለት ግን ሰይጣን በእያንዳንዱ የማያምን ሰው ሕይወት ውስጥ ይሠራል ማለት አይደለም። ሰይጣን ፍጡር እንደ መሆኑ በስፍራ የተወሰነ ነው። በሁሉም ስፍራ ከሚገኘው አምላክ በተቃራኒ፥ ሰይጣን በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ ሊገኝ አይችልም። ነገር ግን የእርሱ ተባባሪ በሆኑት አጋንንትና (ኤፌ. 6፡11–12) በዓለም ሥርዓት ላይ

ባለው ኃይል አማካይነት (ዮሐ. 12፡31) ሰይጣን በማያምኑት ሰዎች ሕይወት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። በሚያምኑትም ላይ ይህንኑ ለማድረግ ይሻል። ሰዎችን «የዓመፃ ልጆች» ለማድረግ ይፈልጋል (ኤፌ. 2፡2፤ 5፡6)። እርሱ ራሱ ለእግዚአብሔር ታዛዥ ስላልነበረ፥ ሌሎችም ለእግዚአብሔር እንዳይታዘዙ ለማድረግ ይጥራል።

ሰዎች እግዚአብሔርን እንዳይታዘዙ ለማድረግ ሰይጣን ከሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች አንዱ ውሸት ነው። ሰይጣን ውሸታም ነው (ዮሐ. 8፡44)። በሰው ልጅ ታሪክ መጀመሪያ ላይ የሰውን ዘር ወደ ኃጢአት የሳበው ይኸው «ሞትን አትሞቱም» የሚለው የሰይጣን ውሸት ነበር። ዛሬ ደኅንነትን ያላገኙ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎች እግዚአብሔርን የማይታዘዙት የሰይጣንን ውሸት ስለሚያምኑ ነው። አንድ ሰው ውሸትን በሚያምንበት ጊዜ የዓመፅ ልጅ ይሆናል።

የማያምኑ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዳይታዘዙ የሚያነሣሣቸው ሦስተኛው ኃይል ሥጋ ነው። ጳውሎስ ሥጋ ሲል ሰውነትን ማለቱ አይደለም፤ ሰውነት በራሱ ኃጢአተኛ አይደለምና። ሥጋ የተባለው ሰውነትንና አእምሮን በመቆጣጠር እግዚአብሔርን እንዳንታዘዝ ለማድረግ የሚጥረውና አብሮን የተወለደው የወደቀው ተፈጥሮአችን ነው። በአንድ ወቅት አንድ ወንጌላዊ ወዳጄ «ውሻህ የሚያደርገውን የሚያደርገው ለምንድን ነው?» በሚል ርእስ ላይ ንግግር እንደሚያደርግ አስታወቆ ስለ ነበር ብዙ የውሻ ወዳጆች ሊሰሙት መጡ። በዚህ ጊዜ የተናገረው ነገር ብዙ ጊዜ ትኩረት የማይሰጠው አሳብ ነበር፤ «ውሻ የውሻን ባሕርይ የሚያሳየው የውሻ ተፈጥሮ ስላለው ነው።» በውሻ ውስጥ የድመት ባሕርይ እንደሚተላለፍ ማድረግ ቢቻል የድመትን ባሕርይ ማሳየቱ የማይቀር ነው። ኃጢአተኛ የኃጢአተኛን ባሕርይ የሚያሳየው ለምንድን ነው? ምክንያቱም የኃጢአት ባሕርይ ስላለው ነው [መዝ. (51)፡5፤ (38)፡3]። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን የኃጢአት ባሕርይ «ሥጋ» ሲል ይጠራዋል።

እንግዲህ ደኅንነትን ያላገኘ ሰው እግዚአብሔርን አለመታዘዙ ያስደንቅ ይሆን? እንዲያ ያለ ሰው የሚኖረው በዓለም፥ በሥጋና በሰይጣን ቁጥጥር ሥር ነው፤ እነዚህ ሦስቱ የእግዚአብሔር ጠላቶች ናቸው። የራሱን ባሕርይ ሊለወጥ ወይም ዓለምና ዲያብሎስን በራሱ ሊያሸንፍ አይችልም። ከውጭ ርዳታ ማግኘት አለበት። ይህ ርዳታ ሊመጣ የሚችለው ከእግዚአብሔር ብቻ ነው።

*መንፈሳዊ ነገርን ማስተዋል አይችልም* (2፡3)። ኃጢአተኛ ሰው የሚኖረው የሥጋን መሻትና የአእምሮን ምኞት ለማስደሰት ነው። ፍላጎቱ በኃጢአት የታሠረ በመሆኑ በኃጢአት የተሞላ ነው።

ደኅንነትን ያላገኘው ሰው መንፈሳዊ ነገርን ማስተዋል አይችልም ስንል ክፋትን ብቻ ይሠራል ወይም መልካምን ሊሠራ አይችልም ማለታችን አይደለም። ነገር ግን ደኅንነትን ለማግኘት ወይም የእግዚአብሔርን የቅድስና ደረጃ ለማሟላት የሚያስችል ተግባር ሊፈጸም አይችልም ማለታችን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ደኅንነትን ያላገኙ ኃጢአተኞች እርስ በርሳቸውና (ሉቃስ 6:33) ለልጆቻቸው (ሉቃ. 11:13) መልካምን እንደሚያደርጉ ተናግሯል፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔርን ሊያስደስት የሚችል መንፈሳዊ ተግባር ሊፈጽሙ አይችሉም። ከመርከቡ መሰበር በኋላ ጳውሎስና ጓደኞቹን የረዱት የመላጥያ አገር ሰዎች መልካም ተግባር እንዳከናወኑ ባይታበልም ገና ደኅንነትን ማግኘት ያስፈልጋቸው ነበር (የሐዋ. 28:1-2)።

*ጠፍቶአል* (2:3)። ከፍጥረታቸው የቁጣ ልጆች ናቸው! በተግባራቸውም የዐመፅ ልጆች ናቸው! ያልዳነ ሰው ቀድሞውኑ ተኰንኖአል (ዮሐ. 3:18)። ፍርዱ ገና ድሮ የተሰጠ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ግን ከምሕረቱ የተነሣ ፍርዱን አዘግይቶአል (2ኛ ጴጥ. 3:8-10)። ሰው ራሱን ሊያድን አይችልም። እግዚአብሔር ግን በጸጋው አማካይነት ሰዎችን ለማዳን የሚችል ሥራ ሠርቶአል። «ነገር ግን እግዚአብሔር!» እነዚህ ሦስት ቃላት የሚያመጡት ለውጥ ምንድን ነው? ይህ ወደ ሁለተኛው ተግባር ይመራናል።

## 2. እግዚአብሔር ስለ እኛ ያከናወነው ተግባር (2:4-9)

አሁን ትኩረት የተሰጠው በኃጢአተኛው ሰው ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ነው። «ደኅንነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው» (ዮናስ 2:9)። እግዚአብሔር ሰዎችን ከኃጢአት መዘዝ ለመታደግ ያከናወናቸው አራት ተግባራት በዚህ ክፍል ተዘርዝረዋል።

*ወደደን* (2:4)። በባሕርዩ «እግዚአብሔር ፍቅር ነው» (1ኛ ዮሐ. 4:8)። ፍቅር የባሕርይ ገንዘብ በመሆኑ ኃጢአተኞች ባይኖሩም እንኳ እግዚአብሔር በፍቅሩ ነዋሪ ነው። የነገረ መለኮት ምሁራን ፍቅር ከእግዚአብሔር ባሕርያት አንዱ እንደሆነ ይናገራሉ። ይሁንና እግዚአብሔር ሁለት ዓይነት ባሕርያት አሉት፤ አንደኛው የባሕርዩ ገንዘብ ሲሆን (ለምሳሌ እንደ ሕይወቱ፥ ፍቅር፥ ቅድስና)፥ ሁለተኛው ደግሞ ከሥነ ፍጥረቱ ጋር የሚጋራቸው አንጻራዊ ባሕርያቱ ናቸው። ለምሳሌ እግዚአብሔር በባሕርዩ እውነት ነው። ነገር ግን ከሰዎች ጋር ግንኙነት በሚያደርግበት ጊዜ ይህ ባሕርዩ ወደ ታማኝነት ይቀየራል። ቅድስናውም ወደ ጽድቅ ይቀየራል።

ፍቅር የእግዚአብሔር የባሕርዩ ገንዘብ ነው፤ ሆኖም ከሰዎች ጋር ግንኙነት በሚያደርገበት ጊዜ ጸጋና ምሕረት ይሆናል። «እግዚአብሔር

በምሕረቱ ባለጠጋ ነው» (2፡4)፤ በጸጋውም እንዲሁ ባለጠጋ ነው (2፡7)። እግዚአብሔር በምሕረቱና በጸጋው ባለጠጋ በመሆኑ ኃጢአተኞች ደኅንነትን ሊያገኙ ችለዋል። አንዳንድ ሰዎች በእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት እንጂ በፍቅሩ እንዳልዳንን ሲገነዘቡ ይደነግጣሉ። ከምሕረቱ የተነሣ የሚገባንን ቅጣት አይሰጠንም፤ ከጸጋው የተነሣ ደግሞ የማይገባንን ይሰጠናል። ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለሞተልን ነው። እግዚአብሔር ለኃጢአት ያለውን ጥላቻና ለኃጢአተኞች ያለውን ፍቅር የገለጸው በጎልጎታ ነው (ሮሜ 5፡8፤ ዮሐ. 3፡16)።

*ሕይወትን ሰጠን* (2፡5)። በኃጢአታችን ሙታን በነበርን ጊዜ ሕይወትን ሰጠን። እግዚአብሔር ይህንን መንፈሳዊ ትንሣኤ ያከናወነው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ቃሉን በመጠቀም ነው። በአራቱ ወንጌላት ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት ሰዎችን ከሞት እንዳስነሣ ተመዝግቦአል። እነዚህም የመበለቲቱ ልጅ (ሉቃ. 7፡11–17)፥ የኢያኢሮስ ልጅ (ዮሐ. 11፡41–46) እና አልዓዛር (ዮሐ. 11፡41–46) ናቸው። ሁሉንም ከሞት ያስነሣው ቃል በመናገር ነው፤ ቃሉም ሕይወትን ሰጣቸው። በእያንዳንዱ ከሞት የማስነሣት ተግባር «የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም» ነው (ዕብ. 4፡12)። እነዚህ ሦስት አካላዊ ትንሣኤዎች አንድ ኃጢአተኛ ቃሉን ሰምቶ በሚያምንበት ጊዜ የሚሆነውን መንፈሳዊ ትንሣኤ የሚያሳዩ ናቸው (ዮሐ. 5፡24)።

*መንፈሳዊ ትንሣኤያችን* ከክርስቶስ ጋር አንድ ስለሚያደርገን የላቀ ስፍራ የሚሰጠው ነው። እግዚአብሔር «ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን» የአካሉ ክፍሎች እንደ መሆናችን ከእርሱ ጋር ተሳስረናል (ኤፌ. 1፡19–20)።

*ከፍ ከፍ አደረገን* (2፡6)። ከሞት ተነሥተን በመቃብር አልተተውንም። ከክርስቶስ ጋር አንድ ስለሆንን ከእርሱ ጋር ከፍ ከፍ በማለት በሰማያዊ ስፍራ ዙፋኑን እንጋራለን። አካላዊ ስፍራችን በምድር ላይ ቢሆንም መንፈሳዊ ስፍራችን ግን በሰማይ ነው፤ «በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን።» እንደ አልዓዛር ሁሉ እኛም ከሞት ተጠርተን ከክርስቶስ ጋር እንድንቀመጥና ከእርሱም ጋር በደስታ እንድንኖር ተደርገናል (ዮሐ. 12፡1–2)።

*ይጠብቀናል* (2፡7–9)። ምንም እንኳ የተቀበልነው ደኅንነት ታላቅ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር እኛን የተቤዠን ከሲኦል ሊታደገን ስለፈለገ ብቻ አይደለም። እግዚአብሔር የተቤዠን በቤተ ክርስቲያን አማካይነት

የእግዚአብሔርን ጸጋ እንድናከብር ነው (ኤፌ. 1፡6፥ 12 እና 14)። ስለሆነም እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ የሚፈጽመው ዘላለማዊ ዓላማ ካለው፣ ለዘላለም ይጠብቀናል። የዳንነው በመልካም ሥራችን ባለመሆኑ በመጥፎ ሥራችንም ምክንያት አንጠፋም። ጸጋ ማለት ነፃ ስጦታ ማለት ነው፤ የዳንነው ከእኛ በሆነ ሥራ አይደለም። የዳንነው እግዚአብሔር በኢየሱስ በኩል በሠራው ሥራ ነው። ደኅንነት ከእግዚአብሔር የምንቀበለው ነፃ ስጦታ ነው። ደኅንነት የእግዚአብሔር ስጦታ እንጂ የድካም ዋጋ አይደለም።

ደኅንነት «በሥራ» ሊገኝ አይችልም፤ ምክንያቱም የደኅንነት ሥራ በመስቀል ላይ ተፈጽሟል። ደኅንነት ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ሥራ ነው፤ ደግሞም የተጠናቀቀ ሥራ ነው (የሐዋ. 17፡1-4፤ 19፡30)። በመሆኑም ልንጨምርበትም ሆነ (ዕብ. 10፡1-14)፤ ልንቀንስበት አንችልም። ኢየሱስ ክርስቶስ በሞተ ጊዜ የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ከላይ ወደ ታች ለሁለት ተከፈለ፤ ይህም ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰው መንገድ እንደተከፈተ ያመለክታል። ምድራዊ መሥዋዕቶች ከእንግዲህ ወዲህ አያስፈልጉም። አንዱ መሥዋዕት ማለትም የእግዚአብሔር በግ ታላቁን የደኅንነት ተግባር ፈጽሟል። ይህን ሁሉ ያደረገው እግዚአብሔር ነው። ያደረገውም በጸጋ ነው።

ኃጢአት ዘወትር ይቃወመናል፤ እግዚአብሔር ግን ዘወትር ይታደገናል። ይሁንና፥ መለወጥ ጅማሬ ብቻ ነው።

## 3.እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ የሚያከናውነው ተግባር (2፡10)

«እኛ ፍጥረቱ ነንና . . . መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።» «ፍጥረቱ» የሚለው ቃል «ፖይዬማ» ከሚል የግሪክ ቃል የተተረጎመ ሲሆን፥ ፍቹውም «ተሠርቶ የተጠናቀቀ» ማለት ነው። በሌላ አገላለጽ መለወጣችን ገና ጅማሬ እንጂ ፍጻሜ አይደለም። እኛ የእግዚአብሔር «አዲስ ፍጥረት» ነን (2ኛ ቆሮ. 5፡17)፤ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ዓይነት ሰው እንሆን ዘንድ በእኛ የጀመረውን ሥራ ይቀጥላል። ዓላማውም ክርስቶስን እንድንመስል ማድረግ ነው (ሮሜ 8፡29)።

እግዚአብሔር በእኛ የሚሠራው እንዴት ነው? በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው። ይኸውም «ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም» በእኛ ውስጥ በማድረግ ነው (ፊልጵ. 2፡13)። ክርስቶስ የመቤዠት ተግባሩን በመስቀል ላይ ከፈጸመ በኋላ ከሞት ተነሥቶ ወደ ሰማይ ዐርጎአል። በዚያም ያልተጠናቀቀውን ሥራ ይኸውም ቤተ ክርስቲያኑን ፍጹም የማድረግ ተግባር ያከናውናል (ኤፌ. 4፡7-16፤ ዕብ. 13፡20-21)። ክርስቶስ በዚህ ምድር ላይ ላለን ሕይወትና

አገልግሎት እያሠለጠነን ነው። ይህንንም ለማድረግ ሦስት ልዩ መሣሪያዎችን ይጠቀማል፦ የእግዚአብሔርን ቃል (1ኛ ተሰ. 2፡13)፥ ጸሎትን (ኤፌ. 3፡20-21) እና መከራን (1ኛ ጴጥ. 4፡11-14)። የእግዚአብሔርን ቃል ስናነብ፥ ስንረዳ፥ ስናሰላስልና ስንመገብ፥ ቃሉ ወደ ሕይወታችን ዘልቆ በመግባት ሕይወታችንን ያነጻል፥ ያለመልማል። በምንጸልይበት ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ያገለግለናል። መከራ ወደ ቃሉና ወደ ጸሎት ይመራናል። ዑደቱ በዚህ ዓይነት ይቀጥላል።

እጅግ በርካታ ክርስቲያኖች ትልቁ ነገር መለወጥ ብቻ እንደ ሆነና ይህንንም የሚከተል ሌላ ነገር እንደሌለ ያስባሉ። ይህ ግን ስሕተት ነው። እዚህ ላይ የአልዓዛርን ትንሣኤ በምሳሌነት ልንጠቀም እንችላለን። ኢየሱስ ክርስቶስ አልዓዛርን ከሞት ካስነሣው በኋላ፥ «ፍቱትና ይሂድ» ሲል ተናግሮአል (ዮሐ. 11፡44)። በሌላ አገላለጽ፥ «አሁን ይህ ሰው ሕይወት አለው። ከፈኑን አንሡለት!» እንደ ማለት ነው። ጳውሎስ በኤፌሶን 4፡22-24 ላይ እንዲህ ሲል ይናገራል፤ «ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፥ በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ፥ ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ»። በቆላስያስ 3፡1 ላይ ደግሞ «እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ . . . በላይ ያለውን እሹ» ይላል።

ያዳነንና ከኃጢአት መቃብር ያነሣን ይኸው የትንሣኤ ኃይል በየዕለቱ ለክርስቶስ እንድንኖርና እንድናከብረው ሊረዳን ይችላል። እግዚአብሔር ውድ ዋጋ ከፍሎ በመስቀል ላይ ስለ እኛ ታላቅ ተግባር አከናውኖአል። ዛሬ በጎልጎታ በተከፈለው ዋጋ ላይ በመመሥረት ክርስቶስን እንመስል ዘንድ በሕይወታችን ውስጥ በመሥራት ላይ ይገኛል። እግዚአብሔር መጀመሪያ ስለ እኛ ሳይሠራና እኛም በልጁ ሳናምን በፊት በውስጣችን ሊሠራ አይችልም። በየዕለቱ ቃሉን በማጥናትና በመጸለይ በቂ ጊዜ መውሰድና በመከራ ጊዜ ራሳችንን ለክርስቶስ አሳልፈን መስጠት የሚኖርብን ለዚህ ነው። እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ የሚሠራው በቃሉ፥ በጸሎትና በመከራ አማካይነት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ መርህ አያሌ ምሳሌዎችን ያቀርባል። እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት ከመሥራቱ በፊት ለ40 ዓመታት በእርሱ ውስጥ ሲሠራ ቆይቷል። ሙሴ በአገልግሎቱ መጀመሪያ አካባቢ ችኩልና በራሱ ጉልበት የሚተማመን ሰው ነበር። አንድ ግብጻዊ ገድሎ ለመሸሽ የተገደደበትም ወቅት ነበር። ይህ መቼም አንድ አገልግሎት ለመጀመር ውጤታማ አሠራር አለመሆኑ ግልጽ ነው። ነገር ግን ለ 40 ዓመታት በበረሃ ውስጥ ራሱን ዝቅ አድርጎ

የእረኝነት ተግባር በሚያከናውንበት ወቅት ሙሴ እግዚአብሔር በሕይወቱ ውስጥ ሲሠራ ተመለከተ። ይህም ለቀጣዮቹ 40 ዓመታት ለታላቅ አገልግሎት አዘጋጅቶታል።

ሌሎችም ምሳሌዎች አሉ። እግዚአብሔር ከፈርኦን ቀጥሎ ያለውን ሥልጣን እስኪሰጠው ደረስ ዮሴፍ ለአሥራ ሦስት ዓመታት ተሠቃይቶአል። ዳዊት በልጅነቱ ለንጉሥነት ቢሾምም ለብዙ ዓመታት በስደት ከተሠቃየ በኋላ ነው ከዙፋኑ ላይ የወጣው። ሐዋርያው ጳውሎስም እንኳ ከተለወጠ በኋላ በዓረቢያ በረሃ ሦስት ዓመታት አሳልፎአል። ይህም እግዚአብሔር ለአገልግሎት እያዘጋጀው የነበረበት ጊዜ መሆኑ አያጠራጥርም። እግዚአብሔር በእኛ በኩል ከመሥራቱ በፊት በውስጣችን መሥራት ይኖርበታል። ይህም ወደ አራተኛው ተግባር ያሸጋግረናል።

## 4. እግዚአብሔር በእኛ በኩል ይሠራል (2፡10)

«መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን»። ደኅንነት ያገኘነው በመልካም ሥራችን አይደለም፤ ይሁንና መልካም ሥራ ለመሥራት ድነናል። ታዋቂው የሥነ-መለኮት ምሁር ጆን ካልቪን፥ «የሚያጸድቀው እምነት ብቻ ነው፤ ነገር ግን የሚያጸድቅ እምነት ብቻውን ሊሆን አይችልም» ሲሉ ጽፈዋል። የዳንነው በእምነትና በመልካም ሥራ ሳይሆን በሚሠራ እምነት ነው። በዚህ ጭብጥ ላይ መሠረታዊ ትምህርት የሚሰጠው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ያዕቆብ ምዕራፍ 2 ነው። በዚህ ስፍራ ጸሐፊው የሚያድን እምነት ሁልጊዜ የተለወጠ ሕይወትን እንደሚያስከትል ያብራራል። እምነት አለኝ ማለት ብቻ በቂ አይደለም፤ እምነታችንን በሥራ ማሳየት አለብን።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ብዙ የተለያዩ ሥራዎች ይናገራል። ማዳን የማይችል «የሕግ ሥራ» አለ (ገላ. 2፡16፤3፡11)። እንዲሁም በገላትያ 5፡19-21 ላይ የተዘረዘሩ «የሥጋ ሥራዎች» አሉ። በዕብራውያን 6፡1 የተጠቀሰው «የሞት ሥራ» ወደ ሞት የሚመራ ሳይሆን አይቀርም። ምክንያቱም «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው» (ሮሜ 6፡23)። በቲቶ 3፡5 ላይ የተወሰነ «የጽድቅ ሥራ» ኃጢአተኞች ደኅንነትን ለማግኘት የሚፈጽሙት ሃይማኖታዊ ተግባር ወይም ሌላ መልካም ተግባር ነው። ኢሳይያስ «ጽድቃችን የመርገም ጨርቅ ነው» ብሎአል (ኢሳ. 64፡6)። ጽድቃችን የመርገም ጨርቅ ከሆነ ኃጢአታችን ምን ይመስል ይሆን!

ጳውሎስ በኤፌሶን 2፡10 ላይ የጠቀሰው ሥራ ሁለት ልዩ ባሕርያት አሉት። አንደኛው «መልካም» ሥራ ነው፤ ይህም «የጨለማ ሥራ» ወይም «ክፉ ሥራ» ከተባለው የሚለይ ነው። ቁጥር 10ን ከቁጥር 2

ጋር ብታነጻጽር ሰይጣን በማያምኑ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ስለሚሠራ ተግባራቸው መልካም እንዳልሆነ እንገነዘባለን። ነገር ግን እግዚአብሔር በአማኞች ሕይወት ውስጥ ስለሚሠራ ሥራዎቹ መልካም ናቸው። ሥራዎቹ መልካም የሆኑት እርሱ ራሱ መልካም ስለሆነ ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር አዲስ ባሕርይ ስለተቀበለና መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ስለሚሠራና በእርሱ አማካይነት እነዚህን መልካም ተግባራት ስለሚያከናውን ነው።

ብዙ ክርስቲያኖች በሕይወታቸው ውስጥ ለመልካም ሥራ የሚሰጡት ስፍራ አነስተኛ መሆኑ አሳዛኝ ነገር ነው። በመልካም ሥራ ስላልዳንን መልካም ሥራ ክፉ እንደሆነ ያስባሉ። ይህ ግን ስሕተት ነው። «መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ» (ማቴ. 5፡16)። ሠናይ ምግባራትን የምንከውነው እግዚአብሔርን ለማክበር እንጂ ለራሳችን ትምክሕት አይደለም። መልካም ሥራ የምንሠራው ራሳችንን ለማክበር ሳይሆን፥ እግዚአብሔርን ለማክበር ነው። ጳውሎስ ሞትን እንኳ የሚጠይቅ ቢሆንም ክርስቶስ በእርሱ እንዲከብር ፈቀደ (ፊልጵ. 1፡20-21)። መልካም ሥራ እንዲበዛልንና (2ኛ ቆሮ. 9፡8) በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እንድናፈራ ተመክረናል (ቆላ. 1፡10)። መጽሐፍ ቅዱስን ስናውቅ «ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀን» እንሆናለን (2ኛ ጢሞ. 3፡17)። አማኞች እንደመሆናችን መልካሙ ለማድረግ ልንቀና ይገባል (ቲቶ. 2፡14) መልካሙ ሥራችን ደግሞ ለእግዚአብሔር የምናቀርበው «መንፈሳዊ መሥዋዕት» ነው (ዕብ. 13፡16)።

እነዚህን መልካም ሥራዎች የምንሠራው እኛ እንዳልሆንን መገንዘቡ አስፈላጊ ነው። እነዚህ እግዚአብሔር በእኛ ልብ ውስጥ የሚያከናውናቸው ሥራዎች ናቸው። «ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና» (ፊልጵ. 2፡13)። ጳውሎስ መልካም ተግባር እንዲያከናውን ያደረገው «የእግዚአብሔር ጸጋ» ነው (1ኛ ቆሮ. 15፡10)። መልካም ሥራዎቻችን ዳግም ለመወለዳችን ማስረጃ ናቸው፥ «በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም» (ማቴ. 7፡21)። በተጨማሪም መልካም ሥራችን ደኅንነትን ላላገኙት ሰዎች ምስክርነት ይሰጣል (1ኛ ጴጥ. 2፡12)። ሰዎች እንዲሰሙንም ያደርጋል።

አንድ መጋቢ ወዳጄ በአቅራቢያዋ የሚገኘውን የጡረታ ቤት ስለምትጎበኝ አንዲት ክርስቲያን ሴት ያጫወተኝ ትዝ ይለኛል። አንድ ቀን አንድ ብቸኝነት የተሰማው ሰው የእራት ሳህኑን እየተመለከተ ፈዝዞ የተቀመጠ ሰው አየች። በርኅራኄ ስሜት፥ «የገጠመህ ችግር አለ?» ስትል ጠየቀችው። ሰውየውም «ችግር አለ?» ሲል መልሶ

ከጠየቃት በኋላ፥ «አዎ፥ አይሁዳዊ እንደመሆኔ ይህንን ምግብ ልበላ አልችልም!» አላት።

«ምን እንዲቀርብልህ ትሻለህ?» ስትል ጠየቀችው

«ትንሽ ሾርባ ባገኝ ጥሩ ነበር!» አላት።

ወደ ቤቷ ሄዳ ሾርባውን ሠርታ መጣችና ባለሥልጣናቱን አስፈቅዳ አቀረበችለት። በተከታታይ ሳምንታት የሚፈልገውን ዓይነት ምግብ ስታመላልስለት ሰነበተች። በመጨረሻም ባቀረበችለት ምስክርነት ሰውዬው በኢየሱስ ክርስቶስ አመነ። ሾርባውን ማዘጋጀት መንፈሳዊ መሥዋዕት ማለት እግዚአብሔርን የሚያከብር መልካም ሥራ ሊሆን ይችላል።

ይሁንና እነዚህ ተግባራት መልካም ብቻ ሳይሆኑ «የተዘጋጁም» ናቸው። «እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን» (ኤፌ. 2፡10)። ይህ ቃል በሌላ ስፍራ የተጠቀሰው በሮሜ 9፡23 ላይ ብቻ ነው፤ «በምሕረቱ ዕቃዎች ላይ የክብሩን ባለጠግነት ይገልጥ ዘንድ . . . » የማያምኑ ሰዎች የሚመላለሱት «በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ» ነው (ኤፌ. 2፡2)፥ አማኞች ግን እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን መልካም ሥራ በመሥራት ይመላለሳሉ።

ይህ እግዚአብሔር ለሕይወታችን ዕቅድ እንዳለውና በፈቃዱ በመመላለስ ዕቅዱን ተግባራዊ ማድረግ እንዳለብን ስለሚያመለክት አስደናቂ አሳብ ነው። ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የሚናገረው ምንም ብናደርግ ሕይወታችንን ስለሚቆጣጠር አንድ የማይታወቅ ኃይል አይደለም። እርሱ የሚናገረው ለእኛ መልካምን ነገር ስለሚያስበው ስለ ሰማያዊ አባታችን መልካም ዕቅድ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚመነጨው ከእግዚአብሔር ልብ ነው። «የእግዚአብሔር ምክር ግን ለዘላለም ይኖራል፤ የልቡም አሳብ ለልጅ ልጅ ነው» [መዝ. (33)፡11]። መንፈሱ ቃሉን ሲገልጥልን እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለውን ታላቅ ፈቃድ እንረዳለን (1ኛ ቆሮ. 2፡9–13)።

ይህንን ምዕራፍ ስናጠቃልል ሕይወታችንን እየገመገምን መቋጨት ጠቃሚ ነው። ከእነዚህ አራት ተግባራት የትኛውን እያከናወንህ ነው? በኢየሱስ ክርስቶስ ስላላመንህ ኃጢአት በሕይወትህ እየሠራ ነው? ከሆነ አሁኑኑ እመን! ለአንተ የሠራውን – በውስጥህ የሠራውን– በአንተ በኩል የሚሠራውን ተግባር እየተለማመድህ ነው?

የለበስኸው የከፈን ጨርቅ ነው? ወይስ የጸጋ? በክርስቶስ ባገኘኸው ነጻነት ደስ እየተሰኘህ ነው? ወይስ በአሮጌው ሕይወት ባሕርያት ታስረሃል? ክርስቲያን እንደመሆንህ፥ ከሞት ተነሥተህ ከዙፋኑ ላይ ተቀምጠሃል። በክርስቶስ ያለህን ስፍራ ተለማመድ! ቀደም ሲል ለአንተ የሠራው ጌታ በውስጥህና በአንተ አማካኝነት በመሥራት ለእግዚአብሔር ክብር የተሰጠ ሕይወት ያጎናጽፍህ ዘንድ ፍቀድለት።

ስለዚህ እናንተ አስቀድሞ በሥራ አሕዛብ የነበራችሁ፥ በሥጋ በእጅ የተገረዙ በተባሉት ያልተገረዙ የተባላችሁ፥ ይህን አስቡ፤ በዚያ ዘመን ከእስራኤል መንግሥት ርቃችሁ ለተስፋውም ቃል ኪዳን እንግዶች ሆናችሁ በዚህም ዓለም ተስፋን አጥታችሁ ከእግዚአብሔርም ተለይታችሁ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ። አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል። እርሱ ሰላማችን ነውና ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ፥ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው። መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ ለእናንተ ሰላምን፥ ቀርበው ለነበሩትም ሰላምን የምስራች ብሎ ሰበከ፤ በእርሱ ሥራ ሁላችንም በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና። እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም። በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤ በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ።

# 5

# ታላቅ የሰላም ተልእኮ

«ሰላም በዘመናችን! ሰላም በክብር!»

እነዚህን ቃላት የተናገሩት የብሪታኒያ ጠቅላይ ሚኒስተር የነበሩት ሰር ኔቪል ቻምበርሌይን መስከረም 1938 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) በጀርመን አገር ተደርጎ በነበረው ኮንፍራንስ ላይ ተካፍለው ሲመለሱ ነው። ቻምበርሌይን የአዶልፍ ሒትለርን ጥቃቶች እንዳስቆሙ እርግጠኛ ነበሩ። ይሁንና ከአንድ ዓመት በኋላ ሒትለር ፖላንድን በመውረሩ ሴፕተምበር 3 ቀን 1939 ብሪታኒያ በጀርመን ላይ ጦርነት በማወጁ የቻምበርሌይን ታላቅ የሰላም ተልዕኮ ተንኮታኮተ።

እንደምናየውና እንደምንሰማው ከሆነ አያሌ የሰላም ተልእኮዎች መና ቀርተዋል። ከ1500 ዓ.ዓ እስከ 850 ዓ.ም. ድረስ የተለያዩ አገሮች በመካከላቸው ሰላም ለመፍጠር 7,500 «ዘላለማዊ ቃል ኪዳኖችን» ተፈራርመዋል። ነገር ግን ከሁለት ዓመታት በላይ የቆየ ቃል ኪዳን የለም። ሁልጊዜ ሊኖር የሚችለው ብቸኛው «ዘላለማዊ ቃል ኪዳን» በዘላለማዊው አምላክ የተደረገውና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የታተመው ቃል ኪዳን ብቻ ነው። ጳውሎስ በዚህ ክፍል የሚገልጸው ይህንኑ የክርስቶስን የሰላም ተልእኮ ነው። ይህን ተልዕኮ መለየት፥ ዕርቅና አንድነት የሚሉት ሦስት ቃላት ጠቅለል አድርገው ሊገልጹት ይችላሉ።

## 1. መለየት፦ አሕዛብ የነበሩበት ሁኔታ (2፡11-12)

በምዕራፍ 2 ውስጥ በሚገኙት የመጀመሪያዎቹ 10 ቁጥሮች ጳውሎስ የኃጢአተኞችን መዳን በጥቅሉ ከገለጸ በኋላ፥ አሁን ደግሞ ክርስቶስ ለአሕዛብ የፈጸመውን ተግባር መግለጽ ይጀምራል። አብዛኛዎቹ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን አባላት ከአሕዛብ ወገን የመጡ ሲሆን፥ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለአይሁድ ሕዝቦች ያለውን ዕቅድ በሚገባ ያውቃሉ። ለበርካታ ምእተ ዓመታት «የተገረዙ» (አይሁዶች) እግዚአብሔር «ያልተገረዙ» (አሕዛብን) እንደማይፈልግ በማሰብ ሲንቁዋቸው ኖረዋል። አንድ አይሁድ ስለተገረዘ ብቻ የእግዚአብሔር ሰው ነው ማለት አይቻልም (ሮሜ 2፡25-29፤ ገላ. 5፡6፤ 6፡15)። በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ «በእጅ ያልተደረገ» ግርዛትን ተቀብለዋል (ቆላ. 2፡11)።

ነገር ግን እግዚአብሔር አብርሃምን ከጠራበት ጊዜ አንሥቶ በእስራኤልና በአሕዛብ መካከል ልዩነት ማድረጉ ግልጽ ነው። ይህንን ልዩነት ያደረገው ግን አይሁዶች እንዲታበዩ ሳይሆን ለአሕዛብ በረከት እንዲሆኑ ነበር። እግዚአብሔር የለያቸው መገለጡንና ቸርነቱን ለአሕዛብ እንዲያስተላልፉ ነበር። የሚያሳዝነው ግን እስራኤል ይህንን ልዩነት ለግል ጥቅሟ እንጂ እግዚአብሔር ለሚፈልገው ነገር ልታውል አልቻለችም። እስራኤላውያን በአካባቢያቸው እንደሚገኙ እግዚአብሔርን እንደማያውቁ ሰዎች ሆኑ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ይቀጣቸው ነበር፤ ምክንያቱም ጥሪያቸውን ጠብቀው በእውነተኛው አምላክ ስም ሕዝቦችን ማገልገል አልቻሉም።

አሕዛብን በግሩም ሁኔታ የሚገልጸው «ያለ. . .» የሚለው ቃል ነው። አሕዛብ በብዙ ነገር ያልታደሉ ነበሩ።

*ያለ ክርስቶስ ነበሩ*— የኤፌሶን ሰዎች ወንጌል ወደ እነርሱ ከመድረሱ በፊት ዝነኛዋን የዲያና ጣዖት ከማምለክ በቀር ስለ ክርስቶስ የሚያውቁት አልነበራቸውም። ጳውሎስ የኤፌሶን ሰዎች ያለ ክርስቶስ የነበሩበት ሁኔታ ፍጹም አሳዛኝ እንደነበረ ስለሚያስረዳ፥ አረማዊ ሃይማኖቶችም እንደ ክርስትናው እምነት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አላቸው የሚሉ ሰዎች አሁን ችግር ይገጥማቸዋል። አይሁድም ሆኑ አሕዛብ ያልዳነ ሰው ሁሉ «ያለ ክርስቶስ» ማለትም ለኩነኔ የተዳረገ መሆኑን ማጤኑ ተገቢ ነው።

*ያለ ዜግነት* – እግዚአብሔር አይሁዶችን ጠርቶ በሕዝብነት አደራጅቶአቸዋል። ሕጉንና በረከቱን ሰጥቶአቸዋል። አንድ አሕዛብ ወደ አይሁድ እምነት ተለውጦ ሕዝቡን ሊቀላቀል ቢችልም ከዚያ ልዩ ሕዝብ ውስጥ እንዳልተወለደ ይታወቃል። ከየትኛውም አሕዛብ ይልቅ እስራኤል የእግዚአብሔር ሕዝብ ነበረች።

*ያለ ቃል ኪዳን* – የእስራኤል በረከት እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ባደረገው ቃል ኪዳን ውስጥ የተገለጸ ሲሆን (ዘፍ. 12፡1–3)፥ ከአሕዛብ ጋር የተደረገ ቃል ኪዳን አልነበረም። አሕዛብ «መጻተኞች» እና «እንግዶች» ነበሩ። አይሁዶች ሁልጊዜ ይህንኑ ያስታውሷቸው ነበር። ብዙ ፈሪሳውያን በየዕለቱ፥ «እግዚአብሔር ሆይ፥ አይሁዳዊ እንጂ፥ አሕዛብ ስላላደረግኸኝ አመሰግንሃለሁ» እያሉ ይጸልዩ ነበሮ።

*ያለ ተስፋ*— የታሪክ ጸሐፊዎች የጥንቱ ዓለም በብርቱ የተስፋ–ቢስነት ዳመና የተጋረደ እንደነበር ይናገራሉ። ፍልስፍናዎች የተራቆቱ፥ ትውፊቶች የተነኑ፥ ሃይማኖቶች ሰዎች ሕይወትን ወይም ሞትን እንዲጋፈጡ ለማድረግ ያልቻሉ ነበሩ። ሰዎች መጋረጃውን አንሥተው

ከሌላኛው ጥግ የተሰፋን መልእክት ለማግኘት ቢጥሩም አልተሳካላቸውም (1ኛ ተሰ. 4፡13-18)።

*ያለ እግዚአብሔር*- ጳውሎስ በአቴንስ እንደተመለከተው ብዙ አማልክት ነበሩ (የሐዋ. 17፡16-23)። በዚያን ጊዜ አንድ ሰው በአቴንስ የአማልክት ቁጥር ከሰዎች እንደሚበዛ ተናግሮአል። ጳውሎስም፥ «መቼም ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ» ሲል ጽፎአል (1ኛ ቆሮ. 8፡5)። ነገር ግን አረማዊ ሰው ምንም ያህል ሃይማኖታዊ ወይም ግብረገባዊ ቢሆንም እውነተኛውን አምላክ አያውቅም ነበር። መዝሙር 115 እውነተኛውን አምላክ ከአረማውያን ጣዖታት ጋር ያነጻጽረዋል።

የአሕዛብ መንፈሳዊ ጉስቁልና በራሳቸው ኃጢአት እንጂ በእግዚአብሔር እንዳልመጣ መገንዘብ ተገቢ ነው። ጳውሎስ አሕዛብ እውነተኛውን አምላክ እያወቁ ሆን ብለው እንዳልታዘዙት ገልጾአል (ሮሜ 1፡18-23)። ሃይማኖታዊ ታሪክ ሰው ብዙ አማልክትን እየሞከረ የኋላ ኋላ እውነተኛውን አምላክ እንዳገኘ አያወሳም። በተቃራኒው ሰው እውነተኛውን አምላክ እያወቀ ሆን ብሎ የሚተውበት ነው። ይህም የውድቀት እንጂ የዕድገት ታሪክ አይደለም! የአሕዛብን የውድቀት ታሪክ ከመጀመሪያዎቹ 11 የዘፍጥረት መጽሐፍ ምዕራፎች ውስጥ እናገኛለን፤ አብርሃም ከተጠራበት ከምዕራፍ 12 ጀምሮ የአይሁዶችን ታሪክ እናገኛለን። እግዚአብሔር አይሁዶችን ከአሕዛብ የለየው አሕዛብንም ለማዳን ነው። «መዳን ከአይሁድ ነውና» (የሐዋ. 4፡22)።

እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ መሆኑን ለመግለጽ ከአብርሃም ጀምሮ አይሁዶችን ጠርቶአል። ቃሉን በአይሁዶች ዘንድ ከማኖሩም በላይ የዓለም አዳኝ የመጣውም በእነርሱ በኩል ነው (ሮሜ 9፡1-5)። ሁለቱም ይድኑ ዘንድ እስራኤል የአሕዛብ ብርሃን ልትሆን ይገባት ነበር። የሚያሳዝነው ግን እስራኤል እንደ አሕዛብ ሆና በመገኘቷ ብርሃኑ ደበዘዘ። ይህ እውነታ ዛሬ ለቤተ ክርስቲያን ማስጠንቀቂያ ሊሆን ይገባል። ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ከተለየች ለዓለም የምታበረክተው አስተዋጽኦ የላቀ ይሆናል።

## 2. ዕርቅ፡-እግዚአብሔር ለአሕዛብ ያደረገው ነገር (2፡13-18)

በቁጥር 13 ላይ «አሁን ግን» የሚለው በቁጥር 4 ላይ «ነገር ግን እግዚአብሔር» ከሚለው ጋር ተጓዳኝ ነው። ሁለቱም እግዚአብሔር በቸርነቱ ወደ ኃጢአተኞች ሕይወት መምጣቱን የሚያመለክቱ አገላለጾች ናቸው። «የጥል ግድግዳ» የዚህ ክፍል ቁልፍ ሐረግ ሲሆን (ቁ. 15-16)፥ ሁለት ገጽታ አለው። ጥሉ በአይሁዶችና በአሕዛብ (ቁ.

13–15) እንዲሁም በኃጢአተኞችና በእግዚአብሔር መካከል የተፈጠረ ጥል ነው (ቁ. 16–18)። እዚህ ላይ ጳውሎስ በታሪክ ውስጥ የታየውን እጅግ የላቀውን የሰላም ተልዕኮ ይገልጻል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ አይሁዶችንና አሕዛብን ብቻ ሳይሆን ሁለቱንም ከራሱ ጋር በአንድ አካል ማለትም በቤተ ክርስቲያን አስታርቆአል።

«አስታረቀ» የሚለው ቃል «ደግሞ ወደ አንድነት አመጣ» የሚል ፍች አለው። ሚስቱ የተለየችው ባል ዕርቅን ይፈልጋል፤ በኮብላይ ልጁ ምክንያት የምትተክዝ እናትም እንዲሁ ደግሞ ኅብረት ለመፍጠር ትናፍቃለች፤ በኃጢአቱ ምክንያት ከደኅንነት የራቀ ኃጢአተኛም ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ አለበት። ኃጢአት በዚህ ዓለም ታላቁ «አለያይ» ነው። ሰዎች በዚህ ምድር መኖር ከጀመሩበት ጊዜ አንሥቶ ሰዎችን ሲለያይ ኖሮአል። አዳምና ሔዋን ኃጢአትን በፈጸሙበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ተለይተዋል። ብዙም ሳይቆይ ልጆቻቸው እርስ በርሳቸው ተለያዩ፤ ቃየልም አቤልን ገደለ። ምድር በፀመፅ ተሞላች (ዘፍጥ. 6፡5–13)፤ ብቸኛው መፍትሔ ፍርድ ነበር። ከጥፋት ውኃ በኋላም ሰዎች በእግዚአብሔርና በሌሎች ሰዎች ላይ ኃጢአትን ከመፈጸም አልታቀቡም። ያለ እግዚአብሔር እርዳታ የራሳቸውን አንድነት ለመመሥረት የፈለጉበትም ሁኔታ ነበር። ውጤቱ ግን ሕዝቦችንና ቋንቋዎችን የደባለቀ ሌላ ፍርድ ነበር። ከዚህ በኋላ ነበር እግዚአብሔር አብርሃምን የጠራውና በሕዝበ– እስራኤል በኩል ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም የመጣው። በመስቀል ላይ የፈጸመው ሥራው በአይሁድና በአሕዛብ፥ በእግዚአብሔርና በኃጢአተኞች መካከል የነበረውን የጥልን ግድግዳ አፈረሰ።

*በአይሁድና በአሕዛብ መካከል የነበረው ጠላትነት* (2፡13–15)– እግዚአብሔር የማዳን ዓላማውን ለመፈጸም ሲል በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ልዩነት አድርጓል። ይህ ዓላማ ከተፈጸመ በኋላ ልዩነት አይኖርም። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ እነዚህ ልዩነቶች ለዘላለም እንዲወገዱ ፈቃዱ ነው። በመሆኑም በኢየሱስ ክርስቶስ የማስታረቅ አገልግሎት ተወግደዋል።

የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ለመረዳት የተቸገረችው ይህንን ትምህርት ነበር። ለብዙ ዓመታት አይሁዶች ከአሕዛብ በሃይማኖት፥ በአለባበስ፥ በአመጋገብና በሕግ ይለዩ ነበር። ጴጥሮስ ወደ አሕዛብ እስከተላከበት ድረስ (የሐዋ. 10) ቤተ ክርስቲያን ምንም ችግር አልገጠማትም። ነገር ግን አይሁዶች በዳኑበት መንገድ አሕዛብ መዳናቸው ችግር መፍጠር ጀመረ። ጴጥሮስ ወደ አሕዛብ ሄዶ ከእነርሱ ጋር አብሮ ስለበላ የአይሁድ ክርስቲያኖች ገሠጹት (የሐዋ. 11)። የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በጉዳዩ ላይ ስብሰባ ተቀመጡ (የሐዋ. 15)። አንድ አሕዛብ

ክርስቲያን ለመሆን አይሁድ መሆን አለበት? ብለው ጠየቁ። ድምዳሜአቸው፥ «የለበትም! አይሁዶችም ሆኑ አሕዛብ የሚድኑት በአንድ ዓይነት መንገድ ነው፤ ይኸውም በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን!» የሚል ነበር። በዚህ መንገድ ጠላትነቱ ተወገደ።

የዚያ ጠላትነት መንስዔው ሕግ ነበር። ለዚህም ምክንያቱ ሕግ በአይሁዶችና በአሕዛብ መካከል ግልጽ ልዩነት የሚያስቀምጥ መሆኑ ነው። የአመጋገብ ሕግጋት ለአይሁዶች እግዚአብሔር ንጹሕ ባልሆኑ ምግቦች መካከል ልዩነቶችን እንዳስቀመጠ ያስገነዝባቸዋል (ዘሌ. 1፡44–47)። አሕዛብ ግን እነዚህን ሕግጋት ስለማይጠብቁ እንደ ርኩሳን ይቆጠሩ ነበር። ነቢዩ ሕዝቅኤል የካህናት ተግባር የተቀደሰውን ከተዋረደው መለየት እንደሆነ ተናግሯል (44፡23)። እግዚአብሔር ለአይሁዶች የሰጣቸው መለኮታዊ ትእዛዛት በአይሁዶችና በሌሎች ሕዝቦች መካከል እንደ ግድግዳ ቆመ። እንዲያውም በአይሁድ ቤተ መቅደስ ውስጥ የአሕዛብን አደባባይ ከሌሎች የቤተ መቅደስ ክፍሎች የሚለይ ግድግዳ ነበር። የከርሰ ምድር ተመራማሪዎች ሄሮድስ ካሠራው የአይሁድ ቤተ መቅደስ ውስጥ ያገኙት የተቀረጸ ጽሑፍ እንዲህ ይነበባል።

> ማንም የውጭ አገር ሰው መቅደሱንና በዙሪያው የሚገኘውን አጥር አልፎ ሊገባ አይችልም። አልፎ የተገኘ ሰው ቢኖር ለሚደርስበት የሞት አደጋ ራሱን እንጂ ማንንም መውቀስ የለበትም።

አይሁድ ጳውሎስን አስረው ለመግደል ሲዝቱ የነበረው ከአሕዛብ ወዳጆቹ ጋር ይህንን ግድግዳ አልፎ ተገኝቷል በማለት ነበር (የሐዋ. 21፡28–31)።

አይሁድና አሕዛብ ይታረቁ ዘንድ ይህ ግድግዳ መወገድ አለበት፤ ኢየሱስ ክርስቶስም በመስቀል ላይ ይህንኑ ፈጸመ። የጥሉ ግድግዳ መወገድ የሚችለው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ብቻ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በሞተበት ጊዜ የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ከሁለት ተከፈለ፤ የጥሉም ግድግዳ ተወገደ። ኢየሱስ ክርስቶስ በጽድቅ ሕይወቱ ሕግ የሚጠይቀውን በመፈጸምና ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረቡ (ገላ. 3፡10–13)፥ አይሁድን ከአሕዛብ የሚለየውን ግድግዳ አስወገደ። ለብዙ ምእተ ዓመታት በመካከላቸው ልዩነት ነበረ። ዛሬ ግን «በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለምና፤ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፤ ለሚጠሩትም ሁሉ ባለጠጋ ነው፤ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና» (ሮሜ 10፡12–13)።

አይሁድና አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ሆነዋል። «እርሱ ሰላማችን ነውና» (ኤፌ. 2:14)። በክርስቶስ አማካይነት ርቀው የነበሩ አሕዛብ ቀርበዋል (ቁ. 13 እና 17)። አይሁድና አሕዛብ አንድ ሆነዋል። ሕግን በማስወገድ ጠላትነትን ማጥፋትና አዲሱን ሰው ማለትም የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን መፍጠር የክርስቶስ ሥራ ውጤቶች ናቸው። «ማስወገድ» ማለት «ጨርሶ ማንሣት» ማለት ነው። አማኞች በክርስቶስ በማመናቸው ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደሉም፤ እንግዲህ ሕግ አይሁድንም ሆነ አሕዛብን አይገዛም። የእግዚአብሔርን ቅድስና የሚገልጸው የሕግ ጽድቅ አሁንም የእግዚአብሔር ሕግ ነው። ይህንን ሕግ በአማኙ ሕይወት ውስጥ ተግባራዊ የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው (ሮሜ 8:1-4)። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን «ልዩነት የለምና» የሚለውን አሳብ ለመገንዘብ ረዥም ጊዜ ወስዶባታል። እንዲያውም አንዳንድ ሃይማኖታዊ ቡድኖች ክርስቲያኖች ከሕግ ሥር ለማስቀመጥ ይጥሩ ስለነበር ትምህርቱን ሊገነዘቡት አልቻሉም (ገላ. 4:8-11፤ 5:1፤ ቆላ. 2:13-23)።

ክርስቶስ ሰላማችን ነው (ኤፌ. 2:14)፤ ክርስቶስ ሰላምን አድርጎአል (ቁ. 15)። በቁጥር 15 ሰላምን ስለማድረግ የሚናገረው ግሥ «መፍጠር» የሚል ፍቾ አለው። የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር አዲስ ፍጥረት ነች (2ኛ ቆሮ. 5:15)። በአሮጌው ፍጥረት ውስጥ የሚገኘው ነገር ሁሉ በኃጢአት ምክንያት ይፈራርሳል፤ በአዲስ ፍጥረት ውስጥ ግን ከጽድቅ የተነሣ አንድነት ይታያል። «አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፤ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፤ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና» (ገላ. 3:28)። የአሕዛብን አሮጌ ስፍራ ከአዲሱ ጋር በማነጻጸር ክርስቶስ በእነርሱ ምትክ በመስቀል ላይ እንዴት የእነርሱን ሥራ እንዳከናወነላቸው መመልከት ይቻላል።

| <u>አሮጌው ስፍራ</u> | <u>አዲሱ ስፍራ</u> |
| --- | --- |
| - ያለ ክርስቶስ | - በክርስቶስ (ኤፌ. 2:13) |
| - መጻተኞች | - ቅዱስ ሕዝብ (1ኛ ጴጥ. 2:9) |
| - እንግዶች | - እንግዶች አይደሉም (ኤፌ. 2:19) |
| - ያለ ተስፋ | - በአንድ ተስፋ የተጠሩ (ኤፌ. 4:4) |
| - ያለ እግዚአብሔር (ኤፌ. 2:12) | - የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት (ኤፌ. 1:3) |

*በእግዚአብሔርና በኃጢአተኞች መካከል ያለው ጠላትነት* (2:16-18)- አሕዛብ ከአይሁድ ጋር መታረቅ ብቻ ሳይሆን ሁለቱም ማለትም አይሁድና አሕዛብ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ያስፈልጋቸዋል።

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 ላይ በተጠቀሰው የኢየሩሳሌሙ ጉባኤ ሐዋርያት የደረሱት ከዚህ ድምዳሜ ላይ ነበር። ጴጥሮስ፥ «ልባቸውን በእምነት ሲያነጻ በእኛና በእነርሱ መካከል አንዳች አልለየም. . . ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እንደ እነርሱ ደግሞ እንድን ዘንድ እናምናለን» ሲል መስክሮአል (የሐዋ. 15:9፥ 11)። ይህ ከአሕዛብ ወገን የሆኑ ሰዎች ክርስቲያን ለመሆን አይሁድ መሆን አለባቸው የሚል አሳብ ሳይሆን አይሁድም ቢሆን እንደ አሕዛብ ኃጢአተኞች መሆናቸውን የሚገልጽ ነው። «ልዩነት የለምና ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል» (ሮሜ 3:23)። አሕዛብንና አይሁድን የለየው ይህ ሕግ ሰዎችንና እግዚአብሔርንም ለያይቶአል። በመሆኑም ክርስቶስ የሕግን ዕርግማን ተሸከመ።

አንድ ቀን አንድ ሰውዬ ከቢሮዬ መጥቶ እርዳታ እንደሚፈልግ ነገረኝ። «ባለቤትና እኔ መቷቷው እንፈልጋለን!» ሲል አጉተመተመ። ሰውዬው እንዲህ ሲል ይቀር መባባል ያስፈልገናል ማለቱ እንደሆነ ተረድቻለሁ። በአንድ በኩል ግን «መቷቷው» የሚለው ትክክለኛ ቃል ነበር። እርስ በርሳቸውና በጌታም ላይ ኃጢአትን ፈጽመው ስለነበር እነዚህ ኃጢአቶች እስካልተሰረዙ ድረስ ኅብረት ሊኖራቸው አይችልም። የፍቅር አምላክ ኃጢአተኛውን ከራሱ ጋር ለማስታረቅ ይሻል። ነገር ግን የቅድስና አምላክ የኃጢአትን ፍርድ ማረጋገጥ ይኖርበታል። እግዚአብሔር ፍቅሩን በመግለጽና የጽድቅን ጥያቄዎች በማሟላት የኃጢአታችን መሥዋዕት ይሆን ዘንድ ልጁን ወደ ምድር በመላክ ችግሩን አቃሎታል። ይህ በርግጥም «መተው» ነበር (ቆላ. 2:13–14 ተመልከት)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላማችን ነው (ኤፌ. 2:14)። እርሱ ሰላምን አደረገ (ቁ.15)፤ ሰላምንም ሰበከ (ቁ. 17)። ፈራጅ በመሆኑ ጦርነት ሊያውጅ መምጣት ይችል ነበር። ነገር ግን ከጸጋው የተነሣ የሰላምን መልእክት ይዞ መጣ (ሉቃ. 2:8–14፤ 4:16–19)። አይሁድና አሕዛብ በክርስቶስ አማካይነት እርስ በርሳቸው ሰላም ያገኙ ሲሆን፥ ሁለቱም ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ በር ተከፍቶላቸዋል (ሮሜ 5:1–2)። ይህ በክርስቶስ ሞት የተቀደደውን መጋረጃ ያስታውሰናል (ማቴ. 27:50–51፤ ዕብ. 10:14–25)። ዕርቅ ፍጹም ሆነ!

## አንድነት፡– የአይሁድና የአሕዛብ በክርስቶስ ያገኙት ስፍራ (2:19–22)

ጳውሎስ የክርስቶስን አንድ የማድረግ ተግባር ለመግለጽ «አንድ» የምትለውን ቃል ብዙ ጊዜ ጠቅሷል። ሁለቱን ያዋሐደ (ቁ. 14)፥ አንድ አዲስ ሰው (ቁ. 15)፥ አንድ አካል (ቁ. 16)፥ አንድ መንፈስ (ቁ. 18)።

መንፈሳዊ ርቀትና ክፍፍል በክርስቶስ ተወግዶአል። በዚህ ምዕራፍ መዝጊያ ላይ ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን አይሁድና አሕዛብ አንድነት የሚገልጹትን ሦስት ማብራሪያዎች አቅርቦአል።

*አንድ ሕዝብ* (2:19)– እስራኤል የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ ናት፤ ሆኖም አዳኛቸውን በመተዋቸው መዘዙን ተግተዋል። መንግሥቱ ከእነርሱ ተወስዶ ፍሬ ለሚያፈራው ሕዝብ ተሰጥቷል (ማቴ. 21:43)። ይህ አዲስ ሕዝብ ቤተ ክርስቲያንን የሚያመለክት ነው፤ «የተመረጠ ትውልድ፥. . . ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን» (1ኛ ጴጥ. 2:9ን ከዘጸአት 19:6 ጋር አነጻጽር)። በብሉይ ኪዳን ሕዝቦች የሚታወቁት ከሴም፥ ከካም፥ ወይም ከያፌት በመወለዳቸው ነበር (ዘፍጥ. 10)። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ እነዚህ ሦስት ቤተሰቦች በክርስቶስ ተዋሕደው እናገኛለን። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8፥ የካም ትውልድ የሆነው ኢትዮጵያዊ ደኅንነትን አግኝቶአል። በሐዋርያት ሥራ 9 የሴም ትውልድ የሆነው የተርሴሱ ሳውል ደኅንነትን አግኝቶ ሐዋርያው ጳውሎስ ተብሏል። በሐዋርያት ሥራ 10 የያፌት ትውልዶች የሆኑት አሕዛብ፥ ሮማዊ ወታደር በነበረው ቆርኔሌዎስ ቤት ደኅንነትን አግኝተዋል። ኃጢአት የሰውን ዘር ከፋፈለ ክርስቶስ ግን በመንፈሱ አንድ አደረገ። አማኞች ሁሉ በሰማያዊ ዜግነት የዚያ «ቅዱስ ሕዝብ» አካል ናቸው (ፊልጵ. 3:20–21)።

*አንድ ቤተሰብ* (2:19)– በክርስቶስ በማመን ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ እንቀላቀላለን። በዚህም ጊዜ እግዚአብሔር አባታችን ይሆናል። ይህ ግሩም የእግዚአብሔር ቤተሰብ በሰማይና በምድር ይኖራል (ኤፌ.3:15)። በሕይወት ያሉት አማኞች በምድር ላይ ሲኖሩ የሞቱት ግን በሰማይ ይኖራሉ። የእግዚአብሔር ልጆች ከምድር በታች (ፊልጵ. 2:10) ወይም በየትኛውም ሌላ ስፍራ አይኖሩም። ምንም ዓይነት የዘር፥ የብሔር ወይም የአካል ልዩነቶች ቢኖሩም፥ ሁላችንም በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የምንገኝ ወንድማማቾችና እኅትማማቾች ነን።

*አንድ ቤተ መቅደስ* (2:20–22)– በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ይመላለስ ነበር (ዘፍጥ. 5:22፥6:9)። በዘጸአት ግን በሕዝቡ መካከል ማደርን መረጠ (ዘጸ. 25:8)። የእስራኤል ኃጢአት ክብሩ እንዲለይ እስካደረገበት ጊዜ ድረስ (1ኛ ሳሙ. 4) እግዚአብሔር በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ይኖር ነበር (ዘጸ. 40:34–38)። ከዚያም እግዚአብሔር በቤተ መቅደስ ውስጥ መኖር ጀመረ (1ኛ ነገ. 8:1–11)። የሚያሳዝነው ግን አሁንም እስራኤል ኃጢአት በመሥራቷ ክብሩ ተለየ (ሕዝ. 10:18–19)። ቀጣዩ የእግዚአብሔር ማደሪያ የክርስቶስ አካል ሆነ (ዮሐ. 1:14)፤ ሰዎች ግን በመስቀል ላይ ሰቀሉት። ዛሬ እግዚአብሔር በመንፈሱ አማካይነት

መቅደሱ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያድራል። እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን ሕንጻን ጨምሮ በሰው እጅ በተሠራ ቤተ መቅደስ ውስጥ አይኖርም (የሐዋ. 7:48-50)። በክርስቶስ በሚያምኑ ሰዎች ልብና (1ኛ ቆሮ. 6-19-20) በጥቅሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይኖራል (ኤፌ. 2:20-22)።

የዚህች ቤተ ክርስቲያን መሠረት የተጣለው በሐዋርያትና በአዲስ ኪዳን ነቢያት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ መሠረቷና (1ኛ ቆሮ. 3:11) የማዕዘን ራሷ ነው [መዝ. (118):22፤ ኢሳ. 8:14]። የማዕዘን ድንጋዩ መዋቅሩን በአንድነት ያጋጥመዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ አይሁድንና አሕዛብን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ አድርጓቸዋል። ይህ የቤተ መቅደሱ መጠቀስ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለነበሩት አይሁዶችም ሆነ አሕዛብ የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል። አይሁዶች ሄሮድስ በኢየሩሳሌም ያሠራውን ቤተ መቅደስ ሲያስቡ፥ አሕዛብ ደግሞ የዲያናን ቤተ ጣዖት ያስባሉ። ሁለቱም ቤተ መቅደሶች ሊጠፉ ተወስነዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ የሚገነባው ሕንጻ ግን ለዘላለም ይኖራል። «ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ» (ማቴ. 16:18)። መንፈስ ቅዱስ ሙት ድንጋዮችን ከኃጢአት ጉድጓድ በማውጣት [መዝ. (40):2]፥ ሕይወትን በመስጠትና ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በማምጣት ይህንን ቤተ መቅደስ ያንጻል (1ኛ ጴጥ. 2:5)። ይህ ቤተ መቅደስ የክርስቶስ አካል በመሆን በልዩ መንገድ ተጋጥሟል ( ኤፌ. 2:21፤ 4:16)፤ በዚህ ዓይነት እያንዳንዱ ብልት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይፈጽማል።

ይህንን ምዕራፍ መለስ ብለህ ስትመለከት እግዚአብሔር በጸጋው ለኃጢአተኞች ስላደረገው ነገር እርሱን ማመስገንህ የማይቀር ነው። በክርስቶስ በኩል ከሞት አስነሥቶ ከዙፋን ላይ አስቀምጦናል። ዕርቅን አድርጎ በመቅደሱ ውስጥ አኑሮናል። መንፈሳዊ ሞትም ሆነ መንፈሳዊ ርቀት የእግዚአብሔርን ጸጋ ሊረታ አይችልም! ያዳነንም በተናጠል ብቻ ሳይሆን እንደ ቤተ ክርስቲያኑ አካል በኅብረትም ነው። የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ አካል መሆን ምንኛ ታላቅ ዕድል ነው!

ይህ ወደ ሁለት ተግባራዊ ተዛምዶዎች ይመራናል።

በመጀመሪያ፥ የእግዚአብሔርን ጸጋ በግልህ ተቀብለሃል? በመንፈሳዊ ሕይወትህ ሙት ነህ? ከእግዚአብሔር ሩቅ ነህ? ወይስ በክርስቶስ አምነህ እርሱ ብቻ የሚሰጠውን የዘላለም ሕይወት ተቀብለሃል? መንፈሳዊ ስፍራህን የማታውቅ ከሆነ ወደ ክርስቶስ ትመለስ ዘንድ አደፋፍርሃለሁ። እንደ ሕዝበ እስራኤል ብዙ መንፈሳዊ

ዕድሎች ተሰጥተውህ ሳለ እነዚህን ዕድሎች የሰጠህን አምላክ ችላ እያልህ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ እንደ አሕዛብ ከእግዚአብሔር ፊትህን መልሰህ ሆን ብለህ በኃጢአትና ባለመታዘዝ እየተመላለስህ ይሆናል። ያለህበት ሁኔታ የትኛውም ቢሆን «ልዩነት የለምና፤ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል» (ሮሜ 3:23)። የክርስቶስን ስም ጥራ፤ እርሱ ያድንሃል።

ሁለተኛ፥ አንተ በክርስቶስ ላይ እውነተኛ እምነት ካለህ ሌሎች በእርሱ እንዲያምኑ ትረዳቸዋለህ? ከሞት እንደመነሣትህ መጠን በአዲስ ሕይወት ትመላለሳለህ? (ሮሜ 6:4)። ይህንን የዘላለም ሕይወት መልካም የምስራች ለሌሎች ታካፍላለህ? አንተ አሁን ከእግዚአብሔር ጋር ጠላት አይደለህም። ከእግዚአብሔር ጋር በመዋጋት ላይ ላሉት የእግዚአብሔርን ሰላም ትነግራቸዋለህ?

ኢየሱስ ክርስቶስ ዕርቅን ተግባራዊ ለማድረግ ሲል ሞቶአል። እኔና አንተ የዕርቁን መልእክት የራሳችን አድርገን ልንኖር ይገባል። እግዚአብሔር የማስታረቅን ቃል በእኛ አኑሮአል (2ኛ ቆሮ. 5:20)። እግሮቻችን በሰላም ወንጌል በመዘጋጀት ተጫምተው ሊቆሙ ይገባል (ኤፌ. 6:15)። «የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና» (ማቴ. 5:9)።

አንድ ወንጌላዊ በመንደር ገበያ ውስጥ እየሰበከ ሳለ አንዳንድ ሰዎች በመልክ ጥፉነቱ ይሳሳቁበት ጀመር። እርሱም ለሕዝቡ፥ «እርግጥ ነው ራሰ በራ በመሆኔ መልካም ጸጉር የለኝም። ጥርሴም የእኔ ባለመሆናቸው ውብ አይደሉም። የጥርስ ሐኪም ነው የተከለልኝ። የሚያምር ፊትም ሆነ ልብስ የምገዛበት ገንዘብ የለኝም። ይህንን ግን አውቃለሁ፤ የሚያምሩ እግሮች አሉኝ» ሲል ከተናገረ በኋላ ኢሳይያስ 52:7 አነበበላቸው። «የምስራች የሚናገር፥ ሰላምንም የሚያወራ. . . ሰው እግሩ በተራሮች ላይ እጅግ ያማረ ነው።» የሚያምር እግር አላችሁ?

ስለዚህም አሕዛብ ስለሆናችሁ ስለ እናንተ የክርስቶስ ኢየሱስ እስር የሆንሁ እኔ ጳውሎስ ለእግዚአብሔር እንበረከካለሁ። ለእናንተ ስለ ተሰጠኝ ስለ እግዚአብሔር ጸጋ መጋቢነት በእርግጥ ሰምታችኋል፤ አስቀድሜ በአጭሩ እንደ ጻፍሁ፥ ይህን ምሥጢር በመግለጥ አስታወቀኝ፤ ይህንም ስታነቡ የክርስቶስን ምሥጢር እንዴት እንደማስተውል ልትመለከቱ ትችላላችሁ፤ ይህም፥ አሕዛብ አብረው እንዲወርሱ፥ በአንድ አካልም አብረው እንዲሆኑ፥ በወንጌልም መስበክ በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነ የተስፋ ቃል አብረው እንዲካፈሉ፥ ለቅዱሳን ሐዋርያትና ለነቢያት በመንፈስ አሁን እንደ ተገለጠ በሌሎቹ ትውልዶች ዘንድ ለሰው ልጆች አልታወቀም።

እንደ ኃይሉ ሥራ እንደ ተሰጠኝም እንደ እግዚአብሔር ጸጋ ስጦታ መጠን የወንጌል አገልጋይ ሆንሁለት። ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ ዘንድ፥ ሁሉንም በፈጠረው በእግዚአብሔር ከዘላለም የተሰወረው የምሥጢር ሥርዓት ምን እንደሆነ ለሁሉ እገልጥ ዘንድ ይህ ጸጋ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ለማንስ ለእኔ ተሰጠ፤ ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተ ክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ፤ ይህም በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የፈጸመው የዘላለም አሳብ ነበረ፥ በእርሱም ዘንድ ባለ እምነታችን በኩል በመታመን ድፍረትና መግባት በእርሱ አለን። ስለዚህ ስለ እናንተ ስላለ መከራዬ እንዳትታክቱ እለምናችኋለሁ፥ ክብራችሁ ነውና።

# 6

# አንድ ምሥጢር አውቃለሁ

በአንድ ወቅት ስለ አንድ ልጅ የአስተዳደግ ሁኔታ ለመመስከር ከፍርድ ችሎት ቀርቤ ነበር። ፍርድ ቤት ስቀርብ የመጀመሪያ ገጠመኜ በመሆኑ ችሎቱ በትልቅ ከተማ ሳይሆን በአነስተኛ የገጠር መንደር ውስጥ በመሆኑ ተደስቻለሁ። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ችሎቱ የሚገኝበት ቦታ ብዙ ለውጥ እንደማያመጣ ተገንዝቤአለሁ። ክሶች ሁሉ አስቸጋሪ ሊሆኑ ስለሚችሉ ምስክር ሆኖ መቅረብ ቀላል ነገር አይደለም።

«ሬቨረንድ፥ እስር ቤት የኖረ ሰው ልጅ ለማሳደግ ይችላል ብለው ያስባሉ?» የሚለው የዐቃቤ ሕጉ የመጀመሪያ ጥያቄ ያልጠበቅሁት በመሆኑ አስገረመኝ።

«አዎን» ወይም «አይደለም» የሚል ምላሽ መስጠት ስለነበረብኝ የተናገርሁት ቃል ዳኛውን ብዙም አላስደሰተውም። ለአፍታ፥ ሳመነታ ቆየሁና፥ «መልካም፥ ሁኔታው በሰውየው ማንነት የሚወሰን ይመስለኛል። አንዳንድ ዝነኛ ሰዎች እስር ቤት ቆይተው ካገኙት ልምድ ዓለምን የተሻለች ስፍራ አድርገዋታል። ለምሳሌ ጆን ቡንያን (የመናኙ ጉዞ ደራሲ)፥ ታላቁ ሐዋርያ ጳውሎስ» ስል ተናገሩሁ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌሎች ምሳሌዎች መስጠት እችል ነበር። ነገር ግን ምላሼ በችሎቱ ተቀባይነት እንዳላገኘ ተገነዘብሁ።

ጳውሎስ ለዚህ መልእክቱ ሁለት ጊዜ እስረኛ እንደሆነ ለአንባቢዎቹ አስታውቆአል (3፡1፤ 4፡1)። በመደምደሚያው ላይ ደግሞ «በሰንሰለት መልእክተኛ የሆንሁ» ሲል ራሱን ይጠራል (6፡20)። የኤፌሶን ሰዎች፥ «ጳውሎስ ለምን በሮም ታሰረ፡ እግዚአብሔር ለምን እንዲህ ዓይነት ነገር እንዲደርስበት አደረገ» እያሉ መጠየቃቸው የማይቀር ነው። በዚህ አንቀጽ ጳውሎስ የነበረበትን ሁኔታ ያብራራል። ይህንንም በማድረግ በዚህ መልእክቱ ከታላላቅ እውነቶች አንዱን ማለትም የቤተ ክርስቲያንን «ምሥጢር» ይገልጻል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ምሥጢር ማለት እንግዳ ወይም ድብቅ ማለት ሳይሆን «እግዚአብሔር ቀደም ሲል የሸሸገውና አሁን ግን ለቤተሰቡ የገለጸው እውነት» ማለት ነው። ምሥጢር የዚህ ዓለም ሰዎች የማያውቁትና የእግዚአብሔር ሕዝብ ግን ተረድተው በአክብሮት የሚይዙት «የተቀደሰ ምሥጢር» ነው።

ጳውሎስ ምሥጢሩን ያብራራል። ምሥጢሩ የአሕዛብ አማኞች ከአይሁድ ክርስቲያኖች ጋር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአንድ አካል

መዋሐዳቸው ነው (3:6)። ቀደም ሲል ይህንኑ የእግዚአብሔርን አዲስ ሥራ የገለጸላቸው በመሆኑ ጽንሰ አሳቡ ለአንባቢዎቹ እንግዳ አልነበረም (1:10፤ 2:11 ፥ 22)፤ አሁን ግን ጳውሎስ የራሱን ሕይወትና አገልግሎት የተቆጣጠረውን የዚህን «የተቀደሰ ምሥጢር» አስደናቂ አንድምታ ያስረዳል። ጳውሎስ ይህንን ክፍል የሚጀምረው ለመልእክቱ ተደራስያን በመጸለይ ነው። በእርግጥ ጳውሎስ የሰጠው ማብራሪያ ጣልቃ ገብ ነው። 3:1ን ከ 3:14 ጋር አነጻጽር። «እረኛ» እና «አሕዛብ» የሚሉትን ቃላት መጠቀሙ ወደዚህ አስፈላጊ ወደሆነው የቤተ ክርስቲያን ምሥጢር ማብራሪያ መርቶታል። በማብራሪያውም ጳውሎስ ምሥጢሩ በአራት ቡድኖች ለተካተቱ ወገኖች አስፈላጊ መሆኑን አስረድቶአል።

## 1. ለጳውሎስ አስፈላጊ ነበር (3:1–5)

በጳውሎስ ሕይወት የምሥጢሩን አስፈላጊነት ለመረዳት በዚህ ክፍል ስለ ራሱ በተናገራቸው ሁለት መግለጫዎች ላይ ማተኮሩ ከሁሉም የተሻለ ይሆናል። ራሱን «እስረኛ» ሲል ይጠራና (3:1)፥ መልሶ ደግሞ «አገልጋይ» ይላል (3:7)።

ጳውሎስ የሚያምኑትን አይሁዶችና አሕዛብ በቤተ ክርስቲያን አንድ አካል ለማድረግ የተወጠነውን የእግዚአብሔርን አዲስ ዕቅድ ስላመነ እስረኛ ነበር። በጳውሎስ ዘመን የነበሩ አጥባቂ አይሁዶችና አሕዛብን እንደ ውሾች ሲቆጥሩ፥ በክርስቶስ ያመኑት አንዳንድ አይሁዶችም ለአሕዛብ ብዙም የተሻለ አመለካከት አልነበራቸውም።

ክርስቶስ ጳውሎስን ያዳነው ከአጥባቂ አይሁዶች መሪነት ነበር (ፊልጵ. 3:1–11፤ ገላ. 1:11–24)። ይሁንና በእግዚአብሔር ፈቃድ የመጀመሪያ አገልግሎቱን አይሁዶችና አሕዛብ በሚገኙበት በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ጀመረ (የሐዋ. 11:19–26)። ያመኑትን አሕዛብ ጉዳይ ለመወሰን በኢየሩሳሌም ስብሰባ በተካሄደበት ወቅት ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ጸጋና የቤተ ክርስቲያንን አንድነት በመደገፍ ጽኑ ንግግር አድርጓል (የሐዋ. 15፤ ገላ. 2:1–10)።

በክርስትና ሕይወቱ መጀመሪያ አንሥቶ ጳውሎስ ለአሕዛብ ወንጌልን ለመስበክ በእግዚአብሔር እንደተጠራ ያውቅ ነበር (የሐዋ. 26:13–18፤9:15)። ጥሪውንም እምቢ አላለም። ጳውሎስ ባገለገለባቸው ስፍራዎች ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ የሆኑ አይሁዶችና አሕዛብ የሚገኙባቸውን አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መሥርቷል (ገላ. 3:28)።

ጳውሎስ «የአሕዛብ ሐዋርያ» ስለነበር (ሮሜ 11:13፤ 15:15–16፤ 1ኛ ጢሞ. 2:7፤ ኤፌ. 3:8)፥ ለአሕዛብ አድልቶ አይሁዶችን በተለይም

በኢየሩሳሌም በይሁዳ የሚገኙትን አይሁዳውያን አማኞች እንደገዳ ተደርጎ ይወቀስ ነበር። ጳውሎስ በይሁዳ ለነበሩት ድሆች የሰበሰበው ልዩ ስጦታ በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናትና ጳውሎስ በመሠረታቸው አብያተ ክርስቲያናት መካከል የሚታየውን በጎ ፈቃድ ሊያሳይ ይገባ ነበር (ሮሜ 15:25-23)። ጳውሎስ በአካል ተገኝቶ ያበረከተላቸውን ስጦታ (የሐዋ. 21:17-19) የይሁዳ ክርስቲያኖች በደስታ ተቀበሉ። ምንም እንኳ ጳውሎስ የአይሁድ አማኞችን ለማርገብ ከፍተኛ እርምጃዎችን ቢወስድም፥ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ብጥብጥ ተነሥቶ ጳውሎስ ለእስር ተዳርጎአል (የሐዋ. 21:30-33)። ጳውሎስ ራሱን ለመከላከል የሰጠውን የሕይወት ምስክርነት «አሕዛብ» የሚል ቃል እስከተናገረበት ጊዜ ድረስ ሲሰሙ ቆይተዋል። ቃሉን ሲጠቀም ግን እንደገና ሁከት ተጀመረ (የሐዋ. 22:22-23)። የተቀረው የሐዋርያት ሥራ ክፍል ጳውሎስ ለአሕዛብ የኢየሱስ ክርስቶስ እስረኛ ሆኖ ከኢየሩሳሌም ወደ ሮም የሄደበትን ሁኔታ ይተርካል (ኤፌ. 3:1)። ጳውሎስ መልእክቱን በማመቻመች የአይሁዶችን ራስ ወዳድነት ቢያረካ ኖሮ ከእስር ሊለቀቅ ይችል ነበር።

ጳውሎስ በምሥጢሩ ምክንያት እስረኛ የነበረ ብቻ ሳይሆን አገልጋይም ነበር። እግዚአብሔር በክርስቶስ የሚገኘውን የምስራች ይዞ ወደ አሕዛብ እንዲሄድ የመጋቢነት አገልግሎት ሰጠው። «መጋቢነት» የሚለው ቃል ከሁለት የግሪክ ቃላት የተገነባ ነው። «አይኮስ» /oikos/ «ቤት» ማለት ሲሆን «ኖሞስ» /nomos/ ደግሞ «ሕግ» ማለት ነው። «ኢኮኖሚ» የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል «አይኮኖሚያ» /oikonomia/ ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደ ሲሆን፥ «የቤት ሕግ» ወይም «መጋቢነት» ወይም «አስተዳደር» የሚል ፍች ይይዛል። እግዚአብሔር በየዘመኑ ሕዝቡን የሚያስተዳድርበት የተለያዩ መርሐ ግብሮች አሉት። ይህንንም የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት «ሥነ መስተዳድር» ሲሉ ይጠሩታል (ኤፌ. 1:9-10)። የእግዚአብሔር መርሆች ባይለወጡም ከሰው ልጆች ጋር የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ጋር በየዘመኑ ይለዋወጣሉ። «ዘመናትን ለይተን ካወቅን መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ ይጣጣማል» ብለዋል ቅዱስ አገስቲን።

እግዚአብሔር ለጳውሎስ የምሥጢርን መጋቢነት በመስጠት ለአሕዛብ እንዲያካፍል አድርጎታል። እነዚህን ሰዎች ወደ ክርስቶስ በመመለስ አጥቢያ ጉባዔዎችን መመሥረቱ ብቻ በቂ አልነበረም። ከአይሁዶች ጋር በእኩል ደረጃ የእግዚአብሔርን ጸጋ በመካፈል እንደ አካሉ ክፍሎች በክርስቶስ የነበራቸውን ግሩም ስፍራ በማሳየት ያስተምራቸው ነበር። ይህ እውነት በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ አልተጠቀሰም። ነገር ግን ለአዲስ ኪዳን ሐዋርያትና ነቢያት በመንፈስ

ቅዱስ አማካይነት ተገልጦላቸዋል (4፡11ን ተመልከት)። እግዚአብሔር ለጳውሎስ በግል ስለገለጸለት ይህንኑ ለአሕዛብ ክርስቲያኖች ማካፈሉ የእርሱ ኃላፊነትን ነበር። ይህ እግዚአብሔር ለእርሱ የሰጠው መጋቢነት ወይም የዘመኑ አገልግሎት ነበር። ጳውሎስ ታማኝ መጋቢ በመሆኑ በሮም ታስሮ ነበር። እንደ ብሉይ ኪዳኑ ዮሴፍ ታማኝ መጋቢ ሆኖ መገኘቱ በውሸት እንዲታሰር አደረገው። በመጨረሻ ግን ለእግዚአብሔር ታላቅ ክብርን፥ ለአይሁዶችና ለአሕዛብ ደግሞ መዳንን አስገኘ።

## 2. ለአሕዛብ አስፈላጊ ነበር (3፡6-8)

በ 2፡11-22 ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሠራው ሥራ ኃጢአተኞችን ለማዳን ታላቅ ተግባር እንዳከናወነ ተመልክተናል። አይሁድና አሕዛብን እንዲሁም ሁለቱንም ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቆአቸዋል። ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የሚያቀርበው ይህንኑ እውነት ሲሆን፥ ምን ያህል አስደሳች እንደሆነ መመልከቱ ቀላል ነው። የምሥጢሩ እውነታ የሚያምኑ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት አዲስ ግንኙነት እንዳላቸው ይገልጣል።

በመጀመሪያ ደረጃ፥ ከአይሁድ ጋር አብረው የሚወርሱና እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ከገባው ቃል ኪዳን የተነሣ የሚሰጣቸውን መንፈሳዊ በረከት የሚካፈሉ ናቸው (ገላ. 2፡29)። የክርስቶስን ባለጸግነት አብረን ስለምንካፈል አይሁድ ወይም አሕዛብ መሆኑ ትርፍም ኪሳራም የለውም። አሕዛብም የቤተ ክርስቲያን ማለትም የክርስቶስ አካል አባላት ናቸው። አንድ አካል አለ (ኤፌ. 4፡4)። የሥጋ ልደታችን የዘር መለያችን ሲሆን፥ መንፈሳዊ ልደታችን ደግሞ የአንድ አካል ክፍሎች በማድረግ ያዋሕደናል (1ኛ ቆሮ. 12፡12-14)። ክርስቶስ የአካሉ ራስ ነው (ኤፌ. 5፡22-23)። እያንዳንዱ አማኝ የአገልግሎቱ ተካፋይ ይሆናል (ኤፌ. 4፡10-13)። በመጨረሻም፥ በአዲስ ግንኙነታቸው አሕዛብ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ተካፋዮች ናቸው። በአንድ ወቅት ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ውጭ ነበሩ (ኤፌ. 2፡12)። አሁን ግን በክርስቶስ አማካይነት የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ከሚያምኑ አይሁድ ጋር ተካፋይ ይሆናሉ። በሮሜ 11፡13-15 ላይ ጳውሎስ ያመኑት አይሁድ እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጠውን መንፈሳዊ በረከት እንደሚካፈሉ ገልጾአል። በሮሜ 11፡1-12 ግን እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ምክንያት ለእስራኤል የገባውን ተስፋ እንዳላጠፈ አስረድቶአል። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የእስራኤልን መንፈሳዊ በረከት ትካፈላለች። አንድ ቀን ግን እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ወደቀደመው ክብራቸው በመመለስ ስለ መሬታቸውና ስለ መንግሥታቸው የገባውን ቃል ኪዳን ይፈጽማል።

ምሥጢሩ ላመኑት አይሁዶች አዲስ ግንኙነት ማጎናጸፍ ብቻ ሳይሆን አዲስ ኃይል እንደተሰጣቸውም ያስረዳል (ኤፌ. 3:7)። ይህ ኃይል በጳውሎስ ሕይወት ውስጥ ተመልክቶአል። እግዚአብሔር በጸጋው ካዳነው በኋላ ለአሕዛብ መጋቢ እንዲሆን ሾመው። እግዚአብሔር ይህንን አገልግሎት የሚፈጽምበትም ኃይል ሰጥቶታል። በዚህ ስፍራ «ሥራ» የሚለው ቃል «እነርጂያ» /energeia/ ማለትም «ኢነርጂ» የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የተገኘበት ነው። «ኃይል» የሚለው «ዳይናሚክ» እና «ዲማሚት» የሚሉ ቃላት የመነጩበት የግሪኩ «ዱናሚስ» /dunamis/ ነው። ጳውሎስ ቀደም ሲል በ 1:19–23 ላይ ስለዚህ ታላቅ ኃይል ገልጾልናል። እንደገና በ 3:20 እና በ4:16 ላይ ይህንኑ አሳብ ይጠቅሳል። ለዕለት ሕይወታችንና አገልግሎታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅ የትንሣኤ ኃይል እንዳለን ልንገነዘብ ይገባል።

በመጨረሻም፥ ለአሕዛብ አዲስ በረከት እንዳላቸው ተገልጾአል። ይህም «ፍለጋ የሌለው የክርስቶስ ባለጠግነት» ነው (3:8)። ቀደም ሲል ጳውሎስ «ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት» (2:7) ሲል ገልጾታል። በዚህ ስፍራ «ፍለጋ የሌለው» ይለዋል። «የማይታወቅ» የሚል ፍች መስጠትም ይቻላል። የመልእክቱ አሳብ እነዚህ ባለጠግነቶች እጅግ ከመብዛታቸው የተነሣ ፍጻሜያቸውን ማደናቀፍ የማይቻል መሆኑ ነው። (አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት «የማይታወቅ» የሚለው በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር የሰወረውንና ሳይታወቅ የቆየውን ምሥጢር ለመግለጽ እንደሚያገለግል ይናገራሉ።)

እያንዳንዱ አማኝ እነዚህን ባለጸግነቶች አግኝቶ ሊጠቀም ይችላል? አዎን! እንዲያውም ጳውሎስ ራሱን ከቅዱሳን ሁሉ በታች አድርጎ ስለሚቆጥር (ቁ. 8) የእግዚአብሔርን ባለጸግነት ለመጠቀም ልዩ ሥልጣን እንደሌለው ተናግሮአል። «ጳውሎስ» የሚለው ቃል በላቲን ቋንቋ «ትንሽ» የሚል ፍች ስላለው ምናልባትም ጳውሎስ ይህንን ስም የተጠቀመው ራሱን እንደ ታላቅ ሰው ስላልቆጠረ ይሆናል (የሐዋ. 13:9)። ራሱን ከሐዋርያት ሁሉ እንደሚያንስ አድርጎ ይጠቅሳል (1ኛ ቆሮ. 15:9)። ነገር ግን ሐዋርያ እንደነበረና ይህም እኛ ከምንለው የላቀ መሆኑን እንገነዘባለን። በዚህ ስፍራ እራሱን የሚጠራው «ከቅዱሳን ሁሉ የማንስ» ብሎ ሳይሆን «ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ የማንስ» በማለት ነው (ቁ. 8)። በ1ኛ ጢሞቴዎስ 1:15 ላይ ከኃጢአተኞች ዋና እንደነበር ይገልጻል። አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ጥልቅ ምሥጢር መረዳቱ በአእምሮው እንዲታበይ አያደርገውም። ይልቁንም የተሰበረና ትሑት ልብ ይሰጠዋል።

### 3. ለመላእክት አስፈላጊ ነው (3፡9–10)

ምናልባትም፥ «እግዚአብሔር ስለ ቤተ ክርስቲያን የነበረውን ምሥጢር ለብዙ ዓመታት ሲገልጽ የቆየው ለምንድን ነው?» ብለህ ትጠይቅ ይሆናል። እግዚአብሔር በእስራኤል አማካይነት አሕዛብን እንደሚያድን በብሉይ ኪዳን በግልጽ የተጠቀሰ ቢሆንም፥ አይሁድና አሕዛብ አንድን ፍጥረት ማለትም የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን አብረው እንደሚመሠርቱ የተገለጸበት ስፍራ የለም። እግዚአብሔር ለጳውሎስና ለጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የገለጸው ይህንን ምሥጢር ነው። ይህን ለመቀበል ለአይሁድ የሚያስቸግር ነበር።

ጳውሎስ «አለቆችና ሥልጣናትም» በዚህ ታላቅ ምሥጢር ውስጥ እንደተሳተፉ ተናግሮአል። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አማካይነት መላእክትን እያስተማረ ነው። ጳውሎስ «አለቆችና ሥልጣናት» ሲል በእግዚአብሔር የተፈጠሩትን መልካምና ክፉ መላእክት መጥቀሱ ነበር (ኤፌ. 1፡21፤ 6፡12፤ ቆላ. 1፡16፤2፡15)። መላእክት ፍጡራን በመሆናቸው ሁሉን አዋቂ አይደሉም። እንዲያውም በብሉይ ኪዳን ዘመን መላእክት የእግዚአብሔርን የደኅንነት ዕቅድ ለማወቅ ይጓጉ እንደነበር ጴጥሮስ ገልጾአል (1ኛ ጴጥ. 1፡10–12)። መላእክት የአጥቢያ ማኅበረ ምእመናን ተግባር እንደሚመለከቱ ተናግሮአል (1ኛ ቆሮ. 11፡10)። «ለዓለም ለመላእክትም ለሰዎችም መጫወቻ ሆነናልና» (1ኛ ቆሮ. 4፡9) በማለት ጳውሎስ ይጽፋል።

ለመሆኑ መላእክት ከቤተ ክርስቲያን የሚማሩት ምንድን ነው? «የእግዚአብሔርን ጥበብ» ይማራሉ (ኤፌ. 3፡10)። መላእክት በፍጥረቱ ውስጥ የታየውን የእግዚአብሔርን ኃይል እንደሚያውቁ አያጠራጥርም። ነገር ግን በአዲሱ ፍጥረት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የታየው የእግዚአብሔር ጥበብ ለእነርሱ አዲስ ነው። ጠቢባን ፈላስፎችን ጨምሮ ያልዳኑት ሰዎች የእግዚአብሔርን የማዳን ዓላማ እንደ ሞኝነት ይቆጥሩታል (1ኛ ቆሮ. 1፡18–31)። መላእክት ግን የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ አይተው ጥበቡን ያመሰግናሉ። ጥበቡ የተገለጸበት ቅጽል በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይተረጎምም ጳውሎስ «ዘርፈ–ብዙ ጥበብ» ሲል ጽፎአል። ይህም «ባለ ብዙ ቀለም» የሚል ፍች ያዘለ ነው። ቃሉ የእግዚአብሔር የደኅንነት ዕቅድ የተወጠነበትን ጥበብ ውበትና ዘርፈ– ብዙነት የሚያሳይ ነው።

ሌላም ሊታይ የሚገባው ገጽታ አለ። ክፉ መላእክት ከእግዚአብሔር ምሥጢር ምን ይማራሉ? መሪያቸው ሰይጣን ምንም ጥበብ እንደሌለው ይገነዘባሉ። ሰይጣን መጽሐፍ ቅዱስን ስለሚያውቅ አዳኝ እንደሚመጣ

ብቻ ሳይሆን የሚመጣበትን ጊዜ፥ አኳኋንና ስፍራ ሳይቀር ከብሉይ ኪዳን ተረድቶአል። ነገር ግን አይሁድና አሕዛብ በቤተ ክርስቲያን የሚዋሐዱበትን ምሥጢር ሰይጣን ከየትኛውም የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ሊያገኝ አይችልም። ሰይጣን ያላመኑ አይሁድ መሚሐቸውን ሳይቀበሉ ሲቀሩና አሕዛብ በመሚሐ ሲያምኑ ሊመለከት ይችል ነበር። ነገር ግን ያመኑት አይሁድና አሕዛብ አንድነትን ፈጥረው ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊ ስፍራ ሲቀመጡና ሙሉ ለሙሉ ሰይጣንን ድል ሲነሡት ሊመለከት አይችልም ነበር። ሰይጣን የመስቀሉን ውጤቶች ቢያውቅ ኖሮ በዚያው አንጻር ዕቅዶቹን እንደሚለውጥ ጥርጥር የለውም።

እግዚአብሔር ከዓለም መጀመሪያ አንሥቶ የሰወረውን ይህንን ምሥጢር አሁን በቤተ ክርስቲያን በኩል ገልጾታል። ጳውሎስን የዚህ ታላቅ እውነት መጋቢ ያደረገውም ለዚሁ ነው። ቁጥር 9፥ «ሰዎች ሁሉ የምሥጢሩ መጋቢነት ምን እንደሆነ እንዲገነዘቡ» ተብሎ ሊነበብ ይገባል። እዚህ ላይ አንድ አስደናቂ እውነት አለ። አማኞች ሁሉ የዚህ ታላቅ እውነት ታማኝ መጋቢያን ሊሆኑ ይገባል! ለጳውሎስ፥ ለአሕዛብና ለመላእክት እጅግ አስፈላጊ የነበረው የተቀደሰ ምሥጢር አሁን በእጆችን ውስጥ ይገኛል።

## 4. ዛሬ ለክርስቲያኖች ያስፈልጋል (3፡11–13)

እግዚአብሔር ጳውሎስን ባዳነ ጊዜ የወንጌሉን ታላቅ እውነት በውስጡ አከማችቶአል (1ኛ ጢሞ. 1፡11)። ጳውሎስም በበኩሉ እነዚህን እውነቶች በታማኝነት ሊጠብቁና ሊያካፍሉ ለሚችሉ ለሌሎች ሰዎች አስተላልፎአል (2ኛ ጢሞ. 2፡2)። «ጢሞቴዎስ ሆይ . . . የተሰጠህን አደራ ጠብቅ» (1ኛ ጢሞ. 6፡20)። በሕይወቱ ፍጻሜ ላይ ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ክብር «ሃይማኖቴን ጠብቄአለሁ» ሊል ችሎአል (2ኛ ጢሞ. 4፡7)። በእነዚያ የሐዋርያነት ዘመኑ የወንጌሉ እውነታዎችና ምሥጢሩ ተጠብቀዋል፥ ተሰብከዋል፥ ሊታመኑ ለሚችሉ ሰዎች በአደራ ተሰጥተዋል።

ይሁንና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚያሳየው ብዙ የእግዚአብሔር ቃል እውነቶች በተከታታይ ምእተ ዓመታት ውስጥ ጠፍተዋል። እግዚአብሔር ሁልጊዜ ጥቂት ታማኝ ሰዎች እንዳሉት ግልጽ ነው። ነገር ግን ብዙ የእግዚአብሔር ቃል እውነቶች በሰው ሠራሽ ሥነ መለኮት፥ ትውፊትና ሥርዓት ሥር ተቀብረዋል። ከዚያም እግዚአብሔር የእውነት ፈላጊዎችን ዓይኖች መክፈት በመጀመሩ እነዚህ ታላላቅ እውነቶች እንደገና ሊገለጡ ችለዋል። ማርቲን ሉተር በእምነት የመጽደቅን መርህ አስተምሮአል። ለሌሎች መንፈሳዊ

መሪዎች የመንፈስ ቅዱስን ማንነትና ተግባር፥ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚናገረውን የከበረ እውነትና ልብ በደስታ አሙቆታል። ሁላችንም በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ በመሆናችን ደስ ይለናል።

ብዙዎች ናፖሊዮን በናፖርት አውሮፓን ሊገዛት ደርሶ እንደነበር እናውቃለን። ናፖሊዮን የሳይንስና የሥነ ጥበብ አፍቃሪ እንደነበር ሊናገር የሚችል ሰው ግን ብዙ አይሆንም። ሰውዬው ግን እንደዚያ ነበር። በሐምሌ 1798 ግብጽን መያዝ የጀመረው ናፖሊዮን በመስከረም 1801 ከአገሪቱ ተገዶ ወጣ። ፖለቲካዊና ወታደራዊ ዕቅዶቹን አስመልክቶ እነዚህ ሦስት ዓመታት ኪሳራ ነበሩ። ነገር ግን ናፖሊዮን በጣም ባስደነቀው የከርሰ ምድር ጥናት እነዚህ ዓመታት ውጤት አስገኝተውለታል። በነሐሴ 1799 በሳንድ የተባለው አንድ የፈረንሳይ ዜጋ ከእስክንድሪያ ሠላሳ ማይሎች ርቆ በሚገኝ ስፍራ የሮዜታን ጽላት አገኘ። ይህ ግኝት ለከርሰ ምድር ተመራማሪዎች የግብጹን ሄሮግሊፊክስ ለመረዳትና ለዘመናዊ የግብጽ ጥናቶች በር ከፍቷል።

«ምሥጢሩ» የእግዚአብሔር «ሮዜታ ጽላት» ነው። ይህ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ተስፋ ለሰጠው፥ ክርስቶስ በወንጌላት ላደረገው፥ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ለፈጸመችው፥ ጳውሎስና ሌሎች ጸሐፊዎች በመልእክቶቻቸው ውስጥ ለጻፉትና እግዚአብሔር በዮሐንስ ራእይ ውስጥ በተጻፈው መሠረት ለማድረግ ቃል ለገባው ሁሉ ቁልፍ ነው። ዛሬ የእግዚአብሔር ዕቅድ «እስራኤል ራስ» እንድትሆን አይደለም (ዘዳ. 28፡1-13)። ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንዲሆን እንጂ። ዛሬ ያለነው ከሙሴና ከነቢያት በተለየ መጋቢነት ውስጥ ስለሆነ እግዚአብሔር በግልጽ የተናገረውን ነገር እንዳናምታታ መጠንቀቅ አለብን።

ብዙ አብያተ ክርስቲያን በዝለት ተሸብበው ፍሬያማ አገልግሎት ሳይሰጡ የሚቀሩት በክርስቶስ ያላቸውን ነገር ስለማያውቁ ነው። ለዚህም ምክንያት መልካም የምሥጢሩ መጋቢያን መንፈሳዊ መሪዎች አለመኖራቸው ነው። የእውነትን ቃል በቅንነት ስለማይናገሩ (2ኛ ጢሞ. 1፡15)፥ ሕዝቡ በክርስቶስ ያለውን መንፈሳዊ ስፍራ በማደናገር በክርስቶስ ያላቸውን መንፈሳዊ ባለጸግነት ይነጠቃሉ።

ይህ ስለ ቤተ ክርስቲያን የተገለጸው ታላቅ እውነት እግዚአብሔር ከጊዜ በኋላ ያሰበው አይደለም። ይህ እግዚአብሔር በክርስቶስ ለመፈጸም ያሰበው ዘላለማዊ ዕቅድ ነው (ኤፌ. 3፡11)። ይህንን እውነት ገሸሽ ማድረግ ማለት ዕቅዱን በወጠነው አብ፥ በሞቱ ተግባራዊ

ባደረገው በወልድና የእግዚአብሔርን ዕቅድ በሕይወታችን እውን ለማድረግ በሚያስበው በመንፈስ ቅዱስ ላይ ማመፅ ማለት ነው። ይህንን እውነት ስትረዳ ታላቅ ልበ ሙሉነትና እምነት ሕይወትህን ይሞላዋል (ቁ. 12)። እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ የሚሠራውን ስታውቅና አብረኸው ስትሠራ በአንተ ውስጥና ለአንተ እንደሚሠራልህ እርግጠኛ ትሆናለህ። ፈቃዱን ለማድረግና እግዚአብሔር ዓላማውን በምድር ላይ እንዲፈጽም ለማገዝ ከልባቸው ለሚፈልጉት ሰዎች መለኮታዊ ባለጸግነቶቹ ቀርበውላቸዋል።

ወንጌሉ መጀመሪያ ለአይሁዶች ስለመጣና በእነርሱ አማካይነት ስለተሰራጨ፥ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ወንጌሉ የአይሁዶች እንደሆነ ታስብ ነበር። ጴጥሮስ በመለኮታዊ ምሪት ወደ አሕዛብ እስከሄደበት የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 ገጠመኝ ድረስ አይሁዳውያን አማኞች አንድ አሕዛብ ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት ወደ አይሁዳዊነት መለወጥ እንደነበረበት ያስቡ ነበር። የእግዚአብሔር መንፈስ ቀስ በቀስ ለአብያተ ክርስቲያናት ገለጸላቸው። ይኸውም ከአይሁድም ሆነ ከአሕዛብ እግዚአብሔር ለራሱ ሕዝብ እየጠራ ነበር (የሐዋ. 15፡14)። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የብሔር፥ የዘር፥ የፖለቲካ፥ የአካል ወይም የማኅበራዊ ጉዳዮች ልዩነት አይደረግም። «አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና» (ገላ. 3፡28)።

በዚህ ዘመን የእግዚአብሔርን ዕቅድ መገንዘብ አማኞች በእግዚአብሔር እንዲታመኑ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በአስቸጋሪ የሕይወት ሁኔታዎችም ውስጥ ብርታትን ይሰጣቸዋል። የጳውሎስ ለአሕዛብ መሠቃየት ለአሕዛብ ክብር ነበር። በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር በቁሳዊ ሀብት፥ በብሔራዊ ፍሬያማነትና በአካላዊ ስኬት ይባርካቸው ነበር (ዘዳ. 28)። በማይታዘዙበት ጊዜ ግን እነዚህን በረከቶች ሁሉ ይወስዱባቸው ነበር። በክርስቲያኖች ውስጥ የሚሠራው በዚህ መንገድ አይደለም። በረከታችን መንፈሳዊ እንጂ ቁሳዊ አይደለም (ኤፌ. 1፡3)። በረከቶቹ ሁሉ ሙሉ በሙሉ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ተሰጥተውናል። እነዚህን በረከቶች የምንቀበለው በእምነት ነው። እግዚአብሔርን አንታዘዝም ብንል በበረከቶቹ መደሰታችንና መበልጸጋችን ይቀራል እንጂ እግዚአብሔር በረከቶቹን መልሶ አይወስዳቸውም። ጳውሎስ ሕይወቱን የሰጠና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አማኝ የነበረ ቢሆንም፥ ለእስራት ተዳርጎአል። ጳውሎስ አካላዊና ቁሳዊ በረከቶች ሕይወቱን የሰጠ ክርስቲያን የሁልጊዜ ንብረቶች እንደማይሆኑ ገልጾአል (2ኛ ቆር. 4፡7-12፤ 11፡23-12፡10)።

በመኪናዬ ውስጥ ያገኘሁትን ካርታ በመጠቀም ወደ አንድ የስብከት ፕሮግራም እያመራሁ ነበር። በሆነ ምክንያት የምፈልገውን አገር አቋራጭ መንገድ ስላልለየሁ አቅጣጫዬን ለማወቅ ስል በነዳጅ ማደያ ስፍራ መኪናዬን አቆምሁ።

«የያዙት ካርታ የድሮ ነው። በቅርቡ የተዘጋጀው ይኸውሎት። ይህን ተከትለው ቢጓዙ የፈለጉበት ያደርስዎታል» አለኝ ነዳጅ አዳዩ። እውነቱን ነበር። የሰጠኝን ካርታ ተከትዬ በመሄድ ከምሰብክበት ስፍራ በጊዜው ደረስሁ።

በቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ምሥጢር የማያውቁ ሰዎች በአሮጌ ካርታ መንፈሳዊ ዕድገት ለማምጣት ይጥራሉ። ወይም ደግሞ በሌላ አባባል በተሳሳተ ንድፍ ሕንጻውን ለመገንባት ይፈልጋሉ። በዚህች ምድር ላይ የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት የአሕዛብ ወይም የአይሁድ ባሕል አፍቃሪ እንዲሆኑ የታሰቡ አይደሉም። የአይሁድ ማኅበረ ምእመናን ከአሕዛብ ማኅበረ ምእመናን ጋር ለመተባበር አለመፈለጋቸው የጀርመን ቤተ ክርስቲያን ከስዊድን ቤተ ክርስቲያን ኅብረት ለማድረግ አትፈልግም እንደ ማለት ነው። የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በባሕል፥ በመደብ ወይም በሌላ በማንኛውም ምድራዊ ልዩነት ልትታሰር አይገባም። ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነት ልትገዛ የሚገባት መንፈሳዊ አካል ናት።

አዎን፥ እግዚአብሔር አንድ ምሥጢር ነበረው። ከእንግዲህ ወዲህ ግን ምሥጢር እንዲሆን አይፈልግም። በክርስቶስ ያለህን ግሩም ስፍራ ከተገነዘብህ በዚያው ብርሃን ተመላለስ። በረከቱንም ለሌሎች አካፍል። ይህ ምሥጢር ለጳውሎስ፥ ለአሕዛብና ለመላእክት አስፈላጊ ነበር። ዛሬም ለእኔና ለአንተ አስፈላጊ ሊሆን ይገባል።

ስለዚህ ምክንያት በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብ ፊት እንበረከካለሁ፤ በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነከሩ ክርስቶስም በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ ባለጠግነት መጠን ይስጣችሁ፤ የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይጸና ዘንድ፥ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፥ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፥ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ።

እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው፥ ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።

# 7

# ብልጽግናህን ከእጅህ አስገባ

ይህ በኤፌሶን ውስጥ ከተጠቀሱት ሁለት ጸሎቶች አንዱ ነው። የመጀመሪያው በ1:15–23 ላይ ቀርቦአል። በመጀመሪያው ጸሎቱ ጳውሎስ አጽንኦት የሰጠው ስለ ምእመናን *የልብ ዓይኖች መብራት* ነበር። በዚህኛው ጸሎት ያተኮረው በምእመናን *ብቃት* ላይ ነው። ይህ በአመዛኙ የማወቅ ጉዳይ ሳይሆን እግዚአብሔር የሰጠንን ከእጃችን የማስገባትና በእምነት የሕይወታችን አካል የማድረግ ጉዳይ ነው። ጳውሎስ ሀብታችሁን ከእጃችሁ እንድታስገቡት፥ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ እንድትገነዘቡና መጠቀም እንድትጀምሩ እፈልጋለሁ እያለ ነበር።

እነዚህ ሁለት ጸሎቶችም ሆኑ ሌሎች የወኅኒ ጸሎቶች (ፊልጵ. 1:9–11፤ ቆላ. 1:9–12) ስለ ሥጋዊና ቁሳዊ ፍላጎቶች ሳይሆን ስለ ውስጣዊ ሰው መንፈሳዊ ፍላጎቶች የሚናገሩ መሆናቸውን ማጤን ተገቢ ነው። ስለ ሥጋዊና ቁሳዊ ነገሮች መጸለይ ስሕተት ባይሆንም በእነዚህ ክፍሎች ጳውሎስ ያተኮረው በመንፈሳዊው ላይ ነው። ጳውሎስ ውስጣዊ ሰው የሚገባውን ዓይነት ሆኖ ከተገኘ ውጫዊው ሰው በጊዜው እንደሚረካ ያውቅ ነበር። ብዙዎቹ ጸሎቶቻችን በቁሳዊና በሥጋዊ ፍላጎቶች ላይ ስለሚያተኩሩ የልቡን የጠለቁ መሻቶች ችላ ብለን እንተዋለን። እነዚህን የወኅኒ ጸሎቶ እንደ ራሳችን ጸሎቶች በመጠቀም እግዚአብሔር ውስጣዊውን ሰውነታችን እንዲረዳን መጠየቁ ጠቃሚ ነው። ከሁሉም የሚልቁ ጉድለቶች የሚገኙት በዚህ ክልል ነውና

## 1. ልመና (3:14–15)

የመጀመሪያው ልባችንን የሚነካው ነገር የጳውሎስ አካላዊ ሁኔታ ነው፤ «እንበረከካለሁ።» (ይህ መቼም ከጳውሎስ ጋር በሰንሰለት ለተጠፈረው የሮም ወታደር አስገራሚ ገጠመኝ ሳይሆን አይቀርም።) ስንጸልይ አካላዊ ሁኔታችን ምን መምሰል እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ምንም አይናገርም። አብርሃም ለሰዶም በጸለየ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ነበር (ዘፍጥ. 18:22)። ሰሎሞንም ቤተ መቅደሱን በመረቀ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ነበር (1ኛ ነገ. 8:22)። ዳዊት ስለ መንግሥቱ የወደፊት ጉዳይ በጸለየ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ተቀምጦ ነበር (1ኛ ዜና 17:16)። ኢየሱስም በጌቴሴማኒ ሲጸልይ በግንባሩ ተደፍቶ ይጸልይ ነበር (ማቴ. 26:39)።

ስለ አካላዊ ሁኔታ በዚህ መልእክት ውስጥ አጽንኦት የተደረገበትን ምክንያት ሳትገነዘብ አትቀርም። ከደኅንነት ርቀው እንደጠፉት ኃጢአተኞች ሙታን ነበርን (2፡1)። በክርስቶስ ባመንን ጊዜ ግን ከሞት አስነሥቶ በሰማያዊ ስፍራ አስቀምጦናል (2፡4-6)። ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊ ስፍራ ስለተቀመጥን የምንመላለሰው እርሱን ለማስደሰት ነው (4፡1፥17፤ 5፡2፥8፥ 15)። ዲያብሎስን ልንቋቋመው እንችላለን (6፡10-13)። መቀመጥን ከመመላለስና ከመቆም ጋር የሚያያይዘው መንበርከክ ነው። እንደ ክርስቲያን ለመሆንና ለመዋጋት የሚያስችለንን የእግዚአብሔርን ባለጸግነቶች የምንቀበለው በጸሎት ነው። ዋናው በጉልበታችን መንበርከካችን ሳይሆን ልባችንን ለጌታ አንበርክከን የሚያስፈልገንን ነገር መጠየቃችን ነው።

ጳውሎስ ጸሎቱን ያቀረበው ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አባት ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጸሎት የሚቀርበው ለአብ በወልድ አማካይነት በመንፈስ ቅዱስ ነው። ምንም እንኳ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ የቀረቡ ጸሎቶች ቢኖሩም (1ኛ ተሰ. 3፡12-13)፥ የተለመደው የጸሎት አቀራረብ ይኸው ነው። በኤፌሶን 1፡3 ላይ ጳውሎስ አብን «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት» ሲል ይጠራዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር ላይ በነበረበት ወቅት ሙሉ በሙሉ በመታዘዝ ስለኖረ አብ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነበር። ይህ አገላለጽ የክርስቶስን ሰው መሆን ያስገነዝበናል። ነገር ግን አብ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ በመሆኑ ነው። ይህም የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ያሳያል።

የዚህ ዓለም ሰዎችም ሆኑ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን አባትነት ይጋራሉ። ጳውሎስ «በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ» መለኮት በሆነው በአብ እንደሚጠራ ገልጾአል። በሰማይም ሆነ በምድር ያለው አባትነት ሁሉ ከዚያ ምንጩንና ስያሜውን ያገኘው ከአብ ነው። እርሱ የመጀመሪያው ምንጭ ሲሆን፥ ሌላው አባትነት ሁሉ ከዚያ የተቀዳ ነው። አዳም ከአፈጣጠሩ አንጻር «የእግዚአብሔር ልጅ» ተብሎ ተጠርቶአል (ሉቃ. 3፡38)። አማኞች በዳግም ልደት የእግዚአብሔር ልጆች ሆነዋል (1ኛ ዮሐ. 3፡1-2፤ ዮሐ. 1፡11-13)። ሰዎች ሁሉ በተፈጥሮአቸው የእግዚአብሔር ልጆች አይደሉም። ይልቁንም ያለመታዘዝና የዓመፅ ልጆች ናቸው (ኤፌ. 2፡2-3)። እንደ ፈጣሪነቱ እግዚአብሔር የእያንዳንዱ ሰው አባት ሲሆን፥ በአዳኝነቱ ግን የሚያምኑት ብቻ አባት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉም ሰዎች የሚድኑበት «ሁሉን አቀፍ አባትነት» የሚባል ነገር የለም። «ዳግመኛ ልትወለድ ያስፈልግሃል» (ዮሐ. 3፡7)።

## 2. ጥያቄ (3፡16–19)

በጳውሎስ ጸሎት ውስጥ አራት ጥያቄዎች አሉ። ይሁንና እያንዳንዳቸውን እንደተነጣጠሉ ጥያቄዎች አድርጎ መውሰድ ተገቢ አይደለም። እነዚህ አራት ጸሎቶች የአንድን ቴሌስኮፕ አራት ክፍሎች ይመስላሉ። አንዱ ጥያቄ ወደ ሌላው ይወስዳል። ጳውሎስ የውስጡ ሰው መንፈሳዊ ብርታትን እንዲያገኝ ይጸልያል። ይህ ደግሞ በበኩሉ ከክርስቶስ ጋር ወደ ጠለቀ ልምምድ ይመራል። የጠለቀው ልምምድ የእግዚአብሔርን ታላቅ ፍቅር እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል። ይህም ወደ እግዚአብሔር ፍጹም ሙላት ደርሰው እንዲሞሉ ያደርጋቸዋል። ስለዚህ ጳውሎስ ይጸልይ የነበረው ለብርታት፥ ለጥልቀት፥ ለእውቀትና ለሙላት ነበር።

*ብርታት* (3፡16)። በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ መኖሩ የመዳኑ ምልክት ነው (ሮሜ 8፡9)። በተጨማሪም የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ክርስቲያናዊ አኗኗርን ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል። ጳውሎስ ለአንባብያኑ የተመኘው ይህንኑ ኃይል ነበር። «መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ» (የሐዋ. 1፡8)። ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር አገልግሎቱን የፈጸመው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደሆነ ሁሉ (ሉቃ. 4፡1፥ 14፤ የሐዋ. 10፡38)፥ ዛሬም ለክርስቲያናዊ አኗኗር ብቸኛው ኃይላችን መንፈስ ቅዱስ ነው። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ 59 ጊዜ ተጠቅሶአል። ይህም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከተጠቀሰበት ጠቅላላ ቁጥር አንድ አራተኛ መሆኑ ነው። ይህም መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ምን ያህል የላቀ ስፍራ እንዳለው ያመለክታል። አንድ ሰው እንዳለው፥ «እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ከዚህ ዓለም ቢወስድ ብዙ ክርስቲያኖች የምናከናውነውን ተግባር እንቀጥላለን፤ ልዩነቱን ግን ማንም ላያስተውለው ይችላል» አሳዛኝ ቢሆንም እውነት ነው።

መንፈስ ቅዱስ የተሰጠን እንደ ክብሩ ባለጠግነት ነው (ቁ. 16)። ክርስቶስ ወደ ክብሩ ሲመለስ በሕዝቡ ውስጥ እንዲያድርና ኃይሉን እንዲሰጣቸው መንፈስ ቅዱስን ላከ። አንድን ነገር በራሳችን ኃይል መሥራት ተገቢ አይደለም። ኃይሉ መላክ አለበት። እግዚአብሔር መንፈሱን ከክብሩ ባለጠግነት ሳይሆን እንደ ክብሩ ባለጠግነት ለእኛ መስጠቱ ምንኛ ታላቅ ነገር ነው። እኔ ብዙ ቢሊዮን ብር ኖሮኝ አሥር ብር ብሰጥህ ካለኝ ሀብት ሰጥቼሃለሁ። ነገር ግን አንድ ሚሊዮን ብር ብሰጥህ እንደ ባለጸግነቴ መጠን ሰጥቼሃለሁ ማለት ነው። የመጀመሪያው የተወሰነ ድርሻ ሲሆን ሁለተኛው ካለው አጠቃላይ ሀብት አንጻር የሚሰጥ ነው።

የውስጡ ሰው ይህንን ኃይል መጠቀም ይችላል። ይህም እግዚአብሔር የሚያድርበትና የሚሠራበት የሰው መንፈሳዊ አካል ማለት ነው። ሙት የነበረው የኃጢአተኛው ሰው ውስጣዊ ሰው (ኤፌ. 2:1) ክርስቶስ ተጋብዞ ሲገባበት ሕያው ይሆናል። ውስጣዊ ሰው ሊያይ [መዝ. (119):18]፥ ሊሰማ (ማቴ. 13:9)፥ ሊቀምስና [መዝ. (34):8] ስሜትን ሊያስተናግድ ይችላል (የሐዋ. 17:27)። እግዚአብሔርን መምሰል ሊያስለምዱት ይገባል (1ኛ ጢሞ. 4:7-8)። ሊነጻና [መዝ. (51):7] ሊመገብም ይገባል (ማቴ. 4:4)። የውጭው ሰው ቢጠፋም የውስጡ ሰው ከአካላዊ መበስበስ ባሻገር ሊታደስ ይችላል (2ኛ ቆሮ. 4:16-18)። ለድል የሚያበቃው ይኸው ውስጣዊ ኃይል ነው።

መንፈስ ቅዱስ የውስጡን ሰው ያበረታታዋል ሲባል ምን ማለት ነው? መንፈሳዊ ሰውነታችን በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ውሎ እያደገ ነው ማለት ነው (ዕብ. 5:12-14)። ለእግዚአብሔር ክብር የመኖር ጥረታችን ተግባራዊ የሚሆነው ለመንፈስ ቅዱስ ራሳችንን ስንሰጥና የውስጡን ሰው እንዲቆጣጠር ስንፈቅድለት ብቻ ነው። ይህም ለውስጣዊው ሰው የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ፥ መጸለይና ማምለክ፥ በንጽሕና መመላለስና የስሜት ሕዋሳቶቻችን ፍቅር በተሞላው ታዛዥነት መጠቀም ማለት ነው።

ጥልቀት (3:17)። በዚህ ስፍራ ጳውሎስ የመንፈሳዊ ጥልቀትን ጽንሰ-አሳብ ለማስረዳት ሦስት ማብራሪያዎችን ተጠቅሞአል። ሦስቱም ማብራሪያዎች መኖር፥ ሥርና መሠረት በሚሉት ሦስት ቃላት ውስጥ ይገኛሉ። «መኖር» የሚለው ቃል (እንደ ዶክተር ኬነት ዊስት አገላለጽ)፥ «ተረጋግቶ መቀመጥ፥ የቤተኛነት ስሜት» የሚል ፍች አለው። ክርስቶስ በኤፌሶን አማኞች ልብ ውስጥ እንዳለ የተረጋገጠ ነው። እንዲህ ባይሆን ኖሮ ጳውሎስ በ 1:1 ላይ «ቅዱሳን» ብሎ ባልጠራቸው ነበር። ጳውሎስ የሚጸልየው ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር የጠለቀ ግንኙነት እንዲኖራቸው ነው። ክርስቶስ በልባቸው ውስጥ ተረጋግቶ እንዲቀመጥ ይሻል። ይህም ግልብ (የላይ ላይ) ሳይሆን እየጠለቀ የሚሄድ ኅብረት ነው።

የአብርሃም ሕይወት ለዚህ እውነት ግሩም ማብራሪያ ነው። እግዚአብሔር አብርሃምን በልጅ ለመባረክ ከሁለት መላእክት ጋር ወደ ድንኳኑ መጣ። ከአብርሃም ጋር እየተነጋገሩ ያቀረበላቸውን ምግብ በሉ። አብርሃም የእምነትና ታዛዥ ሰው በመሆኑ ቤተኝነት ተሰማቸው። ነገር ግን ሦስቱ እንግዶች ሌላ ተግባር ነበራቸው። እግዚአብሔር ከተሞቹን ለማጥፋት ስለወሰነ የሰዶምን ኃጢአቶች መገምገም ነበረባቸው። አማኙ ሎጥ በሰዶም ከተማ ይኖር ስለነበር እግዚአብሔር በፍርዱ ከመምጣቱ በፊት ሊያስጠነቅቀው ፈለገ። ይህም ሆኖ

እግዚአብሔር ራሱ ወደ ሰዶም አልሄደም ነበር። ሁለቱን መላእክት ላካቸው (ዘፍ. 18–19)። ይኸውም እግዚአብሔር በአብርሃም ድንኳን ውስጥ የተሰማው ዓይነት ቤተኛነት በሎጥ ቤት ስላልተሰማው ነው።

«ሥር» የሚለው ቃል የዕፀዋቱን ዓለም እንድናስብ ያደርገናል። አንድ ተክል ምግብና ዕድሜ እንዲያገኝ ከተፈለገ ሥሩን ወደ መሬት መስደድ አለበት። አንድ ክርስቲያንም መንፈሳዊ ሥሩን በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ መስደድ አለበት። መዝሙር 1፥1–3 ለዚህ ቃል ፍጹም ተስማሚ አገላለጽ ሲሆን፥ ኤርምያስ 17፥5–8 አሳቡን ይበልጥ ያብራራዋል። አንድ ክርስቲያን ራሱን ሊጠይቅ ከሚገባቸው ጥያቄዎች አንዱ፥ «ምግቤንና ዕድሜዬን የማገኘው ከየት ነው?» የሚል ነው። በክርስትና ሕይወት ውስጥ ኃይል እንዲኖር ከተፈለገ ጥልቀት የግድ አስፈላጊ ነው። ሥሮቹ ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ይበልጥ እየጠለቁ ሊሄዱ ያሻል።

«መሠረት» የሥነ–ሕንጻ ቃል ነው። ሕንጻው የሚያርፍበትን መሠረት ያመለክታል። በመጋቢነት ባገለገልኋቸው ሁለት አብያተ ክርስቲያናት፥ አዳዲስ ሕንጻዎችን የመሥራት ዕድል ነበረን። ሕንጻውን በምንገነባበት ወቅት ከመሬት ፈቅ የምንል አይመስልም ነበር። በሁለተኛው የሕንጻ ግንባታ ፕሮግራም መሬቱ ረግረግ በመሆኑ ለአፈር ምርመራ ብዙ ገንዘብ ማውጣት ነበረብን። ለረዥም ሳምንታት ሠራተኞቹ ከመሠረቱ ፈቀቅ አላሉም። አንድ ቀን በዚህ አሠራራቸው ሳጉረመርም አርክቴክቱ፥ «ፓስተር፥ ለዚህ ሕንጻ እጅግ አስፈላጊው አካል መሠረቱ ነው። ወደ ውስጥ ጠልቀን ካልሄድን ወደ ላይ ከፍ እያለን ልንሄድ አንችልም» ሲል መለሰልኝ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለእኔ ትልቅ ስብከት ሆነኝ።

የሕይወት መከራዎች የልምምዳችንን ጥልቀት ይፈትናሉ። በአንድ ኮሌጅ ውስጥ የመኝታ ክፍል የሚጋሩ ተማሪዎች በአሳብ ባይስማሙ ሌላ ጓደኛ ይፈልጋሉ፤ በመሠረቱ ጓደኝነት ጊዜያዊ ነገር ነው። ነገር ግን እርስ በርሳቸው የሚዋደዱ ባልና ሚስት ባይስማሙ ችግሮቹን ለመፍታት በሚያደርጉት ጥረት ግንኙነታቸው እየጠለቀ ይሄዳል። በአንድ ተክል ላይ የሚነፍስ ነፋስ የሥሩን ጥንካሬ ገሃድ ያወጣል። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሁለት ቤተ ሠሪዎች የተናገረው ታሪክ አለ። ከእነዚህ ሁለቱ አንዱ መሠረቱን ጠልቆ አልቆፈረም ነበር (ማቴ. 7፥24–29)። ጳውሎስ አማኞች ከክርስቶስ ጋር የጠለቀ ግንኙነት እንዲኖራቸው የጸለየው በጠንካራ ፈተናዎች ወቅት ለመቆም እንዲችሉ ነው።

*ማስተዋል* (3፥18–19)። በቅጡ ለመረዳት የቻልነውን ነገር ገንዘባችን ለማድረግ የማንችልበት ጊዜ አለ። ጳውሎስን ያሳሰበው

የእግዚአብሔርን ስፋ ፍቅር የመረዳታችን ጉዳይ ነው። ጳውሎስ በአራት አቅጣጫዎች እንድንኖር ይፈልጋል። እግዚአብሔር ለአብርሃም ርስትን በሰጠው ጊዜ፥ «ተነሣ በምድር በርዝመትዋም በስፋትዋም ሂድ» ብሎታል (ዘፍጥ. 13፡17)። አብርሃም በእምነት በመራመድ ርስቱን መያዝ ነበረበት። እኛ ግን ዛሬ ርስቱ በአራት አቅጣጫዎች ቀርቦልናል፤ ወርድ፥ ርዝመት፥ ጥልቀትና ቁመት። አራተኛው የእግዚአብሔር አቅጣጫ ፍቅር ነው!

ይሁንና እዚህ ላይ አንድ ውስጠ ወይራ አሳብ አለ። ጳውሎስ ከመታወቅ የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር በግል ደረጃ እንድናውቅ ይሻል። ሊለኩ ባይችሉም አቅጣጫዎች እንዳሉ ግን እንረዳለን። «ከመታወቅ የሚያልፈው የክርስቶስ ፍቅር» «ፍለጋ የሌለው የክርስቶስ ባለጠግነት» ከሚለው ጋር ይመሳሰላል (3፡8)። ብልጽግናችን እጅግ ዘመናዊ በሆኑ ኮምፒዩተሮች እንኳ ሊሰላ እስከማይችል ድረስ በክርስቶስ የተትረፈረፈ ሀብት አለን።

ክርስቲያን ለመንፈሳዊ ሕይወቴ የሚያስፈልጉኝ ነገሮች የሉም ብሎ ሊጨነቅ አይገባም። ለመንፈሳዊ ብርታትና ጥልቀት ቢጸልይ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ጸጋ ባለጠግነቶች ሁሉ ከእጁ ሊያስገባ ይችላል። «ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ» (ፊልጵ. 4፡13)። የዚህ ሁሉ ውጤት ምንድን ነው?

*ሙላት* (3፡19)። ተፈጥሮ ባዶነትን ይጠላል ይባላል። ይህ አየር ወይም ውኃ በፍጥነት ወደ ባዶ ስፍራ የሚፈስበትን ምክንያት ሊያብራራ ይችላል። መለኮታዊ ባሕርይ ባዶነትን ይጠላል። እግዚአብሔር ሙላቱን እንድናገኝ ይሻል። «እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ» የሚለው ትርጉም ትክክለኛ ትርጉም ነው። የምንሞላው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ሲሆን (5፡18)፥ የሙላታችን መለኪያ ራሱ እግዚአብሔር ነው (4፡11-16)። ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ሲመረምሩ የተሳሳተ መለኪያ መጠቀማቸው አሳዛኝ ነገር ነው። ሕይወታችንን በደከሙ ክርስቲያኖች እንለካና፥ «ከእነርሱ እሻላለሁ!» ስንል በትምክህት እንናገራለን። ጳውሎስ መለኪያው ራሱ ክርስቶስ እንደሆነ በመግለጹ ስለማንኛውም ነገር ልንመካ እንደማንችል ያስረዳናል። በክርስቶስ ሙላት ልክ ስንደርስ ከልኩ ደርሰናል ማለት ነው።

በአንድ በኩል ክርስቲያኖች ገና ድሮ በክርስቶስ ሙሉ ሆነዋል (ቆላ. 2፡9-10)። ከያዝነው ስፍራ አኳያ በእርሱ ምሉዓን ሆነናል፤ በተግባር ግን በእምነት በምንረዳው ጸጋ ብቻ ደስ እንሰኛለን። ለተግባራዊነት የሚያስፈልገው ሀብት በቦታው አለ። የሚያስፈልገን ነገር ቢኖር ሀብቱን በመቀበል ደስ መሰኘት ነው። ጳውሎስ ስለዚህ

ሙላት የሚለው ስላለው እዚያ ስንደርስ ተጨማሪ አስተያየቶችን እናቀርባለን (5፡18–21)።

## 3. የማሳረጊያ ጸሎት (3፡20–21)

ይህንኑ የጠለቀ መንፈሳዊ ልምምድ በአንክሮ ከገለጸ በኋላ ጳውሎስ ለጸሎቱ የሚስማማ ማሳረጊያ መስጠቱ አስገራሚ አይሆንም። በዚህ የማሳረጊያ ጸሎት ውስጥ ስለ ሥላሴ የቀረበውን አሳብ እናጢን። ጳውሎስ በእግዚአብሔር ወልድ ስለተገኘውና– በአማኞች ውስጥ በሚያድረው በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኃይል ለእግዚአብሔር አብ ጸልዮአል።

ምናልባትም ይህንኑ የማሳረጊያ ጸሎት ለመረዳት ከሁሉም የሚሻለው በአስተዋጽኦ መልክ መመልከቱ ይሆናል፡–

ለእርሱ
አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው
ከሁሉ ይልቅ
ከምናስበው ሁሉ ይልቅ
ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ

ጳውሎስ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የተገኘውን የእግዚአብሔርን ኃይል ታላቅነት ለመግለጽ የሚያግዙትን ቃላት ሁሉ ለመጠቀም የቆረጠ ይመስላል። ጳውሎስ የቀደሙትን ሁለት ምዕራፎች የደመደመው በክርስቶስ ስለተገኘው ታላቅ ድል እግዚአብሔርን በማመስገን ነበር። የክርስቶስ ኃይል እጅግ ታላቅ በመሆኑ ከሞት ተነሥቶ ወደ ሰማይ እንዳረገ ገልጾአል (1፡19–23)። ኃይሉ እጅግ ታላቅ በመሆኑ አይሁድንና አሕዛብን እርስ በርሳቸውና ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቆአል (2፡19–22)። በዚህ አንቀጽ ግን ጳውሎስ ይህ እጅግ የተትረፈረፈ ኃይል የእኛ እንደሆነ ተናግሮአል! ይህም ከምናስበው ወይም ከምንጠይቀው የበለጠ ነው። በሌላ አገላለጽ፥ እንደ ክርስቶስ ፍቅር ሁሉ የክርስቶስ ኃይል ከሰብአዊ ግንዛቤ ወይም መለኪያ የመጠቀ ነው። እኔና አንተ በድል ለመመላለስና ለመዋጋት ከፈለግን ልንጠቀም የሚገባን ኃይል ይኸው ነው።

«ኃይል» የሚለው ቃል በ 3፡7 ላይ እንደተመለከትነው «ዱናሚስ» ነው። «ሥራ» የሚለውም በ1፡11 እና 19፤ 2፡2፤3፡7፤4፡16 የተጠቀሰው «ኢነርጂያ» (ኢነርጂ) ነው። በባትሪ ውስጥ የሚገኘው ኃይል ጥቅም ላይ ካልዋለ ከንቱ ኃይል ነው። እንዲህ ዓይነቱ ኃይል ክምቹ ኃይል ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ኃይል ግን በሕይወታችን ውስጥ ይሠራል። ይህ ኃይል በውስጥ ሰውነታችን ውስጥ ተግባሩን

ያከናውናል (3፡16)። ፊልጵስዩስ 2፡12–13 ከዚህ አሳብ ጋር የሚመሳሰል ነው። የክርስቶስን የትንሣኤ ኃይል ወደ ሕይወታችን የሚያመጣው መንፈስ ቅዱስ ነው።

በአንድ ወቅት በቺካጎ አንድ አስፈላጊ ቀጠሮ ነበረኝና ወደዚያው ለሄድ መንገዱ ባለፈው ምሽት በጣለው ከባድ በረዶ ተመትቶ ነበር። መኪና ማቆሚያ ስላልነበረኝ መኪናዬ በቆመችበት በበረዶ ተዋጠች። ጠንካራ የበረዶ ግግር በፈረፋንጎውና በፓራውልቱ ሥር ተጣብቆ ነበር። በረዶውን ከጠራርግሁና ካራገፍሁ በኋላ የመኪናዬን የነዳጅ ማጠራቀሚያ ክዳን ለመክፈት ቁልፉን ስጨን እንቢ አለኝ። ደጋግሜ ብሞክር አልሳካ አለኝ። የነዳጅ ጣቢያው ሠራተኛ መኪናዋን ጎንበስ ብሎ ሲመለከት ችግሩን አገኘው። ለካስ በረዶውን ለማንሣት ስሞክር የነዳጅ ማጠራቀሚያውን ክዳን ከባትሪው ጋር የሚያገናኘውን ሽቦ በጥሼው ኖሯል።

እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በብዙ ክርስቲያኖች ላይ የሚደርስ ነው። የኃይል ምንጫቸውን ቆርጠዋል። አለማመን፥ ያልተናዘዝነው ኃጢአት፥ ግድየለሽ አኗኗር፥ ዓለማዊነት ኃይላችንን ሊመዘብርብን ይችላል። «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» (ዮሐ. 15፡5)።

እግዚአብሔር ኃይሉን ለእኛ የሚያካፍለን ለምንድን ነው? ለራሳችን ክብር የሚሆኑ ታላላቅ አብያተ ክርስቲያናትን እንድንገነባ ነው? አይደለም! «ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን . . . ክብር ይሁን!» የእግዚአብሔር መንፈስ የተሰጠው የእግዚአብሔርን ልጅ ለማክበር ነው (ዮሐ. 16፡14)። ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ያለችው ለእግዚአብሔር ልጅ ክብር ነው። ዓላማችን ቤተ ክርስቲያኑን በማነጽ እግዚአብሔርን ማክበር ከሆነ እግዚአብሔር ኃይሉን ይሰጠናል። የእግዚአብሔር መንፈስ የቅንጦት ዕቃ ሳይሆን የግድ ሊኖረን የሚገባ ኃይል ነው።

የሚያስገርመው ግን ዛሬ በኃይሉ የምናከናውነው ተግባር ክርስቶስን በዘመናት ሁሉ የሚያስከብር መሆኑ ነው (3፡21)። የቤተ ክርስቲያን ታላቅ አገልግሎት ገና ወደፊት የሚመጣ ነው። አሁን እዚህ የምናከናውነው ተግባር ክርስቶስን ለዘላለም ወደምናከብርበት ወደ ዘላለም ዘመናት እያዘጋጀን ነው።

እርሱ ሁሉን ማድረግ ይችላል፤ ከሁሉ የበለጠና የላቀ የተትረፈረፈ ነገር፤ ሊያደርግ ይችላል!

ልብህን ለመንፈስ ቅዱስ በመክፈትና ከጳውሎስ ጋር ለውስጣዊ ሰው ጥንካሬ. . . ለአዲስ የጠለቀ ፍቅር . . . ለመንፈሳዊ ግንዛቤ . . . እና ለመንፈሳዊ ሙላት. . . በመጸለይ መንፈሳዊ ባለጸግነት ከእጅህ አግባ።

«አትለምኑምና አትቀበሉም» (ያዕ. 4፡2)።

እንግዲህ በጌታ እስር የሆንሁ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ፤ በትሕትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ፤ በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ። በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ። ነገር ግን እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን። ስለዚህ፦ ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ ይላል። ወደ ምድር ታችኛ ክፍል ደግሞ ወረደ ማለት ካልሆነ፥ ይህ ወጣ ማለትስ ምን ማለት ነው? ይህ የወረደው ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው። እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ። እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኮል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህም እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደፊት አይገባንም፥ ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤ ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ፥ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፥ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።

# 8

# አብረን እንጓዝ

የጳውሎስ መልእክቶች ሁሉ አስተምህሮንና ዕለታዊ ኑሮን በውብ ሁኔታ ሚዛናዊ አድርገው ያቀርባሉ። የኤፌሶን መልእክት ለዚህ ፍጹም ምሳሌ ነው። የመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕራፎች በክርስቶስ ስላገኘው በረከት የሚናገረውን አስተምህሮ ሲያቀርቡ፥ የመጨረሻዎቹ ሦስት ምዕራፎች ደግሞ በክርስቶስ ስለተሰጡን ኃላፊነቶች ያስረዳሉ። በቀደመው ክፍል ውስጥ ቁልፉ አሳብ «በረከት» ሲሆን፥ በዚህ ክፍል ግን «መመላለስ» የሚለው ነው (4:1፥17፤ 5:2፥ 8፥15)። በእነዚህ ሦስት የመጨረሻ ምዕራፎች ውስጥ ጳውሎስ *በአንድነት* (4:1–16)፥ *በንጽሕና* (4:17፥5:17)፥ *በስምምነትና* (5:18–6:9) *በድል* (6:10–24) እንድንመላለስ መክሮናል።

ከታች የተመለከተው አስተዋጽኦ እንደሚያሳየው እነዚህ አራት የመመላለስ ገጽታዎች ጳውሎስ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕራፎች ውስጥ ካስተማራቸው ትምህርቶች ጋር ፍጹም ተመሳሳይ ናቸው።

ክፍሉን ጠለቅ ብለን ከመመልከታችን በፊት በቁጥር አንድ ላይ የሚገኙትን ሁለት ቃላት ማጤን ይኖርብናል፤ እነዚህም «እንግዲህ» እና «እለምናችኋለሁ» የሚሉት ናቸው። «እንግዲህ» የሚለው ቃል ጳውሎስ ምክሮቹን በመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕራፎች ላይ እንደመሠረተ የሚያስረዳ ነው (ሮሜ 12:1–2 ከዚህ አሳብ ጋር የሚሄድ ክፍል ነው)። የክርስትና ሕይወት በጭፍን አመለካከት ላይ የተመሠረተ አይደለም፤ የመጽሐፍ ቅዱስን አስተምህሮ በተረዳን መጠን መጽሐፍ ቅዱስ የሚለንን ነገር ለመታዘዝ ይቀለናል። ሰዎች፥ «ስለ መታዘዝ አስተምህሮ አትንገረኝ– ዝም ብዬ የክርስትና ሕይወቴን እንድኖር ተወኝ!» የሚሉ ከሆነ፥ መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ሕይወት ውስጥ እንዴት እንደሚሠራ አለማወቃቸውን ያሳያሉ። «ትክክለኛውን ሕይወት እስከኖርህ ድረስ የምታምነው ነገር ምንም ለውጥ አያመጣም!» የሚለውም አሳብ ከዚህ የተለየ አይደለም። የምታምነው ነገር በሕይወትህ የሚያመጣው ለውጥ አለ፤ ምክንያቱም የምታምነው ነገር የምትኖረውን ሕይወት ይወስናል።

| ባለጸግነታችን | መመላለሳችን |
| --- | --- |
| - የአካሉ ክፍል ለመሆን ተጠራን (ምዕ. 1) | - በተጠራችሁበት መጠራት እንደሚተባ ተመላለሱ- የአካሉ አንድነት (4፡1-16) |
| - ከሙታን ተነሣን (2፡1-10) | - አሮጌውን ልብስ አውልቁ (4፡17-5፡17)፥ በንጽሕና ተመላለሱ |
| - ታርቀናል (2፡11-22) | - በስምምነት ተመላለሱ (5፡18-6፡9) |
| - ክርስቶስ በሰይጣን ላይ ያቀናጀው ድል ምሥጢር ነው (ምዕ. 3) | - በድል አድራጊነት ተመላለሱ (6፡10-24) |

«እለምናችኋለሁ» የሚለው ቃል እግዚአብሔር በፍቅሩ ለክብሩ እንድንኖር እንደሚያደፋፍረን ያመለክታል። ለብሉይ ኪዳን አይሁዶች እንደተናገረው፥ «ብትታዘዙኝ እባርካችኋለሁ» አላለም። ይልቁንም፥ «ቀደም ብዬ ባርኬሃለሁ፡- አሁን ለጸጋዬና ለፍቅሬ ምላሽ በመስጠት ታዘዘኝ» ብሎአል። ክርስቶስ በሚያስደንቅ መንገድ ስለጠራን በዚያ ጥሪ መመላለስ የእኛ ኃላፊነት ነው።

የእነዚህ አሥራ ስድስት ቁጥሮች ዐቢይ አሳብ አማኞች በክርስቶስ ያገኙትን አንድነት የሚገልጽ ነው። ይህም በመጀመሪያው ክፍል ለቀረበው ትምህርት ተገቢ ተዛምዶ ነው። እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እየሠራ ነው። አይሁድንና አሕዛብን በክርስቶስ ከራሱ ጋር አስታርቆአል። የአማኞች በክርስቶስ አንድ መሆን ቀደም ሲል የተገለጸ መንፈሳዊ እውነት ነው። ኃላፊነታችን እንግዲህ ያንን አንድነት መጠበቅ፥ መንከባከብና ማቆየት ነው። ይህንንም ለማድረግ አራት ዐበይት እውነቶችን ማወቅ ይኖርብናል።

## 1. የአንድነት ጸጋ ( 4፡1-3)

አንድነት ሲባል አንድ ዓይነት ወይም ወጥነት ማለት አይደለም። አንድነት ከውስጥ የሚመጣ መንፈሳዊ ጸጋ ሲሆን፥ አንድ ዓይነት የውጫዊ ውጥረት ውጤት ነው። ጳውሎስ ክርስቲያናዊ አንድነትን ለመግለጽ የሰውን የአካል ክፍሎች ምሳሌ አድርጎ ተጠቅሞአል (1ኛ ቆሮ. 12)። በዚህም ክፍል ተመሳሳይ ምሳሌ አቅርቦአል (ቁ. 13-16)። እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ከሌሎች ቢለይም ሁሉም አንድን አካል በመመሥረት አብረው ይሠራሉ።

የመንፈስ አንድነት ለመጠብቅ ከተፈለገ ለዚህ አስፈላጊ የሆኑ ክርስቲያናዊ ጸጋዎች ሊኖሩን ያሻል። በዚህ ክፍል ሰባት ክርስቲያናዊ ጸጋዎች ተዘርዝረዋል። የመጀመሪያው *ትሕትና ወይም ራስን ዝቅ ማድረግ* ነው። አንድ ሰው እንዳለው፥ «ትሕትና፥ እንዳለህ ባወቅህ ወቅት የምታጣው ጸጋ ነው» ሲል ተናግሮአል። ትሕትና ክርስቶስን ማስቀደም፥ ሌሎችን ማስከተልና ራስን ከመጨረሻው ረድፍ ማስቀመጥ ማለት ነው። ይህም ራስን ማወቅ፥ ራስን መቀበልና ለእግዚአብሔር ክብር ራስን መሆን ነው። ራስህንና ስጦታዎችህን ስለተቀበልህ እግዚአብሔር አይኮንንህም (ሮሜ 12፡3)። ራሳችንን ከሚገባን በላይ ወይም ከሚገባን በታች እንድንመለከት አይፈለግም።

ትሕትና ማለት አቅመ ቢስነት አይደለም። ሙሴ ትሑት ሰው ነበር (ዘኁል. 12፡3)፤ ነገር ግን ታላቅ ኃይል ነበረው። ኢየሱስ ክርስቶስ የዋህና በልቡ ትሑት ነበር (ማቴ. 11፡29)፤ ይሁን እንጂ፥ ገንዘብ ለዋጮችን ከቤተ መቅደስ አባርሮአል። በግሪክ ቋንቋ ይህ ቃል በሽታን ለሚያስታግሥ መድኃኒት፥ ለተገራ ፈረስና ለስለስ ብሎ ለሚነፍስ አየር መግለጫነት ያገለግላል። በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ ከቁጥጥር ሥር የዋለ ኃይል እንዳለ እንመለከታለን።

ከትሕትና ጋር ተያይዞ የተጠቀሰው *ትዕግሥት* ነው። አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ለማስወገድ ከመሞከር ይልቅ ሁኔታውን በትዕግሥት መቀበል ማለት ነው። ትዕግሥት ያለ ፍቅር ተግባራዊ ሊሆን አይችልም። «ፍቅር ይታገሣል፤ ቸርነትንም ያደርጋል» (1ኛ ቆሮ. 13፡14)። የመንፈስ አንድነት (ኤፌ. 4፡3) በመንፈስ የመመላለስ ውጤት በመሆኑ (ገላ. 5፡16)፥ ጳውሎስ ከመንፈስ ፍሬ አንዳንዶቹን እየጠቀሰ ነበር (ገላ. 5፡22-23)።

ለመንፈስ አንድነት አስተዋጽኦ የሚያበረክተው ሌላው ጸጋ *ትጋት* ነው። የቃሉ ቀጥተኛ ፍች «የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ወይም ለማጽናት መጓጓት» የሚል ነው። በአንድ ወቅት አንድ በልምዱ የበሰለ አማኝ በቅርቡ ለተጋቡት ባልና ሚስት፥ «በትዳር ሕይወታችሁ ለመደሰት ተግታችሁ መጣር አለባችሁ» ሲል ሰምቻለሁ። በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ግሥ አንድነትን ለመጠበቅ ዘወትር መትጋት እንዳለብን የሚያመለክት ነው። ሁኔታው ከሁሉም የተሻለ እንደሆነ በምናስብበት ጊዜ ሰይጣን ሊያበላሸው ይችላል። የቤት፥ የሰንበት ትምህርት ቤት ወይም የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አንድነት የእያንዳንዱ ተሳታፊ ኃላፊነት ሲሆን፥ ይህም ማብቂያ የሌለው ተግባር ነው።

የመጨረሻው ጸጋ «ሰላም» ነው— «የሰላም ማሰሪያ» በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጦርነትና ሰላም የተያዘበትን ከሁሉም የበለጠ ግልጽ መንገድ

ለማጤን ያዕቆብ 3፡13-4-10ን ማንበብ መልካም ነው። ለውጫዊ ጦርነት ምክንያቱ ውስጣዊ ጦርነት ነው። አንድ አማኝ ከእግዚአብሔር ጋር ካልተስማማ ከሌሎች አማኞችም ጋር መስማማት አይችልም። የእግዚአብሔር ሰላም ልባችንን ሲገዛ አንድነት ይኖራል (ቆላ. 3፡15)።

## 2. የአንድነት መሠረት (4፡4-6)

ዛሬ ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ መንገድ ክርስቲያኖችን ለማስማማት ይሞክራሉ። ለምሳሌ፥ «እኛ ስለ ፍቅር እንጂ ስለ አስተምህሮ ግድ የለንም። እስኪ አስተምህሮዎቻችንን ወደ ጎን ትተን እርስ በርሳችን እንዋደድ!» ይላሉ። ጳውሎስ ግን በመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕራፎች ውስጥ ስለ መንፈሳዊ አንድነት አልተናገረም፤ የአስተምህሮውን መሠረት እስኪጥል ድረስ መጠበቅ ነበረበት። ክርስቲያኖች ሁሉ በአነስተኛ ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች ላይ ባይስማሙም መሠረታዊ በሆኑ እውነቶች ላይ ግን ይስማማሉ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ በማንኛውም ነገር ላይ የተመሠረተ አንድነት ጽኑ መሠረት ሊኖረው አይችልም። ጳውሎስ በዚህ ስፍራ እውነተኛ ክርስቲያኖችን ሁሉ ሊያስተሳስሩ የሚችሉ ሰባት ነጥቦችን ዘርዝሮአል።

*አንድ አካል* – ይህ እያንዳንዱ አማኝ ዳግም ሲወለድ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የክርስቶስ አካል የሚሆንበት ነው (1ኛ ቆሮ. 12፡12-31)። አንድ አካል እግዚአብሔር በዓለም ዙሪያ ለመሠረታቸው በርካታ አጥቢያ አካላት ምሳሌ ነው። አንድ ሰው የአንዱ አካል አባል መሆኑ የአጥቢያ አካል አባል እንዳይሆን ምክንያት ሊሆነው አይችልም። መንፈሳዊ ስጦታዎቹን ተግባራዊ የሚያደርገውና የሌሎችን ዕድገት ለማገዝ የሚሠራው እዚህ ነውና።

*አንድ መንፈስ*– አንዱ መንፈስ ቅዱስ በሁሉም አማኞች ውስጥ ስለሚያድር በጌታ አንዳችን የሌላው ነን። መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያናዊ አኗኗራችን አስፈላጊ በመሆኑ በኤፌሶን መልእክት ውስጥ ቢያንስ አሥራ ሁለት ጊዜ ተጠቅሶአል።

*በአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ* – ይህ ጌታ ቤተ ክርስቲያኑን ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመውሰድ የሚመጣበትን ሁኔታ ያመለክታል። በውስጣችን ያለው መንፈስ ቅዱስ የዚህ ታላቅ የተስፋ ቃል ማረጋገጫ ነው (1፡13-14)። ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የአንድን አካል ሕልውና የሚገነዘብ፥ በመንፈስ የሚመላለስና የጌታን ምጽአት የሚጠባበቅ አማኝ የሰላም እንጂ የሁከት መልእክተኛ ሊሆን እንደማይችል ገልጾአል።

*አንድ ጌታ* – ይህ ስለ እኛ የሞተው፥ ስለ እኛ የሚኖረውና አንድ ቀን ስለ እኛ የሚመጣው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሁለት አማኞች አንዱን ጌታ እናምናለን እያሉ በአንድነት ለመጓዝ አለመቻላቸው ለማመን የሚያስቸግር ነገር ነው። የሕንድ መንፈሳዊ መሪ ለነበሩት ጋንዲ፥ «በሕንድ አገር ክርስትና እንዳይስፋፋ እንቅፋት የሆነው ችግር ምንድን ነው?» የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። የጋንዲ መልስ «ክርስቲያኖች» የሚል ነበር። የክርስቶስን ጌትነት መቀበሉ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ለሚኖር አንድነት ወሳኝ እርምጃ ነው።

*አንድ እምነት*– ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያስቀመጠው አንድ እውነት አለ፤ ያም እውነት እምነት ነው። ይሁዳ «ለቅዱሳን አንድ ጊዜ የተሰጠው እምነት» ሲል ጽፎአል (ቁ. 3– በ1980 ዓ.ም ትርጉም)። የጥንት ክርስቲያኖች ያስተማሩትን፥ የጠበቁትንና ለሌሎች ያስተላለፉትን መሠረታዊ አስተምህሮ ለይተው አውቀዋል (2ኛ ጢሞ. 2፡2)። ክርስቲያኖች በአንዳንድ የአተረጓጎምና የአኗኗር ጉዳዮች ላይ ሊለያዩ ቢችሉም በእምነት ይስማማሉ። ከእምነት ማፈንገጥ ማለት በክርስቶስ አካል ውስጥ ክፍፍል መፍጠር ነው።

*አንዲት ጥምቀት* – ጳውሎስ እየገለጸ ያለው ስለ አንድ አካል ስለሆነ ይህ «አንዲት ጥምቀት» የተባለው የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት የሚያመለክት ይሆናል። ይህም ኃጢአተኛው በክርስቶስ አምኖ ደኅንነት በሚቀበልበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ አካል ክፍል የሚያደርግበት ነው (1ኛ ቆሮ. 12፡13)። ይህ ከደኅንነት በኋላ የሚከሰት ወይም አማኙ የሚሻውና የሚጸልይበት ጉዳይ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ እንድንሞላ እንጂ (ኤፌ. 5፡8)፥ በመንፈስ ቅዱስ እንድንጠመቅ ያዘዘበት ክፍል የለም፤ በዳግን ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀናልና። አንዱን አካል በተመለከተ አንድ ጥምቀት ማለትም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ብቻ አለ። ነገር ግን የአጥቢያ አማኞችን በተመለከተ ሁለት ጥምቀቶች አሉ– የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና የውኃ ጥምቀት።

*አንድ አምላክና የሁሉም አባት* – ጳውሎስ እግዚአብሔርን እንደ አባት ለመግለጽ ይፈልጋል (1፡3፥17፤2፡18፤3፡14፤5፡20)። እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ ሆኖ በሁሉም አማካይነት በሁሉም ውስጥ የሚሠራ በመሆኑ አማኞች በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ አንድ ሆነው ታይቷል። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የምንገኝ፥ አንዱን አባት የምናፈቅርና የምናገለግል ልጆች በመሆናችን በአንድነት ለመመላለስ ልንቸገር አይገባም። ልክ እንደ ምድራዊ ቤተሰብ፥ በቤተሰብ ውስጥ የፍቅርን አንድነት ለማኖር የተለያዩ አባላት ለመስጠትና ለመውሰድ

ፈቃደኞች ሊሆኑ ይገባል። የእግዚአብሔርም ለማያዊ ቤተሰብ ይህንኑ ማድረግ አለበት። «አባታችን ሆይ» የሚለው ጸሎት የሚጀምረው በ«አባታችን» እንጂ «አባቱ» አይደለም።

ጳውሎስ ክርስቲያኖች ሐሰተኛ አስተምህሮ በመከተል የመንፈስን አንድነት እንዳያበላሹ በሚገባ መክሯል (ሮሜ 16፡17-20)። ሐዋርያው ዮሐንስም ይህንኑ ማስጠንቀቂያ አስተጋብቶአል (2ኛ ዮሐ. 6-11)። የእግዚአብሔር ጥበብ መጀመሪያ ንጽሕና ከዚያ ሰላም የሚል በመሆኑ (ያዕ. 3፡17)፥ አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በተፈለገው ዋጋ ሰላምን ልትከተል አትችልም። ጤናማ እምነት ይዘው ጤናማ የፍቅር ሕይወት የሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት ስላሉ የአስተምህሮ ንጽሕና በራሱ መንፈሳዊ አንድነትን አያመጣም። ጳውሎስ «እውነትን በፍቅር እንናገር» በማለት ሁለቱን ያዋሐደው ለዚህ ነው (ኤፌ. 4፡15)።

## 3. ስጦታዎች ለአንድነት (4፡7-11)

ጳውሎስ ሁሉም ክርስቲያኖች በጋራ ካሉዋቸው ነገሮች በመነሣት – ወደሚለያዩባቸው ነገሮች ያመራል። በመንፈስ አንድነት ውስጥ የሚገኙትን ልዩነቶችና ግለሰባዊነቶች ያብራራል። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ ቢያንስ አንድ መንፈሳዊ ስጦታ ሰጥቷል (1ኛ ቆሮ. 12፡1-12)። ይህም ስጦታ የክርስቶስን አካል አንድ ለማድረግና ለማነጽ ሊያገለግል ይገባል። እዚህ ላይ በመንፈሳዊ ስጦታዎችና በተፈጥሮአዊ ችሎታዎች መካከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ አለብን። በዚህ ዓለም ስንወለድ እግዚአብሔር የተወሰኑ ተፈጥሮአዊ ስጦታዎችን ሰጥቶናል። ይህም ሜካኒክ፥ የኪነ ጥበብ ሰው፥ አትሌት ወይም ከያኒ መሆን ሊሆን ይችላል። በዚህ ረገድ አንዳንድ ሰዎች ከሌሎች የላቁ ቀልጣፋዎች፥ ወይም ጠንካሮች፥ ወይም ችሎታ ያላቸው በመሆናቸው ሁሉም ሰው እኩል አይደለም። በመንፈሳዊ ዓለም ግን ምንም ዓይነት ተፈጥሮአዊ ችሎታ ቢኖረውም ባይኖረውም እያንዳንዱ አማኝ ቢያንስ አንድ መንፈሳዊ ስጦታ አለው። መንፈሳዊ ስጦታ ክርስቶስ እንዲከብርና አማኞች እንዲታነጹ እግዚአብሔርንና ሌሎች ክርስቲያኖችን የማገልገል ብቃት ነው።

አንድ አማኝ ስጦታዎቹን ለይቶ ሊያውቅና ሊያሳድግ የሚችለው እንዴት ነው? በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት በማድረግ ነው። ስጦታዎች የመጫወቻ አሻንጉሊቶች ሳይሆኑ የማነጫ መሣሪያዎች ናቸው። በፍቅር ካልተገለገልንባቸው በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነው የመዋጊያ መሣሪያዎች ይሆናሉ (1ኛ ቆሮ. 12-14)። ክርስቲያኖች የአንድ አካል ክፍሎች በመሆናቸው ተነጣጥለው ሊኖሩ አይገባም።

ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እነዚህን ስጦታዎች እንደሚሰጥ ጳውሎስ አስተምሮአል (ኤፌ. 4፡8–10)። ለዘላለም ድል በመንሣት ወደ ሰማይ አርጎአል። እዚህ ላይ የሚታየው ምርኮኞቹን የሚመራና ከተከታዮቹ ጋር ምርኮውን የሚካፈል የድል አድራጊ ወታደር አዛዥ ምስል ነው። ምርኮኞቹ በዚህ ጊዜ ጠላቶቹ ሳይሆኑ የራሱ ናቸው። በአንድ ወቅት የኃጢአትና የሰይጣን ምርኮኞች የነበሩ ሰዎች የክርስቶስ ምርኮኞች ሆነዋል። ሞትም እንኳ የተሸነፈ ጠላት ነው! ክርስቶስ ወደ ምድር ሲመጣ ከፍተኛ ውርደት ተቀብሎአል (ፊልጵ. 2፡5–11)፥ ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ ግን ከሁሉም የላቀ ክብር አግኝቶአል። ጳውሎስ ዳዊት የጻፈውን የድል መዝሙር ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያዛምደዋል [መዝ. (68)፡18]።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ መንፈሳዊ ስጦታዎች በሦስት ክፍሎች ተዘርዝረዋል — 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡4–11፥27–31፤ ሮሜ 12፡3–8፥ እና ኤፌሶን 4፡11። እነዚህ ስጦታዎች አንድ ዓይነት ባለመሆናቸው ጳውሎስ ምናልባት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን ስጦታዎች ዘርዝሮ አልጨረሰም ይሆናል። ጳውሎስ አንዳንድ ስጦታዎች ከሌሎች በላይ መሆናቸውን ተናግሮአል (1ኛ ቆሮ. 14፡5፥ 39)። በዚህ ክፍል ጳውሎስ አራት ስጦታዎችን ገልጾአል።

*ሐዋርያት*— ቃሉ «ለአንድ ተልዕኮ የተላከ» የሚል ፍች አለው። ኢየሱስ ብዙ ደቀ መዛሙርት ቢኖሩትም አሥራ ሁለት ሐዋርያትን መርጦአል (ማቴ. 10፡1–4)። ደቀ መዝሙር ተከታይ ወይም ተማሪ ሲሆን፥ ሐዋርያ ግን «መለኮታዊ ሹመት የተሰጠው ወኪል» ነው። ሐዋርያት የክርስቶስ ትንሣኤ ምስክር እንዲሆኑና (የሐዋ. 1፡15–22) ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን በአካል እንዲያዩ ዕድል ተሰጥቷቸዋል (1ኛ ቆሮ. 9፡1–2)። በአዲስ ኪዳን አባባል መሠረት ዛሬ ሐዋርያት የሉም። እነዚህ ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን መሠረት በመጣል የረዱ ናቸው– «በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል» (ኤፌ. 2፡20) መሠረቱ አንድ ጊዜ ከተጣለ በኋላ አስፈላጊነታቸው አብቅቶአል። እግዚአብሔር አገልግሎታቸውን በልዩ ተአምራት አጽንቶላቸዋል (ዕብ. 2፡1–4)፥ ስለዚህ ዛሬ እነዚህኑ ተአምራት የግድ መፈለግ አይኖርብንም። ሰፋ ባለው መልክ ግን አማኞች ሁሉ ሐዋርያዊ አገልግሎት አላቸው። «አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ» (ዮሐ. 20፡21)። ነገር ግን «ሐዋርያት ነን» ማለቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም።

*ነቢያት* – አብዛኛውን ጊዜ ነቢያትን የወደፊቱን ነገር ተንባዮች አድርገን እንመለከታቸዋለን፥ ይህ ግን ቀዳሚ ሥራቸው አይደለም። የአዲስ ኪዳን ነቢይ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምር አገልጋይ ነበር

(የሐዋ. 11፡28፤ ኤፌ. 3፡5)። በአዲስ ኪዳን ዘመን አዲስ ኪዳን ተጽፎ ስላላለቀ አማኞች መጽሐፍ ቅዱስ አልነበራቸውም። እነዚህ አጥቢያ ማኅበረ ምእመናን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያውቁት እንዴት ነበር? መንፈስ ቅዱስ የትንቢት ስጦታ ላላቸው ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት ያካፍል ነበር። ጳውሎስ የነቢይነት ስጦታ ምሥጢራትንና እውቀትን ሁሉ ማለትም መንፈሳዊ እውነቶችን መረዳት እንደሆነ ተናግሮአል (1ኛ ቆሮ. 13፡2)። የትንቢት ዓላማ ማነጽ፥ ማበረታታትና ማጽናናት ነው (1ኛ ቆሮ. 14፡3 ቀጥተኛ ትርጉም)። ዛሬ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ እውቀት የሚያገኙት በቀጥታ ከመንፈስ ቅዱስ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከቃሉ ትምህርት ነው። ነቢያት ከሐዋርያት ጋር በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሠረት የመጣል አገልግሎት እንደነበራቸው የሚታወቅ ነው። ዛሬ ግን መሠረቱን የመጣል አገልግሎት ስለተጠናቀቀ አስፈላጊዎች አይደሉም (ኤፌ. 2፡20)።

*ወንጌላውያን* – «ወንጌልን ሰባኪዎች»። እነዚህ ሰዎች ወንጌሉን ሰብከው ኃጢአተኞችን ለማዳን ከቦታ ቦታ ይዘዋወራሉ (የሐዋ. 8፡26–40፤ 21፡28)። አገልጋዮች ሁሉ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ ሊያከናውኑ ይገባል፤ ይህ ማለት ግን ሁሉም አገልጋዮች ወንጌላውያን ናቸው ማለት አይደለም (2ኛ ጢሞ. 4፡5)። ወንጌላውያን የጠፉትን ወደ ክርስቶስ በመመለስ ሐዋርያትና ነቢያት በጣሉት መሠረት ላይ ያንጻሉ። በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እያንዳንዱ አማኝ መስካሪ እንደነበረ ስንመለከት (የሐዋ. 2፡41–47፤11፡19–21)፥ እኛም መመስከር እንዳለብን እንረዳለን። ነገር ግን ዛሬም የወንጌላዊነት ስጦታ ያላቸው ሰዎች አሉ። አንድ አማኝ የዚህ ስጦታ ባለቤት አለመሆኑ ለጠፉት ነፍሳት ከማሰብ ወይም ከመመስከር ሊያቅበው አይችልም።

*እረኞች (መጋቢያን) እና አስተማሪዎች* – እዚህ ላይ «ሌሎቹ» የሚለው ቃል አለመደገሙ ሁለት አገልግሎቶች ያሉት አንድ ኃላፊነት እንዳለ ያመለክታል። እረኝነት ወይም መጋቢነት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የበጎች መንጋ እንደሆነች በማሳየት (የሐዋ. 20፡28)፥ መንጋውን የመመገብና የመምራት ኃላፊነት እንዳለበት ያመለክታል (1ኛ ጴጥ. 5፡1–4– «ሽማግሌ» የሚለው የእረኛ ሌላው ስም ነው)። ይህንንም የሚያደርገው የእግዚአብሔርን ቃል በመመገብ ነው። በጎቹ የሚመሩትና ሥርዓቱን የሚይዙት በቃሉ አማካይነት ነው። ቃለ እግዚአብሔር የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን መጠበቂያና መንከባከቢያ ስለሆነ የትኛውም ዓይነት ማዝናኛ፥ መልካም ኅብረት ወይም ሌላ ሃይማኖታዊ ሥርዓት መተኪያ ስፍራውን ሊወስድ አይችልም።

## 4. የአንድነት ዕድገት (4፡12–16)

ጳውሎስ በዚህ ክፍል ቤተ ክርስቲያን በሁለት ደረጃዎች ከፍሎ እየተመለከተ ነው። ከእውነተኛ አማኞች የተገነባው የክርስቶስ አካል መንፈሳዊ ብስለትን ለማግኘትና እስከ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት ለመድረስ ቀስ በቀስ ሲያድግ ተመለከተ። እንዲሁም በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ አማኞች አንዱ ሌላውን በማገልገልና አብሮ በማደግ መንፈሳዊ አንድነትን ሲቀዳጁ ተመለከተ።

አንድ *በፍሪላንስነት* የሚያገለግል ወንጌላዊ፥ ወዳጁ ወደሆነው ፓስተር በመሄድ የገንዘብ እርዳታ ጠየቀው። ወዳጁም «ከየትኛው ቡድን ጋር ነው የምታገለግለው?» ሲል ጠየቀው።

ሰውየውም «የማትታየው ቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ» ሲል መለሰ። ከዚያም ወዳጁ እንዲህ ሲል ጠየቀው «የትኛው ቤተ ክርስቲያን አባል ነህ?»

አሁንም፥ «የማትታየው ቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ!» ሲል መለሰ።

ወዳጁ ግራ ስለተጋባ «ይህች የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን የምትሰባሰበው መቼ ነው? ፓስተርዋስ ማን ነው?» ሲል ጠየቀው።

ከዚያም ወንጌላዊው «የአንተ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን አይደለችም። እኔ የማትታየው ቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ! ሲል ተናገረ።

«እንግዲያው የማትታይ ቤተ ክርስቲያንህን ለመደገም ይኸውልህ የማይታይ ገንዘብ!» አለ ፓስተሩ ወዳጁ።

ፓስተሩ የአንዱን አካል ህልውና መካዱ አልነበረም። ይልቁንም «የማትታየው ቤተ ክርስቲያን» (ይህ ሐረግ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም) በምትታየው ቤተ ክርስቲያን እንደምታገለግል ለማሳየት በመፈለግ ነው።

ስጦታ ያላቸው መሪዎች «ቅዱሳን የክርስቶስን አካል ለማነጽ ወደሚችሉበት የአገልግሎት ተግባር የማሳደግ» ኃላፊነት አለባቸው። ቅዱሳኑ ይህንን ተግባር ለማከናወን ለመጋቢው አይከፍሉትም። እርሱ በቃሉ አማካይነት ተግባሩን ያከናውኑ ዘንድ ሲያስታጥቃቸው መሪነቱን ይከተሉታል (2ኛ ጢሞ. 3፡13–17)። የቤተ ክርስቲያን ምእመናን የሚያድጉት ቃሉን በመመገብና አንዱ ሌላውን በማገልገል ነው። የመንፈሳዊ ዕድገት የመጀመሪያው ምልክት *ክርስቶስን መምሰል* ነው።

ሁለተኛው ምልክት *ጽናት* ነው። የበሰለ ክርስቲያን በሚያየው ሃይማኖታዊ *ሥርዓት* ሁሉ አይፍገመገምም። የእግዚአብሔርን ልጆች ለማሰርና ወደ ሐሰተኛ ትምህርት ለመከተት የሚሹ ሃይማኖታዊ ጥሪዎች አሉ። የበሰለ ክርስቲያን ግን የሐሰት ትምህርትን በመለየት

ይጠነቀቃል። መናፍቃን ኃጢአተኞችን ወደ ደኅንነት ለመመለስ አይሞክሩም። በችጋር ለሚሠቃየው ሰው የሚያቀብሉት መልካም ዜና ስለሌላቸው ድሆች በሚበዙባቸው አካባቢዎች የነፍስ አድን ተልዕኮዎችን አያካሂዱም። ከዚህ ይልቅ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ያልበሰሉ ክርስቲያኖችን ለማጥመድ ይጥራሉ። በዚህም ምክንያት የሐሰተኛ አስተማሪዎች አባላት የሚመጡት ብዙውን ጊዜ ለሕዝባቸው የእግዚአብሔርን ቃል ከማይመግቡ አብያተ ክርስቲያናት ነው።

ሦስተኛው የብስለት ምልክት *በፍቅር የሚነገር እውነት* ነው–«እውነትን በፍቅር እየያዝን» (4:15)። «ፍቅር የሌለው እውነት ጭካኔ ሲሆን፥ እውነት የሌለው ፍቅር ግብዝነት ነው» የሚለው አባባል ትክክል ነው። ትናንሽ ልጆች እውነትን ከፍቅር ጋር ማጣመር ይቸግራቸዋል። አንድን ሰው ከወደዱና እውነቱ የሚጎዳው ከመሰላቸው እውነቱን ባይሰማው የሚሻል ይመስላቸዋል። ከክርስቲያን ወገኖች ጋር እውነትን በፍቅር ለመካፈል መቻላችን የብስለት ምልክት ነው። «የወዳጅ ማቁሰል የታመነ ነው፤ የጠላት መሳም ግን የበዛ ነው» (ምሳሌ 27:6)።

የመጨረሻው የብስለት ምልክት *ትብብር* ነው (ቁ. 16)። የአንድ አካልና የአጥቢያ አካል ክፍሎች እንደ መሆናችን፥ አንዳችን የሌላው ነን፤ አንዳችን ሌላውን የምንጠቅም ነን፤ አንዳችን ሌላውን የምንፈልግ ነን። እያንዳንዱ አማኝ ምንም የማይጠቅም ቢመስልም ለሌሎች አማኞች የሚያበረክተው አገልግሎት አለው። አካሉ የሚያድገው እያንዳንዱ አማኝ ሲያድግ ነው፤ እያንዳንዱ አማኝ የሚያድገው ደግሞ ቃሉን ሲመገብና ከሌሎች አማኞች ጋር ሲያገለግል ነው። አሁንም በፍቅር ላይ የተሰጠውን አጽንኦት አጢን– «እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ» (4:2)፤ «እውነትን በፍቅር እየያዝን» (4:15)፤ «ራሱን በፍቅር ለማነጽ» (4:16)። ፍቅር በክርስቶስ አካል ውስጥ ትልቅ ስፍራ አለው። ለብቻቸው የተተዉና ችላ የተባሉ ሕፃናት በአግባቡ እንደማያድጉና ለበሽታ እንደሚጋለጡ፥ የፍቅር እንክብካቤ የተደረገላቸው ግን ተገቢውን ዕድገትና ጥንካሬ እንደሚቀዳጁ ጥናቶች ይጠቁማሉ። የእግዚአብሔርም ልጆች ሁኔታ እንዲሁ ነው። ለብቻው ተነጥሎ የሚኖር ክርስቲያን ሌሎችን ሊያገለግል አይችልም። እንግዲህ፥ መንፈሳዊ አንድነት እኛ የምንፈጥረው ነገር አይደለም። ይልቁንም በክርስቶስ ያገኘነው፥ ልንጠብቀውና ልንከባከበው የሚገባ ነገር ነው። እውነት አንድ ያደርጋል፤ ውሸት ግን ይለያያል፤ ፍቅር አንድ ያደርጋል፤ ራስ ወዳድነት ግን ይለያያል። ስለዚህ «እውነትን በፍቅር እየያዝን» አንዳችን ሌላውን እናሠልጥን፤ አንዳችን ሌላውን እናንጽ፤ በዚህ ዓይነት ሁላችንም ክርስቶስን በመምሰል እናድጋለን።

እንግዲህ አሕዛብ ደግሞ በአእምሮአቸው ከንቱነት እንደሚመላለሱ ከእንግዲህ ወዲህ እንዳትመላለሱ እላለሁ፤ በጌታም ሆኜ እመሰክራለሁ። እነርሱ ባለማወቃቸው ጠንቅ በልባቸውም ደንዳንነት ጠንቅ ልቡናቸው ጨለመ፥ ከእግዚአብሔርም ሕይወት ራቁ፤ ደንዝዘውም በመመኘት ርኵሰትን ሁሉ ለማድረግ ራሳቸውን ወደ ሴሰኝነት አሳልፈው ሰጡ። እናንተ ግን ክርስቶስን እንደዚህ አልተማራችሁም፤ በእርግጥ ሰምታችሁታልና፥ እውነትም በኢየሱስ እንዳለ በእርሱ ተምራችኋል፤ ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፥ በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ፥ ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ።

ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፥ እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ። ተቆጡ፤ ኃጢአትንም አታድርጉ፤ በቍጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት። የሰረቀ ከእንግዲህ ወዲህ አይስረቅ፥ ነገር ግን በዚያ ፈንታ ለጎደለው የሚያካፍለው እንዲኖርለት በገዛ እጆቹ መልካምን እየሠራ ይድከም። ለሚሰሙት ጸጋን ይሰጥ ዘንድ፥ እንደሚያስፈልግ ለማነጽ የሚጠቅም ማናቸውም በጎ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ። ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ። መራርነትና ንዴት ቍጣም ጩኸትም መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ። እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፥ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ።

## 9

# አሮጌውን ሰው አስወግዱ!

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው እንድናጠናው ብቻ ሳይሆን እንድንታዘዘውም ጭምር ነው። በኤፌሶን መልእክት ሁለተኛው ክፍል ውስጥ «እንግዲህ» እና «ስለዚህ» የሚሉት ቃላት በተደጋጋሚ ተጠቅሰው የምናገኛቸው በዚህ ምክንያት ነው (4:1፥17፥25፤ 5:1፥7፥14፥17፥24)። ጳውሎስ፥ «ክርስቶስ ያደረገላችሁ ይህን ነው። ስለዚህ እናንተ ደግሞ ለክርስቶስ ልታደርጉለት የሚገባው ይህን ነው» እያለ ነበር። ቃሉን አድራጊዎች እንጂ ሰሚዎች ብቻ መሆን የለብንም (ያዕ. 1:22)። በክርስቶስ መጠራታችን (ኤፌ. 1:18) በአንድነት እንድንመላለስ ሊያነሣሣን ይገባል (4:1-16)። ከሙታን መነሣታችን ደግሞ በንጽሕና (4:17-5-17)፥ ወይም ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች እንደተናገረው በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ሊያነሣሣን ይገባል (ሮሜ 6:4)። በኃጢአታችን የሞትን ሳንሆን በክርስቶስ ሕያዋን ነን፤ ስለሆነም አሮጌውን ሰው አስወግደን አዲሱን ሰው ልንለብስ ያሻል (ቁ. 22፥ 24)። የከፋን ጨርቁን አስወግደን የጸጋውን ልብስ ልንደርብ ይገባል!

### 1. የጳውሎስ ምክር (4:17-19)

በክርስትና ሕይወት ውስጥ የሚከሰቱ አንዳንድ አሉታዊ ነገሮች አሉ። ከነዚህም አንዱ እንደ አሕዛብ መኖር ነው። ክርስቲያን በዙሪያው እንደሚገኙት ዓለማውያን መኖር የለበትም። እነርሱ «በበደላቸውና በኃጢአታቸው ሙታን» ናቸው (2:1)፤ እርሱ ግን ከሙታን ተነሥቶ በክርስቶስ የዘላለምን ሕይወት ተቀብሏል። ጳውሎስ በዳኑትና ባልዳኑት መካከል ያሉትን ልዩነቶች አብራርቶአል።

በመጀመሪያ ደረጃ የክርስቲያኖች *አስተሳሰብ* ከዓለማውያኑ የተለየ ነው። ጳውሎስ በአስተሳሰብ ላይ አጽንኦት ለማድረግ የተጠቀመባቸውን አገላለጾች አጢን፦ አእምሮ (ቁ. 17 እና 23)፥ አለማወቅ (ቁ. 18)፥ ልቡና (ቁ. 18)፥ ክርስቶስን መማር (ቁ. 20)። ደኅንነት የሚጀምረው ከንስሐ ሲሆን፥ ይህም የአስተሳሰብ ለውጥ ነው። አንድ ሰው በክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ እሴቶችን፥ ግቦቹንና ስለ ሕይወት ያለውን አመለካከት ጨምሮ ጠቅላላ ርእዮተ ዓለሙ ይቀየራል። ያልዳኑት ሰዎች አእምሮ ምን ችግር አለበት? አንደኛው አስተሳሰባቸው ከንቱ ነው። ምንም ዓላማ የላቸውም። እግዚአብሔርን ስለማያውቁ በአካባቢያቸው ያለውን ዓለምም ሆነ ራሳቸውን በትክክል

ሊረዱ አይችሉም። በሮሜ 1፡21-25 አሳዛኝ ገለጻ ተሰጥቶአል። ዛሬ በዓለማችን ብዙ እውቀት ቢኖርም ያንን ያህል ጥበብ አይታይም። ቶሮዩ እንዳሉት፥ «የምንጓዝበት መንገድ የተቃና ነው፤ ግባችን ግን የተቃወሰ ነው»።

ያልዳነ ሰው አስተሳሰብ የጨለመ በመሆኑ ከንቱ ነው። በጨለማ ውስጥ ተወዝፎ ሳለ መጽሐፍ ቅዱስን ችላ ብሎ ዘመናዊ ፍልስፍና በመከተሉ የነቃ መስሎ ይሰማዋል። «ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ» (ሮሜ 1፡22)። ሰይጣን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኘውን እውነት እንዲያዩ ስለማይፈልግ የማያምኑትን ሰዎች አእምሮ አሳውሮአል (2ኛ ቆሮ. 4፡3-6)። ዓይኖቻቸው በመታወራቸው ለማየት አለመቻላቸው ብቻ ሳይሆን አእምሮአቸው ስለጨለመ ስለ መንፈሳዊ ነገሮች ትክክለኛ ግንዛቤ ሊኖራቸው አይችልም።

ከዚህ መንፈሳዊ ዕውርነት የተነሣ ያልዳነ ሰው ሙት ነው። እውነትና ሕይወት ጎን ለጎን (አብረው) የሚሄዱ ነገሮች ናቸው። የእግዚአብሔርን ሕይወት የምንቀበለው የእግዚአብሔርን እውነት ስናምን ነው። ነገር ግን የማያምኑ ሰዎች ከዚህ መንፈሳዊ ጥፋት ለመውጣት የሚያስችል ኃይል ያላቸው ሊመስለን ይችላል። የልባቸው ድንዳኔ ግን አስሮና ተብትቦ ይዟቸዋል። ራሳቸውን ለኃጢአት ስለሰጡ ኃጢአት ይገዛቸዋል። የእነዚህን ሦስት ቁጥሮች ግልጽ ማብራሪያ ለማግኘት ሮሜ 1፡18-32ን አንብብ።

ክርስቲያኖች ያልዳኑ ሰዎች እንደሚኖሩት ዓይነት ኑሮ ሊኖሩ አይችሉም፤ ምክንያቱም በሕይወታቸው ውስጥ ከሞት የመነሣት ተአምር ተፈጽሟል። የክርስቲያን ሕይወት ዓላማ ያለው እንጂ ከንቱ አይደለም። አእምሮው በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ተሞልቷል፤ ልቡም በእግዚአብሔር ሕይወት ሙላት ተጥለቅልቋል። ሰውነቱን እንደ ጽድቅ ዕቃ ለእግዚአብሔር አሳልፎ ይሰጣል እንጂ (ሮሜ 6፡13)፥ ለብልሹ ምኞት መርኪያ አይሰጥም። በምንም መልኩ ቢሆን አማኞች ከማያምኑ ሰዎች የተለዩ ናቸው፤ ስለዚህ እንዳልዳኑት ሰዎች መመላለስ የለባቸውም።

## 2. የጳውሎስ ምክንያት (4፡20-24)

ጳውሎስ ከተደራሲያኑ መንፈሳዊ ሕይወት በመነሣት ቀደም ሲል የሰጣቸውን ምክር ከዚህ ቀጥሎ በሚያቀርብላቸው ምክንያት ይበልጥ ያጠናክረዋል። አሁንም ትኩረት የተሰጠው ለአማኙ አስተሳሰብ ወይም አመለካከት ነው። «እናንተ ግን ክርስቶስን እንደዚህ አልተማራችሁትም» (ቁ. 20)። «ስለ ክርስቶስ ተምራችኋል» አላለም፤ ምክንያቱም በክርስቶስ ሳይድኑ ስለ ክርስቶስ መማር ይቻላል።

«ክርስቶስን መማር» ማለት ከክርስቶስ ጋር የግል ግንኙነት ማድረግና በየዕለቱ እርሱን ይበልጥ እያወቁ መሄድ ነው። ስለ ሰር ዊንስተን ቸርችል የሚናገሩ ብዙ መጻሕፍት ስላሉኝ ስለኚህ ታላቅ ሰው ልማርና መጽሐፍ ልጽፍ እችላለሁ። ነገር ግን ሰውዬው በሕይወት ስለሌሉ እርሳቸውን ልማር አልችልም። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሕያው ነው! ስለሆነም ከእርሱ ጋር የግል ኅብረት በማድረግ «ክርስቶስን ልማር» እችላለሁ።

ይህ ኅብረት በቃለ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን እውነት ልማር እችላለሁ። የእግዚአብሔርን ቃል በተሻለ መንገድ ስረዳ የእግዚአብሔርን ልጅ በተሻለ መንገድ አውቀዋለሁ። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ነው (ሉቃስ 24:27፤ ዮሐ. 5:39)። ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ነገሮች ሲያውቅ ያልዳነ ሰው ግን መንፈሳዊ ዕውር ነው። አማኝ ዕለት በዕለት ከክርስቶስ ጋር ባለው ግንኙነት ሲያድግ፥ የማያምን ሰው ግን ክርስቶስን አያውቀውም። እውነትን አምነናል፤ ሕይወትን አግኝተናል፤ ስለሆነም የምንመላለሰው «እኔ. . . መንገድ ነኝ» ብሎ በተናገረው በክርስቶስ እንጂ በማያምነው ዓለም መንገድ አይደለም።

ይሁንና ይህ የተቀበልነው ደኅንነት ጥልቅ ትርጉም አለው፤ በእግዚአብሔር ፊት የስፍራ ለውጥ አጎናጽፎናል። አሮጌው ሕይወት ስለተወገደ በክርስቶስ አማካይነት በአዲስ ሕይወት ልንመላለስ እንችላለን። ቁጥር 22–24 የሮሜ 5–8 ማጠቃለያ ነው፤ በዚህ ክፍል ጳውሎስ አማኞች ከክርስቶስ ጋር በሞቱ፥ በቀብሩና በትንሣኤው እንደተባበሩ ገልጾአል። ይህንኑ አሳብ በኤፌሶን 2:4–6 እና ቆላስይስ 3 ላይ ተጠቅሶአል። እንደ ክርስቲያኖች አእምሮአችንን መቀየር ብቻ ሳይሆን ዜግነታችንንም ለውጠናል። አሁን በክርስቶስ የእግዚአብሔር አዲስ ፍጥረት አካል ስለሆንን (2ኛ ቆሮ. 5:17)፥ የአሮጌው ፍጥረት አሳቦችና መሻቶች ሊገዙን አይገባም።

የዚህ ታላቅ እውነት ማብራሪያ በዮሐንስ 11 ማለት በአልዓዛር ትንሣኤ ተመልክቷል። ኢየሱስ ክርስቶስና ደቀ መዛሙርቱ ቢታንያ ሲደርሱ የጌታ ወዳጅ የነበረው አልዓዛር ከሞተ አራት ቀናት ሆኖት ነበር፥ ማርታ በዚህ ጊዜ የበሰበሰው አስከሬን መሽተት እንደሚጀምር አምና ነበር፥ (ዮሐ. 11:39)። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ብቻ በመናገሩ አልዓዛር ሕያው ሆኖ ከመቃብር ወጣ። ይህም የዮሐንስ 5:24 ማብራሪያ ነው። ጌታችን ቀጥሎ የተናገራቸውን ቃላት ልብ እንበል፤ «ፍቱትና ይሂድ» (ቁ. 44)። ከፈኑን አንሡለት! አልዓዛር ሕያው ስለሆነ የአሮጌው ሞት ግዛት አካል አልነበረም። ለምን የከፈን ጨርቅ ለብሰህ ትሄዳለህ? አሮጌውን አውልቅና አዲሱን ልበስ!

የጳውሎስ ማሳመኛ ምክንያት ይህ ነበር- ከእንግዲህ በክርስቶስ የአዲስ ፍጥረት አካል እንጂ የአሮጌው ኃጢአት አካል አይደለንም! ስለሆነም የከፈን ጨርቁን እናስወግድ! ይህንን የምናደርገው እንዴት ነው? «በአእምሮአችሁ መንፈስ ታደሱ» (ቁ. 23)። ደኅንነት ወደ አንድ ሂደት የሚመራ መንገድ ነው። በክርስቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በአዲሱ ፍጥረት ውስጥ አዲስ ስፍራ ተሰጥቶናል። ነገር ግን ዕለት በዕለት እርሱ የሰጠንን ስፍራ በእምነት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል። ሁለንተናችንን ለእርሱ ስንሰጥ የእግዚአብሔር ቃል አእምሮአችንን ያድሳል (ሮሜ 12፡1-2)። «በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው» (ዮሐ. 17፡17)። አእምሮአችን የእግዚአብሔርን ቃል እውነት በሚረዳበት ጊዜ ቀስ በቀስ በመንፈስ ቅዱስ ይታደሳል። ይህም መታደስ ወደ ተለወጠ ሕይወት ይመራል። ነገሩን በሥጋዊ መንገድ ስናስበው እኛ የምንበላውን ነን፤ በመንፈሳዊ መንገድ ስናስበው ደግሞ እኛ የምናስበውን ነን። «በልቡ እንዳሰበ እንዲሁ ነውና» (ምሳሌ 23፡7)። በየዕለቱ ቃሉን ማሰላሰል፥ መጸለይና ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ማድረግ የሚያስፈልገን ለዚህ ነው።

### 3. ተዛምዶ (4፡25-32)

ጳውሎስ አንድን መርህ በማብራራት ብቻ አይወሰንም። ጳውሎስ ኃጢአቶችን እስከመዘርዘር ድረስ በመዝለቅ ከተለያዩ የሕይወት ክፍሎች ጋር ያዛምዳል። ጳውሎስ በዚህ ክፍል አምስት የተለያዩ ኃጢአቶችን ከዘረዘረ በኋላ እንድናስወግዳቸው ገልጾአል። ምክንያቱንም አቅርቦልናል።

*ውሸት* (ቁ. 25)- ይህ ለማታለል ሲባል ከእውነት የሚቃረን አሳብ መናገር ነው። ከቀኑ ስድስት ሰዓት መሆኑን ከተናገርሁ በኋላ ሰዓቴ ትክክል እንዳልሆነ ባውቅ አልዋሽሁም። ነገር ግን ይህንኑ የተሳሳተ መረጃ የሰጠሁህ ለስብሰባው በሰዓቱ እንዳትደርስ ለማድረግና ከዚህም ጥቅም ለማግኘት ከሆነ፥ ይህ ውሸት ነው። ሰይጣን ውሸታም ነው (ዮሐ. 8፡44)፤ እግዚአብሔር ውሸተኛ እንደሆነ እንድናምንለት ይፈልጋል። «በውኑ እግዚአብሔር . . . አዝዞአልን?» (ዘፍጥ. 3፡1)። እውነትን ስንነጋገር የእግዚአብሔር መንፈስ ይሠራል፤ ውሸትን ስንነጋገር ሰይጣን ይሠራል። ውሸትን በመናገር ሰዎችን የምንረዳ ቢመስለንም እውነቱ ግን እንዲህ አይደለም። አሳዛኝ መዘዞች እንዳለው ለጊዜው ባናስተውልም የኋላ ኋላ ግን መቆጥቆጡ የማይቀር ነው። «ውሸትም ሁሉ ከእውነት እንዳልሆነ ስለምታውቁ. . .» (1ኛ ዮሐ. 1፡21)። ውሸትን ለሚወዱትና ለሚያደርጉት ሲዖል ተዘጋጅቶላቸዋል (ራእይ 22፡15)። ይህ ማለት ውሸትን አንድ ጊዜ እንኳ የተናገረ ሰው ወደ ሲዖል ይሄዳል ማለት አይደለም። ነገር ግን ውሸት ሕይወታቸውን

የተቆጣጠራቸው፥ ውሸትን የሚወዱና የሚናገሩ ሁሉ ለዘላለም በሲኦል ይሠቃያሉ። የክርስቲያን ሕይወት በእውነት መሪነት የሚሠራ ነው።

ጳውሎስ እውነትን ስለመናገር የሰጠውን ምክንያት ልብ እንበል፤ በክርስቶስ አንዳችን የሌላው ነን። አካሉን በፍቅር እንድናንጽና (4:16) አካሉን በእውነት እንድናንጽ አበረታቶናል። «እውነትን በፍቅር እንያዝ» (4:15)። አንዳችን የሌላው ብልት በመሆናችን፥ ሌሎችን መጥቀማችን የማይቀር ነው፥ ከእውነት ውጭ እርስ በርሳችን ልንተናነጽ አንችልም! በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ፍርድ የተሰጠበት የመጀመሪያው ኃጢአት ውሸትን መናገር ነበር (የሐዋ. 5:1–11)።

*ቁጣ* (ቁ. 26–27)– ደስ የማያሰኝ ነገር ሲገጥመን እንቆጣለን። ቁጣ በራሱ ኃጢአት አይደለም፤ እግዚአብሔርም ራሱ የተቆጣበት ጊዜ ነበርና (ዘዳ. 9:8፥ 20፤ መዝ. 2:12)። «የእግዚአብሔር ቁጣ» የሚለው ሐረግ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተደጋግሞ ተጠቅሶአል (ዘኍል. 25:4፤ ኤር. 4:8፤ 12:13)። የእግዚአብሔር ቅዱስ ቁጣ ጌታችን ቤተ መቅደሱን በማንጻት እንዳሳየው በኃጢአት ላይ የሚሰጠው ፍርድ ነው (ማቴ. 21:12–13)። ቁጣ እሳት ይመስል የሚነድ መሆኑም ተገልጾአል (ዘፍጥ. 30:2፤ ዘዳ. 6:15)። አንዳንድ ጊዜ የሰዎች ቁጣ እሳት ይመስል የሚነድ መሆኑም ተገልጾአል (ዘፍጥ. 30:2፤ ዘዳ. 6:15)። አንዳንድ ጊዜ የሰዎች ቁጣ ውስጥ ውስጡን የሚስፋፋ ክፋት ሊሆን ይችላል። በሌላ ጊዜ ደግሞ ከመቅጽበት ገንፍሎ ሊቀጣጠል ይችላል።

ስሜቶቻችን በኃጢአት የተበከሉ በመሆናቸውና በነገሮች ሁሉ የእግዚአብሔርን ዓይነት እውቀት ስለሌለን፥ እውነተኛውን የተቀደሰ ወይም የጽድቅ ቁጣ መቆጣት አንችልም። ከእኛ በተቃራኒው እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በግልጽ ይመለከታል፤ አጥርቶም ያውቃል። የአዲስ ኪዳን መርህ አማኞች በኃጢአት ላይ እንዲቆጡና ሰዎችን ግን እንዲወዱ የሚያበረታታ ነው። «እግዚአብሔርን የምትወድዱ ክፋትን ጥሉ» [መዝ. (97):10]።

ኃጢአትን ሳያደርጉ መቆጣት ይቻላል። ኃጢአትን ካደረግን ግን በቁጣችን ላይ ፀሐይ ሳትጠልቅ ጉዳዩን በፍጥነት ማስተካከል ይኖርብናል። «ከባለጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ» (ማቴ. 5:25)። «ሄደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው» (ማቴ. 18:15)። የቁጣ እሳት በፍቅር ይቅርታ ካልተዳፈነ ተቀጣጥሎ የእግዚአብሔርን ሥራ ያበላሻል። እንደ ኢየሱስ አገላለጽ፥ ቁጣ የግድያ የመጀመሪያው ደረጃ ነው (ማቴ. 5:21–26)፥ ምክንያቱም ቁጣ ነፍሰ ገዳይ ለሆነው ሰይጣን ዕድል ፈንታ ይሰጣል (ዮሐ. 8:44)። እግዚአብሔርንና ሕዝቡን

የሚጠላው ሰይጣን በአማኞች ልብ ውስጥ የቁጣን እሳት ሲመለከት፥ ከእሳቱ ላይ ነዳጅ በመጨመር በእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል። ውሸትም ሆነ ቁጣ ለሰይጣን ፈንታ ይሰጡታል (ቁጥር 27)።

በቺካጎ ከተማ ውስጥ ከሚፈጸሙት 36 ሞቶች አንዱ በሰው እጅ የሚካሄድ ሲሆን፥ ብዙዎቹ ግድያዎች የሚካሄዱት በዘመዶችና በጓደኞች አማካይነት እንደሆነ ይነገራል። ሁለት ጓደኞች (ባብዛኛው ቁማር ሲጫወቱ) ሙግት ይገጥማሉ። አንዱ በንዴት እየጦፈ ይሄድና ጠብመጃውን ወይም ጩቤውን መዝዞ ይገድለዋል። ሆሬስ፥ «ቁጣ ጊዜያዊ ዕብደት ነው» ማለቱ ትክክል ነው።

አንዲት ሴት፥ «አፈነዳውና በዚያው ይወጣልኛል» ስትል ለንዴቷ ጠበቃ ለመቆም ጥራለች።

«አዎ፥ ልክ እንደ ጥይት። ነገር ግን ከተኩሱ በኋላ የሚከሰተውን አደጋ አስቢው» ሲል አንድ ወዳጇ ምላሽ ሰጥቷታል።

አርስቶትል፥ «ማንም ሊቆጣ ይችላል። ነገር ግን የሚመለከተውን ሰው፥ በትክክለኛው ደረጃ፥ በትክክለኛው ሰዓት፥ ለትክክለኛው ዓላማና በትክክለኛው መንገድ መቆጣት ቀላል አይደለም» ብሏል።

ሰሎሞን ጥሩ መፍትሔ አቅርቦአል፤ «የለዘበች ምላስ ቁጣን ትመልሳለች፤ ሸካራ ቃል ግን ቁጣን ታስነሣለች» (ምሳሌ 15፡1)።

*ስርቆት* (ቁ. 28)– «አትስረቅ» የሚለው ከአሥርቱ ትእዛዛት አንዱ ነው። እግዚአብሔር ይህንን ትእዛዝ ሲሰጥ የግል ባለቤትነትን መሥርቷል። አንድ ሰው በጉልበቱ ትርፍ ሊያገኝና ያንን ትርፍ አስቀምጦ ተስማሚ በመሰለው መንገድ የመጠቀም መብት አለው። እግዚአብሔር ለአይሁዶች ስለ ንብረት አያያዝ ብዙ ሕግጋትን የሰጠ ሲሆን፥ እነዚህ ሕጎች ዛሬ የሕጋችን አካል ሆነዋል። መስረቅ በጳውሎስ ዘመን በተለይ በባሪያዎች የሚፈጸም ኃጢአት ነበር። ባሪያዎች የሕግ ከለላ የሌላቸውና የሚያስፈልጋቸውን ለማግኘት የሚቸገሩ ሰዎች ነበሩ። ጳውሎስ ለቲቶ ሲጽፍ፥ ባሪያዎች ሳይሰርቁ ለጌቶቻቸው በታማኝነት እንዲገዙ እንዲያበረታታቸው አሳስቦታል (ቲቶ 2፡10)። ይህም ሆኖ፥ ባሪያዎች ብቻ ሳይሆኑ ሰዎች ሁሉ ይሰርቁ ነበር። ይህንን የምንገነዘበው ጳውሎስ የጻፈው በሥራ ለተቀጠሩት የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በመሆኑ ነው (ኤፌ. 4፡28)።

ሰይጣን ውሸታም ነፍሰ ገዳይ እንደ ሆነ ሁሉ ሌባም ነው። «ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣምና» (ዮሐ. 10፡10)። ይሁዳን ለስርቆት ያነሣሣው ሰይጣን ነው (ዮሐ. 12፡6)። ከቻለ

በእኛም ላይ ይህንኑ ተግባር ከመፈጸም አይመለስም። ሔዋንን በፈተናት ጊዜ ያልተፈቀደውን ፍሬ ወስዳ እንድትበላ በማድረግ የሌብነትን ተግባር አስፈጽሞአታል። እርሷም በበኩሏ አዳምን ለሌብነት ዳርጋለች። የመጀመሪያው አዳም የስርቆት ወንጀል በመፈጸሙ ከኤድን ገነት ተባረረ። የኋለኛው አዳም ክርስቶስ ግን ሌባውን፥ «ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ» ብሎታል (ሉቃ. 23፡43)።

ጳውሎስ ምክሩን ያስተላለፈው ስሜት በሚነካ መንገድ ነው። አንዳችን የሌላው ብልቶች ስለሆንን እውነት መናገር አለብን። ለዲያብሎስ ፈንታ እንዳንሰጥ ቁጣችንን መቆጣጠር አለብን። ችግረኞችን ለመርዳት እንድንችል መሥራት እንጂ መስረቅ የለብንም። ጳውሎስ «የሚያስፈልገውን ለማግኘት ይሥራ፤ ይህም ለመስረቅ እንዳይፈተን ያደርገዋል» ማለት እንደነበረበት ልናስብ ትችላለህ። እርሱ ግን ሥራን ወደ ላቀ ደረጃ በማድረስ፥ ሌሎችን ለመርዳት ስንል መሥራት እንዳለብን ገልጾአል። ብንሰርቅ ሌሎችን እንጎዳለን። ስለሆነም ሌሎችን ለመርዳት እንችል ዘንድ መሥራት አለብን። ጥሩ ሥራ እንኳ የራስ ወዳድነት ተግባር ሊሆን ስለሚችል ጳውሎስ ይህንን ለማስወገድ ይጥራል። እንዳውም በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን፥ «ሊሠራ የማይወድ አይብላ» የሚል መሠረታዊ ደንብ ነበር (2ኛ ተሰ. 3፡10)። ሰነፍ ክርስቲያን፥ ሌሎችንና እግዚአብሔርን ይበዘብዛል። በመሠረቱ ጳውሎስ የተናገረው ከሕመም የተነሣ መሥራት የማይችሉትን ሳይሆን ሊሠሩ የሚፈልጉትን ነው።

ጳውሎስ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን በሚያደራጅበት ወቅት እንኳ በድንኳን እየሠራ የትጉ ሠራተኛ ምሳሌ ነበር። የአይሁድ መምህራን (ራባይ)፥ «ልጅህን ሥራ ካላስተማርህ ስርቆትን ታስተምረዋለህ ማለት ነው» የሚል አባባል ነበራቸው። እያንዳንዱ አይሁዳዊ ራባይ ሥራን ይማራል። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጠራቸው ሰዎች ሁሉ ጥሪው በደረሳቸው ወቅት በሥራ ላይ ነበሩ። ሙሴ በጎችን ሲያግድ፥ ጌዴዎን ስንዴ ይወቃ ነበር። ዳዊት የአባቱን መንጋ ሲጠብቅ፥ የመጀመሪያዎቹ አራት ደቀ መዛሙርት ዓሣ ያሰግሩ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ አናጺ ነበር።

*ክፉ ቃል* (ቁ. 29)– አፍና ልብ የተያያዙ ናቸው። «በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና» (ማቴ. 13፡34)። አንድ ሰው ክርስቲያን ሲሆን ከንግግሩ ለውጥ እንጠብቃለን። በሮሜ መጽሐፍ ውስጥ ክርስቶስ የሰውን ንግግር እንዴት እንደሚለውጥ መመልከቱ አስገራሚ ነው። በርግማንና መራርነት የተሞላው የኃጢአተኛ አፍ (ሮሜ 3፡14) በክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ በደስታ «ኢየሱስ ጌታ ነው» ይላል (ሮሜ 10፡9–10)። እንደተኮነነ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት

በዝምታ ተሸብቦ የነበረው አፍ (ሮሜ 3፡19) እንደ አማኝ እግዚአብሔርን ለማመስገን ይከፈታል (ሮሜ 15፡6)። ልባችን ሲለወጥ የአፋችንም ቃል ይለወጣል። ጳውሎስ ልዩነቱን ያውቅ ነበር። ደኅንነትን ያላገኘ ራባይ በነበረ ጊዜ ግን ለውጥ ተከሰተ። «እነሆ፥ እርሱ ይጸልያል» (የሐዋ. 9፡12)። በእምነት ሰዎችን ከማሳደድ ወደ መጸለይ ተሻገረ።

በማቴዎስ 7፡17–18 የተጠቀሰው «ክፉ» የሚለው ቃል የበሰበሰን ፍሬ ያመለክታል። «የማይረባ፥ መጥፎ፥ ወይም የበሰበሰ» ማለት ነው። የምንናገረው ቃል «ቆሻሻ» እና እርባና ቢስ ሊሆን አይገባም። አንዳንድ ጊዜ አካባቢያችንን በመምሰል ያንን ያህል መንፈሳዊ አለመሆናችንን ልናሳያቸውና ልናስደስታቸው እንሞክራለን። ጴጥሮስ በአንዲት ሴት የክርስቶስ ደቀ መዝሙር መሆኑ ሲገለጥ የዚህ ዓይነት ገጠመኝ ደርሶበታል። «በዚያን ጊዜ– ሰውየውን አላወቀውም ብሎ ሊረግምና ሊምል ጀመረ» (ማቴ. 26፡24)። አፋችን ቆሻሻ ቃል በሚናገርበት ጊዜ የአሮጌው ሕይወት ፍላጎቶች ሊያቆጠቁጡ ይችላሉ (ቆላ. 3፡8)። ከመዳናችን በፊት በመንፈስ ሙታን እንደነበርን አስታውስ (ኤፌ. 2፡1–3)። እንደ አልዓዛር ከበሰበስን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መዓዛ አይኖረንም። ጳውሎስ፥ «ጉሮሮአቸው እንደተከፈተ መቃብር ነው» ማለቱ የሚያስገርም አይደለም (ሮሜ 3፡13)።

መፍትሔው ልባችንን በበረከት መሙላት ነው። ከልብህ እውነትና ንጽሕና ብቻ ይወጣ ዘንድ ልብህን በክርስቶስ ፍቅር ሙላው። ጳውሎስ የእግዚአብሔርን የጸጋ ጨው በምንናገረው ነገር ውስጥ እንድንጨምር መክሮናል። «ንግግራችሁ ሁልጊዜ በጨው እንደተቀመመ በጸጋ ይሁን» (ቆላ. 4፡6)። ከአፋችን የሚወጣው ቃል ለክፋም ሆነ ለበጎ ኃይል እንዳለው አትዘንጋ። ጳውሎስ የሚሰሙንን የሚሰብር ሳይሆን የሚያንጽ ቃል እንድንናገር ይመክረናል። ቃላችን ጸጋን በመስጠት ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ሊስብ ይገባል። ሰይጣን ሰዎችን የሚሰብርና የክርስቶስን ሥራ የሚያፈርስ ቃል መስማት ስለሚያስደስተው ሰዎች ይህንኑ ያደርጉ ዘንድ ያበረታታል። የአንደበትን ኃይል ለማወቅ ከፈለግህ ያዕቆብ ምዕራፍ 3 አንብብ።

*መራርነት* (ቁ. 30–32)– እነዚህ ቁጥሮች በልባችን ስላለው አሳብ በማስጠንቀቅ ጳውሎስ ስለ ቁጣ የገለጸውን አሳብ ያጎላሉ። መራርነት ጠቅላላውን ውስጣዊ ማንነት የሚያበላሽ የተከማቸ ጥላቻ ነው። አንድ ሰው የማንወደውን ተግባር ሲፈጽም በመመልከታችን ጥላቻ ያድርብናል። «ባሎች ሆይ፥ ሚስቶቻችሁን ውደዱ። መራርም አትሁኑባቸው» (ቆላ. 3፡19)። መራርነት ወደ ቁጣ ይመራል። ይህም

በውስጥ የተከማቸው ጥላቻ የሚያፈተልክበት ውጫዊ የስሜት መገንፈል ነው። ብዙውን ጊዜ ቁጣና ንዴት ወደ ድብድብ ወይም ስድብ ይመራሉ። የመጀመሪያው በጡንቻ መደባደብ ሲሆን፥ ሁለተኛው በቃላት መደባደብ ነው። ክርስቲያኖች የዚህ ዓይነት ባሕርይ ያሳያሉ ብሎ ለማመን ቢያስቸግርም፥ ጳውሎስ ከዚህ እኩይ ምግባር የጸዱ ባለመሆናቸው ማስጠንቀቂያ ጽፎላቸዋል። «ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ፥ እነሆ፥ መልካም ነው፤ እነሆም፥ ያማረ ነው» [መዝ. (133):1]።

አንድ ቀን አንድ መልከ ቀና ሸምገል ያለ ሰውዬ ወደ ጥናት ክፍሌ መጥቶ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት እንዳስፈጽምለት ጠየቀኝ። እኔም የማላውቃቸውን ሰዎች ለማጋባት ስለምቸገር እጮኛውን እንዲያመጣትና እንድንወያይ ጠየቅሁት። «እርሷ ከመምጣቷ በፊት ስለዚህ ጋብቻ ላስረዳዎት የምፈልገው ነገር አለኝ። እኔና እርሷ ከዚህ በፊት ተጋብተን ነበር። ከሠላሳ ዓመታት በፊት በሆነ ነገር ተጣላንና በነገሩ ተበሳጭቼ ስለነበር ተለያየን። ከዚያም የጅልነት እርምጃ በመውሰድ ተፋታን። እንደሚመስለኝ ሁለታችንም ይቅር ለመባባል በጣም ኩራተኞች ነበርን። እነዚያን ሁሉ ዓመታት ለየብቻችን አሳልፈን አሁን ምን ያህል ሞኞች እንደነበርን ተረዳን። መራርነታችን የሕይወትን ደስታዎች ቀምቶናል። አሁን እንደገና ተጋብተን እግዚአብሔር ከመሞታችን በፊት ጥቂት የደስታ ዓመታትን ይሰጠን እንደሆነ እንሻለን» ሲል ተናገረ። ብዙውን ጊዜ በውኃ ቀጠነ የሚጀመር መራርነት ትዳሮችን፥ አብያተ ክርስቲያናትንና ጓደኝነትን ያፈርሳል።

ጳውሎስ መራርነትን ለምን ማስወገድ እንዳለብን ሦስት ምክንያቶችን ይሰጠናል። አንደኛው፥ *መንፈስ ቅዱስን ያሳዝናል።* መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ ስለሚኖር ልባችን በመራርነትና በቁጣ ከተሞላ፥ መንፈስ ቅዱስ ያዝናል። ወላጆች የሆንን ሰዎች ልጆቻችን ሲጣሉ ስናይ የዚሁ ዓይነት ስሜት በመጠኑም ቢሆን ይሰማናል። መንፈስ ቅዱስ እጅግ ደስ የሚሰኘው ፍቅር፥ ደስታና ሰላም በሰፈነበት ነው። እነዚህም እርሱን በምንታዘዝበት ጊዜ በሕይወታችን ውስጥ የሚያመርታቸው «የመንፈስ ፍሬ» ናቸው። መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ ወደ ቤቱ እስከሚወስደን ድረስ ስላተመን ትቶን አይሄድም። ምንም እንኳ በኃጢአት ባሕርያችን ምክንያት ደኅንነታችንን ባናጣም፥ የደኅንነትን ደስታና የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ልንለማመድ አንችልም።

ሁለተኛ፥ *ኃጢአታችን ለእኛ ሲል የሞተውን የእግዚአብሔርን ልጅ ያሳዝነዋል።* ሦስተኛ፥ በክርስቶስ ባመንን ጊዜ ይቅር ያለንን

እግዚአብሔር አብን ያሳዝነዋል። እዚህ ላይ ጳውሎስ የመራርነትን መሠረታዊ መንስዔ ጠቅሶአል፤ ሰዎችን ይቀር ለማለት አለመቻልና ይቅር ያለማለት መንፈስ፥ የዲያብሎስ የመዝናኛ ስፍራ ሲሆን፥ ብዙም ሳይቆይ የክርስቲያኖች የውጊያ ሜዳ ይሆናል። አንድ ሰው አውቆም ሆነ ሳያውቅ ቢበድለንና እኛም ይቅር ባንለው በውስጣችን ልብን የሚያደነድን መራርነት ይጎለብታል። በዚህ ጊዜ የምንጎዳው ራሳችንን እንጂ የበደለንን ሰው አይደለም። በልባችን ውስጥ የተከማቸ መራርነት ሰይጣን ሰዎችን በሚያይበት መንገድ እንድናያቸው ያደርገናል፤ በመሠረቱ ግን ሰዎችን ማየት ያለብን እግዚአብሔር እኛን እንዳየን ነው። እግዚአብሔር በቸርነቱ ይቅር ስላለን እኛም ሌሎችን ይቅር ልንላቸው ይገባል። ይቅርታን በማድረግ በረከትን የምናገኝ መሆኑ ቢታወቅም፥ ይቅር የምንለው ለጥቅማችን ወይም ይቅር ለምንለው ሰው ጥቅም ብለን አይደለም—ለክርስቶስ ብለን እንጂ! ይቅር ለማለትና ለመርሳት መማር ከአስደሳች ክርስቲያናዊ ምሥጢራት አንዱ ነው።

በንጽሕና የመመላለስን አነሣሽ ውስጣዊ ምክንያቶች ደግመህ ከልስ፤ እርስ በርሳችን ብልቶች ነን፤ ሰይጣን በሕይወታችን ስፍራ ለማግኘት ይሻል፤ ከሌሎች ጋር መካፈል አለብን፤ እርስ በርሳችን መተናነጽ አለብን፤ እግዚአብሔርን ማሳዘን የለብንም። ከሁሉም በላይ ከሙታን ከተነሣን ዘንዳ ለምን የከፈን ጨርቅ እንለብሳለን? ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ አልዓዛር እንደተናገረው ስለ አንተም፥ «ፍቱትና ይሂድ!» ይላል።

እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፥ ክርስቶስም ደግሞ እንደ ወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ በፍቅር ተመላለሱ።

ለቅዱሳን እንደሚገባ ግን ዝሙትና ርኵሰት ሁሉ ወይም መመኘት በእናንተ ዘንድ ከቶ አይሰማ፤ የሚያሳፍር ነገርም የስንፍና ንግግርም ወይም ዋዛ የማይገቡ ናቸውና አይሁኑ፥ ይልቁን ምስጋና እንጂ። ይህን እወቁ፤ አመንዝራም ቢሆን ወይም ርኵስ ወይም የሚመኝ በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት የለውም። ከዚህ የተነሣ በማይታዘዙት ልጆች ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ይመጣልና ማንም በከንቱ ንግግር አያታልላችሁ። እንግዲህ ከእነርሱ ጋር ተካፋዮች አትሁኑ፤ ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና፥ አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ፤ የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ፥ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ። ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፥ ይልቁን ግለጡት እንጂ፥ እነርሱ በስውር ስለሚያደርጉት መናገር እንኳ ነውር ነውና፤ ሁሉ ግን በብርሃን ሲገለጥ ይታያል፤ የሚታየው ሁሉ ብርሃን ነውና። ስለዚህ፡- አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሣ ክርስቶስም ያበራልሃል ይላል።

እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ፤ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ። ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ።

# 10

# አባታችንን መምሰል

በቁጥር 1 ላይ «መከተል» የሚለው ቃል «መምሰል» የሚል ትርጉም ስላለው ዐረፍተ ነገሩን፥ «እንደተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትመስሉ ሁኑ» ብሎ መተርጎም ይቻላል። ይህ የክፍሉ ጭብጥ ነው። ጳውሎስ ልጆች ወላጆቻቸውን እንደሚመስሉ በመግለጽ ማሳመኛውን ያቀርባል። ይህም ልጆች ላሉዋቸው ሰዎች አንድም አበረታች አልያም አሳፋሪ እውነት ነው። ልጅ ከመኪናው ፊት ወንበር ተቀምጦ እንደ አባቱ ለመንዳት ሲሞክር አይተህ ታውቃለህ? ወይም ሣር እንደሚያጭድ በመምሰል በዚሁ ተግባር ላይ ከተሰማራው አባቱ ኋላ ኋላ ሲከተል አይተህ ታውቃለህ? ወይም ደግሞ በአሳዛኝ መልኩ እንደ አባቱ ሲጋራ ሲያጨስ ወይም አልኮል ሲጠጣ? ምናልባትም ልጆች ከሁሉም በላይ የሚማሩት በማየትና በመኮረጅ ነው።

እኛም የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን አባታችንን ልንኮርጅ ይገባል። በዚህ ክፍል ለቀረቡት ሦስት ምክሮች መሠረቱ ይኸው ነው። እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ (1ኛ ዮሐ. 4:8) በፍቅር ተመላለሱ (5:1–2)። እግዚአብሔር ብርሃን ስለሆነ (1ኛ ዮሐ. 1:5) እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ (5:8)። እግዚአብሔር እውነት ስለሆነ (1ኛ ዮሐ. 5:6) በጥበብ ተመላለሱ (5:15–17)። ጳውሎስ «ተመላለሱ» ሲለን በንጽሕና እንድንመላለስ ነው የሚፈልገው፤ አጥብቆም የሚመክረን በንጽሕና እንድንመላለስ ነው።

## 1. በፍቅር ተመላለሱ (5:1–2)

ይህ ምክር ቀደም ሲል ጳውሎስ ስለ መራርነትና ቁጣ ማስጠንቀቂያ ከሰጠባቸው የምዕራፍ አራት ሁለት የመጨረሻ ቁጥሮች ጋር ይዛመዳል። እነዚህ አመለካከቶች በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ መከሰታቸው አሳዛኝ ነገር ነው። እንደ መጋቢነቴ፥ የቀብር ሥነ ሥርዓቶችንና ጋብቻዎችን በማስፈጽምበት ወቅት በሰዎች ሕይወት ውስጥ ክፋትንና መራርነትን ተመልክቻለሁ። ወዳጅ የሞተበትን ሰው ኀዘን ወይም የጋብቻን ደስታ በሚካፈሉበት ጊዜ ሰዎች ያለፈውን በደል ረስተው እርስ በርሳቸው ለመስማማት የተሻለ አጋጣሚ ይፈጠርላቸዋል ብለህ ታስብ ይሆናል። ይህ ግን እውነት አይደለም። መራርነትን ለማስወገድ እውነተኛ የልብ ፍቅር ያስፈልጋል። «ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናልና» (1ኛ ጴጥ. 4:8)።

ጳውሎስ ክርስቲያን ለምን በፍቅር መመላለስ እንዳለበት አያሌ ምክንያቶችን አቅርቦአል።

*የእግዚአብሔር ልጅ ነው።* በእምነት አማካይነት በክርስቶስ ዳግም በተወለድን ጊዜ «ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች» ሆነናል (2ኛ ጴጥ. 1:4)። እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ የእግዚአብሔር ልጆች በፍቅር መመላለስ ይኖርባቸዋል። ጳውሎስ አንባብያኑ በፍቅር እንዲመላለሱ ሲያበረታታ ለክርስትና ባዕድ የሆነ ነገር እየጠየቃቸው አልነበረም። ምክንያቱም የተቀበልነው አዲሱ ባሕርይ ራሱን በፍቅር ለመግለጽ የሚፈልግ ነው። በመሠረቱ አሮጌው ባሕርይ ራስ ወዳድ ነው፤ በዚህም ምክንያት ቅጥሮችን ይገነባል፤ ጦርነቶችንም ያውጃል። አዲሱ ባሕርይ ግን አፍቃሪ ስለሆነ ድልድዮችን ያንጻል፤ ሰላምን ያውጃል።

*የእግዚአብሔር ውድ ልጅ ነው።* «እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ»። እስቲ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው ለእኛም እንደተናገረ አስብ፤ «የምወደው ልጄ ይህ ነው» (ማቴ. 3:17)። አብ የልጁን ያህል ይወደናል (ዮሐ. 17:23)። በአኗኗራችን ፍቅራችንን ልንገልጽለት ወደሚገባ የፍቅር ግንኙነት መጥተናል። አብ ለእኛ ያለውን ፍቅር ለመግለጽ ከዚህ በላይ ምን ሊያደርግ ይችል ነበር? እርሱን ለማስደሰት በፍቅር መመላለሱ ይበዛብን ይሆን?

*በትልቅ ዋጋ ተገዝቶአል።* «ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም» (ዮሐ. 15:13)። እርሱ ግን ሕይወቱን ለጠላቶቹ ሰጠ (ሮሜ 5:10)። ለእርሱ ያለን ፍቅር ለፍቅሩ የምንሰጠው ምላሽ ነው። ጳውሎስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ያቀረበውን መሥዋዕት፥ በብሉይ ኪዳን በቤተ መቅደሱ መሠዊያ ላይ ከሚቀርበው ጣፋጭ ሽታ ጋር ያነጻጽረዋል (ዘሌዋ. 1:9፥ 13፥17፤ 2:9)። የጣፋጭ ሽታው መልእክት መሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መሆኑ ነው። ይህ ማለት ግን ኃጢአት ሞትን በመጠየቁ ወይም ልጁ የጠፉትን ኃጢአተኞች ለማዳን በመሞቱ ደስ ይሰኛል ማለት አይደለም። ይልቁንም የክርስቶስ ሞት የእግዚአብሔርን ቅዱስ ሕግ በማርካት ለእግዚአብሔር አስደሳችና ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት ይሆናል ማለት ነው። ጣፋጭ ሽታ የሚሆኑ መሥዋዕቶች በዘሌዋውያን 1–3 ላይ ተብራርተዋል። እነዚህም የሚቃጠል መሥዋዕት፥ የእህል ቁርባንና የደኅንነት መሥዋዕት ናቸው። የሚቃጠል መሥዋዕት ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ያሳየውን ፍጹም መታዘዝ ሲያመለክት፥ የእህሉ ቁርባን የባሕርዩን ፍጹምነት ያሳያል፤ የደኅንነቱ መሥዋዕት ደግሞ በኃጢአተኞችና በእግዚአብሔር መካከል የዕርቅ ሥራ መሥራቱን ያስረዳል። የኃጢአት መሥዋዕትና የበደል መሥዋዕት

(ዘሌዋ. 4–5) ክርስቶስ የኃጢአተኛውን ስፍራ የሚወስድበትን ሁኔታ የሚያመለክቱ በመሆናቸው እንደ ጣፋጭ ሽታ አልተቆጠሩም። ኃጢአት ምንም የሚያስደስት ነገር የለውም።

ፍቅር በክርስትና ሕይወት ውስጥ መሠረታዊ ጉዳይ በመሆኑ፥ ጳውሎስ «በፍቅር ተመላለሱ» በማለት ይጀምራል። በፍቅር ብንመላለስ እግዚአብሔርን ካለመታዘዝና ሰዎችንም ከመጉዳት እንታቀባለን፤ «ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታልና» (ሮሜ 13፡8)። መንፈስ ቅዱስ ይህንን ፍቅር በልባችን ውስጥ ያፈሰዋል (ሮሜ 5፡5)።

## 2. እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ (5፡3–14)

እግዚአብሔር ብርሃን ስለሆነና እኛም አባታችንን ስለምንመስል፥ በብርሃን በመመላለስ ከኃጢአት ጨለማ ልንርቅ ይገባል። ጳውሎስ ሐሳቡን ለማብራራት ሲል ስለ ክርስቲያኖች ሦስት መግለጫዎችን ይሰጣል።

*ቅዱሳን ነን* (5፡3–4)። ይህም ማለት ከዓለም የተለየን በመሆናችን ከእንግዲህ በአካባቢያችን ያለው ጨለማ አካል አይደለንም። «ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ ተጠርተናል» (1ኛ ጴጥ. 2፡9)። በጨለማው ዓለም ኃጢአት ውስጥ ለመዘፈቅ ቅዱሳን የተቀበሉት ሕይወት አይፈቅድላቸውም። ጳውሎስ በዚያን ዘመንም ሆነ ዛሬ ተስፋፍተው ከሚገኙት የዝሙትና የርኩሰት ኃጢአቶች እንዲጠበቁ ይመክራል። እነዚህ ኃጢአቶች የክርስቲያኖችንም ሕይወት በመውረር ለአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትም የጎን ውጋት መሆናቸው አሳዛኝ ነገር ነው። መመኘት ከዝሙት ጎን መቀመጡ አለቦታው የተሰለፈ ሊያስመስለው ይችል ይሆናል፤ ሁለቱም ኃጢአቶች የዚያው የወደቀ ሰብአዊ ባሕርይ የተለያዩ አገላለጾች ናቸው። ይኸውም ከቁጥጥር ሥር ያልዋለ ፍላጎት ነው። የሚመኘውም ሆነ የሚያመነዝረው ሰው የራሱ ባልሆነው ነገር ፍላጎቱን ለማርካት ይሻል። የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት (1ኛ ዮሐ. 2፡16) ሁለቱንም ኃጢአቶች ይገልጻል። ይህ «በእናንተ ዘንድ ከቶ አይሰማ!» ብሏል ጳውሎስ።

በቁጥር 4 ላይ አማኞችን ስለ አንደበት ኃጢአት አስጠንቅቆአቸዋል። እነዚህ በመሠረቱ የልብ ኃጢአቶች ናቸው። በቁጥር 3 እና 4 ላይ የተዘረዘሩት ኃጢአቶች ያላቸውን ዝምድና መረዳት ከባድ አይደለም። ሰዎች ፍላጎታቸውን በንግግራቸው ይገልጻሉ። የወሲብ ኃጢአት የሚፈጽሙ ሰዎች ስለዚሁ ጉዳይ ማውራት ይፈልጋሉ። አንዱን ሰው የሚያስለቅሱና የሚያስቁ ነገሮች የባሕርዩ አመልካከቶች ናቸው። የእግዚአብሔር ቅዱሳን በጸያፍ ቋንቋዎች ሊዝናኑ አይችሉም። የስንፍና ንግግር እንደ ቀልድ የሚታይ

ሳይሆን ሰውየውን የሚያቃልልና ሌሎችን የማያንጽ ወይም ለሚሰሙት ጸጋን የማይሰጥ ጣእም– አልባ ጨዋታ ነው (ኤፌ. 4:29)። ጳውሎስ የሚናገረው ምንም ዓላማ ስለሌለው የስንፍና ንግግር እንጂ ጨዋታን አልኮነነም።

*ዋዛ* «በቀላሉ የሚለወጥ» የሚል ፍች ካለው ቃል የተተረጎመ ነው። ይህ የትኛውንም አሳብ ወደ ቀልድ ሊለወጥ የሚችለውን የንግግር ችሎታ ያለውን ሰው የሚያመለክት ነው። የቀልድ ስጦታ ትልቅ በረከት ቢሆንም፥ ከቆሸሸ አእምሮ ወይም ፍላጎት ጋር በሚያያዝበት ጊዜ እርግማን ይሆናል። በቀልደኝነታቸው የሚታወቁ አንዳንድ ሰዎች የትኛውንም ውይይት የዋዛ ፈዛዛ ንግግር የማድረግ ባሕርይ አላቸው። ከዚህ ይልቅ የምስጋና ቃል መናገሩ ምንኛ የተሻለ ነው! ይህ ለእግዚአብሔር ክብር ለመስጠትና ውይይቱን ንጹሕ ለማድረግ ከሁሉም የተሻለ መንገድ ነው።

አንዲት ክርስቲያን ሴት ለጓደኛዋ ክብር በተዘጋጀው የእራት ግብዣ ላይ ስትገኝ ከምግቡ ቀጥሎ የኮሜዲ ፕሮግራም እንደሚካሄድ አላወቀችም ነበር። ኮሜዲያን ተብየው ይህችው ክርስቲያን እንግዳ የተቀደሰ አድርጋ የምትይዘውን ሁሉ የሚያንቋሽሽ ዝግጅት በማቅረብ ሕዝቡን ለማዝናናት ጣረ። በአንድ ነጥብ ላይ የኮሜዲያኑ ጉሮሮ በመድረቁ፥ «እባክህ አንድ ብርጭቆ ውኃ አምጣልኝ» ሲል አስተናባሪውን ለመነው።

ክርስቲያኗ ሴት፥ «የጥርስ ሳሙናና ብሩሽም ጨምረህ አምጣለት!» ስትል ተናገረች። ሳሙና የሰውየውን ንግግር አጥቦ ሊያጠራ ባይችልም፥ ያች እኅት ግን መልእክቷን አስተላልፋለች። የእግዚአብሔርን ቃል በልባቸው የያዙ ክርስቲያኖች (ቆላ. 3:16) ንግግራቸውን ሁልጊዜ በጨው ይቀምሙታል (ቆላ. 4:8)፤ የልብ ጸጋ የከንፈርም ጸጋ ነውና።

*ነገሥታት ነን* (5:5–6)። በክርስቶስ ባመንን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ገብተናል (ዮሐ. 3:3)። ነገር ግን በሚመለስበት ጊዜ የምናገኘውን የመንግሥቱን ሙሉ መገለጥ እየተጠባበቅን ነው (2ኛ ጢሞ. 4:1)። ጳውሎስ ዘወትርና ሆን ብለው ኃጢአትን የሚፈጽሙ ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ ገልጾአል። «እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም» (ገላ. 5:21)። በምግባራቸው ንጹሐን ያልሆኑና ሌሰኞች ከአመንዝሮች ጋር ይፈረድባቸዋል። እነዚህ ማስጠንቀቂያዎች የሚያካትቱት ልማዳዊውን የኃጢአት ተግባር እንጂ በአጋጣሚ የሚፈጸመውን አይደለም። ዳዊት ዝሙት ቢፈጽምም እግዚአብሔር

ይቅር ብሎት ወደ ሰማይ ወስዶታል። ዳዊት ለኃጢአቱ ቢቀጣም እግዚአብሔር አልጣለውም።

በጳውሎስ ዘመን ክርስቲያኖች ኃጢአትን የመሥራት ነጻነት አላቸው የሚሉ ሐሰተኛ ክርስቲያኖች ነበሩ። እነዚህ አሳቾች ክርስቲያኖች በኃጢአታቸው ቢቀጥሉና ይህም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከመግባት የሚከለክላቸው ምንም ነገር የለም በማለት ክርስቲያኖችን ለማሳመን ይጥሩ ነበር። «በጸጋ ስለዳናችሁ የእግዚአብሔር ጸጋ ይበዛ ዘንድ በኃጢአት ጽኑ!» ይሉ ነበር። ጳውሎስ ለዚህ የሞኝነት ክርክር በሮሜ 6 ላይ ምላሽ ሰጥቷል። «የአማኝ ኃጢአት ከማያምነው ሰው ኃጢአት የተለየ ነው!» አዎን፤ የአማኙ ኃጢአት የከፋ ነው። እግዚአብሔር ኃጢአትን የትም ስፍራ ቢያገኝ ይቀጣል። በመሆኑም ከልጆቹ ውስጥ ኃጢአትን ማየት አይፈልግም። እውነተኛ ክርስቲያን ደኅንነቱን ሊያጣ ይችላል ብዬ አላምንም፤ ነገር ግን የእምነቱን እውነተኛነት ታዛዥ በሆነ ሕይወት ማረጋገጥ አለበት።

እውነተኛ አማኞች ሳይሆኑ እንደ አማኝ ለመታየት የሚሞክሩ ብዙ ሰዎች አሉ (ማቴ. 7:21–23)። ክርስቲያን ኃጢአት ሊሠራ አይችልም የሚል አስተያየት የለኝም፤ ነገር ግን ኃጢአት ከሕይወቱ እየተወገደ ይሄዳል። ክርስቲያን ንጉሥ በመሆኑ ከእግዚአብሔር መንግሥት ውጭ ባለው የጠፋ ዓለም ውስጥ በመውደቅ ክብሩን አያዋርድም።

*ብርሃን ነን* (5:7–14)። ጳውሎስ ተደራስያኑ «እንደ ብርሃን ልጆች እንዲመላለሱ» ስለሚመክር ይህ የምንባብ ዐብይ አሳብ ነው። በእግዚአብሔር ልጅና ባልዳነው ሰው መካከል ስላሉት ንጽጽሮች የሚገልጸውን የ2ኛ ቆሮንቶስ 6:14–7:1 ክፍል ማንበቡ ጠቃሚ ነው። ጳውሎስ የተናገረው በጨለማ ውስጥ እንደነበርን ሳይሆን «ጨለማ እንደነበርን» ነው። አሁን ከዳንን ዘንዳ፥ «ብርሃን ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?» መንፈሳዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ብርሃን ፍሬን ሲያፈራ ጨለማ ግን ፍሬ የለውም። «የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና።» በአንድ ጊዜ በጨለማና ብርሃን ውስጥ መሆን አይቻልም!»

ብርሃኑ በጎነትን ያፈራል። ይህም ከመንፈስ ፍሬ መገለጫዎች አንዱ ነው (ገላ. 5:22)። በጎነት በተግባር የተገለጸ ፍቅር ነው። ጽድቅ ማለት በእግዚአብሔርና በሰዎች ፊት ትክክለኛና ቀጥተኛ ሕይወት መኖር ማለት ነው። እነዚህ ሁለቱም በእውነት ላይ የተመሠረቱ ናቸው። እውነት ደግሞ ከእግዚአብሔር ቃልና ከፈቃዱ ጋር መስማማት ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ብርሃንና ጨለማ ብዙ አስተምሮአል። «መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ» (ማቴ. 5፡16)። «ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፥ ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም፤ እውነትን የሚያደርግ ግን ሥራው በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደሆነ ይገለጥ ዘንድ ብርሃን ይመጣል» (ዮሐ. 3፡20-21)።

«እንደ እግዚአብሔር ልጆች መመላለስ» ማለት በእግዚአብሔር ፊት ምንም ነገር ሳይሸሽጉ መኖር ማለት ነው። ሌሎች ሰዎች ልባችንንና አእምሮአችንን ስለማያዩ ከእነርሱ መሸሸግ ቀላል ነው። ነገር ግን «እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖች ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ፥ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም» (ዕብ. 4፡13)። ወደ ስብሰባ የምንጓዘው በአውሮፕላን ነው፤ በዚህ ጊዜ እኔም ሆንሁ ዕቃዎቼ በሙሉ እንዲፈተሹ አደርጋለሁ፤ ይህንን የማደርገው በደስታ ነው። ምክንያቱም ፍተሻው ቦምብ የያዙ ሰዎችን ያጋልጣል። የምደብቀው ነገር ስለሌለኝ «በቁጥጥር መስመር» ለማለፍም ሆነ ዕቃዎቼን በኤክስሬይ መሣሪያ እንዲፈተሹ ለማድረግ አልፈራም።

አንድ ደራሲ የቻርልስ ስፐርጀንን የሕይወት ታሪክ ለመጻፍ ፈቃድ ሲጠይቅ፥ ታላቁ ሰባኪ የሚከተለውን ተናገሩ፥ «ሕይወቴን በሰማይም ላይ ልትጽፍ ትችላለህ፤ የምደብቀው ነገር የለኝም!»

ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ልጆች መመላለስ ማለት በዕለታዊ ሕይወታችን የእግዚአብሔርን ብርሃን መግለጥ ማለትም ነው። በባሕርያችንና በሥራችን የእግዚአብሔርን ብርሃን ወደ ጨለማው ዓለም እናመጣዋለን። እንደ እግዚአብሔር ብርሃን እንደመሆናችን፥ ሰዎች ወደ ክርስቶስ የሚመጡበትን መንገድ እናሳያቸዋለን። ያልዳነው ሰው አእምሮ በሰይጣን የታወረና (2ኛ ቆሮ. 4፡3-4) በኃጢአት የጨለመ ነው (ኤፌ. 4፡17-19)። ብርሃኑ ወደ እርሱ የሚደርሰው ስለ ክርስቶስ ስንነግረው ብቻ ነው። አንድ ጤነኛ ሰው በሽተኛውን እንደሚረዳ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ የጠፋውን ኃጢአተኛ ከጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሃን ሊመራ ይችላል።

ብርሃን እግዚአብሔርን ይገልጣል። ብርሃን ፍሬን ያፈራል። ይሁንና ብርሃን ስሕተትንም ያጋልጣል። ሕይወትን ለማጥፋት እስካልፈለገ ድረስ የትኛውም ሐኪም በጨለማ ውስጥ የቀዶ ሕክምና ተግባር ሊያከናውን አይችልም። አንድ አርቲስት በጨለማ ውስጥ ጥሩ ሥዕል ሊሠራ አይችልም። ብርሃኑ እውነቱን በመግለጥ የነገሮችን እውነተኛ

ባሕርይ ያሳያል። ያልዳነው ሰው ከቤተ ክርስቲያንና ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚርቀው ለዚህ ነው። የእግዚአብሔር ብርሃን እውነተኛው ባሕርዩን ስለሚገለጥ ተገልጦ የሚታየው ብዙም አስደሳች አይሆንም። እኛ ክርስቲያኖች በብርሃን ስንመላለስ ከጨለማ ጋር ኅብረትን አናደርግም እያልን ነው፤ ደግሞም የኃጢአትን ጨለማ እየገለጥን ነው።

ኢየሱስ «እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ» (ዮሐ. 12፡46) አለ። ለደቀ መዛሙርቱም፥ «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» ብሎአቸዋል (ማቴ. 5፡14)። በምድር ላይ በነበረበት ወቅት የባሕርዩና የተግባሩ ፍጽምና በአካባቢው የነበሩትን ሰዎች ኃጢአት ገልጦ አሳይቷል። የሃይማኖት መሪዎች የጠሉትና ሊያጠፉት የፈለጉት በአንድ በኩል በዚህ ምክንያት ነበር። «እኔ መጥቼ ባልነገርኋቸውስ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር፤ አሁን ግን ለኃጢአታቸው ምክንያት የላቸውም» (ዮሐ. 15፡22)። አንድ ጤነኛ ሰው በሆስፒታል ውስጥ የሚኀበኛቸውን የአካል ጉዳተኞችና ሕሙማን ባለማወቅ በሽተኞች ናችሁ እንደሚላቸው ሁሉ፥ አንድ ክርስቲያንም እንደ ክርስቲያን በመኖር ብቻ የአካባቢውን ጨለማና ኃጢአት ይገልጣል። ጳውሎስ አዎንታዊውን በብርሃን የመመላለስ ተግባር በመፈጸምና አሉታዊውን የጨለማ ኑሮ በመኮነን ሚዛናዊ ሕይወት እንድንመራ ጠይቆናል። በጨለማ ያሉትን ኃጢአተኞች መግለጥ ብቻ በቂ አይደለም አይደለም። ኃጢአትንም መግለጥ ብቻ በቂ አይደለም። ፍሬ ማፍራት አለብን።

ቁጥር 12 ግን ጥንቃቄ እንድንወስድ ያሳስበናል። ፍሬ የሌለውን የጨለማ ሥራ ስንገልጥ ጥንቃቄ መውሰድ አለብን። የዛሬ ዘመን ሰዎች «የሆነውን በግልጽ ተናገር!» የሚል መርህ የያዙ ይመስላል። ነገር ግን የጨለማውን ቆሻሻ ነገሮች በመግለጡ ረገድ አደገኛ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ሳናውቅ ኃጢአትን ስለምናስተዋውቅ ኃጢአትን ልናስፋፋ ስለምንችል ነው። ጳውሎስ፥ «እነርሱ በስውር ስለሚያደርጉት መናገር እንኳ ነውር (አሳፋሪ) ነውና» ብሎአል (ኤፌ. 5፡12)። አንዳንድ ሰባኪዎች ስሜትን ለሚኮረኩሩ አገላለጾች ትኩረት ስለሚሰጡ አላስፈላጊ ነገሮችንም ይናገራሉ። «ነገር ግን ለበጎ ነገር ጥበበኞች ለክፉም የዋሆች እንድትሆኑ እወዳለሁ» (ሮሜ 16፡19)።

በወጣቶች አገልግሎት ላይ የተሰማራ አንድ ወዳጄ ወጣቶች የሚያነብቡትን ሁሉ ማንበቡ እነርሱን በበለጠ ለማወቅ ይረዳኛል በሚል ስሜት የጀመረው ጉዞ አእምሮውን በመበከሉ በኃጢአት የወደቀበትን አጋጣሚ አስታውሳለሁ። አማኙ የሞተውን አካል መበስበስ ለማሳየት የአስከሬን ምርመራ ማድረግ አያስፈልገውም።

የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር «ብርሃኑን ማብራት ነው!» የሚታየው ሁሉ ብርሃን ነውና» (ኤፌ. 5:13)።

ስለ ብርሃን ስታስብ በአዲስ ዕለት ስለመጓዝ ታስባለህ። ጳውሎስ ይህንኑ ምስል ከኢሳይያስ 60:1 ላይ በመውሰድ በራሱ አገላለጽ አቅርቦአል (ቁ. 14)። በሮሜ 13:11-13 እና 1ኛ ተሰሎንቄ 5:1-10ም ተመሳሳይ ገለጻ ቀርቦአል። ክርስቶስ ከሞት በተነሣበት በዚያ የትንሣኤ ማለዳ ለዓለም አዲስ ቀን ወጥቶ ነበር። ክርስቲያኖች በኃጢአትና በሞት አላንቀላፉም። በእርሱ በእምነት አማካይነት ከሞት ተነሥተናል። በመቃብሩ ስፍራ የነበረው ጨለማ አልፎአል፤ አሁን የምንመላለሰው በደኅንነት ብርሃን ነው። ደኅንነት የአዲስ ዕለት ጅማሬ በመሆኑ በጨለማ እንዳሉት ሳይሆን በብርሃን እንዳሉት ልንመላለስ ይገባል። «አልዓዛር ሆይ፥ ና ውጣ!»

አማኝ ከጨለማ ጋር ጉዳይ የለውም። እርሱ ቅዱስ ነው፤ ማለትም «በቅዱሳን ርስት በብርሃን እንድንካፈል» አድርጎናል (ቆላ. 1:12)። ከጨለማው ኃይል ነፃ ወጥቶ ወደ ልጁ መንግሥት ስለ ፈለሰ (ቆላ. 1:13)፥ እርሱ ንጉሥ ነው። እርሱ በጌታ ብርሃን ነው (ኤፌ. 5:8)።

## 3. በጥበብ ተመላለሱ (5:15-17)

«እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ» የሚለው ሐረግ አካባቢያችንን እንድንመለከት የሚጋብዝ ነው። የዚህ ተቃራኒው በግዴለሽነት መመላለስ፥ ሳያስቡና ሳያስተውሉ መራመድ ነው። የክርስትና ሕይወት የዕድል ሕይወት አይደለም። በጥበብ በመመላለስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ልንፈጽም ይገባል።

ቁጥር 14 እና 15 ተያዥ ናቸው። ጳውሎስ፥ «በቅዠት አትመላለሱ! ንቁ! ዓይኖቻችሁን ክፈቱ! ከቀኑ ልታተርፉ የምትችሉትን ከማትረፍ ወደ ኋላ አትበሉ!» የሚል ይመስላል። ብዙ ክርስቲያኖች ነን የሚሉ ወገኖች በእንቅልፍ እንደሚጓዙ ሰዎች በሕይወት ውስጥ ሲዋልሉ ማየቱ አሳዛኝ ነገር ነው። እነዚህ ሰዎች በጉዞአችን ለምን ትክክልና ጠንቃቆች መሆን እንዳለብን አያሌ ምክንያቶችን አቅርቦአል።

*የጥበብ ምልክት ነው* (ቁ. 15)። በነፋስና በማዕበል የሚገላበጥ ሰው ሞኝ ነው። ብልህ ሰው ግን መንገዱን በመወሰንና መልሕቁን በመትከል ከሚፈልገው ስፍራ እስኪደርስ ድረስ ጀልባውን እየመራው ይሄዳል። አንድ ሰው ቤት በሚሠራበት ጊዜ መጀመሪያ ንድፍን ያዘጋጃል። ነገር ግን መልካም አጋጣሚዎችን በጥበብ ለመጠቀም ይችሉ ዘንድ የዕለት ሕይወታቸውን በዕቅድ የሚመሩ ክርስቲያኖች ምን ያህል ናቸው? እርግጥ ነው ቀን የሚያመጣውን አናውቅም (ያዕ.

4:13–17)። የታቀደ ሕይወት ያልተጠበቁትን ክስተቶች ለመቋቋም የተሻለ አማራጭ መሆኑም ደግሞ እውነት ነው። «አንድ ፓይለት የት ማረፍ እንዳለበት ካላወቀ የሚገጥመው ነፋስ የሚበጅ ነፋስ አይደለም» የተባለው እውነት ነው።

*ሕይወት አጭር ናት* (ቁ. 16)። «ዘመኑን ዋጁ»። አንድ ጥንታዊ የቻይናውያን አባባል እንደሚያስረዳው፥ «መልካም ዕድል ወዳንተ በቀረበ ጊዜ ትይዘው ዘንድ መያዣውን ይዘረጋልሃል። አንዴ ካመለጠህ ግን ልታገኘው አትችልም»። «መልካም አጋጣሚ»ን የሚያመለክተው የእንግሊዝኛ <<Opportunity>> (ግልጽ ባይሆንም አሳቡ «ዘመኑን ዋጁ» በሚለው ውስጥ ይገኛል) ከላቲን ቋንቋ የመጣ ሲሆን፥ ፍችውም «ወደ ወደቡ» የሚል ነው። ይም አንድ መርከብ ነፋሱንና ማዕበሉን ተቋቁሞ ከወደቡ በሰላም መድረሱን የሚያመለክት ነው። የሕይወት አጭር መሆን እግዚአብሔር የሚሰጠንን መልካም ዕድሎች ከሁሉም በላቀ መንገድ ለመጠቀም ትልቁ ምክንያት ነው።

*ቀኖቹ ክፉዎች ናቸው* (ቁ. 16)። በጳውሎስ ዘመን ይህ የሮም ስደት እየቀረበ መምጣቱን የሚያስረዳ ነበር (1ኛ ጴጥ. 4:12–19)። በማኅበረሰቡ ውስጥ ኃጢአት በመስፋፋቱ ከመቅጽበት ሊጠፋ የሚችለውን መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ ኃጢአተኛውን ወደ ደኅንነት አለመመለሱ ምን ያህል የሞኝነት ተግባር ነው! ጳውሎስ ይህንን መልእክት በጻፈበት ወቅት ቀኖቹ ክፉዎች ከነበሩ ዛሬስ ምን ይመስሉ ይሆን?

*እግዚአብሔር አእምሮ ሰጥቶናል* (ቁ. 17)። «ማስተዋል» የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅና ማድረግን ያሳያል። እጅግ ብዙ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ እንደ ምትሃት ስለሚቆጥሩት አስቦ መራመድን ገሸሽ ያደርጉታል። ይህ ግን የተሳሳተ ብቻ ሳይሆን አደገኛም አስተሳሰብ ነው። እግዚአብሔር አእምሮአችንን ሲያድሰው ፈቃዱን እንረዳለን (ሮሜ 12:1–2)። ይህ ተሐድሶ የእግዚአብሔር ቃል፥ የጸሎት፥ የማሰላሰልና የአምልኮ ውጤት ነው። እግዚአብሔር አእምሮ ከሰጠህ እንድትጠቀምበት ይጠብቅሃል። ይህም ማለት የእግዚአብሔርን ፈቅድ ለማወቅ መረጃ መሰብሰብ፥ መገምገም፥ መመዘንና ጥበቡንም እንዲሰጥይህ መጸለይ ማለት ነው (ያዕ. 1:5)። እግዚአብሔር ፈቃዱን እንድናውቅ ብቻ ሳይሆን እንድናስተውልም ይፈልጋል።

*እግዚአብሔር ለሕይወታችን ዕቅድ አለው* (ቁ. 17)። ጳውሎስ ቀደም ሲል ይህንኑ ዕቅድ ጠቅሶአል (ኤፌ. 2:10)። እግዚአብሔር ካዳነኝ ለሕይወቴ ዓላማ አለው። እኔም ያንን ዓላማ ማወቅና ሕይወቴን

በዚያ ዓላማ መሠረት መምራት ይኖርብኛል። ዕቅዱንም የሚገልጽልን በቃሉ (ቆላ. 1፡9–10)፥ በልባችን ውስጥ ባለው መንፈስ ቅዱስና (ቆላ. 3፡15) በሁኔታዎች አማካይነት ነው (ሮሜ 8፡28)። ክርስቲያን እግዚአብሔር እንዲያደርግ የሚፈልገውን ስለሚያውቅ በጥንቃቄና በትክክል ተግባሩን ሊያከናውን ይችላል። ንድፉን እንደሚከተል አናጺ ማለት የሕንጻ መሐንዲስ ያቀደውን ተግባር ያከናውናል።

«በንጽሕና መመላለስ» ብለን የጠራነው ክፍል በዚህ ይጠናቀቃል። የክፍሉ ትኩረት አሮጌውን ሕይወት በመተው በአካባቢያችን ያለውን ዓለምን ሳይሆን እግዚአብሔርን እየመሰልን በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ማደፋፈር ነው። በሚቀጥለው ክፍል ደግሞ ጳውሎስ «በስምምነት ተመላለሱ» ይለናል። ጳውሎስ በክርስቶስ ያገኘነው ሕይወት መንግሥተ ሰማይን ወደ ሰዎች እንዴት እንደሚያመጣ ያሳየናል።

መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና፤ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊ ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፤ ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ።

ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ። ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደሆነ ባል የሚት ራስ ነውና። ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ። ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ። እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ ሥጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባቸዋል። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል፤ ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፥ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን፥ ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት፥ ይመግበዋል ይከባከበውማል። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፥ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ። ሆኖም ከእናንተ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት፥ ሚስቱም ባልዋን ትፍራ።

# 11

# መንግሥተ ሰማይ በቤትህ

ቻርልስ ሄደን ስፐርጀን፥ «ቤት እንደ እግዚአብሔር ቃል ሲመራ መላእክት አብረውን እንዲኖሩ ልንጠይቃቸው እንችላለን። እነርሱም አብረውን በመኖራቸው ማንነታቸውን አያጡም» ብለዋል።

ችግሩ ክርስቲያን ነን የሚሉ ቤተሰቦች እንኳ በእግዚአብሔር ቃል የማይመሩ በመሆናቸው ውጤቱ አስከፊ መሆኑ ነው። በአንዳንድ ቤቶች መላእክት የቤቱ እንግዳ መሆን ሲገባቸው አጋንንት ቤቱን ወርሰውት ይገኛል። በአሜሪካ ከሦስት ጋብቻዎች መካከል አንዱ በፍቺ አደባባይ ህልውናውን ያጣል። በአንድ ቤት ውስጥ ከሚኖሩ ባሎችና ሚስቶችም ምን ያህሎቹ ስሜታዊ ፍች እንደፈጸሙ የሚያውቅ የለም። ባለ ቅኔው ዊልያም ኮውፐር ቤተሰብን፥ «የኃጢአትን ውድቀት የተቋቋመው ብቸኛው የገነት በረከት» እያለ ቢጽፍም፥ ብዙ ቤቶች ከገነት ይልቅ የሲኦል ደጆች ሆነዋል።

መፍትሔው የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው! እንደ ባሎችና ሚስቶች (5፡22-33)፥ ወላጆችና ልጆች (6፡1-4)፥ ብሎም አሠሪዎችና ሠራተኞች (6፡5-9) ተስማምተን ልንኖር የምንችለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው። የመንግሥተ ሰማይን ጣዕም በምድር ላይ እንድናጣጥም ከተፈለገ ጳውሎስ የገለጸው የእግዚአብሔር ሕዝብ አንድነት (4፡16) በዕለታዊ ሕይወታችን መታየት አለበት።

እግዚአብሔር «መንፈስ ይሙላባችሁ» ሲል የሰጠውን ትእዛዝ እንድንፈጽም ይጠብቅብናል። ትእዛዙ በብዙ ቁጥር የተነገረ በመሆኑ («ይሙላባችሁ») ለተመረጡት ጥቂት ሰዎች ሳይሆን ለክርስቲያኖች ሁሉ ነው። ግሡ የአሁን ጊዜ በመሆኑ «ሳታቋርጡ ተሞሉ» የሚል መልእክት ያስተላልፋል። ስለሆነም ይህ በአንዳንድ ልዩ አጋጣሚዎች ብቻ ሳይሆን በየዕለቱ ልንለማመደው የሚገባ ነው። ግሡ ድርጊት ተቀባይ እንጂ አድራጊ አይደለም። ይህም እኛ ራሳችንን ልንሞላ አንችልም፤ መንፈስ ቅዱስ እንዲሞላን ግን ልንፈቅድለት እንደምንችል ያሳያል። «ይሙላባችሁ» የሚለው ቃል ባዶ ዕቃ በውኃ እንደሚሞላ እኛም ባዶ ዕቃዎች ነን የሚል አሳብ የለውም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «መሞላት» ማለት «በቁጥጥር ሥር መዋል» ማለት ነው። «በቁጣ ተሞሉ» (ሉቃ. 4፡28) ማለት በቁጣ ቁጥጥር ሥር ዋሉ ማለት ነው። ሰዎቹ በቁጣ ኃይል ኢየሱስ ክርስቶስን ሊገድሉ መነሣታቸው ተጠቅሶአል። «አይሁድም ቅንዓት ሞላባቸው» ማለት (የሐዋ. 13፡45)

በቅንዓት ቁጥጥር ሥር እንደ ዋሉና የጳውሎስንና የበርናባስን አገልግሎት እንደተቃወሙ የሚያሳይ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ተሞላን ማለት መንፈስ ቅዱስ አእምሮአችንን፥ ስሜታችንንና ፈቃዳችንን ባለማቋረጥ ተቆጣጠረው ማለት ነው።

አንድ ሰው ክርስቶስን የግል አዳኙ አድርጎ በሚያምንበት ጊዜ ወዲያውኑ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ወደ ክርስቶስ አካል ይጨመራል (2ኛ ቆሮ. 12፡13)። ይህ በደኅንነት ጊዜ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚፈጸም ተግባር በመሆኑ በየትኛውም የአዲስ ኪዳን ክፍል በመንፈስ ቅዱስ እንድንጠመቅ አልታዘዝንም። በበዓለ ኀምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀው የክርስቶስ አካል ሆኑ (የሐዋ. 1፡4-5)። በተጨማሪም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተዋል (የሐዋ. 2፡4)። ለክርስቶስ ለመመስከር የሚያስፈልጋቸውን ኃይል የሰጠው ይሄው ሙላት ነበር (የሐዋ. 1፡8)። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ላይ የአይሁድ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ፤ በምዕራፍ 10 የአሕዛብ አማኞች በተመሳሳይ መንገድ ተጠመቁ (የሐዋ. 10፡44-48፤ 11፡15-17)። ስለሆነም የክርስቶስ አካል ከአይሁድና ከአሕዛብ የተገነባ ነው (ኤፌ. 2፡11-22)። ያ በሁለት ደረጃዎች የተፈጸመው ታሪካዊ ጥምቀት በድጋሚ አልተፈጸመም፤ ልክ የጎልጎታውም ታሪክ ሞት እንዳልተደገመ ሁሉ። ነገር ግን ኃጢአተኛው በክርስቶስ ሲያምንና መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ አካል እንዲያደርገው ወደ እርሱ ሲገባ ያ ጥምቀት ግላዊ ይሆናል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ማለት እኔ የክርስቶስ አካል ክፍል ነኝ ማለት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ማለት አካሌ የክርስቶስ ነው ማለት ነው።

ብዙውን ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለስብከትና ለምስክርነት አስፈላጊ እንደሆነ እናስባለን። ይህም እውነት ነው (የሐዋ. 4፡8፥ 31፤ 6፡3፥5፤ 7፡55፤ 14፡9 ተመልከት። ሐዋርያት ከበዓለ ኀምሳው ገጠመኝ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ በተደጋጋሚ ተሞልተዋል።) ነገር ግን ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለቤተሰብ ሕይወትም እንደሚያስፈልግ ገልጾአል። ቤታችን ምድረ ገነት እንዲሆን ከተፈለገ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ልንመላለስ ይገባል። ዳሩ ግን አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አለመሞላቱን የሚያውቀው እንዴት ነው? ጳውሎስ በአማኙ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት የሚያረጋግጡ ሦስት መረጃዎች እንዳሉ ጽፎአል፤ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው አማኝ *ደስተኛ* (5፡9)፥ *ዘወትር የሚያመሰግንና* (ቁ. 20) *ታዛዥ* ይሆናል (21፡33)። ጳውሎስ ስለ ተአምራት፥ ልሳናት ወይም ስለ ሌሎች ልዩ መገለጦች የተናገረው ነገር የለም። እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር በመዋል ደስተኛ፥ የሚያመሰግንና

የሚታዘዝ ከሆነ ቤተሰባዊ ሕይወቱ ምድረ ገነት ሊሆን እንደሚችል አስረድቶአል።

## 1. ደስተኛ (5፡19)

ደስታ አንድ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው (ገላ. 5፡22)። ክርስቲያናዊ ደስታ እንደ አካባቢው ሁኔታ የሚወሰን ወሰን ወይም እንደ ቴርሞ ሜትር የሚወጣና የሚወርድ ተለዋዋጭ ስሜት አይደለም። ክርስቲያናዊ ደስታ ከዙሪያችን ባሻገር የምንዋኝበት ጥልቅ የብቃትና የልበ ሙሉነት ልምምድ ነው። ክርስቲያን በሥቃይና በመከራ ውስጥ እንኳ ሊደሰት ይችላል። የዚህ ዓይነት ደስታ እንደ ቴርሞ ሜትር ተለዋዋጭ ሳይሆን እንደ ቴርሞስታት ነው። ከሁኔታዎች ጋር እንደ መውጣትና መውረድ የሁኔታዎችን መንፈሳዊ ሙቀት ይወስናል። ጳውሎስ ይህንን በውብ ብዕሩ እንዲህ ሲል ገልጾታል፤ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ «የምኖርበት ይበቃኛል ማለትን ተምሬአለሁና» (ፊልጵ. 4፡11)።

ጳውሎስ ይህንን ጥበብ ለማብራራት ግልጽ የሆነውን የስካር ገጠመኝ ተጠቅሞአል። «መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ» (ቁ. 18)። በበዓለ ኀምሳ ቀን አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ ሕዝቡ ጉሽ የወይን ጠጅ ጠጥተው እንደሰከሩ ተናግሯል (የሐዋ. 2፡13–15)። አማኞች በጣም ሲደሰቱ ስለተመለከቱ በዙሪያቸው ያለው ዓለም ከዚህ የተሻለ ማነጻጸሪያ ሊያገኙ አልቻሉም ነበር። ይሁንና ከንጽጽሩ አንዳንድ ተግባራዊ ትምህርቶችን መማር ይቻላል። በመጀመሪያ ደረጃ የሰከረው ሰውዬ በሌላው ኃይል ቁጥጥር ሥር ነው። አልኮል አእምሮን የመቆጣጠር ኃይል አለው። ጭንቀቱ ሁሉ ተወግዶለት የእፎይታ ስሜት ይሰማዋል። በቤቱ ውስጥ የተገኘውን ሰው ሁሉ ሊስም ይችላል። ምንም እንኳ ድርጊቱ አሳፋሪ ቢሆንም የሰከረ ሰው ራሱን ለመግለጽ አያፍርም። በሕይወቱ ውስጥ ያለውንም ነገር እንዳለ ይዘከዝካል።

እስኪ ይህንኑ መግለጫ በመንፈበ ቅዱስ ወደ ተሞላው አማኝ እናዙረው። እግዚአብሔር ሕይወቱን ስለሚቆጣጠር ጥልቅ ሐሤት ይሰማዋል። ለእግዚአብሔር ክብር ራሱን ለመግለጽ አይፈራም። የሰከረ ሰው አልኮሉ አእምሮውን ስለሚቆጣጠረው ከቁጥጥር ውጭ መሆኑ ግልጽ ነው። አማኙ ግን ራሱን ይገዛል። ይህም እግዚአብሔር እንደሚቆጣጠረው የሚያሳይ ነው። ራስን መግዛት አንዱ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው (ገላ. 5፡23)። የነቢያት መንፈስ ለነቢያት ይገዛል (1ኛ ቆሮ. 14፡32)። ሰካራሙ ራሱን ሲያጃጅል በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ውስጥ የሚኖረው ክርስቲያን እግዚአብሔርን ከማስከበሩም በላይ

ለክርስቶስ ምኝ ለመሆን ፈቃደኛ ነው (4:10)። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው አማኝ ሲመሰክር ሰካራሙ ስለ ራሱ አዋጅ ይናገራል።

በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ በደስታ መስከ ላይ ከሚፈነጭ አማኝ ጋር አብሮ መኖሩም ሆነ መሥራቱ አስቸጋሪ አይሆንም። ልቡም ሆነ ከንፈሩ መንፈሳዊ ቅኔ ይቀኛል። ይህም የልቡን ንቅዘት በዘፈኑ ከሚገልጽ ሰካራም ዜማ የተለየ ነው። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው ክርስቲያን ዝማሬ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚወርድለት ነው። ይህም ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል ውጭ ሊዘምረው የማይችለው ነው። እግዚአብሔር በሌሊት መዝሙርን ይሰጣል [መዝ. (42):28]። ጳውሎስና ሲላስ በፊልጵስዩስ ታስረው ሳሉ ከሚደርስባቸው ሥቃይ ባሻገር መንፈሳዊ ዝማሬ ሊዘምሩ ችለዋል (የሐዋ. 16:25)። በውጤቱም የወኅኒው ጠባቂና ቤተሰቡ በክርስቶስ አመኑ። በዚያ የእኩለ ሌሊት ሰዓት ምን ያህል አስደሳች ጊዜ ነበራቸው! ደስታውን ለማጣጣም አላስፈለጋቸውም ነበር።

«በሰፈርህ ያለው ቡና ቤት በከተማዪቱ ከሚገኙት ስፍራዎች ሁሉ የላቀ ነው!» በ«ዓመታዊው የቡና ቤቶች ወር» ውስጥ ይህ መፈክር በአንድ የታወቀ ጋዜጣ የፊት ገጽ ላይ ወጥቶ አየሁ። የጋዜጣውን እውነተኛነት ለመፈተን ጋዜጣውን ለአያሌ ሳምንታት በመከታተል ከቡና ቤቶች ጋር የሚዛመዱ ጽሑፎችን ማጠራቀም ጀመርሁ። የሚገርመው ሁሉም ቡና ቤቶች የድብድብና የነፍስ–ገዳይ ጎሬ ነበሩ። በከተማዪቱ ውስጥ ከሚገኙት ስፍራዎች ሁሉ ምቹ የሆነው ቦታ! ይህ ማስታወቂያ ግን አብረው የሚጠጡ ሰዎች ብዙውን ጊዜ የሚተዛዘኑና የሚግባቡ መሆናቸውን እንዳስተውል አደረገኝ። ይህ አልኮልን ለመደገፍ የሚቀርብ ማስረጃ ባይሆንም አንድ ጥሩ ነጥብ ያብራራል፤ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ክርስቲያኖች በአንድነት ሲቀመጡ ደስ ይላቸዋል፤ በጌታ ባላቸውም አንድነት ደስ ይላቸዋል። የዓለምን ሐሰተኛ ማነቃቂያ መጠቀም አያስፈልጋቸውም። መንፈስ ቅዱስ አላቸው፤ የሚያስፈልጋቸውም ይኸው ነው።

## 2. አመስጋኝ (5:20)

አንድ ሰው ስለ ቤት ሲናገር፥ «ከሁሉም የተሻለ መስተንግዶ የምናገኝበትና ከሁሉም የላቀ የምንነጫነጭበት ስፍራ» ነው ብሏል። ይህ ምንኛ እውነት ነው! አንድ ጊዜ አንድ ታዳጊ ወጣት፥ «አባቴ ሊቆጣን ወይም ስለ ትምህርት ውጤት ለመጠየቅ ካልፈለገ በቀር አያነጋግረኝም። ምን አለ አንዳንዴ ቢያበረታታኝ?» ሲል ምሬቱን ገልጾልኛል። የጋብቻ አማካሪዎች እንደሚነግሩን፥ ከጋብቻ ችግሮች ዋነኛው አንዱ ሌላውን ቸል ማለቱ ነው። የደስተኛ ቤተሰብ ምሥጢሩ

አንዱ ስለ ሌላው እግዚአብሔርን ማመስገኑ ነው። የማመስገንን ጸጋ የሚሰጠን መንፈስ ቅዱስ ነው።

አመስጋኝ ልብ በቤተሰብ ውስጥ ስምምነት የሚፈጥረው እንዴት ነው? አንደኛው ከልቡ አመስጋኝ የሆነ ሰው በሌሎች ምክንያት እንደተባረከ የሚገነዘብ መሆኑ ነው። ይህም የትሕትና ምልክት ነው። ኑሮውን ያሳካለት ይህ ዓለም እንደሆነ የሚያስብ ሰው መቼም ቢሆን ለምንም ነገር አያመሰግንም። ለሌሎች መልካም ነገር ለማድረግ የሚያነሣሣው ሌሎች እንዲያገለግሉት ስለሚፈልግ ብቻ ነው። አመስጋኝ ልብ ብዙውን ጊዜ ትሕትናን በመላበስ እግዚአብሔር የመልካምና የፍጹም ስጦታ ሁሉ ምንጭ እንደሆነ በደስታ ይገነዘባል (ያዕ. 1:17)። በዮሐንስ ምዕራፍ 12 ላይ ማርያም ለኢየሱስ ክርስቶስ እንዳበረከተችው ስጦታ፤ ምስጋና ቤትን በመልካም መዓዛ ይሞላል።

ሁላችንም በአንዳንድ ልዩ አጋጣሚዎች ለተደረጉልን ነገሮች አመስጋኞች መሆናችን ግልጽ ነው። ጳውሎስ ግን ተደራስያኑ ስለ ሁሉም ነገር ሁልጊዜ እንዲያመሰግኑ አዞአቸዋል። ይህ ምክር በራሱ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚያስፈልገን ያረጋግጣል። ይህንን ትእዛዝ በራሳችን ብርታት ልንጠብቅ አንችልምና። ለመሆኑ መከራ ሲደርስብን፥ ሰዎች ሲያስቀይሙን፥ የምንወዳቸው ሰዎች በሞት ሲለዩን ከልባችን ልናመሰግን እንችላለን? ጳውሎስ ይህንን መልእክት በሚጽፍበት ጊዜ እስረኛ እንደነበረና ነገር ግን እግዚአብሔር በእርሱ አማካይነትና ለእርሱ በሚያደርገው ነገር አመስጋኝ እንደነበረ አስተውል (ኤፌ. 1:16፤ 5:4፥ 20፤ ቆላ. 1:3፥ 12፤ 2:7፤ 3:17፤ 4:2፤ ፊልጵ. 1:3)። ክርስቲያን በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ ልቡን ከማጉረምረምና ከኀዘን ለመጠበቅ ወዲያውኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ ይኖርበታል። ክርስቲያን ማጉረምረም በሚጀምርበት ጊዜ ዲያብሎስ ወደ እርሱ ይጠጋል። በመንፈስ ቅዱስ የሚታገዝ ምስጋና ግን ዲያብሎስን በማሸነፍ እግዚአብሔርን ያስከብራል። «በሁሉ አመስግኑ፥ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና» (1ኛ ተሰ. 5:18)።

«ምስጋና» የሚለው ቃል «ጸጋ» ከተተረጎመበት ሥረወ-ቃል የተገኘ ነው። የእግዚአብሔርን ጸጋ ከተቀበልን እግዚአብሔር ወደ እኛ ለሚያመጣው ነገር ሁሉ አመስጋኞች ልንሆን ይገባል። «ምስጋና» እና «ማሰብ»ም ከተመሳሳይ ሥረወ-ቃል የተገኙ ናቸው። የበለጠ ማሰብ ስንችል የበለጠ አመስጋኞች እንሆናለን።

## 3. መገዛት (5፡21–33)

ጳውሎስ በባልና በሚስት (5፡21–33)፥ በወላጆችና በልጆች (6፡1–4)፥ በጌቶችና በባሪያዎች (6፡5–9) መካከል ሊኖር ስለሚገባው ስምምነት በሚገባ ጽፎአል፤ አንዱ ለሌላው መገዛት አለበት። ይህ ማለት ልጆች ወላጆቻቸውን ይዘዙ ወይም ጌቶች ለባሪያዎቻቸው ይታዘዙ ማለት ይሆን? አይደለም! መገዛት ከሥልጣን ጋ ር ምንም ግንኙነት የለውም፤ ይልቁንም ሥልጣን እንዴት በሥራ ላይ መዋል እንዳለበት የሚገልጽ ነው፤ እንዴት እንደሚሰጥና እንዴት መቀበል እንደሚገባ የሚያሳይ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ ሌሎችን ዝቅ አድርገው እንዳይመለከቱና ራሳቸውንም ከፍ ከፍ እንዳያደርጉ አስተምሯል። የሚያሳዝነው ትምህርቱን ሳይረዱት ቀርተው በመጨረሻው እራት ላይ እንኳ «ከሁሉም የሚበልጠው ማን ነው?» የሚል ርእስ አንሥተው መሟገታቸው ነበር (ሉቃስ 22፡24–27)። ኢየሱስ ክርስቶስ እግራቸውን ባጠበ ጊዜ ከሁሉም የሚበልጠው እንደ ፈሪሳውያን የራሱን ሥልጣን የሚያደራጅና ሥልጣኑንም የሚያሳይ ሰው ሳይሆን ሕዝቡን ለማነጽ ሥልጣኑን የሚጠቀም ሰው እንደሆነ ገልጾአል። ሌላው ከእኛ እንደሚሻል አድርገን መቁጠር አለብን (ፊልጵ. 2፡1–4፤ ሮሜ 12፡10)። በተፈጥሮአችን ራሳችንን ከፍ ከፍ ለማድረግ እንሻለን። መንፈስ ቅዱስ ግን ራሳችንን እንድናስገዛ ያግዘናል።

ጳውሎስ ለባሎችና ሚስቶች የጻፈውን መልእክት በምናጠናበት ጊዜ ለአማኞች እንደ ጻፈ አስታውስ። ጳውሎስ ሴቶች ከወንዶች እንደሚያንሱ ወይም ሁሉም ሴቶች በሁሉም ሁኔታ ውስጥ ለሁሉም ወንዶች ይገዙ የሚል አመለካከት እንዳላንጸባረቀ ግልጽ ነው። ክርስቶስንና ቤተ ክርስቲያንን እንደ ምሳሌ መጠቀሙ ስለ ክርስቲያናዊ ጋብቻ የሚጽፍ መሆኑን ያስረዳል።

*ሚስቶች ሆይ፥ ለባሎቻችሁ ተገዙ* (5፡22–24)። ለዚህ ሁለት ምክንያቶችን ሰጥቶአል፤ እነዚህም የክርስቶስ ጌትነትና (ቁ. 22) በክርስቶስ ያለ ወንድ ራስነት ናቸው (ቁ. 23)። ክርስቲያን ሚስት ራሷን ለክርስቶስ ስታስገዛና እርሱ የሕይወቷ ጌታ እንዲሆን ስትፈቅድ ለባልዋ ለመገዛት አትቸገርም። ይህ ማለት ግን የባሏ ባሪያ ትሆናለች ማለት አይደለም። ባልም ራሱ ለክርስቶስ ይገዛልና። ሁለቱም በክርስቶስ ጌትነት ሥር የሚኖሩ ከሆነ ከስምምነት ውጭ የሚፈጠር ነገር አይኖርም። ራስ መሆን ማለት አምባገነን መሆን ማለት አይደለም። «አንዱ ለሌላው፥ ሁለቱም ለጌታቸው» ይገዛሉ። ክርስቲያን ባልና ሚስት እግዚአብሔር ለግል ሕይወታቸውና ለቤተሰባቸው ያለውን ፈቃድ ለማወቅ አብረው ሊጸልዩና ቃሉን ሊያጠኑ ይገባል።

እንደ መጋቢነቴ ያጋጠሙኝ የጋብቻ ግጭቶች ባል እና /ወይም/ ሚስት ለክርስቶስ ለመገዛት፥ ቃሉን ለማጥናትና በየቀኑ ፈቃዱን ለመፈጸም ካለመቻላቸው የመነጩ ናቸው።

ይህም ለምን ክርስቲያን ክርስቲያንን ማግባትና ከማያምን ሰው ጋር በማይመች አካሄድ መጠመድ እንደሌለበት ያሳያል (2ኛ ቆሮ. 6፡14-18)። ክርስቲያኑ ለጌታ ከተገዛ የእግዚአብሔርን ቃል የሚተላለፍ ቤተሰብ ለመመሥረት አይሞክርም። እንዲህ ዓይነቱ ቤተሰብ ገና ከጅማሬው የእርስ በርስ ጦርነትን ይጋብዛል። ሌላም አስፈላጊ ነገር አለ። ክርስቲያን ባለትዳሮች ከመጋባታቸው በፊት እንኳ ለክርስቶስ ጌትነት መገዛት አለባቸው። ባልና ሚስት አብረው ካልጸለዩና ከልባቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከቃሉ ውስጥ ካልፈለጉ ጋብቻቸው በደካማ መሠረት ላይ ይጣላል። ከጋብቻ በፊት የተፈጸሙ ኃጢአቶች ከጋብቻ በኋላ ችግር ይፈጥራሉ። እግዚአብሔር ይቅር ማለት ቢችልም፥ አንድ ውድ ነገር ግን ጠፍቷል። የቀድሞው የሙዲ ባይብል ኢንስቲትዩት ፕሬዚደንት ዶክተር ዊልያም ካልበረትሰን ይቅር የተባሉ ኃጢአቶች ስለሚያስከትሉት አሳዛኝ መዘዝ የሚሰጡት ማስጠንቀቂያ እውነት ነው። ስለሆነም በትጭጭት ላይ የሚገኙ ሰዎች ይህንን ማስጠንቀቂያ ልብ ሊሉ ይገባል።

*ባሎች ሆይ፥ ሚስቶቻችሁን ውደዱ* (5፡25-33)። ጳውሎስ ለክርስቲያን ባሎች የሚናገረው ለሚስቶች ከተናገረው የሚጠነክር ነው። ለባሎች የሰጠው ትእዛዝ ከባድ ነው። «ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ» ብሎአል። ጳውሎስ በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያብራራ አሳብ ስለተመለከተ፥ የትዳርን ፍቅር፥ እጅግ ወደ ላቀ ደረጃ አድርሶታል። እግዚአብሔር ጋብቻን የመረጠው ለብዙ ምክንያቶች ነው። ከእነዚህም አንዱ የሰውን ስሜታዊ ፍላጎት እንዲያሟላ ነው። «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም» (ዘፍጥ. 2፡18)። በተጨማሪም ጋብቻ ልጆችን በማፍራት ዘር እንዲቀጥል በማድረግ ማኅበራዊ ዓላማን ይፈጽማል (ዘፍጥ. 1፡28)። ጳውሎስ ወንድና ሴት ከእግዚአብሔር የተቀበሉአቸውን ተገቢ ፍላጎቶች ለማሟላት የሚያገለግልበትን ሥጋዊ ዓላማም ገልጾአል (1ኛ ቆሮ. 7፡1-3)። በኤፌሶን ምዕራፍ 5 ላይ ግን ጳውሎስ የጋብቻን መንፈሳዊ ዓላማም አመልክቷል። ይህም ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው የክርስቶስን ፍቅርና መገዛት ተግባራዊ ሲያደርጉት የሚፈጸም ነው (ኤፌ. 5፡22-23)።

ባል ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ያሳየውን ፍቅር ሞዴል ከወሰደው ለሚስቱ የመሥዋዕትነት ፍቅር ማሳየቱ አይቀርም (ቁ. 25)። ክርስቶስ

ራሱን ለቤተ ክርስቲያን ስለሰጠ አፍቃሪ ባል ለሚስቱ ሕይወቱን ይሰጣል። ያዕቆብ ራሔልን ከልቡ ስላፈቀራት እርሷን ለማግኘት ሲል ለአባቷ የአሥራ አራት ዓመታት የመሥዋዕትነት አገልግሎት አበርክቷል። እውነተኛ ክርስቲያናዊ ፍቅር የራሱን አይሻም (1ኛ ቆሮ. 13፡5)–ስግብግብ አይደለም። ባል ለክርስቶስ የተገዛና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ከሆነ ሚስቱ ክርስቶስን በቤቷ እንድታገለግልና እንድታከብር ያደርጋታል።

የባል ፍቅር የሚቀድስም ይሆናል (ቁ. 26–27)። «መቀደስ» ማለት «መለየት» ማለት ነው። በጋብቻ ሥርዓት ባል ከሚስቱ ጋር ለመሆን ከወላጆቹ ሲለይ፥ ሚስትም ከባልዋ ጋር ለመሆን ትለያለች። በዚህ እግዚአብሔር ባዘጋጀው ውህደት ውስጥ የሚከሰት ማንኛውም ጣልቃ–ገብነት ኃጢአት ነው። ዛሬ ክርስቶስ በቃሉ አገልግሎት ቤተ ክርስቲያኑን እያነጻት ነው (ዮሐ. 15፡3፤ 17፡17)። ሁለቱም ክርስቶስን ይመስሉ ዘንድ ባል ለሚስቱ ያለው ፍቅር እርሷን (እና እርሱን) የሚያነጻ መሆን አለበት። ሥጋዊ ግንኙነታቸውም ሳይቀር ግላዊ ደስታና መንፈሳዊ በረከት ይሆን ዘንድ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ሊውል ይገባል (1ኛ ቆሮ. 7፡3–5)። ባል ለሁለታቸውም የሚጠቅምና የሚቀድስ ፍቅር ማሳየት እንጂ ሚስቱን ለራሱ የእርካታ መጠቀሚያ ማድረግ የለበትም። ክርስቶስ የቤተሰብ ራስ የሆነበት ጋብቻ ዘወትር ያድጋል። ፍቅር ሁልጊዜም ይሰፋል፤ ያድጋልም፤ ራስ ወዳድነት ግን የዚህን ተቃራኒ ያስከትላል።

ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ፍጹም አይደለችም። እድፈትና የፊት መጨማደድ አለባት። እድፈት በውጫዊ ብልሽት የሚከሰት ሲሆን፥ የፊት መጨማደድ ግን ከውስጣዊ መበስበስ የሚመጣ ነው። ቤተ ክርስቲያን በዓለም ስለምትበከል ባለማቋረጥ ልትነጻ ያሻል። የሚያነጻት ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ነው (ያዕ. 1፡27)። የፊት መጨማደድ የሽምግልናና የውስጣዊ መበስበስ ምልክት በመሆኑ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይህ ሊከሰት አይገባም። ቤተ ክርስቲያን በቃሉ ስትታነጽ የፊት መጨማደድ ሊወገድ ይገባል። ቤተ ክርስቲያን እንደ ውብ ሙሽራ ንጹሕና ወጣት ልትሆን ያሻል። ይህም የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ሲጠቀም የሚፈጸም ነው። አንድ ቀን በቤተ ክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ በሰማይ «የከበረች ቤተ ክርስቲያን» ትሆናለች (ይሁዳ 24)።

ባል ለሚስቱ የመሥዋዕትነትና የቅድስና ብቻ ሳይሆን እርኪም ፍቅር ሊያሳይ ይገባል (ቁ. 28–30)። በጋብቻ ግንኙነት ባልና ሚስት «አንድ ሥጋ» ይሆናሉ። ስለሆነም አንዱ አካል ለሌላው የሚያደርገው ነገር ሁሉ ለራሱ የሚያደርገው ነው። ይህ የጋራ እርካታ ነው። ባልና

ሚስት አንድ ሥጋ በመሆናቸው ሚስቱን የሚወድ ባል ራሱን ይወዳል። ሲያፈቅራት ይመግባታል። ፍቅር የክርስቶስ አካል አያያዥ እንደሆነ ሁሉ (ኤፌ. 4፡16)፥ ፍቅር የቤተሰብም እንክብካቤ ነው። ስንቶች ናቸው «የፍቅር ረሃብተኛ ነኝ» የሚሉት። የባልና ሚስት ፍቅር አካላዊ፥ ስሜታዊና መንፈሳዊ ጉድለታቸውን በመሙላት የክርስቲያን ባለትዳሮችን ረሃብ ሊያስወግድ ይገባል። ሁለቱም ለጌታና ለእርስ በርሳቸው ከተገዙ እርካታን በማግኘት ወደ ሌላ የእርካታ ምንጭ ከመቅበዝበዝ ይታቀባሉ።

ክርስቲያን ቤቶች ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያንጸባርቁ ሊሆን ይገባል። እያንዳንዱ የክርስቶስ አካል ብልት ስለሆነ አካሉን በፍቅር ለማነጽ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ አለበት (ኤፌ. 4፡16)። ከክርስቶስ ጋር አንድ ነን። ቤተ ክርስቲያን የእርሱ አካልና ሙሽራ ስትሆን፥ ክርስቲያናዊ ቤተሰብ የዚህ ግንኙነት መለኮታዊ መግለጫ ነው። ይህም ጋብቻ ትልቅ ነገር መሆኑን ያሳያል።

ጳውሎስ የሔዋንን መፈጠርና የመጀመሪያውን ቤተሰብ መመሥረት ጠቅሶአል (ዘፍጥ. 2፡18-24)። አዳም ሙሽራዪቱን ለማግኘት የአካሉን ክፍል ሲሰጥ፥ ክርስቶስ ግን ሙሽራዪቱን በመስቀል ላይ ለመዋጀት ሙሉ በሙሉ ራሱን ሰጥቷል። ኃጢአተኞች ሰዎች የክርስቶስን ጎን ወጉ። ባልና ሚስት የተዋሐዱ በመሆናቸው «አንድ ሥጋ» ናቸው። ጥምረታቸው ከወላጆችና ልጆች የቀረበ ነው። አማኝ ከክርስቶስ ጋር የሚኖረው ጥምረት ደግሞ ከዚህ የቀረበና ከሰብአዊ ጋብቻ ባሻገር ለዘላለም የሚኖር ነው። ጳውሎስ ባል ሚስቱን ሊወድና ሚስት ደግሞ ባልዋን ልታከብር እንደሚገባ፥ ይህም የመንፈስ ቅዱስን ኃይል እንደሚጠይቅ በመምከር ክፍሉን ደምድሟል።

ክርስቲያን ባልና ሚስት የሚያስችል የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና የሚያበረታታ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌነት ካላቸው፥ ብዙ ክርስቲያናዊ ጋብቻዎች የሚፈርሱት ለምንድን ነው? እርምጃቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ የሌለበት ነው ማለት ነው። ሁለት ክርስቲያኖች ስለተዋወቁና ስለተግባቡ ብቻ መጋባት እንዳለባቸው አያመለክትም። እንዲያውም ሁሉም አማኝ ማግባት የለበትም። አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች ሳያገቡ እንዲኖሩ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው (ማቴ. 19፡12፤ 1ኛ ቆሮ. 7፡7-9)። ለአማኝ ዓለማዊ ከሆነ ሰው ጋር መጋባት ትክክል እንዳልሆነ ሁሉ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭም አማኝ ለአማኝ ጋብቻ መፈጸሙ ትክክል አይደለም።

ነገር ግን ሁለት ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ፈቃድ ቢጋቡ እንኳ ቤታቸው እግዚአብሔር የሚፈልገው ዓይነትና ያማረ ኅብረት የነገሠበት ይሆን ዘንድ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ መኖር አለባቸው። ፍቅር የመንፈስ ፍሬ ነው (ገላ. 5፡22)። ባልም ሆነ ሚስት በመንፈስ የማይመላለሱ ከሆነ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13 ላይ በግሩም ሁኔታ የተገለጸውን የክርስቶስን ፍቅር ሊጋሩ አይችሉም። የቁሳዊ ችግሮች ሁሉ ሥር ኃጢአት ነው፤ የኃጢአት ሁሉ ሥር ራስ ወዳድነት ነው። ራስ ወዳድነትን ለማሸነፍ ደግሞ ብቸኛው መንገድ ለክርስቶስና ለእርስ በርስ መገዛት ነው። በምንገዛበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሊሞላንና ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ባፈቀረበት መንገድ እርስ በርሳችን በመሥዋዕትነት፥ በቅድስናና በሚያረካ መልኩ እንድንዋደድ ይረዳናል።

በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት አንድ ሰው መጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ሊኖረው ይገባል። ማለትም ክርስቲያን ሊሆን ይገባል። ከዚያም ክርስቶስን ለማክበር ከልቡ ሊሻ ይገባል፤ መንፈስ ቅዱስ የተሰጠው ለዚህ ነውና (ዮሐ. 16፡14)። መንፈስ ቅዱስ ይጠቀምብናል እንጂ እኛ አንጠቀምበትም። ከኃይሉ ውጭ ምንም ልናደርግ እንደማንችል በመግለጽ ለእግዚአብሔር ሙላት በጥልቀት ልንጠማ ይገባል። የዮሐንስ 7፡37–39ን የተስፋ ቃል ራሳችን ልናደርግ ይገባል፤ ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ! በእምነት ራስህን ለክርስቶስ አሳልፈህ ስጥ። በእምነት የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ይሰጥህ ዘንድ ጠይቀው። በእምነት ተቀበል። በሕይወትህ ውስጥ እንደ ደስታ፥ ምስጋናና ታዛዥነት ካቆጠቆጡ፥ እግዚአብሔር ጸሎትህን እንደመለሰልህ ትገነዘባለህ።

አንድ ሊታሰብበት የሚገባ ተጨማሪ ነጥብ አለ። የእግዚአብሔር መንፈስ በሕይወታችን ለመሥራት የእግዚአብሔርን ቃል ይጠቀማል። ቆላስይስ 3፡16–4፡1ን ብታነብ ከኤፌሶን ምንባብ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ታገኘዋለህ። ብሎም በእግዚአብሔር ቃል መሞላት ደስታን፥ የሚያመሰግንና የሚታዘዝ ሕይወትን እንደሚያፈልቅ ትረዳለህ። በሌላ አገላለጽ፥ የእግዚአብሔር ቃል ሲቆጣጠርህ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይሞላሃል። ባሎችና ሚስቶች ብቻ ሳይሆኑ ክርስቲያኖች ሁሉ በየቀኑ የክርስቶስ ቃል በልባቸው ውስጥ በሙላት እንዲኖር ለመፍቀድ ጊዜ ሊወስዱ ያሻል። በዚህ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ደስተኞች፥ የሚያመሰግኑና የሚታዘዙ ሰዎች ያደርገን ዘንድ በሕይወታችን ይሠራል። ይህም መንግሥተ ሰማይን በቤትህ ውስጥ እንደ ማግኘት ነው።

ልጆች ሆይ፥ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፥ ይህ የሚገባ ነውና። መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር፤ እርስዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት። እናንተም አባቶች ሆይ፥ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጉአቸው እንጂ አታስቆጡአቸው።

ባሪያዎች ሆይ፥ ለክርስቶስ እንደምትታዘዙ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ በልባችሁ ቅንነት በሥጋ ጌቶቻችሁ ለሆኑ ታዘዙ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያደርጉ እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች እንጂ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ አትሁኑ። ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምትገዙ በትጋትና በበጎ ፈቃድ ተገዙ፤ ባሪያ ቢሆን ወይም ጨዋ ሰው፥ እያንዳንዱ የሚያደርገውን መልካም ነገር ሁሉ ከጌታ በብድራት እንዲቀበለው ታውቃላችሁና። እናንተም ጌቶች ሆይ፥ ዛቻውን ትታችሁ እንዲሁ አድርጉላቸው፥ በእነርሱና በእናንተ ላይ የሚገዛው ጌታ በሰማይ እንዳለ ለሰው ፊትም እንዳያደላ ታውቃላችሁና።

12

# የክርስቶስን ጌትነት መኖር

ስለ አንድ ዓመፀኛ ልጅ የቀረበውን የቴሌቪዥን ዝግጅት ከተመለከተ በኋላ አንድ ባል ለሚስቱ፥ «ምን ዓይነት ጥፋት ነው! ትውልዳችን የተበላሸው የቱ ላይ ነው?» ሲል ጠየቃት። ሚስቱም በርጋታ፥ «ልጆችን በወለድን ጊዜ» ስትል መለሰችለት።

የዘመኑን ማኅበረሰብ በምንመለከትበት ጊዜ ጥላቻ፥ ክፍፍልና ዓመፅ ይታይበታል። ባሎችና ሚስቶች ይፋታሉ፤ ልጆች በወላጆቻቸው ላይ ያምፃሉ፤ ሠራተኞችና አሠሪዎች ችግሮችን ለማስወገድና ምርታማነትን ለማሳደግ አዳዲስ መንገዶችን እየፈለጉ ናቸው። እንደ ትምህርት፥ የመንግሥት ሕግና የመሳሰሉት ዘዴዎች ቢሞከሩም ውጤት አላመጡም። ጳውሎስ ለቤተሰባዊና ማኅበረሰባዊ ችግሮች ያቀረበው መፍትሔ ዳግም መወለድ ማለትም ከእግዚአብሔር ዘንድ አዲስ ልብ ማግኘት፥ ለክርስቶስና አንዳችን ለሌላው መገዛት የሚል ነው። የእግዚአብሔር ትልቁ ዓላማ ሁሉንም በክርስቶስ መጠቅለል ነው (ኤፌ. 1፡10)። ይህ መንፈሳዊ ስምምነት ለክርስቶስ ጌትነት በሚገዙ አማኞች ሕይወት እንደሚጀምር ጳውሎስ ገልጾአል።

በዚህ ክፍል ጳውሎስ አራት ክርስቲያናዊ ቡድኖች እንዴት በክርስቶስ አንድነት መኖር እንደሚገባቸው መክሮአቸዋል።

## 1. ክርስቲያን ልጆች (6፡1–3)

ጳውሎስ ወላጆች ልጆቻቸውን እንዲመክሩ ከመናገሩ ይልቅ ራሱ በቀጥታ መክሮአቸዋል። ይህ መልእክት በሚነበብበት ጉባዔ ውስጥ ልጆችም ነበሩ። ጳውሎስ የጻፈውን ሁሉ ተረድተው ይሆን? እኛስ እንረደዋለን? ክርስቲያን ቤተሰቦች አብረው ያመልካሉ። ወላጆችም በቤት ውስጥ ለልጆቻቸው የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚገልጹላቸው አይጠረጠርም። ልጆች ወላጆቻቸውን ለምን መታዘዝ እንዳለባቸው ጳውሎስ አራት ምክንያቶችን ሰጥቷል።

*ክርስቲያኖች ስለሆኑ።* ይህ ማሳመኛ «ለእያንዳንዳችሁ» በጌታ ፍቅር የተገዛችሁ ሁኑ (5፡21) የሚለው የጠቅላላው ክፍል ጭብጥ ተዛምዶ ነው። አንድ ሰው ክርስቲያን በሚሆንበት ጊዜ ከተለመዱት የሕይወት ግዴታዎች ነፃ አይሆንም። ጳውሎስ ለቆላስይስ «ይህ ለጌታ ደስ የሚያሰኝ ነውና» (3፡20) የሚል ምክር ለግሶአል። የቤተሰብ ስምምነት በሚከተለው መልኩ ቀርቦአል፤ ሚስት ለክርስቶስ

እንደምትገዛ ለባሏ መገዛት አለባት፤ ባል ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቱን መውደድ አለበት። ልጆችም ለወላጆቻቸው «በጌታ» መታዘዝ አለባቸው።

*ታዛዥነት ተገቢ ነው።* እግዚአብሔር በመሠረተው ተፈጥሮ ውስጥ የአንድን ተግባር ትክክለኛነት የሚያሳይ ሥርዓት አለ። ወላጆች ልጆቻቸውን ወደዚህ ዓለም ስላመጡና ከልጆቻቸው የበለጠ እውቀትና ጥበብ ስላላቸው ልጆች ወላጆቻቸውን ሊታዘዙ ይገባል። በዕድሜያቸው ልጅ የሆኑ እንስሳት እንኳ ሳይቀር ታዛዥነትን ይማራሉ። የዘመኑ የኤፌሶን 6፡1 ትርጓሜ፥ «ወላጆች ሆይ፥ ልጆቻችሁን ታዘዙ፤ ይህ እነርሱን የሚያስደስትና ለቤተሰብ ሰላምን የሚያመጣ ነውና» የሚል ይሆናል። ይህ ግን የእግዚአብሔርን የፍጥረት ሥርዓት ይቃረናል።

*ታዛዥነት በትእዛዝ ተሰጥቶአል* (6:2)። በዚህ ስፍራ ጳውሎስ ከአሠርቱ ትእዛዛት አምስተኛውን በመጥቀስ (ዘጸአ. 20:12፤ ዘዳ. 5:16) ከአዲስ ኪዳን አማኞች ጋር ያዛምዳል። ይህ ማለት ግን ልጆች ከሕግ በታች ናቸው ማለት አይደለም፤ ክርስቶስ ከሕግ እርግማንና እስራት ነፃ አውጥቶናልና (ገላ. 3:13፤ 5:1)። ነገር ግን የሕግ ጽድቅ አሁንም የእግዚአብሔር ቅድስና መግለጥ ሲሆን፥ መንፈስ ቅዱስ ቅድስናውን በዕለታዊ ሕይወታችን እንድናከናውን ያስችለናል (ሮሜ 8:1–4)። ከሰንበት ሕግ በቀር አሠርቱን ትእዛዛት አማኞች እንዲጠብቋቸው በአዲስ ኪዳን ተደግመው ቀርበዋል። በብሉይ ኪዳን አንድ አይሁዳዊ ወላጆችን ማክበር እንዳለበት ሁሉ በአዲስ ኪዳንም አንድ ክርስቲያን ወላጆቹን ማክበር አለበት።

ወላጆቻችንን ማክበር ማለት ከመታዘዝ ያለፈ ነው። ወላጆቻችንን ማክበር ማለት ፍቅርና አክብሮት ማሳየት፥ እስከሚፈልጉን ድረስ መንከባከብ፥ ብሎም በአኗኗራችን እነርሱን ማስከበር ማለት ነው። ወጣቶች ለመጋባት ፈልገው እኔ ዘንድ ሲመጡ ወላጆቻቸው በጉዳዩ ላይ ተስማምተው እንደሆነ ጠየቅኋቸው። እርስ በርሳቸው ከተያዩ በኋላ «ስለዚህ ጉዳይ ይጠይቁናል ብለን አልገመትንም» አሉኝ። ወላጆች በእነርሱ ጋብቻ የመደሰት መብት እንዳላቸውና እነርሱን ገለል ማድረግ ምናልባት ሊጠገን የማይችል ቁስል ሊያስከትል እንደሚችል ለአንድ ሰዓታት ያህል ገለጽሁላቸው። «አማኞች ባይሆኑም እንኳ ወላጆቻችሁ ናቸውና ልትወዱዋቸውና ልታከብሩዋቸው ይገባል» አልኋቸው። ወጣቶቹ በመጨረሻው ተስማሙና አብረን የወጠንናቸው ዕቅዶች የሁለቱንም ቤተሰቦች አስደሰቱ። የመጀመሪያውን ዕቅድ ተከትለን ቢሆን ኖሮ ወላጆቻቸውን በማግለላቸው ምስክርነታቸውን ሊያጡ የነበሩት ተጋቢዎች አሁን ለኢየሱስ ክርስቶስ መልካም ምስክርነት ሊሰጡ ችለዋል።

መታዘዝ በረከትን ያመጣል (6፡2–3)። ከአሠርቱ ትእዛዛት አምስተኛው የተስፋ ቃል አለው፤ «እግዚአብሔር በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም» (ዘዳግ. 20፡12)። ይህ የተስፋ ቃል መጀመሪያ አይሁዶች ወደ ከነዓን በገቡበት ጊዜ ከሕይወታቸው ጋር የተዛመደ ሲሆን፥ ጳውሎስም ከዛሬዎቹ አማኞች ጋር አዛምዶታል። ርስት የሚለውን ምድር በሚለው ይተካና ወላጆቹን የሚያከብር ክርስቲያን ልጅ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሁለት በረከቶችን ሊጠባበቅ እንደሚችል ገልጾአል። መልካም የሚሆንለት ከመሆኑም በላይ በምድር ላይ ረዥም ዘመን ይኖራል። ይህ ማለት በወጣትነቱ የሞተ ሰው ሁሉ ወላጆቹን ያላከበረ ነው ማለት አይደለም። ጳውሎስ ልጆች ወላጆቻቸውን በሚታዘዙበት ጊዜ ከብዙ ኃጢአትና አደጋ በማመለጥ ሕይወታቸውን ሊያሳጥሩ ከሚችሉ ነገሮች እንደሚርቁ የሚያስረዳ መርህ ማስቀመጡ ነበር። ይህም ሆኖ የሕይወት መለኪያው ረዥም ዕድሜ ብቻ አይደለም። የልምድ ብቃትም ራሱ የሕይወት መለኪያ ነው። በምድር ላይ ምንም ያህል ዓመትም ቢኖር እግዚአብሔር የታዛዥን ልጅ ዕድሜ በምድር ላይ ይባርካል። ኃጢአት ሁልጊዜ ሲያራቁተን፥ ታዛዥነት ሁልጊዜ ያሳድገናል።

ስለሆነም፥ አንድ ልጅ ወላጆቹ ስለወለዱት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ስላዘዘው ጭምር አባቱንና እናቱን ሊያከብር ይገባል። ወላጆችን አለመታዘዝ በእግዚአብሔር ላይ እንደ ማመፅ ነው። ዛሬ በቤት ውስጥ የሚስተዋለው አሳዛኝ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ቃል ቸል ከማለት የመጣ ነው (ሮሜ 1፡28–30፤ 2ኛ ጢሞ. 3፡1–5)። በተፈጥሮአቸው ልጆች ራስ ወዳድነት የሚያጠቃቸው ቢሆንም፥ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አማካይነት ወላጆቻቸውን በመታዘዝ እግዚአብሔርን ሊያከብሩ ይችላሉ።

## 2. ክርስቲያን አባቶች (6፡4)

ልጆች እንዲሁ ከተተዉ ዓመፀኞች ስለሚሆኑ ወላጆች ልጆቻቸውን ሊያስተምሩ ይገባል። ከዓመታት በፊት የወቅቱ የዊንድሰር መስፍን፥ «በቤት ውስጥ ከልጆች በስተቀር ሁሉንም ነገር ‹ሪሞት ኮንትሮል› በመሳሰሉ የኤሌክትሪክ ዘዴዎች መቆጣጠር ይቻላል» ብለው ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድም በመጥፎ ምሳሌነታቸው አልያም በተገቢው መንገድ ልጆቻቸውን ባለመቅጣታቸው የልጆቻቸውን ሕይወት ያበላሹ ግለሰቦች ተጠቅሰዋል። ዳዊት አቤሴሎምን በማሞላቀቁ ለመጥፎ ምሳሌነት በመዳረግ አሳዛኝ ውጤቶችን አፍርቷል። ኤሊ ልጆቹን ባለመቅጣቱ ስሙን ከማዋረድ አልፈው ለእስራኤል ሽንፈት ምክንያት ሆነዋል። ይስሐቅ በስተርጅናው አካባቢ ዔሳውን በመውደዱና ሚስቱ ደግሞ ያዕቆብን በማስበለጧ ቤተሰቡ

ሊከፋፈል ችሏል። እግዚአብሔር በፈቃዱ ታድጎ በግብፅ ታላቅ ሰው ያደረገው ዮሴፍም በያዕቆብ ፊት ከወንድሞቹ ሁሉ በላይ ውድ ነበር። ጳውሎስ አባት ለልጆቹ አያሌ ኃላፊነቶች እንዳሉት ተናግሯል።

*ሊያስቆጣቸው አይገባም።* በጳውሎስ ዘመን አባት በቤተሰቡ ላይ ከፍተኛ ሥልጣን ነበረው። በአንድ የሮም ቤተሰብ ውስጥ ልጅ ሲወለድ በአባቱ ፊት ይቀርብ ነበር። አንሥቶ ከአቀፈው በቤተሰቡ አባል እንዲሆን ፈቀደ ማለት ነበር። አንሥቶ ካላቀፈው ግን አልተቀበለውም ማለት ነበር። በዚህ ጊዜ ልጁ ሊሸጥ ወይም በይፋ ሊገደል ይችላል። የአባት ፍቅር እንዲህ ዓይነቶቹን የጭካኔ ተግባር እንደሚያሸንፍ ባይጠረጠርም፥ እነዚህ እርምጃዎች በዘመኑ ሕግ ድጋፍ ነበራቸው። ጳውሎስ ወላጆች ልጆቻቸውን እንዲያበረታቱና እንዲያንጹ እንጂ በሥልጣናቸው ተጠቅመው እንዳይበድሏቸው ተናግሮአል። ለቆላስይስ ሰዎች ሲጽፍ፥ «አባቶች ሆይ፥ ልባቸው እንዳይዝል ልጆቻሁን አታበሳጩአቸው» ብሏል (ቆላ. 3፡21)። ስለሆነም የማበሳጨት ተቃራኒው ማበረታታት ነው።

ክርስቲያን ተማሪዎች በሚገኙበት ቡድን ስለ ጸሎት እያስተማርሁ ነበር፤ ሰማያዊ አባታችን በምንጠራው ጊዜ ሁሉ ሊሰማን ዝግጁ እንደሆነ ገለጽሁላቸው። አሳቤንም ለማብራራት የቤተ ክርስቲያናችን ጸሐፊ በእኔ የተዘጋጀ የሰዎች የስም ዝርዝር እንደያዘችና እነዚህ ሰዎች በፈለጉት ሰዓት ሁሉ ከእኔ ጋር ሊገናኙ እንደሚችሉ ገለጽሁላቸው። በአገልጋዮች ስብሰባ ወይም በማማከር ተግባር ላይ እያለሁ እንኳ ከእነዚህ ሰዎች አንዱ ከደወለልኝ ወዲያውኑ ልታገናኘን ይገባ ነበር። ከዚህ ዝርዝር በመጀመሪያ ረድፍ ላይ የተቀመጠው ቤተሰቤ ነበር። ምንም እንኳ ነገሩ ለእኔ ብዙም አስፈላጊ መስሎ ባይታየኝም ቤተሰቤ ከጎናቸው እንዳለሁላቸው ሊያውቁ ይገባል። «ከትምህርቱ በኋላ ከተማሪዎቹ አንዱ፥ ማደጎ ልጅ አድርገው ሊቀበሉኝ ይችላሉ? በጣም የምፈልገውን የአባቴን ማበረታቻ ላገኝ አልቻልሁም!» ሲል ገለጸልኝ።

አባቶች የሆነ ያልሆነውንም በማውራት ልጆቻቸውን ያበሳጫሉ። የሚያበሳጩዋቸውም ከማሞገስ ይልቅ በመኮነን፤ በፊታቸው በአንድ አቋም ባለመጽናት፥ በአግባቡ ባለመቅጣትና በቤተሰብ መካከል በማድላት ነው። ከዚህ በተጨማሪ የገቡትን ቃል ባለመፈጸምና ለልጆቻቸው ትልቅ የሆነውን ነገር እነርሱ በማቃለል ነው። ክርስቲያን ወላጆች ለልጆቻቸው ጉድለቶችና ችግሮች ልባቸው ይሳሳ ዘንድ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ያስፈልጋቸዋል።

*ሊንከባከባቸው ይገባል።* ምንባቡ፥ «በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጉአቸው እንጂ» ይላል። «አሳድጉአቸው» ተብሎ የተተረጎመው

ግሥ በ 5:29 ላይ «ይመግበዋል» የተባለው ነው። ክርስቲያን ባል በጌታ ፍቅር ሚስቱንና ልጆቹን መንከባከብ አለበት። ምግብ፥ መጠለያና ልብስ በማቅረብ አካላዊ እንክብካቤ ከማድረግ በተጨማሪ መንፈሳዊና ስሜታዊ እንክብካቤ ማድረግም አለበት። የኢየሱስ ክርስቶስ አስተዳደግ አእምሮአዊ፥ አካላዊ፥ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ገጽታዎችን የሚያካትት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በየትኛውም ስፍራ ቤተሰብ እንጂ ድርጅቶች ልጆችን እንዲያሳድጉ አልተጠየቁም። እግዚአብሔር ለልጆች የሚያስፈልገው ሥልጠና በወላጆች እንዲሰጥ ይሻል።

*ሊቀጣቸው ይገባል።* «መንከባከብ» በሚለው ቃል ውስጥ በቅጣት የመማርም አሳብ ተካትቷል። ይህም በዕብራውያን ምዕራፍ 12 ላይ «ቅጣት» ተብሎ ተተርጉሟል። አንዳንድ ዘመናዊ የሥነ–ልቡና ምሁራን ጥንቷዊውን የቅጣት መንገድ ይቃወማሉ፤ ብዙ የትምህርት ባለሙያዎችም ይህንኑ ፍልስፍና ይከተላሉ። «ልጆች ራሳቸውን መግለጽ አለባቸው። ከቀጣችኋቸው ባሕርያቸውን ልትሸፍኑባቸው ትችላላችሁ» ይሉናል። ነገር ግን ቅጣት መሠረታዊ የሕይወት መርህ ሲሆን፥ የፍቅርን መኖር የሚያረጋግጥ መሣሪያ ነው። «ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና» (ዕብ. 12:6)። «ልጁን የሚወድድ ግን ተግቶ ይገሥጸዋል» (ምሳሌ 13:24)።

ይህም ሆኖ፥ አቀጣጣችን በተገቢው መንገድ ሊካሄድ ይገባል። በመጀመሪያ ደረጃ በጥላቻ ሳይሆን በፍቅር መቅጣት ይኖርብናል። ይህም የልጃችንን አካል፥ መንፈስ ወይም ሁለቱንም እንዳንጎዳ ያግዘናል። ተቀጥተን በሥርዓት ካላደግን ልጆቻችንን ልንቀጣ አንችልም። ልጆቹን አለመቅጣት ደግሞ ጥሩ ልጅ ወይም ጥሩ ወላጅ ሊፈጥር አይችልም።

ቅጣታችን ተገቢና ቀጣይ ሊሆን ይገባል። አንድ ጊዜ አንድ ታዳጊ ወጣት፥ «አባቴ ትንኝ ለመግደል መድፍ ከመተኮስ አይመለስም! አንዳንዴ አጥፍቼም እንኳ አልቀጣም። ሌላ ጊዜ ደግሞ ለተበላሸው ነገር ሁሉ ተጠያቂው እኔ እሆናለሁ» ሲል ገልጾልኛል። ቀጣይነት ኖሮት በፍቅር የሚካሄድ ቅጣት ለልጅ ዋስትናን ይሰጠዋል። ልጁ በአሳባችን ላይስማማ ይችላል፤ ሆኖም ራሱን መጠበቅ እስኪችል ድረስ በዙሪያው ቅጥሮችን በመሥራት እየተጠነቀቅንለት መሆኑን ይረዳል።

«ወላጆቼ እስኪቀጡኝ ድረስ አልገደዳቸውምና ምን ያህል እርምጃ መውሰድ እንዳለብኝ አላውቅም ነበር። ቅጣቱ ለእነርሱ አስፈላጊ ካልሆነ ለእኔስ ምን ያደርግልኛል? ስል አሰብሁ» ብላኛለች አንዲት ኮብላይ ልጅ።

ሊያስተምራቸውና ሊያበረታታቸው ይገባል። ይህ «ምክር» የተባለው ቃል ፍች ነው። ወላጆች ልጆቻቸውን ለማሳደግ በተግባር ብቻ ሳይሆን በቃልም መጠቀም ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ በመጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ አባት ለልጁ ጥበብን ሲያካፍል እንመለከታለን። ልጆቻችን የምንሰጣቸውን ምክር ሁሉ ላይወዱት ይችላሉ፤ ሆኖም ይህ እነርሱን ከማስተማርና ከማበረታታት ግዴታችን ነፃ አያደርገንም። የምናቀርብላቸው ትምህርት ሁልጊዜም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ሊጣጣም ይገባል (2ኛ ጢሞ. 3፡13-17 ተመልከት)።

የበላይ ችሎቱ በሕዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚካሄደውን ጸሎት በመቃወም ሕግ ሲያወጣ፥ ታዋቂው ካርቱኒስት በዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ ላይ ካርቱን ሥዕል አቅርቦ ነበር። በካርቱን ሥዕሉ ላይ አንድ የተበሳጨ አባት በቤተሰቦቹ ላይ ጋዜጣ እያውለበለበ፥ «ምን እንድናደርግ ነው የሚፈልጉት? በቤት የሕፃናትን ጸሎት እንድናዳምጥ ነው?» ሲል ይጮኋል። መልሱ፥ አዎ! ልጆች በቤት ውስጥ ስለ ክርስቶስና ስለ ክርስቲያናዊ ሕይወት ሊማሩ ይገባል ነው። ወላጆች የማስተማር ኃላፊነታቸውን ለሰንበት ትምህርት ቤት መምህራን ከመተው ይልቅ ልጆቻቸውን ማስተማር የሚጀምሩበት ጊዜው አሁን ነው።

## 3. ክርስቲያን ሠራተኞች (6፡5-8)

«ባሪያዎች» የሚለው ቃል ከጌቶቻቸው ሥር የሚተዳደሩትን ክርስቲያኖች የሚያመለክት ሲሆን፥ ዛሬ ለክርስቲያን ሠራተኞች ልንጠቀምበት እንችላለን። በወቅቱ ሰዎችን ባርያ ማድረግ በሕግ የተደገፈ በመሆኑ በዚያን ጊዜ በሮም መንግሥት ውስጥ ስድስት ሚሊዮን ባሮች እንደነበሩ ይገመታል። ምንም እንኳ የወንጌሉ ጠቅላላ ጭብጥ ባርነትን የሚቃወም ቢሆንም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ግን ባርነት በግልጽ የተወገዘበት ስፍራ የለም። የጳውሎስ አገልግሎት ያተኮረው ወንጌሉን በመስበክና ኃጢአተኞችን ወደ ክርስቶስ በመመለስ ላይ እንጂ የሮምን መንግሥት ወይም ከተቋሞቿ አንዱን በመናድ ላይ አልነበረም። ምንም እንኳ የወንጌል ስርጭቱ ውጤት የኋላ ኋላ የሮምን መንግሥት ቢያፈራርሱም፥ ይህ ግን የጳውሎስ ዋነኛ ዓላማ አልነበረም። የዊስሊና የዋይትፊልድ ስብከት የባርነትንንና የልጆችን በሥራ መጠመድ እንዳስወገደ፥ የሴቶችን መብት እንዳስከበረና ለድሆች እንክብካቤ የሚደረግበትን መንገድ እንዳመቻቸ ሁሉ፥ የጳውሎስም አገልግሎት ለባርነት መሞትና ለነጻነት መወለድ መሠረት ጥሏል። ይህም ሆኖ፥ ጳውሎስ ማኅበራዊ ሥርዓትን ከቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አሠራር ጋር ላለማቀላቀል ጥንቃቄ አድርጓል (1ኛ ቆሮ. 7፡20-24)።

ጳውሎስ ሠራተኞች ታዛዥነትን ያሳዩ ዘንድ አያሌ ምክንያቶችን አቅርቧል። በመጀመሪያ በእርግጥ የሚያገለግሉት ክርስቶስን ነው፤ «በሥጋ ጌቶች እንደ ነበሩዋቸው ቢታወቅም እውነተኛ ጌታቸው በሰማይ የሚኖረው ክርስቶስ ነበር» (ቁ. 9)። አሠሪውና ሠራተኛው ክርስቲያን መሆናቸው ለሁለቱም አነስተኛ ሥራ ለማከናወን ማመኻኛ አይሆንም። ይልቁንም እንዳቸው ለሌላቸው ታማኝ የሚሆኑበት ጥሩ ምክንያት ነው። ሥራተኛው አሠሪውን የጥቅም መሣሪያ ከማድረግ ይልቅ በአግባቡ ሊያከናውን ይገባል። በሥራ ላይ ጥሩ ምስክር መሆን የሚቻለው ተገቢውን ኃላፊነት በሚገባ መወጣት ሲቻል ነው። ክርስቲያን ሠራተኛ ለታይታ ማለትም አለቃው ብቻ በሚያየው ጊዜ መሥራትን ወይም ደግሞ ታታሪ ሠራተኛ ለመምሰል መጣርን ማስወገድ ይኖርበታል።

ሁለተኛው ምክንያት ጥሩ ተግባር ማከናወን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ክርስትና ዓለማዊና መንፈሳዊ የሚባል ሥራ አያውቅም። አንድ ክርስቲያን አንድ መልካም ተግባር ለክርስቶስ አገልግሎት ይሆን ዘንድ በተገቢው መንገድ በመሥራት እግዚአብሔርን ሊያከብር ይችላል። ስለሆነም ይህ ክርስቶስን የምናገለግልበትና እግዚአብሔርን የምናከብርበት ዕድል ነው። ከዚህም የተነሣ ክርስቶስን ስለሚያገለግልና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለሚያደርግ ሥራውን ከልብ መሥራት አለበት። ባሪያዎችን በመናቅ የሚቀርቡላቸው ሥራዎች ቢኖሩም እንኳ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚጻረሩ እስካልሆኑ ድረስ ሊያከናውኗቸው ይገባል። «የልብ ቅንነት» እና «ከልብ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም» በሥራ ላይ ሊኖር የሚገባውን ትክክለኛ ዝንባሌ የሚያሳዩ ናቸው።

የጳውሎስ ሦስተኛው ነጥብ ጌታ የሚሸልማቸው መሆኑ ነው (ቁ. 8)። በዚያን ዘመን ባሪያዎች ምንም ያህል ትምህርት ቢኖራቸውም እንደ ዕቃ ይቆጠሩ ነበር። የተማረና የሠለጠነ ባሪያ ክርስቲያን በሚሆንበት ጊዜ በእምነቱ ምክንያት ጌታው ከቀድሞው የበለጠ ሊጨቁነው ይችላል። ይህ ግን በሚችለው ሁሉ መልካም ሥራ ከመሥራት ሊያቅበው አይገባም (1ኛ ጴጥ. 2፡18-25)። የምናገለግለው ሰዎችን ሳይሆን ክርስቶስን ነው። ሽልማታችንንም የምንቀበለው ከክርስቶስ እንጂ ከሰዎች አይደለም።

አንድ ሽማግሌ ለብዙ ዓመታት በአፍሪካ አሕጉር የወንጌል አገልግሎት ሲያበረክቱ ቆይተው ወደ አገራቸው ወደ አሜሪካ እየተመለሱ ነበር። ሽማግሌው በተሳፈሩበት በዚያው መርከብ ውስጥ በአፍሪካ የአደን ተግባር ሲያከናውኑ የቆዩት ፕሬዘዳንት ቴዎዶር ሩዝቬልትም ነበሩ። መርከቡ ኒውዮርክ ሲደርስ እጅግ ብዙ ሰዎችና

ጋዜጠኞች ፕሬዘዳንቱን ሲያጨናንቋቸው ሽማግሌው የወንጌል አገልጋይና ባለቤታቸው ግን ማንም ቦታ ሳይሰጣቸው ከመርከቡ ወጥተው ወደ ምዕራብ ከመሄዳቸው ምሽቱን ወደሚያሳልፉበት ሆቴል አመሩ።

«ነገሩ ልክ አይመስልም!» ሲሉ ተናገሩ በሁኔታው የተቆጡት ሽማግሌ። «ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለመመለስ የሕይወት ዘመናችንን ሁሉ በአፍሪካ ቆይተን ስንመለስ አቀባበል የሚያደርግልን አንድም ሰው የለም። ምንም ሽልማት አልተሰጠንም። ፕሬዘዳንቱ ግን እንስሳትን ገድለው ስለተመለሱ ንጉሣዊ አቀባበል ተደረገላቸው!»

ከማረፋቸው በፊት እየጸለዩ ሳሉ የጌታ ድምፅ፥ «ሽልማታችሁን ለምን እንዳልተቀበላችሁ ታውቃላችሁ፥ ልጆቼ? ምክንያቱም ገና ከቤታችሁ ስላልደረሳችሁ ነው!» ሲል ተናገራቸው።

## 4. ክርስቲያን አሠሪዎች (6፡9)

የክርስትና እምነት ማኅበራዊ ወይም ባሕላዊ ልዩነቶች በመፋቅ ስምምነትን አያመጣም። ባሪያዎችም ሆኑ ጌቶች በክርስቶስ ሲያምኑ በዚያው ደረጃቸው ሊኖሩ ይችላሉ። የክርስትና እምነት ስምምነትን የሚያመጣው በልብ ውስጥ በመሥራት ነው። ክርስቶስ የሚሰጠን አዲስ ዓላማን እንጂ አዲስ አደረጃጀት አይደለም። ጌቶችም ሆኑ ባሮች ጌታን እያገለገሉ ሲሆን፥ በዚህ ዓይነት ለእግዚአብሔር ክብር አብረው ሊሠሩ ይችላሉ። አንድ ክርስቲያን ጌታ ለሠራተኞቹ ያለው ኃላፊነት ምንድን ነው?

*ደኅንነታቸውን ሊሻ ይገባል።* «እንዲሁ አድርጉላቸው።» አንድ አሠሪ ሠራተኞቹ ከልባቸው እንዲሠሩለት ከፈለገ እርሱም ከልቡ ሊያስብላቸው ይገባል። ሠራተኞች ይህንኑ እንዲያደርጉለት የሚፈልግ ከሆነ አሠሪው ጌታን ከልቡ ሊያገለግል ይገባል። ሊበዘብዛቸው ግን አይገባም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለዚህ ምሳሌ ከሚሆኑት አንዱ በመጽሐፈ ሩት ውስጥ የሚገኘው ቦዔዝ ነው። ለሠራተኞቹ፥ «እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን!» የሚል ሰላምታ ይሰጣቸው ነበር። እነርሱም፥ «እግዚአብሔር ይባርክህ!» ብለው ይመልሱለታል (ሩት 2፡4)። ቦዔዝ ሠራተኞቹ ጉድለት እንዳይታይባቸው የሚሳሳ ሲሆን፥ ለእንግዳዪቱ ሩትም የልግስና ተግባር አድርጓል። ከሠራተኞቹ ጋር መከባበር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት የነበረው ሲሆን፥ መሻቱም ጌታን ማክበር ነበር። አንድ ሠራተኛ፥ «አለቃዬ ክርስቲያን ነው፤ ሆኖም ክርስቲያን መሆኑ አይታወቅም» ሲል መስማቱ አሳዛኝ ነው።

*ሊዝትባቸው አይገባም።* ብዙዎቹ ተግባራዊ የሮም ጌቶች የሚያምፅባቸውን ባሪያ የመግደል ሕጋዊ ሥልጣን ነበራቸው። ባሪያ በብዙ ገንዘብ ስለሚሸጥ ባሮቹን መግደል ገንዘባቸውን ማባከን ይሆንባቸዋል። ጳውሎስ ታዛዥነትንና ጥሩ አገልግሎትን ለማግኘት ጌቶች ከዛቻ ይልቅ የተሻለ መንገድ ሊጠቀሙ እንደሚችሉ ገልጾአል። ባሮች በፍርሃት ሲዋጡ ሥራቸውን እንደሚገባ ማከናወን አይችሉም፤ የዚህ ዓይነቱም ድርጊት ረዥም ዕድሜ ሊኖረው እንደማይችል አስተምሮአል። የሚሻለው «በጽድቅና በቅንነት» ማስተዳደሩ ነው (ቆላ. 4፡1)። ሠራተኛው የሥራውን ውጤት እንዲጋራ ከተደረገ የተሻለና የበለጠ ተግባር ያከናውናል። ብሉይ ኪዳንም ይህንኑ ምክር ይሰጣል፤ «በጽኑ እጅ አትግዛው፥ ነገር ግን አምላክህን ፍራ» (ዘሌዋ. 25፡43)።

*ለጌታ መገዛት አለበት።* «በእናንተ ላይ የሚገዛው ጌታ በሰማይ እንዳለ» (ቁ. 9)። ይህ በክርስቶስ ጌትነት ሥር መኖር ነው። ሚስት ለጌታ እንደምትገዛ ለባሏ ትገዛለች (5፡22)። ባልም ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቱን ይወዳታል (5፡25)። ልጆች ለወላጆቻቸው በጌታ ሲገዙላቸው (6፡1)፥ ወላጆችም ልጆቻቸውን በጌታ ምክርና ተግሣጽ ያሳድጓቸዋል (6፡4)። ባሪያዎች ለክርስቶስ እንደሚገዙ ለጌቶቻቸውም ይገዛሉ (6፡5)። ጌቶች ባሪያዎቻቸውን የሰማዩ ጌታቸው በሚያስተናግዳቸው መንገድ ሊያስተናግዱቻቸው ይገባል። እያንዳንዱ ሰው ለጌታ ከተገዛ ከእርሱ በላይ ላሉት የመገዛት ችግር አይኖርበትም።

ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ለመሆን መንገዱ ባሪያ መሆን እንደሆነ ገልጾአል (ማቴ. 25፡21)። ከሥልጣን ሥር ያልሆነ ሰው ሥልጣን የመጠቀም መብት የለውም። እንደ ዮሴፍ፥ ሙሴ፥ ኢያሱ፥ ዳዊት፥ ነህምያና ሌሎች ታላላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ገዥዎች ከመሆናቸው በፊት ባሪያዎች እንዲሆኑ የተደረገው ለዚህ ነው። አንድ ሰው ወደ መሪነት ደረጃ ከደረሰ በኋላም አገልጋይ ሆኖ መምራት አለበት። «አለቃ የሁሉ አገልጋይ ነው» የሚል የአፍሪካውያን አባባል አለ። ጌታችንም ጌታ ሊሆን የሚወድ የሌሎች አገልጋይ መሆን እንዳለበት ተናግሮአል (ማቴ. 20፡27)።

አንድ ወዳጄ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሾም ኃላፊነቱ ናላውን አዞረው። ሹመቱ ያመጣለትን ጥቅም እንጂ ለሥራው ትኩረት ሊሰጥ አልቻለም። በዚህ ጊዜ የድርጅቱ ምርት በመቀነሱ ቦርዱ ከሥልጣኑ አወረደው። ወዳጄ በሰማይ አለቃ እንዳለው ስለዘነጋ በምድር ላይ ጥሩ አለቃ ሊሆን አልቻለም።

ሊያደላ አይገባም። እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላም። ባሪያም ሆነ ጌታ ኃጢአትን ከፈጸመ ይፈረድበታል። ከታዘዘ ደግሞ ባሪያ ወይም ጌታ ሳይል ይሸልመዋል (ቁ. 8)። አንድ ክርስቲያን አሠሪ በሥልጣኑ ብቻ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያገኘው በረከት አይኖርም። ክርስቲያን አለቃ በሚያሠራቸው ሰዎች ላይ አድልዎ ማሳየት የለበትም። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን፥ «አንድን እንኳ በአድልዎ ሳታደርግ፥ እነዚህን ያለ መዘንበል እንድትጠብቅ» ሲል አስጠንቅቆታል (1ኛ ጢሞ. 5፡21)። የአንድን መሪ ተከታታዮች ከሚከፋፍሉና ታማኝነታቸውን ከሚቀንሱ ነገሮች መካከል አንዱ አድልዎ ነው።

«በስምምነት መመላለስ» ብለን የሰየምነው ክፍል በዚህ ይጠናቀቃል። በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላን፥ ደስተኞች፥ የምናመሰግንና የምንገዛ ሰዎች ከሆንን ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በስምምነት ልንኖርና ልንሠራ እንችላለን። በተጨማሪም ከእኛ ጋር ለማይስማሙ ዓለማውያን እንኳ ለመመስከር ይቀለናል። ፍቅር የመንፈስ ፍሬ ነው፤ ይህም በዓለም ትልቁ የመንፈስ ፍሬ ነው፤ ደግሞም በዓለም ትልቁ አያያዥ ኃይል ነው!

በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ። የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ። እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፥ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጾች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤ የመዳንንም ራስ ቊር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤ ደግሞ የወንጌልን ምሥጢር በግልጥ እንዳስታውቅ አፌን በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ስለ እኔ ለምኑ፤ ስለ ወንጌልም በሰንሰለት መልእክተኛ የሆንሁ፥ መናገር እንደሚገባኝ ስለ እርሱ በግልጥ እናገር ዘንድ ለምኑ።

ነገር ግን እንዴት እንዳለሁ ኑሮዬን እንድታውቁ የተወደደ ወንድምና በጌታ የታመነ አገልጋይ ቲኪቆስ ሁሉን ያስታውቃችኋል፤ ወሬአችንን እንድታውቁና ልባችሁን እንዲያጽናና ወደ እናንተ የምልከው ስለዚህ ምክንያት ነው።

ከእግዚአብሔር አብ፥ ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምና ፍቅር ከእምነት ጋር ለወንድሞች ይሁን። ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ባለመጥፋት ከሚወዱ ሁሉ ጋር ጸጋ ይሁን፤ አሜን።

## 13

# መንፈሳዊ ውጊያ

ሆነም ቀረ እያንዳንዱ አማኝ የክርስትና ሕይወት የጨዋታ ሜዳ ሳይሆን የጦር ሜዳ መሆኑን ይገነዘባል። ከጌታ ውጭ ቢገጥመው ሊዘነጣጥለው የሚችለው ጠንካራ ጠላት እንዳለበትም ይረዳል። ጳውሎስ አማኝ ከሰይጣን ጋር የሚያደርገውን ግጭት ለማብራራት ወታደራዊ አገላለጽ መጠቀሙ ተገቢ ነው። እርሱ ራሱ ከሮም ወታደር ጋር በሰንሰለት የታሰረ ከመሆኑም በላይ (6፡20)፥ አንባቢያኑም ወታደሮችንና የውትድርና መሣሪያዎችን ያውቁ ነበር። ወታደራዊ አገላለጾች ጳውሎስ ብዙውን ጊዜ የሚጠቀምባቸው ናቸው (2ኛ ጢሞ. 2፡3፤ 4፡7፤ 1ኛ ጢሞ. 6፡12፤ 2ኛ ቆሮ. 10፡4)።

እኛ ክርስቲያኖች፥ ዓለም ሥጋና ሰይጣን የሚባሉ ሦስት ጠላቶች ይዋጉናል (ኤፌ. 2፡1-3)። ዓለም ከእግዚአብሔር ጋር የሚቃረነውን መዋቅር ያመለክታል። ተግባሩ የሥጋ ምኞትን፥ የዓይን አምሮትንና ትምክህትን ማጋፈር ነው (1ኛ ዮሐ. 2፡15-17)። «ከእግዚአብሔር ውጭ የሆነ ኅብረተሰብ» የተሰኘው አባባል ግልጽና ትክክለኛው «የዓለም» ፍች ነው። «ሥጋ» ከአዳም የተቀበልነው አሮጌው ባሕርይ ነው። ይህ እግዚአብሔርን የሚያስደስት መንፈሳዊ ተግባር መፈጸም አይችልም። በሞቱና በትንሣኤው ክርስቶስ ዓለምን (ዮሐ. 16፡33፤ ገላ. 6፡14)፥ ሥጋንና (ገላ. 2፡20፤ ሮሜ 6፡1-6)፥ ዲያብሎስን (ኤፌ. 1፡19-23) አሸንፎአል ። በሌላ አገላለጽ እኛ ክርስቲያኖች ለድል አንዋጋም፤ ከድል ምሽግ እንዋጋለን እንጂ። የእግዚአብሔር መንፈስ የክርስቶስን ድል የእኛ ድል እንድናደርግ ያግዘናል።

## 1. ጠላት (16፡10-12)

የስለላ ጓድ የጦር ሠራዊቱ የጠላትን አቅም በሚገባ እንዲያውቁ ስለሚያደርግ፥ በጦርነት ውስጥ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ የላቀ ነው። ጠላታችን ማን እንደሆነ፥ የት እንደሚገኝና ምን ሊያደርግ እንደሚችል ካላወቅን፥ ድል ለመምታት እንቸገራለን። በኤፌሶን ምዕራፍ 6 ብቻ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ፥ እግዚአብሔር ስለ ጠላታችን ያስተምረናል። ስለሆነም ልንዘነጋ ምንም ምክንያት የለንም።

*መሪው ዲያብሎስ።* ጠላታችን የተለያዩ ስሞች አሉት። ዲያብሎስ ማለት ከሳሽ ማለት ነው። ይህም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ቀንም ሆነ ሌሊት በዙፋኑ ፊት ስለሚከሳቸው ነው (ራእይ 12፡7-11)። ሰይጣን

ማለት ባላጋራ ማለት ነው። ለዚህም ምክንያቱ የእግዚአብሔር ጠላት መሆኑ ነው። በተጨማሪም፥ ፈታኙ (ማቴ. 4፡3)፥ ነፍሰ ገዳይና ሐሰተኛ ተብሎ ተጠርቶአል (ዮሐ. 8፡44)። ከአንበሳ (1ኛ 5፡8)፥ ከእባብና (ዘፍጥ. 3፡1፤ ራእይ 12፡9) ከብርሃን መልአክ ጋር ከመነጻጸሩም በላይ (2ኛ ቆሮ. 11፡13-15)፥ የዚህ ዓለም አምላክ እንደሆነም ተገልጾአል (2ኛ ቆሮ. 4፡4)።

ለመሆኑ እግዚአብሔርን ለመቃወምና ሥራውን ለማፍረስ የሚሻው ይህ መንፈሳዊ ፍጥረት ከየት መጣ? ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት እንደሚያምኑት፥ ሰይጣን መጀመሪያ ሲፈጠር የንጋት ኮከብና ሉሲፈር ነበር (ኢሳ. 14፡12-15)። የጣለውም በትዕቢትና የእግዚአብሔርን ዙፋን ለመውረስ በመፈለጉ ነው። ከሰይጣን መፈጠር ጋር የተያያዙ ብዙ ምሥጢራት ቢኖሩም፥ አሠራሩና አካሄዱ ግን ምሥጢር አይደለም። ፍጡርና ዘላለማዊ ባለመሆኑ እንደ እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ፥ ሁሉን ቻይ ወይም በሁሉም ስፍራ የሚገኝ አይደለም። እንዲህ ከሆነ በተለያዩ የዓለም ክፍተኛ ተግባር ሊያከናውን የሚችለው እንዴት ነው? መልሱ በተደራጁ ረዳቶቹ አማካይነት ነው የሚል ነው።

*የሰይጣን ረዳቶች።* ጳውሎስ አለቆች፥ ሥልጣናት፥ ገዢዎችና በሰማያዊ ስፍራ የሚገኙ የክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት ሲል ጠርቶአቸዋል (ቁ. 12)። ቻርልስ ቢ. ዊልያምስ ይህንን ክፍል፥ «የምንዋጋው ከሰብአዊ ጠላቶች ጋር ብቻ ሳይሆን፥ ከሥልጣናት፥ ከአለቆችና ከዚህ የጨለማ ዓለም ኃይላት ጋር ጭምር ነው። ይህም ማለት በሰማያዊ ውጊያ ክፉ መንፈሳዊ ኃይላት ይገዳደሩናል ማለት ነው» ሲሉ ተርጉመዋል። (ዘ ኒው ቴስታመንት ኢን ዘ ላንጉጅ ኦፍ ዘ ፒፕል "The New Testament in the Language of the People") ይህም የሰይጣን በአማኞች ላይ ለሚሰነዘረው ጥቃት እገዛ የሚያደርጉለት ሁነኛ አጋንንታዊ ሠራዊት እንዳሉት ያመለክታል። ሐዋርያው ዮሐንስ ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ የዐመፅ ተግባር በፈጸመ ጊዜ አንድ ሦስተኛ የሚሆኑ መላእክት አብረውት እንደ ወደቁ ፍንጭ ሰጥቷል (ራእይ 12፡4)። ዳንኤል በበኩሉ የሰይጣንን መላእክት የአገሮችን ጉዳይ በመቆጣጠሩ ረገድ ከእግዚአብሔር መላእክት ጋር እንደሚታገሉ አመልክቷል (ዳን. 10፡13-20)። መንፈሳዊ ጦርነት በዚህ ዓለምና በሰማያዊ ስፍራ በመካሄድ ላይ ይገኛል። እኛም የዚህ ጦርነት አካል ነን። ይህንን ስንገነዘብ በድል እንመለከታለን። ይህም ለእኛም ሆነ ለእግዚአብሔር ወሳኝ ጉዳይ ነው።

ዋናው የምንዋጋው ከሰዎች ጋር እንዳልሆነ መገንዘቡ ነው። የምንዋጋው ከመንፈሳዊ ኃይላት ጋር ነው። ሰዎችን በመቆጣጠር

የእግዚአብሔርን ሥራ እንዲቃወሙ የሚያደርገውን ሰይጣንን መዋጋት ሲገባን ሰዎችን በመዋጋት ጊዜያችንን እናባክናለን። ጳውሎስ በኤፌሶን ባገለገለ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንን ሊያወድም የሚችል ብጥብጥ ተነሥቶ ነበር (የሐዋ. 19:21-41)። ብጥብጡ የተከሰተው በድሜጥሮስና በተባባሪዎቹ ብቻ ሳይሆን በሰይጣንና በተባባሪዎቹም ጭምር ነበር። ጳውሎስና ቤተ ክርስቲያኒቱ ጸልየው የሰጠው ምክር ለመንፈሳዊ ውጊያ ሳይጠቅም አይቀርም፤ «ከንጉሡ በቀር ታናሽ ቢሆን ወይም ታላቅ ከማናቸውም ጋር አትግጠሙ» (1ኛ ነገሥ. 22:31)።

*የሰይጣን ችሎታ።* ጳውሎስ ከሰጠን ምክሮች እንደምንረዳው፥ ሰይጣን ብርቱ ጠላት ነው (ቁ. 10-12)። እርሱን ለመቋቋም የእግዚአብሔር ኃይል ያስፈልገናል። ከአንበሳና ከዘንዶ ጋር የተነጻጸረው ለቀልድ አይደለም። ኃይሉ በሰው አካል፥ በቤተሰብ፥ በሀብትና በወዳጆች ላይ ምን ሊያስከትል እንደሚችል ከመጽሐፈ ኢዮብ መረዳት ይቻላል። ኢየሱስ ሰይጣን ሊሰርቅ፥ ሊያርድና ሊያጠፋ እንደሚመጣ ገልጾአል (ዮሐ. 10:10)። ሰይጣን ብርቱ ብቻ ሳይሆን ብልህና ረቂቅም ጭምር በመሆኑ ይህንኑ ክፋቱን መዋጋት አለብን። ክርስቲያን የሰይጣንን አሳብ አይስተውም (2ኛ ቆሮ. 2:11)። አንዳንድ ሰዎች ብልጣብልጦች ሆነው በሽንገላ ይናገራሉ (ኤፌ. 4:14)፥ ከበስተኋላቸው ግን ዋንኛው ሸንጋይ ዲያብሎስ ይኖራል። ሰይጣን የብርሃን መልአክ በመምሰል (2ኛ ቆሮ. 11:14) ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት እንዳያስተውሉ አእምሮአቸውን ለማጨለም ይሻል። ጳውሎስ እንድንዋጋ ሲጠይቀን ታዛቢዎች ብቻ ሳንሆን በውጊያው ውስጥ እንደተሳተፍን ያሳያል። ሰይጣን ውጫዊ ጠላታችን የሆኑትን ዓለምና ሥጋችንን በመጠቀም ሊያሸንፈን ይፈልጋል። መሣሪያዎቹና የውጊያ ዕቅዶቹ የሚታዩ አይደሉም።

## 2. የመዋጊያው መሣሪያ (6:13-17)

የምንዋጋው በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ ከሚገኙት ጠላቶች ጋር በመሆኑ፥ ለማጥቃትም ሆነ ለመከላከል ልዩ መሣሪያዎች ያስፈልጉናል። እግዚአብሔር «ሙሉ የጦር ዕቃ» ስለሰጠን ከጦር ዕቃው መቀነስ የለብንም። ሰይጣን ዕድል ፈንታ የሚያገኝበትን ጊዜ መፈለጉ የማይቀር ነው (ኤፌ. 4:27)። ጳውሎስ ተደራስያኑ የእግዚአብሔርን ጦር ዕቃ እንሥተው ሰይጣንን እንዲቋቋሙ አዞአል። ይህም በእምነት የሚካሄድ ተግባር ነው። ክርስቶስ ቀደም ሲል ሰይጣንን እንዳሸነፈና መንፈሳዊ መሣሪያዎችም እንደተሰጡን በመገንዘብ፥ እግዚአብሔር የሚሰጠንን ተቀብለን ጠላታችንን ለመዋጋት እንወጣለን። ቀኑ ክፉ ነው፤ ጠላትም እንደዚሁ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል? (ሮሜ 8:31)።

*የእውነት መታጠቂያ* (6:14)። እውነት ሕይወታቸውን የተቆጣጠረ አማኞች ሐሰተኛ የሆነውን ሰይጣንን ያሸንፋሉ (ዮሐ. 8:44)። መታጠቂያው ሌሎች የጦር መሣሪያዎችን በአንድነት ስለሚያስተሳስር፥ እውነት ለድል ነሺ ክርስቲያን ሕይወት እጅግ አስፈላጊ ነው። ንጹሕ ሕሊና ያለው እውነተኛ ሰው ጠላትን ያለፍርሃት ሊጋፈጥ ይችላል። በተጨማሪም መታጠቂያው ሰይፍ የሚያዝበት ነው። እውነትን ካልተለማመድን የእውነት ቃል ልንጠቀም አንችልም። ውሸት ወደ ክርስቲያን ሕይወት ከገባ ሁሉም ነገር ይበላሻል። ከአንድ ዓመት ለሚበልጥ ጊዜ ንጉሥ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ስለፈጸመው ኃጢአት እየዋሸ ኖሯል። በዚህ ጊዜ የተሳካለት ነገር አልነበረም። በኃጢአት የከፈለውን ዋጋ ከመዝሙር (51) እና (32) ማንበብ ይቻላል።

*የጽድቅ ጥሩር* (6:14)። ከብረት ወይም ከሰንሰለት የሚሠራው ይህ መሣሪያ ሰውነትን ከአንገት እስከ ወገብ ድረስ የሚሸፍን ነው። ይህም አማኙ በክርስቶስ ያገኘውን ጽድቅና (2ኛ ቆሮ. 5:21) በክርስቶስ ያለውን የጽድቅ ሕይወት እንደ ምሳሌ ያሳያል (ኤፌ. 4:24)። ሰይጣን ከሳሽ እንደ ሆነ ቢታወቅም፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚመላለሰውን አማኝ ሊከስ አይችልም። የምንመራው ሕይወት አንድም በሰይጣን ጥቃት ላይ በርትተን እንድንቆም ያበረታታናል ወይም ሰይጣን እንዲያሸንፈን ሁኔታዎችን ያመቻችለታል (ቁ. 7)። ሰይጣን ክርስቲያኑን በሚከስበት ጊዜ ለክርስቲያኑ ስለ ደኅንነቱ ማረጋገጫ የሚሰጠው የክርስቶስ ጽድቅ ነው። ይህም ሆኖ፥ በክርስቶስ ያገኘው ጽድቅ በዕለት ተዕለት ተግባራዊ ጽድቅ ካልተደገፈ ሰይጣን እንዲያጠቃን በር ይከፍታል።

*የወንጌሉ ጫማ* (6:15)–። የሮም ወታደሮች በጦርነት ጊዜ ምቾት እንዲሰጣቸው የሚያደርጉት ጫማ ሰንደል ጫማ ነበር። እኛም ጦርነቱን እንድንቋቋምና እንድናሸንፍ ከተፈለገ የወንጌሉ ጫማ ያስፈልገናል። ከወንጌሉ የሚመጣ የእግዚአብሔር ሰላም ስላለን (ሮሜ 5:1)፥ የሰይጣንን ወይም የሰዎችን ጥቃት ልንፈራ አይገባም። ዲያብሎስን ለማሸነፍ እንድንችል ከሌሎችና ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ሊኖረን ይገባል (ያዕ. 4: 1–7)። ጫማው ግን ሌላም ፍች አለው። በየቀኑ የሰላሙን ወንጌል ለጠፋው ዓለም ለማካፈል መዘጋጀት አለብን። እንደሚመሰክረው አማኝ ያህል ድል ነሺ ክርስቲያን የለም። የወንጌሉን ጫማ ካጠለቅን በኢሳይያስ 52:7 እና በሮሜ 10:15 ላይ የተጠቀሱት «ያማሩ እግሮች» አሉን ማለት ነው። ሰይጣን ጦርነት ከፍቶአል፤ እኛ ግን የሰላም አምባሳደሮች ነን (2ኛ ቆሮ. 5:18–21)። በመሆኑም በሄድንበት ሁሉ የሰላሙን ወንጌል ይዘን እንሄዳለን።

*የእምነት ጋሻ* (6:16)። ጋሻ ብዙውን ጊዜ ከእንጨት ተሠርቶ በጠንካራ ቆዳ የሚለበጥ ሲሆን፥ መጠኑም አራት ጫማ በሁለት ጫማ ነው። ወታደሩ በፊቱ ላይ በማድረግ ከጦር፥ ከፍላጻና ከተወርዋሪ እሳት ይከላከላል። የጋሻዎቹ ጫፎች አመቺ ሆነው ስለተሠሩ ወታደሮቹ በማገጣጠም ጋሻዎቹን እንደ ጠንካራ ግድግዳ በመጠቀም ወደ ጠላት ሊገሰግሱ ይችላሉ። ይህም እኛ ክርስቲያኖች በጦሩ ሜዳ ውስጥ ብቻችንን እንዳልሆንን ያመለክታል። በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው እምነት ሕያው እምነት እንጂ የማያድነው እምነት አይደለም። ይህም በእግዚአብሔር ቃልና ተስፋዎች መታመን ነው። እምነት ከሰይጣን ጥቃቶች የሚጠብቀን የመከላከያ መሣሪያ ነው። በጳውሎስ ዘመን፥ ፍላጻዎቹ በጠላት ላይ ከመወርወራቸው በፊት በጫፉ ላይ እሳት ይደረግባቸዋል፤ ሰይጣንም እንደ ውሸት፥ ክፉ አሳብ፥ ጥላቻ፥ ጥርጣሬና ኃጢአትን የመሥራት ፍላጎት የመሳሰሉትን እሳቶች ወደ ልባችን ይወረውራል። እነዚህን እሳቶች በእምነት ካላጠፋናቸው እግዚአብሔርን እንዳንታዘዝ የሚያደርግ እሳት ከልባችን ሊያቀጣጥሉ ይችላሉ። ሰይጣን እሳቱን መቼ እንደሚወረውርብን ስለማናውቅ ሁልጊዜ የእምነትን ጋሻ በመጠቀም በእምነት መመላለስ ይኖርብናል።

*የመዳን ራስ ቁር።* (6:17)– ሰይጣን አእምሮን ለማጥቃት ይፈልጋል። ይህ ሔዋንን ያሸነፈበት መንገድ ነበር (ዘፍጥ. 3፤ 2ኛ ቆሮ. 11:1–3)። የራስ ቁር ከእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር የዋለን አእምሮ ያመለክታል። ብዙ ክርቲያኖች በክርስትና ዕድገት፥ አገልግሎትና ድል ዐቢይ ሚና የሚጫወተውን እውቀት ማጥላላታቸው አሳዛኝ ነገር ነው። እግዚአብሔር አእምሮውን የተቆጣጠረ አማኝ ሰይጣን ወደ ጥፋት ሊመራው አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት የመጽሐፍ ቅዱስን አስተምህሮዎች የሚረዳ አማኝ በቀላሉ ሊሳሳት አይችልም። «እውነትም በኢየሱስ እንዳለ» ከእርሱ ልንማር ይገባል (ኤፌ. 4:21)። በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት ልናድግ ያሻል (2ኛ ጴጥ. 3:18)። ጳውሎስ ባላገለገለባቸው ስፍራዎች ሁሉ ለአዳዲስ አማኞች የእግዚአብሔርን ቃል ያስተምር ነበር። ይህም የራስ ቁር ከሰይጣን ውሸቶች ጠብቆአቸዋል።

አንድ ቀን ቀደም ሲል የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን ሆኖ ያገለገለውንና በወቅቱ በሐሰት ትምህርት የተወሰደውን ሰው ኅበኘሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ከፍተን እያነበብን የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ላሳየው ብሞክር አእምሮው በውሸት የጨለመ ይመስል ለመቀበል ተቸገረ። «እንዴት መጽሐፍ ቅዱስን ከምታስተምር ቤተ ክርስቲያን ወጥተህ ወደዚህ ስሕተት ውስጥ ገባህ?» ስለው የሰጠኝ ምላሽ አስደነገጠኝ። «ውድ ሰባኪ፥ ለዚህ የምትወቀሰው ቤተ

ክርስቲያንን ነው» ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የማውቀው ነገር አልነበረም። እነርሱም ብዙ አላስተማሩኝም። መጽሐፍ ቅዱስ ላጠና ፈለግሁ፤ ነገር ግን እንዴት እንደሚጠና የነገረኝ አልነበረም። ከዚያም ዲያቆን አደረጉኝ። እኔ ለዚያ ዝግጁ አልነበርሁምና ሥልጣኑ በዛብኝ። ይህ ሰውዬ መጽሐፍ ቅዱስ በሬዲዮ ሲሰበክ ሰማሁና አንድ ነገር የሚያውቅ መሰለኝ። መጽሔቶቹንና መጻሕፍቶቹን ማንበብ ቀጠልሁና እነሆ አሁን ሰውየው አባባሉ ትክክል እንደሆነ አምኜው አረፍሁ።

ቤተ ክርስቲያኒቱ ለዚህ ሰውዬ የመዳንን የራስ ቁር አለመስጠቷ የሚያሳዝን ነገር ነው። በ2ኛ ጢሞቴዎስ 2:2 ላይ የሚገኘውን እውነት ተግባራዊ አድርገው ቢሆን ኖሮ ይህ ሰው የጦርነቱ ሰለባ ላይሆን ይችል ነበር።

*የመንፈስ ሰይፍ* (6:17)። ይህ እግዚአብሔር የሚሰጠን መሣሪያ ነው። የሮም ወታደር ለጨበጣ ውጊያ የሚያገለግል ሰይፍ ይታጠቅ ነበር። ሰይፍ ሥጋን እንደሚወጋ ሁሉ የእግዚአብሔርም ቃል የሰውን ውስጣዊ ማንነት የመውጋት ብቃት አለው (ዕብ. 4:12)። ቃሉ ስለ ኃጢአታችን ተናግሮ ባሳመንን ጊዜ ልባችን ተነክቶአል (የሐዋ. 2:37፤ 5:33)። በአትክልቱ ስፍራ ኢየሱስን ለመከላከል ሰይፍ ይዞ የነበረው ጴጥሮስ (ሉቃ. 22:47–51) በበዓለ ኀምሳ ቀን የመንፈስ ሰይፍ የላቀ ተግባር እንደሚፈጽም ተገንዝቦአል። በምድራዊ ሰይፍ ሊያሸንፍ የሞከረው ሙሴም (ዘጸአ. 2:11–15) ግብጽን ለመርታት የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ መሆኑን ተረድቶአል።

ምድራዊ ሰይፍ ሰውነትን ሲወጋ የእግዚአብሔር ቃል ግን ልብን ይወጋል። ምድራዊ ሰይፍ በአገልግሎት ብዛት እየደነዘዘ ሲመጣ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ዘወትር መጠቀሙ ግን በሕይወታችን የበለጠ ስለታም ሆኖ እንዲሠራ ያደርገዋል። ምድራዊ ሰይፍ የወታደሩን እጅ ሲሻ፥ የመንፈስ ሰይፍቱን ሕያው ሆኖ የሚሠራ በመሆኑ ኃይል አለው (ዕብ. 4:12)። ቃሉን የጻፈው መንፈስ ቅዱስ ቃሉን በእምነት ስንጠቀም ይሠራበታል። ምድራዊ ሰይፍ ለመጉዳትና ለመግደል ሲያቆስል የመንፈስ ሰይፍ ግን ለመፈወስና ሕይወትን ለመስጠት ያቆስላል። ነገር ግን ሰይፉን በሰይጣን ላይ በምንጠቀምበት ጊዜ ሰይጣንን ሽባ በማድረግ የእግዚአብሔርን ሥራ እንዳያደናቅፍ እናደርገዋለን።

ክርስቶስ በምድረ በዳ በሰይጣን በተፈተነ ጊዜ፥ የመንፈስ ሰይፍ በመጠቀም ሰይጣንን አሸንፎአል። ኢየሱስ ሦስት ጊዜ፥ «እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል» እያለ መልሶአል (ማቴ. 4:1–13)። ሰይጣንም የእግዚአብሔርን ቃል ሊጠቅስ እንደሚችል ልብ በል፤ «ተብሎ

ተጽፎአልና» (ሉቃስ 4፡1–13)። ነገር ግን ሙሉ በሙሉ አይጠቅሰውም። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል የሚጠቅሰው እኛን ለማደናገር ስለሆነ የሰይጣንን ቃል አንድ በአንድ ማወቁ ወሳኝ ነው። «የፈለግኸውን ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ አስደግፈህ ልታረጋግጥ ትችላለህ» የሚሉ ሰዎች አሉ። ይህንን ማድረግ የሚቻለው ጥቅሶችን ከዓውዳቸው ውጭ መዝዞ በማውጣት፥ የማይፈልጉትን ቃላት ገለል በማድረግና ከዛሬዎቹ ክርስቲያኖች ሕይወት ጋር የማይዛመዱትን ጥቅሶች በመጠቀም ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ባወቅህ መጠን የሰይጣንን ውሸቶች በመረዳት የሚያቀርባቸውን ግብዣዎች መናቅ የበለጠ ይቀልሃል።

በአንድ በኩል የእግዚአብሔር የጦር ዕቃ በሙሉ የኢየሱስ ክርስቶስ መግለጫ ነው። ክርስቶስ እውነት (ዮሐ. 14፡6)፥ ሰላምና (ኤፌ. 2፡14) ጽድቃችን ነው (2ኛ ቆሮ. 5፡21)። የእርሱ ታማኝነት እምነታችንን ተግባራዊ ያደርገዋል (ገላ. 2፡20)። እርሱ ደኅንነታችን ነው (ሉቃ. 2፡30)። እርሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው (ዮሐ. 1፡1፥14)። በመሆኑም በኢየሱስ ክርስቶስ በምናምንበት ጊዜ የጦር ዕቃውን ተቀብለናል ማለት ነው። ጳውሎስ የሮሜ ሰዎች በጦር ዕቃው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ገልጾላቸዋል (ሮሜ 13፡11–14)። ንቁ (ቁ.11)፥ ኃጢአትን አስወግዱ፤ የብርሃንን ዕቃ ጦር ልበሱ (ቁ. 12)። ይህንን የምናደርገው ኢየሱስ ክርስቶስን በመልበስ ነው (ቁ.14)። የጦር ዕቃውን የለበስን ብንሆንም በየዕለቱ ልንለማመድበት ይገባል። ንጉሥ ዳዊት የጦር ዕቃውን አስቀምጦ ወደ ቤተ መቅደሱ ሲመለስ በጦር ሜዳ ቢሆን ከሚያጋጥመው የከፋ አደጋ ጠበቀው (2ኛ ሳሙ. 11)። ከሰይጣን ተንኮል ፍጹም የራቅን ባለመሆኑ፥ የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ ከመልበስ ልንታቀብ አይገባም።

### 3. ኃይል (6፡18–20)

ክርስቲያን የጦር ዕቃ ሊጠቀም የሚችለው በጸሎት አማካይነት ነው። ምንም ያህል ብርቱና ስጦታ ያለን ሰዎች እንደሆንን ብናስብም ጦርነቱን በራሳችን ኃይል ልናካሂድ አንችልም። አማሌቅ እስራኤልን በወጋበት ሰዓት ኢያሱ ሰይፍ እየመዘዘ ሳለ ሙሴ በተራራው ራስ ላይ ሆኖ ይጸልይ ነበር (ዘጸአ. 17፡8–16)። አማሌቅን ለማሸነፍ የሙሴ ጸሎትና የኢያሱ ውጊያ አስፈላጊ ነበር። ጸሎት የድል ኃይል ነው። ማንኛውም ጸሎት ግን ለዚህ ድል አያበቃንም። ጳውሎስ ሰይጣንን ለማሸነፍ እንዴት መጸለይ እንዳለብን ገልጾአል።

*ሁልጊዜ ጸልዩ*። ይህ ሁልጊዜ ጸሎትን ማነብነብ አይደለም። እግዚአብሔር የሚሰማን ለረዥም ጊዜ ስለጸለይን አይደለም (ማቴ.

6:7)። «ሳታቋርጡ ጸልዩ» (1ኛ ተሰ. 5:17) የሚለው ቃል፥ «ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ይኑራችሁ፤ ከአደጋ ተጠበቁ» ማለት ነው። በምትጸልይበት ጊዜ «ጌታ ሆይ፥ ወደ አንተ መጥቻለሁ» ማለት የለብህም፤ ከእርሱ አልተለየህም። ክርስቲያን ሁልጊዜ ለፈተናና ለዲያብሎስ ጥቃት የተጋለጠ በመሆኑ ሁልጊዜ መጸለይ አለበት። ሳያቋርጡ መጸለይ እንዳለባቸው የዘነጉ ክርስቲያኖች ለድንገተኛ ጥቃት የተጋለጡ ናቸው።

*በጸሎት ሁሉ።* ጸሎት አንድ ዓይነት ብቻ ሳይሆን፥ ልመና፥ ምልጃ፥ እና ምስጋና ያለበት ነው (ፊልጵ. 4:6፤ 1ኛ ጢሞ. 2:1)። ለልመና ብቻ የሚጸልይ አማኝ በምስጋናና በምልጃ የሚገኙትን በረከቶች ያጣል። እንዲያውም ምስጋና ሰይጣንን ለማሸነፍ የሚያስችል ጽኑ መሣሪያ ነው። ጸሎት ነገሮችን የሚለውጠውን ያህል ምስጋናም ነገሮችን ይለውጣል። ለሌሎች መማለዱ ለሕይወታችን ድልን ሊያመጣ ይችላል። ኢዮብ ስለ ወዳጆቹ በጸለየ ጊዜ እግዚአብሔር ምርኮውን መልሶለታል (ኢዮብ 42:10)።

*በመንፈስ ጸልዩ።* የመጽሐፍ ቅዱስ የጸሎት «ፎርሙላ» ለአብ በወልድ በኩል በመንፈስ ቅዱስ መጸለይ እንዳለብን ያስገነዝበናል። በሮሜ 8:26–27 ላይ እንደተገለጸው፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ሆነን መጸለይ የምንችለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው። በብሉይ ኪዳን የመገናኛ ድንኳን፥ ካህኑ ዕጣኑን የሚያጥነው ከመጋረጃው ፊት ባለው አነስተኛ የወርቅ መሠውያ ላይ ነበር (ዘጸ. 30:1–10፤ ሉቃ. 1:1–11)። ዕጣን የጸሎት ምሳሌ ነው። ዕጣኑ እንደ ሰው አሳብ ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ዕቅድ መቀላቀል ነበረበት። በመሠውያው ላይ ያለው እሳት የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው። ይህም ጸሎታችንን ወስዶ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ የሚያቀጣጥለው እርሱ ስለሆነ ነው። በሥጋ ብርቱ ጸሎት እየጸለዩ ወደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመድረስ ይቻላል። እንዲሁም ደግሞ በጸጥታ በመንፈስ እየጸለዩ የእግዚአብሔር ክንድ ታላላቅ ነገሮችን ሲፈጽም መመልከት ይቻላል።

*ዓይኖቻችሁ ተከፍተው ጸልዩ።* «በመጽናት ሁሉ ትጉ» የሚለው ሐረግ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ስፍራዎች ተጠቅሶአል። ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች እየጠገነ ሳለ ጠላት ሥራውን ለማደናቀፍ በሚጥርበት ወቅት፥ ነህምያ ነቅቶ በመጸለይ ጠላትን አሸንፎአል። «ወደ አምላካችንም ጸለይን፤ ከእነርሱም የተነሣ በአንጻራቸው ተጠባባቂዎች በሌሊትና በቀን አደረግን» (ነህ. 4:9)። በሰይጣን (ኤፌ. 6:18)፥ በሥጋና (ማር. 14:38) በዓለም (ማር. 13:33) ላይ ድልን መቀዳጀት የሚቻለው ነቅቶ በመጸለይ ነው። ጴጥሮስ መጸለይ በሚኖርበት ሰዓት በማንቀላፋቱ ድሉ የሰይጣን ሆነ (ማር. 14:29–31፥

67–72)። ሰይጣን ሥራ በሚጀምርበት ጊዜ ለመቆጣጠር እንችል ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተን እግዚአብሔር የሰጠንን ችሎታ ልንጠቀም ይገባል።

*በጸሎት መጽናት።* መጽናት ማለት የያዙትን ነገር ሳይለቁ ተግቶ መቀጠል ነው። የጥንት አማኞች የጸለዩት በዚህ መንገድ ሲሆን (የሐዋ. 1:14፤ 2:42፤ 6:4)፥ እኛም በዚህ መንገድ መጸለይ ይኖርብናል (ሮሜ 12:12)። በጸሎት መጽናት (መትጋት) ማለት የእግዚአብሔርን ክንድ መጠምዘዝ ማለት ሳይሆን መልሱን እስክናገኝ ድረስ ለማረፍ አለመቻል ነው። ሮበርት ሎው እንደሚሉት፥ «ጸሎት የሰውን ፈቃድ በሰማይ መፈጸም ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በምድር መፈጸም ነው።» ብዙዎቻችን እግዚአብሔር መልሱን ሊሰጠን ሲል መጸለያችንን እናቆማለን። ሁሉም ሰው ሌሊቱን ሁሉ በጸሎት የማሳለፍ ብቃት ላይኖረው ቢችልም፥ ብዙዎቻችን አሁን ከምናደርገው በላይ በጸሎት ልንተጋ እንችላለን። ጴጥሮስ በእስር ቤት በነበረ ጊዜ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ያለማቋረጥ ጸለየች። እግዚአብሔር በመጨረሻው ሰዓት መሻታቸውን ፈጸመላቸው (የሐዋ. 12:1–19)። መንፈስ ቅዱስ እስኪያቆምህ ወይም እግዚአብሔር መሻትህን እስኪሰጥህ ድረስ መጸለይህን ቀጥል። ጸሎትህን ለማቋረጥ ስትዳዳ እግዚአብሔር መልሱን ይሰጥሃል።

*ስለ ቅዱሳን ሁሉ ጸልዩ።* የጌታ ጸሎት የሚጀምረው «አባት ሆይ፥» በሚል ሳይሆን «አባታችን ሆይ» በሚል ሐረግ ነው። ለእግዚአብሔር እንደሚነገር ታላቅ የቤተሰብ አካል ለሌሎች የቤተሰብ አካላትም መጸለይ ይኖርብናል። ሦስተኛ ሰማይ ላይ ደርሶ የተመለሰው ጳውሎስ እንኳ የኤፌሶን ክርስቲያኖችን የጸሎት ድጋፍ ጠይቋል። ጳውሎስ የቅዱሳንን ጸሎት ከፈለገ እኛስ ምን ያህል አብልጠን ልንሻ ይገባል! የእኔ ጸሎት ሌላው አማኝ ሰይጣንን እንዲያሸንፍ የሚረዳው ከሆነ ድሉ እኔንም ይረዳኛል። ጳውሎስ የጸሎት ድጋፍ የጠየቀው ለግል ጥቅሙ ሳይሆን ውጤታማ ምስክርነት ለመስጠት እንዲችል ነበር።

## 4. ማበረታቻ (6:21–24)

ውጊያውን የምንጋፈጠው ብቻችንን አይደለም። ሌሎችም አብረውን የሚዋጉ አማኞች ስላሉ እርስ በርሳችን ልንበረታታ ይገባል። ጳውሎስ የኤፌሶንን አማኞች ሲያጽናና ቲኪቆስ ለጳውሎስ መጽናኛ ነበር (የሐዋ. 20:4)። ጳውሎስ ቲኪቆስ መጽናኛ ይሆናቸው ዘንድ ቲኪቆስን ወደ ኤፌሶን ክርስቲያኖች ሊልከው ፈልጎ ነበር። ጳውሎስ የራሱን ጉዳይ ለራሱ የሚያስቀር ዓይነት አገልጋይ አልነበረም። እግዚአብሔር እያደረገ ያለውን ጸሎታቸው እንዴት እየተመለሰ እንደሆነና ሰይጣን

ሥራውን ለማደናቀፍ ምን እያደረገ እንዳለ እንዲያውቁ ይፈልግ ነበር። በራስ ወዳድነት ዓላማ ተጠፍሮ ከእነርሱ አንዳች ጥቅም ለማግኘት የሚጥር ሰው አልነበርም።

የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል መሆን ምን ያህል አጽናኝ ነገር ነው! በአዲስ ኪዳን ውስጥ በየትኛውም ስፍራ ከሌሎች አማኞች ተነጥሎ የሚኖር አማኝ አናገኝም። ክርስቲያኖች እንደ በጎች አብረው የሚሰማሩ ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ሠራዊት ስትሆን ወታደሮቹ አብረው ሊሰለፉና ሊዋጉ ይገባል።

ጳውሎስ ይህንን መልእክት ሲጨርስ የተጠቀማቸውን ቃላት አስተውል– ሰላም– ፍቅር– እምነት– ጸጋ! በሮም ታስሮ የነበረ ቢሆንም፥ ከንጉሥ በላይ ባለጸጋ ነበር። በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብንሆንም፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በሰማያዊ በረከት ሁሉ ተባርከናል።

ወዳጄ ሆይ፥ ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለጸግነት ውረስ!

# ምዕራፍ አንድ

## ሕያዋን ቅዱሳን

(ኤፌሶን 1፡1-3)

1. ሀብታም ብትሆን ሕይወትህ ምን ይመስላል?
2. የኤፌሶን መጽሐፍ እንዴት በመንፈሳዊ ሕይወታችን ልንበለጽግ እንደምንችል ይነግረናል። ኤፌሶን 1፡1-3 አንብብ። ይህን መልእክት ስለ ጻፈው ሰው ምን የምታውቀው ነገር አለህ?
3. ጳውሎስ የዚህን መልእክት ተቀባዮች የገለጻቸው እንዴት ነበር?
4. ቅዱሳን የሚለው ቃል ምን ፍች አለው?
5. የሐዋርያት ሥራ 18፡24-19፡4፤ 20፡17-18 አንብቡ። ስለ ኤፌሶን አማኞችና በዚያ ስላለው ነገር የተረዳኸው ምንድን ነው?
6. ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች ሰላምታ ያቀረበው እንዴት ነበር? ለምን?
7. በዚህ መልእክት ውስጥ የጳውሎስ ጭብጥ ምንድን ነው?
8. «መንፈሳዊ በረከት ሁሉ» የተባለው ምንድን ነው? በረከቱን እንዴት ማግኘት ይቻላል?
9. ኤፌሶንን በምናጠናበት ጊዜ ክርስቶስ የሰጠንን ሁሉ ለማግኘት ምን ልናደርግ እንችላለን?

# ምዕራፍ ሁለት

## በክርስቶስ ምን ያህል በልጽገሃል!

(ኤፌሶን 1፡4–14)

1. ባለፈው ሳምንት ያገኘኸው በረከት ምንድን ነው?
2. ኤፌሶን 1፡4–14 አንብብ። ከእግዚአብሔር አብ የምናገኛቸው በረከቶች ምንድን ናቸው?
3. እግዚአብሔር ለበረከቶቹ የመረጠን ለምንድን ነው?
4. ስለ መንፈሳዊ ልጅነትህ ግለጽ።
5. ከእግዚአብሔር ወልድ የምታገኛቸው በረከቶች ምንድን ናቸው?
6. በመቤዠትና በይቅርታ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
7. ጳውሎስ በቁጥር 11 ላይ የጠቀሰው ርስት ምንድን ነው?
8. ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የምናገኛቸው በረከቶች ምንድን ናቸው?
9. በመንፈስ ቅዱስ መታተም ምንድን ነው?
10. ሦስቱ የሥላሴ አካላት በደኅንነታችን ውስጥ የተሳተፉት እንዴት ነው?
11. ከዚህ የኤፌሶን ምንባብ ስለ መንፈሳዊ በረከት ምን ተማርህ?
12. በኤፌሶን 1፡4–14 ከተገለጹት በረከቶች የተለማመድሃቸው የትኞቹ ናቸው?

# ምዕራፍ ሦስት

## የሂሳብ መዝገብ

(የኤፌሶን 1፥15–23)

1. በኤፌሶን 1፥15–23 ጳውሎስ የጸለየውን ጸሎት አንብብ። ለሰዎቹ እንዲጸልይ ጳውሎስን ያነሣሣው ምንድን ነው?
2. አራቱ ዐበይት ጥያቄዎች ምን ነበሩ?
3. ጳውሎስ ለእነዚህ የተለዩ ጥያቄዎች የጸለየው ለምንድን ነው?
4. በቁጥር 18 ላይ «የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ» ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. እግዚአብሔር ኃይሉን ያሳየን እንዴት ነው?
6. የእግዚአብሔር ኃይል የሚያስፈልገን ለምንድን ነው?
7. ዛሬ ላለነው ክርስቲያኖች የእነዚህ የጸሎት ጥያቄዎች ጠቀሜታ ምንድን ነው?
8. የጳውሎስ ጸሎት እኛ ከምንጸልየው ጸሎት ጋር የሚነጻጸረው እንዴት ነው?
9. የጳውሎስን ምሳሌነት ለመከተል በጸሎት ሕይወትህ ልትለውጣቸው የሚገቡ ነገሮች ምንድን ናቸው?

# ምዕራፍ አራት

## ከመቃብሩ ውጡ

(ኤፌሶን 2፡1–10)

1. ኤፌሶን 2፡1–10 አንብቡ። የኤፌሶን ሰዎች ከመዳናቸው በፊት ምን ዓይነት መንፈሳዊ ስፍራ ነበራቸው?
2. እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ለእኛ ያደረጋቸውና ጳውሎስ በዚህ ክፍል የጠቀሳቸው አራት ነገሮች ምንድን ናቸው?
3. ጳውሎስ ከቁጥር 1–3 የሚያምኑትን ሰዎች የገለጸው እንዴት ነው?
4. እግዚአብሔር ሙታንን የሚያስነሣው እንዴት ነው?
5. የዳነ ሰው እንዴት ይለያል?
6. ሰው ደኅንነትን የሚያገኘው እንዴት ነው?
7. በመልካም ሥራና በደኅንነት መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?
8. በቁጥር 10 ላይ የተጠቀሰው «ሥራ» ምን ፋይዳ አለው?
9. አሁን አሁን እግዚአብሔር በሕይወትህ የሚሠራቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?
10. እንደ ክርስቲያኖች ልንፈጽማቸው የሚገቡን አንዳንድ መልካም ሥራዎች ምንድን ናቸው?
11. በዚህ ሳምንት የትኛውን ትፈጽማለህ?

# ምዕራፍ አምስት

## ታላቅ የሰላም ተልዕኮ

(ኤፌሶን 2፡11–22)

1. ዛሬ ሰዎች «ሰላም» የሚለውን ቃል ሲጠቀሙ የሚያስተላልፉት አሳብ ምንድን ነው?
2. ኤፌሶን 2፡11–22 አንብብ። በቁ. 1–10 እና በቁ. 11–22 የተከሰተው ለውጥ ምንድን ነው?
3. ያለ ክርስቶስ የሆኑትን አሕዛብ ጳውሎስ የገለጻቸው እንዴት ነው?
4. ኢየሱስ ክርስቶስ ለአሕዛብ ምን አደረገ?
5. ከሌላ ሰው ጋር መታረቅ ማለት ምን ማለት ነው?
6. የሰውና የእግዚአብሔር ዕርቅ ያስፈለገው ለምንድን ነው?
7. የአይሁድና የአሕዛብ ዕርቅ የሚጠቅመው ለምንድን ነው?
8. አይሁድና አሕዛብ በክርስቶስ አንድ መሆናቸውን እንዴት እናውቃለን?
9. የኤፌሶን 2፡11–22 ዐቢይ መልእክት ምንድን ነው?
10. የእግዚአብሔር ሰላም ዛሬ ሰዎች ከሚጠሩት «ሰላም» ጋር የሚነጻጸረው እንዴት ነው?
11. ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ ምን እያደረግህ ነው?

# ምዕራፍ ስድስት

## አንድ ምሥጢር አውቃለሁ

(ኤፌሶን 3፡1–13)

1. ኤፌሶን 1–13ን አንብብና በዚህ ክፍል ውስጥ ጳውሎስ የጠቀሰውን ምሥጢር አብራራ።
2. ጳውሎስ ይህንን ምሥጢር እንዴት አወቀ?
3. ይህ ምንባብ ከኤፌሶን 2፡11–22 ጋር እንዴት ይዛመዳል?
4. ጳውሎስ ይህንን ምሥጢር ሲናገር አራት ቡድኖችን እያሰበ ነበር። እነዚህ ቡድኖች እነማን ናቸው? ምሥጢሩ ለእያንዳንዳቸው አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?
5. አማኞችና አብያተ ክርስቲያናት እግዚአብሔር የሚፈልግባቸውን ዓይነት ልበ ሙሉነትና ድፍረት ያጡት ለምንድን ነው?
6. ጳውሎስ ስለገለጸው ምሥጢር ከአሕዛብ ወገን የሆኑት የኤፌሶን ሰዎች ምን ዓይነት ምላሽ የሰጡ ይመስልሃል?
7. ይህንን ምሥጢር ማወቅ እንዴት ያበረታታሃል?

# ምዕራፍ ሰባት

## ብልጽግናህን ከእጅህ አስገባ

(ኤፌሶን 3፡14–21)

1. ባለፉት ቀናት የጸለይሃቸውን ጸሎት አስብ። እግዚአብሔር እንዴት የሚገመግማቸው ይመስልሃል? ለምን?
2. ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች የጻፈውን ሁለተኛ ጸሎት 3፡14–19 አንብብ። ጉልበቱን ለእግዚአብሔር የሚያንበረክከው ለምንድን ነው?
3. የጳውሎስ ጸሎት ያተኮረባቸው አራት ነጥቦች ምንድን ናቸው?
4. መንፈስ ቅዱስ ውስጣዊ ማንነታችንን የሚያጸናው እንዴት ነው?
5. ክርስቶስ በእኛ ልብ ውስጥ ያድራል ሲባል ምን ማለት ነው?
6. ከአእምሮአችን የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር እንዴት እንረዳለን?
7. የእግዚአብሔርን ሙላት በተግባራዊ መንገዶች እንዴት ልንለማመድ እንችላለን?
8. በጳውሎስ ጸሎት ውስጥ አራቱ ጥያቄዎች የተያዙት እንዴት ነው?
9. ከጳውሎስ ጸሎት ይበልጥ ያስደመመህ ምንድን ነው? ለምን?
10. ቁጥር 20 እና 21ን አንብብና ጳውሎስ ጸሎቱን ለምን በዚህ ቡራኬ እንደመደመ ግለጽ።

# አብረን እንጓዝ

(ኤፌሶን 4፡1–16)

1. ለአንድ የስፖርት ቡድን ስኬታማነት አስተዋጽኦ የሚያደርገው ምን ይመስልሃል?
2. ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን ፍሬያማነት አስተዋጽኦ የሚያደርገው ዐቢይ ጉዳይ የጠቀሰበትን ኤፌሶን 4፡1–16 አንብብ። በዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ ሦስት ምዕራፎች በኋላ የተደረገው የትኩረት ለውጥ ምንድን ነው?
3. ጳውሎስ እስረኛ መሆኑን በድጋሚ የገለጸው ለምንድን ነው?
4. የአማኞችን ተገቢ ሕይወት ዘይቤ ለይተው የሚያሳዩ ባሕርያት የትኞቹ ናቸው?
5. የመንፈስ አንድነት ምንድን ነው?
6. በአማኞች መካከል ለሚኖር አንድነት ብቸኛው መሠረት ምንድን ነው?
7. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሰውን አንድነት የሚያመጡት መንፈሳዊ ስጦታዎች ምንድን ናቸው? እነዚህን ስጦታዎች እንዴት እናገኛለን?
8. እነዚህ የተለያዩ ስጦታዎች የአካሉን አንድነት የሚያንጹት እንዴት ነው?
9. ጳውሎስ የጠቀሳቸው የመንፈሳዊ ዕድገት መረጃዎች ምንድን ናቸው?
10. በክርስቶስ ያለንን መንፈሳዊ አንድነት እንዴት ልንጠብቅ እንችላለን?

## አሮጌውን ሰው አስወግዱ!

(ኤፌሶን 4:17-32)

1. ነገሮች አሮጌ ሲሆኑብህ ምን ታደርጋቸዋለህ?
2. ኤፌሶን 4:17-32 አንብብና ጳውሎስ አሮጌውን ወይም ያልዳነውን ሰው ከአዲሱ ወይም ከዳነው ጋር እንዴት እንደሚያነጻጽር ግለጽ።
3. ይህ አገላለጽ ቀደም ሲል በኤፌሶን 2:1-9 ስለዳኑትና ስላልዳኑት ሰዎች ከተናገረው አሳብ ጋር የሚነጻጸረው እንዴት ነው?
4. አማኞች ከመዳናቸው በፊት ይኖሩ ከነበረው ሕይወት የተለየ ኑሮ መምራት ያለባቸው ለምንድን ነው?
5. ጳውሎስ እንድናስወግዳቸው በ25-32 ላይ የዘረዘራቸው ኃጢአቶች ምንድን ናቸው? ለምን?
6. እነዚህን ኃጢአቶች እያንዳንዳቸውን በምን ልንተካቸው ይገባል?
7. መንፈስ ቅዱስን የምናሳዝነው እንዴት ነው?
8. ኃጢአታችን ሌላውን ሰው የሚጎዳው እንዴት ነው?
9. አዲሱን ሰው የምንለብሰው ለምን ዓላማ ሊሆን ይገባል?
10. ክርስቲያን ከሆንህ በኋላ ያስወገድኸው አሮጌ ኃጢአት ምንድን ነው?
11. አሮጌውን ሰው አውልቀህ አዲሱን ሰው ልትለብስ የምትችለው እንዴት ነው?

# ምዕራፍ አሥር

## አባታችንን መምሠል

(ኤፌሶን 5፥1–17)

1. ልጅ ወላጁን የሚከርጅባቸው አንዳንድ መንገዶች የትኞቹ ናቸው?
2. ኤፌሶን 5፥1–17 አንብብ። በዚህ ምንባብ ውስጥ ጳውሎስ አማኞች ሰማያዊ አባታቸውን የሚከርጁባቸውን ሦስት መንገዶች ገልጾአል። ዘርዝራቸው።
3. ክርስቲያኖች በፍቅር መመላለስ የሚኖርባቸው ለምንድን ነው?
4. የእግዚአብሔርን ፍቅር ልንቀዳ የምንችልባቸው አንዳንድ መንገዶች የትኞቹ ናቸው?
5. ጳውሎስ እንደ ብርሃን ልጆች መመላለሳችንን የገለጸው እንዴት ነው?
6. እንደ አማኞች ልናስወግዳቸው የሚገቡን የዛሬው ዘመን ኃጢአቶች ምንድን ናቸው?
7. ጳውሎስ የጻፈው ሦስተኛው መመላለስ ለአማኞች የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?
8. በጥበብ ልንመላለስ ወይም ልንኖር የምንችለው እንዴት ነው?
9. እነዚህ ሦስት መመላለሶች በ 4፥17–5፥17 ከተጠቀሰው ማለትም በንጽሕና ከመመላለሳችን ጭብጥ ጋር የሚዛመዱት እንዴት ነው?
10. ከእነዚህ ሦስት መመላለሶች፥ በመንፈሳዊ ሕይወትህ ይበልጥ ልታተኩርበት የምትፈልገው የትኛውን ነው? እንዴት ትለማመደዋለህ?

# ምዕራፍ አሥራ አንድ

## መንግሥተ ሰማይን በቤትህ

(ኤፌሶን 5፡18–33)

1. ብዙውን ጊዜ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ አለመስማማትን ለማሳየት የሚገለጹት አመለካከቶች ምንድን ናቸው?
2. ኤፌሶን 5፡18–33 አንብብ። ጳውሎስ በአማኞችና በተለይ ደግሞ በቤተሰብ ውስጥ ሊኖር ስለሚገባው ስምምነት ገልጾአል። የስምምነት መሠረታዊ ቁልፉ ምንድን ነው?
3. በስምምነት የመኖርን ትእዛዝ የምንታዘዘው እንዴት ነው? (ቆላስይስ 3፡16–17ንም ተመልከት።)
4. ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የጠቀሰው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክት ምንድን ነው?
5. የአመስጋኝ ሕይወት መሠረት ምን ይመስልሃል?
6. ለሌላው ሰው መገዛት ማለት ምን ማለት ነው?
7. መገዛት ለስምምነት አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?
8. ለብዙ ሰዎች መገዛት ከባድ የሚሆነው ለምንድን ነው?
9. በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው ምን ዓይነት ግንኙነት ይኖራቸዋል?
10. በቤተሰብህ ውስጥ ስምምነትን ለማስፋፋት በዚህ ሳምንት ልታደርግ የምትችለው አንድ ነገር ምንድን ነው?

# ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## የክርስቶስን ጌትነት መኖር

(ኤፌሶን 6፡1–9)

1. ከአንተ በሥልጣን ለሚበልጥ ሰው መገዛት ምን ያህል እንደሚከብድ ወይም እንደሚቀል ግለጽ። ለምን?
2. ኤፌሶን 6፡1–9 አንብብና ክርስቲያን ልጆች ለምን ወላጆቻቸውን መታዘዝ እንዳለባቸው አስረዳ።
3. አባቶች ልጆቻቸውን እንዳያበሳጩ ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?
4. አባቶች ልጆቻቸውን ሊንከባከቡና ሊያስተምሩ የሚችሉት እንዴት ነው?
5. ክርስቲያን ሠራተኞች በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸውን እንዴት ሊያሳዩ ይችላሉ?
6. ጳውሎስ አገልጋዮች (ባሮች) ጌቶቻቸውን ይታዘዙ ዘንድ ምን ዓይነት ምክር ሰጣቸው?
7. ጌቶች ከአገልጋዮች (ከባሮቻቸው) ጋር እንዴት ስምምነት ሊፈጥሩ ይችላሉ?
8. በዚህ ሳምንት ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ስምምነት የምትፈጥርባቸው ሁነኛ መንገዶች ምንድን ናቸው?

# ምዕራፍ 13

## መንፈሳዊ ውጊያ

(ኤፌሶን 6፡10–24)

1. «የክርስትና ሕይወት የጦር ሜዳ እንጂ የኳስ ሜዳ አይደለም!» የሚለውን አባባል ትቃወማለህ ወይስ ትደግፋለህ? ለምን?
2. ኤፌሶን 6፡10–24 አንብብ። ጳውሎስ በጌታ እንድንበረታ የነገረን ለምንድን ነው?
3. የክርስትና ሕይወት የጦር ሜዳን የሚመስለው እንዴት ነው?
4. ጳውሎስ የምንዋጋውን ጠላት የገለጸው እንዴት ነው?
5. በጠላታችን ላይ ድል እንነሣ ዘንድ እግዚአብሔር የሰጠን መሣሪያዎች ምንድን ናቸው?
6. የእያንዳንዱ መሣሪያ ጥቅም ምንድን ነው?
7. ፈተና በሚገጥመን ጊዜ እያንዳንዱን መሣሪያ ተግባራዊ በሆነ መንገድ እንዴት ልንጠቀምበት እንችላለን?
8. ጳውሎስ ይህንን መልእክት ሲደመድም የኤፌሶንን ሰዎች ለመንፈሳዊ ውጊያ ያበረታታቸው እንዴት ነው?
9. በኤፌሶን መልእክት ጥናት ውስጥ በሕይወትህ ትልቅ ለውጥ ያመጣ ምን ትምህርት አገኘህ?

ከ30 ሺህ የሚበልጡ የ«...ሁን» ተከታታይ መጻሕፍት ታትመዋል!

# ከቶ የማይጠፋ በረከት ትሻለህ?

የኑሮ ውድነት ብዙዎቻችንን ያሳስበናል። የዕቃዎች ዋጋ ወደ ላይ እያሻቀበ ሲሄድ፥ ገንዘቡ ደግሞ ዋጋ እያጣ ይሄዳል። ምድራዊ ብልጽግና የሚጨበጥ ነገር አይደለም። ይህ መጽሐፍ ሕይወትህንና አመለካከትህን ሊለውጥ የሚችለውን በረከት ከየት እንደምታገኝ ይነግርሃል። ዶክተር ዌርዝቢ እንደሚሉት «ሰዎች ዛሬ የሁሉንም ነገር ዋጋ ያውቃሉ፤ የሕይወትን ፋይዳ ግን አያውቁም።»

## ይህ መጽሐፍ

- በክርስቲያናዊ ቤተሰብና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ስላለው ዝምድና ያስተምርሃል።
- ሰይጣን ክርስቲያኖችን ለማጥመድ የሚጠቀምባቸውን ስልቶችና ክርስቲያኖች በሰይጣን ላይ ድልን እንዴት እንደሚቀዳጁ ያስተምርሃል።
- በክርስቶስ ካገኘነው ታላቅ በረከት የተነሣ ከእያንዳንዱ ክርስቲያን የሚጠበቀው ኃላፊነት ምን እንደሆነ ያስተምርሃል።

በእርግጥም **እውነተኛውን በረከት** ልታገኝ ትችላለህ!

ዶክተር ዋረን ዌርዝቢ ከሁሉም በላይ የሚታወቁት በደራሲነታቸው፥ በመጋቢነታቸውና በሬድዮ መምህርነታቸው ነው። ለብዙ ዓመታት የሺካጎው የሙዲ መታሰቢያ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን፥ በቅርቡ ደግሞ «ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንመለስ» ለተባለው የሬድዮ ፕሮግራም ዋና ዳይሬክተርና የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ሆነው አገልግለዋል። እነዚህን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ማብራሪያዎች ጨምሮ፥ ከ100 በላይ መጻሕፍት ጽፈው ለኅትመት አብቅተዋል።

የግል እና የቡድን የጥናት መምሪያም ተካትቶአል።

BIBLE BASED BOOKS

Be Rich

Printed by SIM Press